የፔንሲልቬንያ አሽከርካሪዎች መመሪያ መጽሐፍ

pennsylvania
DEPARTMENT OF TRANSPORTATION
Bureau of Driver Licensing
www.dmv.pa.gov

PUB 95 (4-21) Amharic

መንገዱን ከሞተር ሳይክሎች እና ተሽከርካሪዎች ጋራ መጋራት

የዛሬ የሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች ጓደኞች፣ ዘመዶች እና ጎረቤቶች ናቸው። የሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ እንደሌሎች ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች ተመሳሳይ መብቶች እና ኃላፊነቶች አሏቸው። አሽከርካሪዎች ይህንን መገንዘብ እና በእጅጉ ቅርብ ርቀት ተጠግተው በማሽከርከር የሞተር ሳይክሎችን መንገድ ማጣበብ ወይም የሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች ያሏቸውን የመንገድ መብቶችን ለመንጠቅ መሞከር የለባቸውም።

በየዓመቱ በፔንስልቬንያ መንገዶች ወደ 4,000 የሚጠጉ የሞተር ሳይክል አደጋዎች ይከሰታሉ። ከእነዚህ ውስጥ ግማሽ የሚሆኑት በሞተር ሳይክል እና በሌላ ተሽከርካሪ መካከል የተከሰቱ ግጭቶች ናቸው። እና ከእነዚህ አደጋዎች ውስጥ ሁለት-ሶስተኛ የሚሆኑት በሞተር ሳይክል አሽከርካሪው ምክንያት የተከሰቱ ሳይሆኑ በሌላኛው ተሽከርካሪ ነጂ ስህተት ምክንያት የተከሰቱ ናቸው።

የሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች መኖራቸውን እና አለመኖራቸውን ልብ ይበሉ፤ ሞተር ሳይክሎች ትንሽ እንደሆኑ እና ለማየት አስቸጋሪ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገንዘቡ። ሞተርሳይክሎች ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ይልቅ መጠናቸው አነስተኛ ስለሆነ፣ እየተጠጉ ያሉ ሞተርሳይክሎችን ፍጥነት እና ርቀት ለማወቅ አስቸጋሪ ሊያደርግባቸው ይችላል።

የሞተርሳይክል አሽከርካሪው እንቅስቃሴ አስቀድመው ግምት ውስጥ ያስገቡ። ለመኪና አሽከርካሪዎች ብዙም አስቸጋሪ ያልሆኑ የመንገድ ሁኔታዎች፣ ለሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች ግን ትልቅ አደጋን ሊያስከትሉ ይችላሉ።

ሞተርሳይክልን ተከትለው በሚያሽከረክሩበት ወቅት ጊዜ ተጨማሪ ርቀት በመካከላችሁ እንዲኖር ያድርጉ፤ የሞተርሳይክል አሽከርካሪው ድንገተኛ አደጋ ካጋጠመው ለመንቀሳቀስ ወይም ለማቆም በቂ ጊዜ እንዲኖሮት ለማድረግ የሦስት ወይም አራት ሰከንድ ርቀት ይኑራችሁ። ደረቅ በሆኑ ሁኔታዎች፣ ሞተርሳይክሎች ከመኪና በበለጠ ፍጥነት መቆም ይችላሉ።

ስትዞሩ ወይም ወደ ትራፊክ ስትገቡ፣ አስቀድመው ምልክት ስጡ፤ የሞተርሳይክል አሽከርካሪው የትራፊኩን ፍሰት አስቀድሞ እንዲያውቅና ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ መስመር እንዲይዝ መስመር ከመቀየርዎ ወይም ወደ የትራፊክ ፍሰት ውስጥ ከመቀላቀልዎ በፊት ምልክት ይስጡ።

በሞተር ሳይክል ላይ ባሉ ብልጭ ድርግም በሚሉ የማዞሪያ ምልክቶች እንዳይታለሉ - የሞተር ሳይክል ምልክቶች ብዙውን ጊዜ በእራሳቸውን የሚጠፉ አይደሉም፤ እና አሽከርካሪዎች አንዳንድ ጊዜ እነሱን ማጥፋት ይረሳሉ፤ ይህም ሊያዘናጋዎት ይችላል። ከመቀጠልዎ በፊት ሞተርሳይክሉ እንደሚዞር እርግጠኛ እስኪሆኑ ድረስ ይጠብቁ።

ሞተርሳይክሎችን ያክብሩ ሞተርሳይክል መንገድ ላይ እንዳለ ማንኛውም ተሽከርካሪ ተመሳሳይ መብቶች ያሉት ትልቅ መጠን ያለው ተሽከርካሪ ነው። ሞተር ሳይክል አሽከርካሪ ሙሉውን መስመር (ሌን) እንዲጠቀም ይፍቀዱለት። ምንም እንኳን በአንድ ትራፊክ መስመር (ሌን) ውስጥ ለሌላ ተሽከርካሪ እና ለሞተር ሳይክል በቂ ቦታ ያለ ቢመስልም፣ ሞተር ሳይክሉ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለመንቀሳቀስ ቦታ እንደሚያስፈልገው ያስታውሱ። አንድ የትራፊክ መስመርን (ሌን) አይጋሩ።

የመንገድ ትራፊክ አደጋዎች በእነዚህ ከፍተኛ አደጋ ባለባቸው ሁኔታዎች ላይ የመከሰት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው፡-

ወደ ግራ በሚታጠፉበት ወቅት
ከሞተር ሳይክል አደጋዎች ውስጥ ግማሽ ያህሉ የሚከሰቱት ከሌላ ተሽከርካሪ ጋር ነው። ወደ 40 በመቶ የሚሆኑት አደጋዎች የተከሰቱት ሌላኛው ተሽከርካሪ ከሞተር ሳይክል አሽከርካሪው ፊት ለፊት ወደ ግራ በሚታጠፍበት ወቅት ነው።

ለአሽከርካሪዎች ለማየት በሚያዳግቱ ቦታዎች
ሞተር ሳይክሎች መጠናቸው አነስተኛ ስለሆነ ለተሽከርካሪዎች ለማየት አዳጋች በሆኑ ቦታዎች በቀላሉ ሊደበቁ ወይም አሽከርካሪዎች ቶሎ ብለው ሲቃኙ ላይታዩ እንደሚችሉ አስታውሱ። የትራፊክ መስመሮችን ከመግባትዎ ወይም ከመውጣትዎ በፊት እና በመገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶች ውስጥ ሁል ጊዜ መስተዋቶችን እና ለማየት አዳጋች የሆኑ ቦታዎችን በማጤን የሞተር ብስክሌቶች መኖራቸውን በደንብ ያጢኑ።

አደገኛ የመንገድ ሁኔታዎች
የሞተርሳይክል አሽከርካሪዎች እንደ ጉድጓዶች፣ ጠጠሮች፣ እርጥበት ወይም የሚያንሸራትቱ መንገዶች፣ የመንገድ ስንጥቆች፣ የባቡር ሐዲድ መሻገሪያዎች እና ጎድጎድ ያሉ የመንገድ እና የትራፊክ ሁኔታዎችን ለመከላከል በድንገት ፍጥነታቸውን ሊቀይሩ ወይም የመንገድ መስመራቸውን (ሌናቸው) ሊቀይሩ ሊገደዱ ይችላሉ።

የከባቢ አየር ሁኔታዎች
መንገዱ እርጥብ ወይም በረዷማ በሚሆንበት ጊዜ የሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪውን የማቆም ወይም የመቆጣጠር አቅማቸው አስችጋሪ ይሆንባቸዋል።

ኃይለኛ ንፋስ
አሽከርካሪው ዝግጁ ካልነበረ ጠንካራ የሆነ የንፋስ ኃይል ሞተር ሳይክልን ሙሉ መስመር ሊያንቀሳቅሰው ይችላል። በሌላ የትራፊክ መስመር (ሌን) ካሉ ትልልቅ መኪኖች ምክንያት የሚመጣ ድንገተኛ ኃይለኛ ንፋስ አደገኛ ሊሆን ይችላል።

ትልልቅ ተሽከርካሪዎች
እንደ ቫኖች ወይም የጭነት መኪና ያሉ ትላልቅ ተሽከርካሪዎች ሞተር ሳይክልን ከአሽከርካሪው እይታ ሊከልሉ ይችላሉ። የሞተር ሳይክል አሽከርካሪው ሳይታሰብ ከየት እንደመጣ ሳይታወቅ ከማንኛውም ቦታ ብቅ ሊል ይችላል።

መንገዱን በጋራ መጠቀም አሽከርካሪዎች እና የሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች የትብብርን አስፈላጊነት እንደሚገነዘቡ ማሳያ ነው። የአሽከርካሪዎችን ጨዋነት የጎደለው ባህሪ በማስወገድ እንዲሁም ተሽከርካሪዎችን በአስተዋይነት፣ በህግና በስርዓት በመንዳት የመኪና እና የሞተር ሳይክል አሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ በሰላም አብረው መጓዝ ይችላሉ።

መግቢያ

ይህ መመሪያ ደህንነቱ የተጠበቀ አሽከርካሪ እንድትሆኑ ለመርዳት የተዘጋጀ ነው። **በውስጡም ስለ ፔንስልቬንያ የማሽከርከር ህጎች አካትቶ የያዘ ነው። ይህ ሰነድ ህጎቹን ለመረዳት የሚረዳ መመሪያ እንጂ የፔንስልቬንያ አሽከርካሪዎችን እና ተሽከርካሪዎችን የሚመለከቱ ህጎች ሙሉ በሙሉ የያዘውን የፔንስልቬንያ የተሽከርካሪ ሕግን ሊተካ አይችልም። በተጨማሪም፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉት መረጃዎች ሊቀየሩ እንደሚችሉ ልብ ሊባል ይገባል።**

የዚህ መምርያ አላማ የመንጃ ፍቃድ ፈተና እንድትወስዱ እና የፔንስልቬንያ መንጃ ፍቃድ እንድታገኙ ዝግጁ እንድትሆኑ ማድረግ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉት የመንገድ ደንቦች እና የትራፊክ አጠቃቀም መመሪያዎች በፔንስልቬንያ ሕግ ለሚታወቁ ሦስት ዓይነት ተሽከርካሪዎች ማለትም ብስክሌቶች፣ በፈረስ የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች እና ሞተር ለተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች ሁሉ ተፈጻሚነት አላቸው። ለምሳሌ፣ ሁሉም ብስክሌተኞች፣ ልክ እንደ የሌሎች ተሽከርካሪዎች አሽከርካሪዎች በቀይ መብራቶች ላይ ማቆም ይጠበቅባቸዋል።

መንዳት እየተማሩ ከሆነ፣ ይህ መመሪያ ለአሽከርካሪዎች ፈተና የሚያስፈልግዎትን ሁሉንም መረጃ ይሰጥዎታል። ቀድሞውኑ የፔንስልቬንያ መንጃ ፈቃድ ካለዎት፣ ይህንን መመሪያ ከዚህ በፊት የረሷቸውን የትራፊክ ህጎችን ለማስታወስ፣ ወይም ፈቃዱን ካገኙ በኋላ ስለተጨመሩ ወይም ስለተቀየሩ ህጎች ለማወቅ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

አስፈላጊ

የእውቀት መለኪያ ፈተና ከመውሰድዎ በፊት የንግድ-ያልሆነ የተማሪዎች ፈቃድ ቅጽ DL-180 ን የግድ መሙላት ይጠበቅብዎታል።
ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ወላጅዎ ወይም አሳዳጊዎ የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፈቃድ ቅጽ DL-180TD ን መሙላት ይኖርባቸዋል።

ሁለቱንም ቅጾች በድረ-ገጻችን www.dmv.pa.gov ላይ በገጹ አናት ላይ ባለው “Forms and Publications” የሚለውን ማስፈንጠርያ በመጫን ማግኘት ይችላሉ።

ማሽከርከር ልዩ ጥቅም እንጂ መብት አይደለም። ይህ ልዩ ጥቅምም ከብዙ ኃላፊነቶች ጋር አብሮ ይመጣል። እጅግ አስፈላጊ ከሆኑ ኃላፊነቶች አንዱ መጠጥ ከጠጡ በፍጹም ማሽከርከር የለብዎትም የሚል ነው።

በአቅራቢያዎ ያለውን የመንጃ ፍቃድ መስጫ ማዕከል የሥራ ሰዓት ለማወቅ፣ ቅጾችንና መረጃዎችን ለማውረድ እንዲሁም የመንገድ የተግባር ፈተና ቀጠሮ ለመያዝ የፔንዶትን (PennDOT) የአሽከርካሪዎች እና የተሽከርካሪዎች አገልግሎት ድረ ገጽ www.dmv.pa.govን ይጎብኙ።

ድንቅ በሆነችው ክፍለ ሀገራችን (ክልላችን) በደህና ለማሽከርከር እና ልዩ ጥቅምዎትን ለመጠቀም እንዲችሉ ይህንን መመሪያ በሚገባ አንብቡ፤ የመንገድ ደንቦችን ተረዱ፤ እንዲሁም የተግባር ልምምዶችን ያድርጉ።

ይህ ሕትመት የሚሸጥ አይደለም።

የማውጫ ሰንጠረዥ

ምዕራፍ 1 - የንግድ-ያልሆነ የተማሪዎች ፈቃድ መረጃ 1
የተማሪ ፈቃድ ለማግኘት ስለማመልከት 1
የአካል ክፍል ለጋሽ የመሆን መለያ 2
የቀድሞ ወታደር የመሆን ማረጋገጫ መለያ (ስያሜ). 2
የማህበራዊ ደህንነት (የሶሻል ሴኩሪቲ) ቁጥር መረጃ 3
የፔንስልቬንያ የአይን እይታ መመዘኛዎች 3
የፔንስልቬንያ መንጃ ፈቃድ የሚያስፈልገው ማነው? 3
የታዳጊዎች የትምህርት ፍቃድ መረጃ 3
የታዳጊዎች (የጁኒየሮች) መንጃ ፍቃድ መረጃ 3
ምን አይነት የመንጃ ፍቃድ ክፍል (ክላስ) ነው የሚያስፈልግዎት?. 4
የመንጃ ፍቃድ ክፍሎች (ክላሶች) 4
ፈተናዎች 5
የእውቀት መመዘኛ ፈተና. 5
የመንገድየተግባር ፈተና 5

ምዕራፍ 2 - የትራፊክ መብራት ምልክቶች፣ የመንገድ ዳር ምልክቶች እና የትራፊክ መስመር ምልክቶች 7
የትራፊክ መብራት ምልክቶች 7
ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ የትራፊክ መብራቶች እንዲሁም የቀስት ምልክቶች 7
ብልጭ የሚሉ የትራፊክ መብራት ምልክቶች 8
የማይሰሩ የትራፊክ መብራቶች. 8
ራምፕ-መለኪያ የትራፊክ መብራት ምልክቶች 8
የመንገድ መስመር (ሌይን) አጠቃቀም የሚቆጣጠሩ የትራፊክ መብራት ምልክቶች. 8
የእግረኛ የትራፊክ መብራት ምልክቶች 9
የትምህርት ቤት አከባቢ የትራፊክ መብራት ምልክቶች. 9
የባቡር ማቋረጫ የትራፊክ መብራት ምልክቶች 9
ምልክቶች. 10
የመቆጣጠሪያ ምልክቶች 10
የማስጠንቀቂያ ምልክቶች. 13
የመመሪያ ምልክቶች 19
የትራፊክ መስመር ምልክቶች 22
ምዕራፍ 2 ማጠቃለያ ጥያቄዎች 23
ምዕራፍ 2 የመልስ ቁልፍ 30

ምዕራፍ 3 - ማሽከርከርን መማር. 31
በመጀመሪያ ደህንነትን ማረጋገጥ. 31
የተሽከርካሪ ፍተሻዎች፡- ለመንዳት ስለ መዘጋጀት. 31
አሽከርካሪ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች 32
ትኩረት አለመስጠት 32
የጤና ምክንያቶች 33
አልኮል እና መንዳት. 33
አደንዛዥ እጾች እና ማሽከርከር. 34
የዕለት ተዕለት የማሽከርከር ክህሎቶች 35
ርቀትን ጠብቆ ስለማሽከርከር 35
ፍጥነትን መቆጣጠር. 38
መታጠፍ፣ የትራፊክ ፍሰትን መቀላቀል እና ማለፍ. 45
መገናኛ መንገዶች ላይ በአግባቡ ስለማሽከርከር 48
ኩርባዎች ላይ በአግባቡ ማሽከርከር 51
አውራ ጎዳናዎች ላይ እና የድልድይ መንገዶች ላይ ስለማሽከርከር 52
ፓርኪንግ. 52
በትይዩ መኪና የማቆም (ፓራለል ፓርኪንግ) ጠቃሚ ምክሮች. 53
የተለዩ ሁኔታዎች እና ድንገተኛ ሁኔታዎች. 54
የስራ ቀጠናዎች 54
በባቡር ሐዲድ መሻገሪያዎች. 55
መንገዱን ከእግረኞች፣ ከብስክሌተኞች፣ ከሞተር ብስክሌተኞች እና ከሞፔድ አሽከርካሪዎች ጋር መጋራት. 55
መንገዱን ከጭነት መኪናዎች እና ከአውቶቡሶች ጋር መጋራት 56
የትምህርት ቤት አውቶቡሶች 58
የአደጋ ጊዜ መኪናዎች እና ሁኔታዎች. 59
ለድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ቦታ የመልቀቅ ህግ 59
በፈረስ የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች እና በፈረስ የሚጓዙ ሰዎች . 59
በክፍት የጭነት መኪና ውስጥ ያሉ ተሳፋሪዎች 59
የበረዶ ማጽጃ መኪኖች 60
የመንገድ ላይ ቁጣን መቋቋም. 60
ድንገተኛ የመንዳት ሁኔታዎችን መፍታት 60
የቀብር ሥነ-ስርዓት ሰልፍ. 64
ምዕራፍ 3 ማጠቃለያ ጥያቄዎች 65
ምዕራፍ 3 የመልስ ቁልፍ 78

ምዕራፍ 4 - የመንዳት ታሪክ መረጃ .79
የፔንሲልቫኒያ የነጥብ አሰጣጥ ስርዓት. 79
ፖሊስ ካቆመዎት ምን ማድረግ አለብዎት. 80
አደጋዎች 81
ከፖሊስ መሸሽ ወይም ማምለጥ. 81
በአልኮል ወይም በህግ ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር ተጽዕኖ ስር ማሽከርከር 81
ከህጋዊ ዕድሜ በታች መጠጣት. 84
የመንጃ ፈቃድ ስምምነት (DLC) 84
ምዕራፍ 4 የማጠቃለያ ጥያቄዎች 86
ምዕራፍ 4 የመልስ ቁልፍ 88

ምዕራፍ 5 - ህጎች እና ተዛማጅ ጉዳዮች 89
ስም ወይም አድራሻ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ የሚያስፈልግ ማስታወቂያ 89
የመቀመጫ ቀበቶ ህግ 89
የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መቀመጫ ህግ 90
ለልጆች እና ለቤት እንስሳት የደህንነት ምክሮች 90
የአየር ከረጢት ደህንነት መረጃ 91
የአሜሪካውያን አካል ጉዳተኞች ህግ (ADA) 91
ለአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች. 92
ቆሻሻን መጣልን የሚከለክል ህግ 92
የተሽከርካሪ ደህንነት እና ልቀቶች ፍተሻ. 92
ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማለፍ ህጉ ነው. 92
የጽሑፍ መልእክት መላላክን የሚከለክል ሕግ. 93
አደገኛ ሁኔታዎችን ስለሚያመለክቱ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች ሕግ መታዘዝ 93

ምዕራፍ 6 - ማጣቀሻዎች. 94
የመንገድ ላይ የተግባር ፈተና እና ልዩ የነጥብ ፈተና ቀጠሮዎች . . 94
ለንግድ አለማዎች የማይውል መንጃ ፍቃድ የሶስተኛ ወገን የፈተና ፕሮግራም 94
በበይነመረብ ላይ የሚገኙ የዲፓርትመንት ቅጾች እና ህትመቶች . . 94
ክልል አቀፍ እና ካውንቲ አቀፍ ካርታዎች. 94
ሌላ መረጃ 94
511PA. 94
በካርቦን ሞኖክሳይድ መመረዝ 95

ምዕራፍ 1:
የንግድ-ያልሆነ የተማሪዎች ፈቃድ መረጃ

ይህ ምዕራፍ የፔንሲልቬንያን የተማሪዎች ፈቃድ ለማግኘት ማወቅ የሚያስፈልግዎትን መረጃ ያቀርባል። በዚህ ውስጥ የተብራሩት ጉዳዮች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

- የተማሪ ፈቃድ ለማግኘት ስለ ማመልከት
- ፈተናዎች

የተማሪ ፈቃድ ለማግኘት ስለማመልከት

በፔንስልቬንያ ውስጥ ተሽከርካሪ ከማሽከርከርዎ በፊት የተማሪ ፈቃድ ማውጣት አለብዎት። የመንጃ ፈቃድዎን ለማግኘት የእይታ ምርመራ፣ የዕውቀት መመዘኛ እና የመንገድ የተግባር ፈተናዎችን መውሰድ እና ማለፍ ይጠበቅብዎታል። ለንግድ-ላልሆነ የተማሪዎች ፈቃድ ማመልከቻ የሆነው DL-180 የሚሰራው፣ የአካል ምርመራዎ ከተደረገበት ቀን አንስቶ ለአንድ (1) አመት ያህል ነው፤ ሆኖም ግን የአካል ምርመራው የተደረገበት ቀን ከ የ16ኛ ዓመት የልደት ቀንዎ በፊት ከስድስት (6) ወር መብለጥ የለበትም።

ዕድሜዎ 16 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፣ ለንግድ አገልግሎት የማይውል የተማሪ ፈቃድዎን ለማግኘት ከዚህ በታች ያሉትን መምሪያዎችን ይከተሉ። ከ16ኛ ዓመት ልደትዎት በፊት ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት አይችሉም።

1. በድረ-ገጻችን www.dmv.pa.gov ላይኛው ክፍል ላይ ካለው ቅጾች እና ህትመቶች የሚለውን በመጫን የንግድ-ያልሆነ የተማሪ ፈቃድ ማመልከቻ የሆነውን DL-180 ማግኘት እና መሙላት ይችላሉ።
2. የጤና አገልግሎት ሰጪዎ የንግድ-ያልሆነ የተማሪ ፈቃድ ማመልከቻ በሆነው በ DL-180 ጀርባ ላይ መሙላት አለበት። ቅጹ ከ16ኛ ዓመት ልደትዎ ከስድስት (6) ወራት በፊት መሞላት የለበትም። ሁሉም መረጃዎች መሞላት አለባቸው።
3. የመንጃ ፈቃድ ፈታኙ የንግድ-ያልሆነ የተማሪ ፈቃድ ማመልከቻ የሆነውን DL-180 ቅጽ ላይ ያለው መረጃ የህክምና መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ካልቻለ የተማሪ ፈቃድዎ ሊዘገይ ይችላል። ተጨማሪ የሕክምና ምርመራዎችን ማድረግ ሊያስፈልግዎ ይችላል። የማሽከርከር ችሎታዎን በእጅጉ የሚጎዳ ሁኔታ ካለብዎ፣ ድርብ ቁጥጥር ያለው የተማሪ ፈቃድ (dual control learner's permit) እንዲያገኙ እና ሰርተፍኬት ባለው አስተማሪ ስር እንዲማሩ ሊጠየቁ ይችላሉ።
4. እድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ወላጅዎ፣ አሳዳጊዎ፣ የወላጆች ተተኪ ሰው ወይም 18 አመት የሞላቸው ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የትዳር አጋርዎ በድረ ገጻችን www.dmv.pa.gov ላይ በሚገኘው የቅጾች እና ህትመቶች አገናኝ ስር የሚገኘውን የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፈቃድ ፎርም DL-180TD መሙላት ይኖርባቸዋል። ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ በወላጅ ምትክ የቁም ሰው ወይም 18 ዓመት የሞላቸው ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የትዳር አጋርዎ አመልካቹን/አመልካችዋን አብረው መሄድ ካልቻሉ DL-180TD በወላጅ፣ አሳዳጊ፣ **<u>በወላጅ ምትክ በቆሙ ሰው ወይም በ18 ዓመት የሞላቸው ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የትዳር አጋር ፊት መፈረም ይኖርበታል።</u>** ትክክለኛ መታወቂያ መያዝ ያስፈልጋል፤ የአያት ስሞች የተለያዩ ከሆኑ ዝምድናን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያስፈልጋል። እድሜዎ ከ18 ዓመት በላይ ከሆነ ሁለት (2) የመኖሪያ አድራሻ ማረጋገጫዎችን ማቅረብ ይጠበቅብዎታል:-
    - ወቅታዊ የፍጆታ ክፍያዎች (ውሃ፣ ጋዝ፣ መብራት፣ ኬብል፣ ወዘተ)።
    - የግብር መዝገቦች።
    - የኪራይ ስምምነቶች።
    - W-2 ቅጽ።
    - አሁናዊ የጦር መሳሪያዎች ፈቃድ (ለዩናይትድ ስቴትስ ዜጎች ብቻ)።
    - የሞርጌጅ ሰነዶች።

መመሪያውን ካነበቡ እና ከላይ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች ከተከተሉ በኋላ የዕውቀት መመዘኛ ፈተናዎን ለመውሰድ ዝግጁ ሲሆኑ **ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነገሮች ይዘው ወደ መንጃ ፈቃድ መስጫ ማዕከል** ይምጡ:-

- ሞልተው ያጠናቀቁት የንግድ-ያልሆነ የተማሪ ፈቃድ ማመልከቻ የሆነውን DL-180 ቅጽ። **ይህን ቅጽ በፖስታ እንዳይልኩ።** እድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ፣ ሞልተው ያጠናቀቁትን የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፈቃድ ፎርም DL-180TD ይዘው መምጣትዎን እንዳይረሱ።
- የትውልድ ቀን እና መታወቂያ ማረጋገጫ። እነዚህ ሰነዶች ዋናዎች (ኦሪጅናሎች) መሆን አለባቸው፤ (ፎቶ ኮፒዎች ተቀባይነት **አይኖራቸውም**)።
- የእርስዎ የማህበራዊ ዋስትና (ሶሻል ሴኩሪቲ) ካርድ።
- ተፈጻሚ የሚሆኑ ክፍያዎች። (ማስታወሻ: እባክዎን ተቀባይነት ያላቸውን የክፍያ አማራጮች ለማየት የቅጹን ጀርባ ይመልከቱ)

እባክዎን ያስተውሉ: የልደት ቀንዎን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የመታወቂያ ዓይነቶች ከክፍያዎቹ ጋር የንግድ-ያልሆነ የተማሪዎች ፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ DL-180 ጀርባ ላይ ተዘርዝረዋል።

እይታዎን በጤና ባለሙያዎ ወይም በአይን ሐኪም ካልተመረመሩ፣ እይታዎን በመንጃ ፈቃድ መስጫ ማዕከል ውስጥ ምርመራ ይደረግልዎታል። መነጽር ወይም ኮንታክት ሌንሶችን የሚጠቀሙ ከሆነ እባክዎን ከእርስዎ ጋር ይዘው ይምጡ። ከዚያም በመቀጠል በዚህ መመሪያ ውስጥ የተገለጹትን ምልክቶች፣ ሕጎች፣ የመንዳት መመሪያዎች እና ደህንነታቸው የተጠበቁ ልምዶችን በተመለከተ የዕውቀት መመዘኛ ፈተናውን ይወስዳሉ። የዕውቀት መመዘኛ ፈተናውን ካለፉ በኋላ ፈታኙ ለአንድ (1) አመት የሚሰራ የተማሪዎች ፈቃድ ይሰጥዎታል። የተማሪ ፈቃድዎን ከተቀበሉ በኋላ ማሽከርከር መለማመድ መጀመር ይችላሉ። ፔንዶት (PennDOT) ታዳጊ አሽከርካሪዎች የመንገድ የተግባር ፈተናቸውን በዚህ ወቅት ላይ ቀጠሮ እንዲይዙ

ይመክራል፤ ነገር ግን የፈተናው ቀን በታዳጊው የተማሪ ፈቃድ ላይ ከተጻፈው ብቁ መሆን ከሚችሉበት ቀን በፊት መሆን የለበትም።

ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ፣ የመንገድ የተግባር ፈተና ከመውሰድዎ በፊት ቢያንስ 65 ሰዓታት ተሽከርካሪን በመንዳት ክህሎት ግንባታ ላይ ማዋል ይጠበቅብዎታል፤ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 10 ሰዓታት ምሽት እና አምስት (5) ሰዓታት ደግሞ በመጥፎ የአየር ሁኔታ ውስጥ መንዳት ይኖርብዎታል። ይህ ስልጠና ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጥሩ አሽከርካሪ ለመሆን የሚያስፈልጉትን ክህሎቶች ለመማር ያግዝዎታል።

ያስታውሱ፦ ቢያንስ 21 አመት የሞላው መንጃ ፍቃድ ያለው አሽከርካሪ ወይም ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም በወላጅ ምትክ የቆመ ሰው እና 18 አመት የሞላቸው ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው የትዳር አጋር መንጃ ፍቃድ ይዘው ሁል ጊዜ ከእርስዎ ጋር በተሽከርካሪው የፊት ወንበር ላይ በመሆን መጓዝ አለባቸው። በተጨማሪም ከ18 ዓመት በታች የሆኑ አሽከርካሪዎች በተሽከርካሪው ውስጥ ካሉ የደህንነት ቀበቶዎች ቁጥር በላይ ተሳፋሪዎች መያዝ አይችሉም።

ፈቃድዎን ከወሰዱ በኃላ አስገዳጅ የሆኑትን ስድስት (6) ወራት ከጠበቁ እና ቢያንስ 10 ሰአታት በምሽት ማሽከርከር እና አምስት (5) ሰአታት በመጥፎ የአየር ሁኔታ ውስጥ ማሽከርከርን ጨምሮ ያሳለፉትን የ65 ሰአታት የክህሎት ግንባታ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ካገኙ በኋላ የመንገድ የተግባር ፈተናዎን መውሰድ ይችላሉ። የተማሪ ፈቃድዎ ጊዜው ካለፈበት ወይም የመንገድ የተግባር ፈተናዎን በሶስት (3) ሙከራዎች ውስጥ ማለፍ ካልቻሉ የንግድ-ያልሆነ የተማሪ ፈቃድ ማመልከቻዎን ለማግኘት ለመጨመር/ለማራዘም/ለመተካት/ለመቀየር/ለማስተካከል ይችላሉ።

የተማሪ ፈቃድዎን ከፔንስልቬንያ ግዛት ውጭ ለመንዳት እየተጠቀሙበት ከሆነ፣ እባክዎን የተማሪ ፈቃድዎ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ የኢንሹራንስ ኩባንያዎን እና የሌላኛውን ግዛት የትራንስፖርት መምሪያ ጋር ያረጋግጡ።

በተማሪ ፈቃድዎ ላይ ያለ ማንኛውም መረጃ ትክክል ካልሆነ፣ ለፈተና ወደ መንጃ ፈቃድ ማዕከል ሲመጡ፣ ትክክለኛውን መረጃ የሚያሳይ ማስረጃ ይዘው በመምጣት ለፈታኙ ያሳዩ።

የዕውቀት መመዘኛ ፈተናውን ካላለፉ ፈታኙ የንግድ-ያልሆነ የተማሪ ፈቃድ ማመልከቻ የሆነውን DL-180 እና የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፈቃድ ቅፅ DL 180TD መልሶ ይሰጥዎታል። የእውቀት መመዘኛ ፈተናውን በማንኛውም ቀን እና ቦታ መውሰድ ይችላሉ፤ ነገር ግን አንድ ግዜ ብቻ ነው መፈተን የሚችሉት። ድጋሚ ሲፈተኑ ከእርስዎ ጋር ይዘው መምጣት ስላለቦት ቅጾችዎን ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ማስቀመጥ አለብዎት።

የአካል ክፍል ለጋሽ የመሆን መለያ

የፔንስልቬንያ መንጃ ፈቃድዎን በሚያድሱበት ጊዜ ሁሉ፣ በመንጃ ፈቃድዎ ላይ "የአካል ክፍል ለጋሽ" ("ORGAN DONOR") የሚል ስያሜ እንዲኖርዎት ይፈልጉ እንደሆነ የሚጠየቁ ይሆናል። ወደ ፎቶ መንጃ ፈቃድ መስጫ ቦታ ከመሄድዎ በፊት እባክዎን አስቀድመው ይወስኑ። በፎቶ መንጃ ፈቃድ ማዕከል የአካል ክፍል ለጋሽ ለመሆን "ፍቃደኛ መሆንዎ ሲገልጹ" "የአካል ክፍል ለጋሽ" የሚሉት ቃላት በመንጃ ፈቃዶት ላይ ይታተማሉ።

እድሜያቸው ከ18 አመት በታች የሆኑ አመልካቾች የአካል ክፍል ለጋሽነትን በመንጃ ፈቃዳቸው ላይ እንዲጻፍ መጠየቅ እና ማግኘት ይችላሉ፤ ሆኖም ግን ከወላጅ፣ ከአሳዳጊ፣ ከወላጅ ምትክ ወይም ከ18 ዓመት በላይ የሆናቸው ትዳር ጓደኛቸው የጽሁፍ ፍቃድ ማቅረብ አለባቸው። በወላጅ ወይም በአሳዳጊ ፈቃድ ቅጽ DL-180TD ላይ ተገቢውን ቦታ ላይ ምልክት በማድረግ ፍቅድ መስጠታቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ። የአካል ክፍል እና ቲሹ ልገሳ መረጃ ለማግኘት 1-877-DONOR-PA ን ያነጋግሩ።

እንዲሁም www.dmv.pa.gov ላይ ባለው ድረ-ገጾችን "የአካል ክፍል ለጋሽ" የሚል ስያሜን ወደ የእርስዎ የአሽከርካሪ መዝገብ ማከል ይችላሉ። በዚህ የአገልግሎት መስመር (ቻነል) አማካኝነት ከመንጃ ፈቃድዎ ጋር የሚይዙት ካርድ የማዘጋጀት እድል ይሰጥዎታል።

የአካል ክፍል ልገሳ ትረስት ፈንድ (ODTF (ኦ.ዲ.ቲ.ኤፍ))
ለገቨርነር ሮበርት ፒ. ኬይሲ ሜሞሪያል የአካል ክፍል እና ቲሹ ልገሳ ትረስት ፈንድ መለገስ ይችላሉ። ትረስት ፈንዱ በኮመንዌልዝ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የአካል ክፍሎች ልገሳ ፕሮግራሞችን ለመደገፍና ስለእነዚህ ፕሮግራሞች ለሕዝብ መረጃ ለማቅረብ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግ ይሆናል። ለዚህ ፈንድ መዋጮ ለማድረግ ፍላጎት ካለዎት የመንጃ ፈቃድዎ ቅጽ ላይ ምልክት ያድርጉ። ድጋፉ የመንጃ ፈቃድ ክፍያ ላይ የሚታከል ሲሆን ቅጽዎን ለፔንዶት (PennDOT) በሚልኩበት ወቅት ክፍያዎ ውስጥ መካተት ይኖርበታል።

የቀድሞ ወታደር የመሆን ማረጋገጫ መለያ (ስያሜ)

የዩናይትድ ስቴትስ ጦር ኃይሎች የቀድሞ ወታደር እንደነበሩ በግልጽ የሚያመለክተው የቀድሞ ወታደር የመሆን ማረጋገጫ መለያ (ስያሜ) መንጃ ፈቃድዎ ላይ እንዲታከል ማድረግ ይችላሉ። እንዲህ ለማድረግ ብቁ ለመሆንም፣ የተጠባባቂ አካል ወይም የብሄራዊ ጥበቃን ጨምሮ በዩናይትድ ስቴትስ ጦር ሃይሎች ውስጥ ያገለገሉና በክብር ባለሆኑ ሁኔታዎች ከእንደዚህ አይነት አገልግሎቶች ያልተባረሩ ወይም ያልተሰናበቱ መሆን አለብዎት።

የቀድሞ ወታደሮች ትረስት ፈንድ (VTF)
ለVTF (ቪ.ቲ.ኤፍ) ታክስ ተቀናሽ መዋጮ ማድረግ ይችላሉ። የእርስዎ መዋጮ ለፔንስልቬንያ የቀድሞ ወታደሮች እና ቤተሰቦቻቸው ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ የሚረዳ ይሆናል። ይህ ተጨማሪ መዋጮ የመደበኛ ክፍያው አካል ስላልሆነ፣ እባክዎ የለገሱትን መጠን በክፍያዎ ላይ ጨምረው ያያይዙ። እንዲሁም፣ የእርስዎ አስተዋፅዖ በአግባቡ መያዙን ለማረጋገጥ እባክዎ በቅጹ ላይ ያለ ተገቢውን ሳፅን ላይ ምልክት ያድርጉ።

የማህበራዊ ደህንነት (የሶሻል ሴኩሪቲ) ቁጥር መረጃ

ክፍል በፔንስልቬንያ የተሽከርካሪ ህግ ክፍል 1510(a) እና/ወይም 1609(a)(4) ድንጋጌዎች መሰረት የእርስዎን የማህበራዊ ደህንነት (የሶሻል ሴኩሪቲ) ቁጥር፣ ቁመት እና የአይን ቀለም በሕግ የመሰብሰብ ግዴታ አለበት። ይህ መረጃ የመንጃ ፈቃድ ማጭበርበርን ለመቀነስ በሚደረገው ጥረት እንደ መለያ መረጃ በመሆን ያገለግላል። የማህበራዊ ደህንነት (የሶሻል ሴኩሪቲ) ቁጥርዎ በይፋ በሚታየው የመንጃ ፈቃድ መረጃዎ ውስጥ አይካተትም። የማህበራዊ ደህንነት (የሶሻል ሴኩሪቲ) ቁጥር ማንነትን ለመለየት እንዲያስችል በክልል (በስቴት) የፈቃድ ባለስልጣናት ጥቅም ላይ እንዲውል የፌዴራል ሕግ ይፈቅዳል። የማህበራዊ ደህንነት (የሶሻል ሴኩሪቲ) ቁጥርዎ በእርሶ የተማሪ ፍቃድ ወይም በመንጃ ፍቃድ ላይ አይታተምም።

የፔንስልቬንያ የአይን እይታ መመዘኛዎች

በአንዱ አይንዎ ደካማ እይታ ቢኖርብዎትም መንጃ ፈቃድ ማውጣት ይችላሉ፤ ሆኖም ግን መነጽር ወይም ኮንታክት ሌንስ ማድረግ፣ በቀን ብርሀን ብቻ መንዳት ወይም የጎን መስተዋት ያላቸው ተሽከርካሪዎችን ብቻ እንዲነዱ ሊገደዱ ይችላሉ።

የማየት አቅምዎ የእይታ መመዘኛዎችን ማሟላት/ማለፍ ካልቻለ፣ ፈታኙ የአይን ምርመራ ቅጽ DL-102 ሪፖርት የሚሰጥዎት ይሆናል። የዓይን ጤና ባለሙያ፣ የአይን ቀዶ ጥገና ሃኪም ወይም የቤተሰብ ሐኪም አይንዎን እንዲመረምሩ እና ይህንን ቅጽ እንዲሞላልዎት ማድረግ አለብዎት። ቅጹ ከተሞላ በኋላ ምርመራውን ለመቀጠል ወደ መንጃ ፍቃድ መስጫ ተቋም መምጣት ይችላሉ።

የፔንስልቬንያ መንጃ ፈቃድ የሚያስፈልገው ማነው?

- ከአገራቸው ህጋዊ የውጭ መንጃ ፈቃድ ያላቸው ግለሰቦች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከገቡበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ወይም የውጭ ፈቃዳቸው እስኪያልቅ ድረስ ከሁለቱ አንዱ ቀድሞ እስኪደረስ ባለው ግዜ ውስጥ በፔንስልቬንያ ውስጥ መንዳት ይፈቀድላቸዋል። ዓለም አቀፍ የመንጃ ፈቃድ ቢኖርዎት ይበልጥ ተመራጭ ነው፤ ነገር ግን አስገዳጅ አይደለም። ከፈረንሳይ፣ ከጀርመን፣ ከኮሪያ እና ከታይዋን አገሮች ጋር በተደረገው የጋራ ስምምነት መሰረት የመንገድ የተግባር ፈተና ወይም የዕውቀት መመዘኛ ፈተና መውሰድ ሳያስፈልጎት ትክክለኛ የንግድ ያልሆነ መንጃ ፍቃድ ማስተላለፍ ይቻላል፤ ነገር ግን የአይን ምርመራ ማድረግ ይኖርብዎታል። (ከፖርቶ ሪኮ፣ ከፈረንሳይ ወይም ከጀርመን የመጣ መንጃ ፈቃድ ዝውውር በመጣበት ተመሳሳይ ቀን (ባመለከቱበት ቀን ውስጥ) ሊጠናቀቅ አይችልም።)
- በፔንስልቬንያ የሚኖሩ ቢያንስ 16 አመት የሞላቸው እና ባለ ሞተር ተሽከርካሪዎችን መንዳት የሚፈልጉ ግለሰቦች።
- በቅርቡ ወደ ፔንስልቬንያ የገቡ እና ፔንስልቬንያ ውስጥ ለመኖር ያሰቡ ሰዎች - ከሌላ ክልል ወይም ከካናዳ ህጋዊ መንጃ ፈቃድ ካለዎት ወደ ፔንስልቬንያ ከገቡ በ60 ቀናት ውስጥ የፔንስልቬንያ መንጃ ፈቃድ ማውጣት እና የሌላ ስቴቱን (ክልሉን) መንጃ ፈቃድ ማስረከብ አለብዎት።
- ህጋዊ መኖሪያቸው ፔንስልቬንያ የሆነ የዩናይትድ ስቴትስ ጦር ሃይሎች አባላት - ይህም በፔንስልቬንያ ውስጥ የሚገኙትን የተጠባባቂ ክፍሎች አባላትን የሚያጠቃልል ሲሆን፣ ወታደራዊ ያልሆነ ተሽከርካሪ ለመጠቀም መንጃ ፍቃድ ማውጣት ይኖርባቸዋል።

የታዳጊዎች የትምህርት ፍቃድ መረጃ

የእርስዎ የተማሪ ፈቃድ በመጀመሪያ የተማሪ ፈቃድ ላይ ከታተመበት ቀን ጀምሮ ለአንድ (1) ዓመት ብቻ የሚያገለግ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ውስጥ፣ እድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ የመንዳት መብትዎ ላይ የተወሰኑ ገደቦች አሉ። እነዚህም፡-

- ማሽከርከር የሚችሉት ቢያንስ 21 አመት በሆነው መንጃ ፍቃድ ባለው አሽከርካሪ ክትትል ስር ወይም ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ የወላጆች ምትክ ሆኖ የቆመ ሰው ወይም 18 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ እና መንጃ ፍቃድ ያለው የትዳር አጋር ክትትል ስር ብቻ ነው። ክትትል የሚያደርገው አሽከርካሪ ግለሰብ ከፊት ወንበር ላይ መቀመጥ አለበት።
- በሚያሽከረክሩት ተሽከርካሪ ውስጥ ከሚገኙት የወንበር የደህንነት ቀበቶዎች ብዛት በላይ ተሳፋሪዎችን መጫን አይፈቀድልዎትም።

የታዳጊዎች (የጁኒየሮች) መንጃ ፍቃድ መረጃ

ልክ እንደ የታዳጊዎች የተማሪ ፍቃድ ሁሉ የታዳጊዎች (የጁኒየሮች) መንጃ ፍቃድም የተወሰኑ ገደቦች አሉት። እነዚህም፡-

- ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ በወላጅ ምትክ ያለ ሰው ወይም 18 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የትዳር ጓደኛ ከእርሶዎ ጋር ካልሆኑ በስተቀር ከከሰዓት 11 ፒ.ኤም እስከ ንጋት 5 ኤ.ኤም ባለው ግዜው ውስጥ ማሽከርከር አይፈቀድሎትም።

  ነገር ግን፣ በሕዝብ ወይም በበጎ አድራጎት አገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉ ከሆነ፣ የእሳት አደጋ መከላከያ የበጎ ፈቃደኞች አባል ከሆኑ ወይም በነዚያ ሰዓታት ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ከሆነ ከምሽቱ ከከሰዓት 11 ፒ.ኤም እስከ ንጋት 5 ኤ.ኤም ድረስ ባለው ግዜ ውስጥ ማሽከርከር ይችላሉ። በነዚህ አጋጣሚዎች፣ የእንቅስቃሴዎችዎን ሊሆን የሚችል መርሃ ግብር የሚያመለክት ከቀጣሪዎ፣ ከአለቃዎ ወይም ከእሳት አደጋ መሪዎ የተረጋገጠ ቃለ መሃላ ወይም የፍቃድ የምስክር ወረቀት መያዝ አለብዎት። ይህ ማረጋገጫ ያለው ሰነድ ከመንጃ ፍቃድዎ ጋር መያዝ ይኖርብዎታል።
- በሚያሽከረክሩት ተሽከርካሪ ውስጥ ከሚገኙት የወንበር የደህንነት ቀበቶዎች ብዛት በላይ ተሳፋሪዎችን መጫን አይፈቀድልዎትም።
- ከእርስዎ ጋር በተሽከርካሪው ውስጥ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ በወላጅ ምትክ የቆመ ሰው ወይም 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የትዳር ጓደኛ ከሌለ በስተቀር፣ ቀጥተኛ ዝምድና ያላቸው የቤተሰብ አባል ያልሆኑ ከ18 ዓመት በታች የሆነ ከአንድ (1) በላይ ተሳፋሪን መያዝ አይፈቀድልዎትም። በመጀመሪያዎቹ ስድስት (6) ወራት በጁኒየር መንጃ ፈቃድ ከነዱ በኋላ ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ የወላጅ ምትክ፣ ወይም ዕድሚያቸው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የትዳር ጓደኛ ከእርስዎ ጋር በተሽከራካሪው ውስጥ ካልሆነ በስተቀር የቅርብ የቤተሰብ አባል ያልሆኑ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ከሶስት (3) የማይበልጡ ተሳፋሪዎች እንዲይዙ አይፈቀድሎትም። የጨመረው የተሳፋሪዎች መጠን ገደብ፣ ከዚህ በፊት ባጋጠመ

ግጭት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ጥፋተኛ የነበረ ወይም በማናቸውም የመንዳት ጥሰት የተከሰሰ ማንኛውንም ታዳጊ (ጁኒየር) አሽከርካሪ አያካትትም።

- ስድስት (6) ወይም ከዚያ በላይ ነጥቦችን ካከማቹ ወይም ከተቀመጠው የፍጥነት ገደብ በሰዓት 26 ማይል ወይም ከዚያ በላይ በማሽከርከር ጥፋተኛ ከተባሉ የግዴታ የ 90 ቀናት እገዳ ይጣልብዎታል።
- ለአንድ (1) አመት ያህል የጀማሪ (ጁኒየር) መንጃ ፍቃድ ከያዙ በኋላ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ካሟሉ መደበኛ መንጃ ፍቃድ ሊያገኙ ይችላሉ:-
  - በፒ.ኤ (PA) የትምህርት መምሪያ የፀደቀውን የአሽከርካሪ ማሰልጠኛ ትምህርት (ኮርስ) ማለፍ አለብዎት።
  - ለአንድ (1) አመት ያህል እርስዎ በከፊል ወይም ሙሉ ጥፋተኛ የሚሆኑበት የትራፊክ አደጋ ውስጥ ተሳታፊ አለመሆን (አደጋ አለማድረስ)።
  - ለአንድ (1) አመት በማንኛውም የፔንስልቬንያ ተሽከርካሪ ህግ ጥሰት ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው አለመገኘት።
  - የወላጅዎ፣ የአሳዳጊዎ፣ የወላጅ ተተኪ ወይም ቢያንስ 18 ዓመት የሞላቸው የትዳር ጓደኛዎ ፈቃድ ሊኖሮት ይገባል።

እነዚህን መስፈርቶች ካሟሉ ከታዳጊ (ጁኒየር) መንጃ ፍቃድነት ወደ መደበኛ መንጃ ፍቃድ ለመቀየር የሚያስፈልገውን DL-59 ቅጽ በመሙላት ለመደበኛ መንጃ ፍቃድ ማመልከት ይችላሉ። 18 አመት ሲሞላዎት የእርስዎ የታዳጊ (ጁኒየር) መንጃ ፍቃድ በቀጥታ (በራስ ሰር) መደበኛ መንጃ ፍቃድ ይሆናል።

ምን አይነት የመንጃ ፍቃድ ክፍል (ክላስ) ነው የሚያስፈልግዎት?

በፔንስልቬንያ፣ የመንጃ ፈቃዶች የሚሰጡት በሚያሽከረክሩት የተሽከርካሪ ክፍል እና ዓይነት መሰረት በማድርግ ነው። ስለዚህ ሊኖርዎት የሚገባው የመንጃ ፍቃድ ክፍል (ክላስ) በዋነኝነት እርስዎ በሚጠቀሙት የተሽከርካሪ ዓይነት ላይ የተመሰረተ ነው። በአብዛኛው የፔንስልቬንያ መንጃ ፍቃድ ለማግኘት የሚያመለክቱ ሰዎች መደበኛ ተሳፋሪዎችን የሚጭኑ ተሽከርካሪዎች፣ ፒክ አፕ መኪኖች ወይም የቫኖች አሽከርካሪዎች ናቸው። **ይህ መመሪያ እነዚህ አይነት ተሽከርካሪዎችን ለመንዳት የሚያስፈልገውን የንግድ-ያልሆነ Class C (የክፍል ሲ) መንጃ ፍቃድ ለማውጣት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ ነው።**

የመንጃ ፍቃድ ክፍሎች (ክላሶች)

- **CLASS A (ክፍል ኤ) (ቢያንስ 18 ዓመት):-** አጠቃላይ የተሽከርካሪ ክብደት ከተጎታቾች አንድ ላይ 26,001 ፓውንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ እንዲሁም የሚጎተት/ቱ ተሽከርካሪ/ዎች ከ10,000 ፓውንድ በላይ ክብደት ያላቸውን ተሽከርካሪዎች መንዳት ያስፈልጋል። ምሳሌ:- የሚጎትተው ተሽከርካሪ 11,000 ፓውንድ ሲመዘን እና ተጎታች ተሽከርካሪው ደግሞ 15,500 ፓውንድ ሲሆን (ጠቅላላ ጥምር ክብደት 26,500 ፓውንድ) ክብደት ያለው የመዝናኛ ተሽከርካሪ በሚሆንበት ወቅት።
- **Class B (ክፍል ቢ) (ዝቅተኛው ዕድሜ 18):-** ከ26,000 ፓውንድ በላይ ክብደት ያለው ነጠላ ተሽከርካሪ መንዳት ያስፈልጋል። ለምሳሌ:- 26,001 ፓውንድ ወይም ከዚያ በላይ ክብደት ያላቸው የመኪና ቤቶች (ሞተር ሆምስ)።
- **CLASS C (ክፍል ሲ) (ዝቅተኛው ዕድሜ 16):-** ፣ CLASS C የሚሰጠው CLASS M መመዘኛ ከሚያስፈልጋቸው፣ እና የ CLASS A ወይም CLASS B መመዘኛዎችን ለማያሟሉ ብቃታቸውን ላሳዩ እድሜያቸው 16 ዓመት ለሆኑ ሰዎች የC መንጃ ፈቃድ ይሰጣል። የእሳት አደጋ መከላከያ ኃላፊ ወይም የነፍስ አድን ወይም የአደጋ ጊዜ ቡድን ኃላፊ ፈቃድ ያለው ማንኛውም የእሳት አደጋ ሰራተኛ ወይም የነፍስ አድን ወይም የአደጋ ጊዜ ቡድን አባል የሆነ CLASS C መንጃ ፍቃድ ያለው ለእሳት አደጋ መከላከያ መምሪያ፣ ለነፍስ አድን ወይም ለአደጋ ጊዜ ቡድን ወይም ለማዘጋጃ ቤት የተመዘገበ ማንኛውንም የእሳት አደጋ ወይም የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪ እንዲያሽከረክር ይፈቀድለታል። CLASS C መንጃ ፍቃድ ያለው ሰው አውቶማቲክ ማርሽ ቦክስ ያለው በሞተር የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ሳይክል ማሽከርከር ይችላል፤ ይህ ሞተር ሳይክል 50 ሲሲ ወይም ከዚያ በታች የሆነ የሲሊንደር አቅም ያለው ወይም ሶስት ጎማ ያለው የተዘጋ ካቢኔ ያለው መሆን አለበት።
- **CLASS M (ክፍል ኤም) (ዝቅተኛው ዕድሜ 16):** CLASS M መንጃ ፍቃድ ሞተር ሳይክል ወይም በሞተር የሚንቀሳቀስ ሳይክል ለመንዳት ብቁ መሆናቸውን ላሳዩ 16 አመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የሚሰጥ ነው። አንድ ሰው ሞተር ሳይክልን ወይም በሞተር የሚንቀሳቀስ ሳይክልን ለመንዳት ብቻ ብቁ ከሆነ የ CLASS M መንጃ ፈቃድ ይሰጠዋል። በሞተር የሚንቀሳቀስ ሳይክል ተጠቅመው ፈተናውን ከተፈተኑ በ መንጃ ፍቃዳቻን ላይ “8” የሚል የገደብ ምልክት የሚጻፍ ይሆናል። ይህ ገደብም ሞተርሳይክል እንዳያሽከረክሩ የሚከለክልዎት ይሆናል። ከሁለት (2) ጎማዎች በላይ ባለው ሞተር ሳይክል ላይ ፈተናውን ከወሰዱ "9" የሚል ምልክት በመንጃ ፍቃድዎ ላይ ይጻፋል። ይህ ገደብ ባለ ሁለት ጎማ ሞተር ሳይክል እንዳትነዱ ይከለክዎታል። እባክዎን የፔንስልቬንያ የሞተር ሳይክል የአሽከርካሪዎች መመሪያ PUB 147 ወይም በፔንዶት (PennDOT) አሽከርካሪዎች እና ተሽከርካሪዎች አገልግሎቶች ድህረ ገጽ በሚገኘው የሞተር ሳይክል መረጃ ማዕከል ውስጥ የሞፔዶች፣ የሞተር የሚነዱ ሳይክሎች እና የሞተር ሳይክሎች መረጃን ይመልከቱ።
- **ንግድ ነክ ክፍል A፣ B ወይም C:** የንግድ መንጃ ፍቃድ የሚፈልጉ አሽከርካሪዎች ለፈተና ለመዘጋጀት የሚያስፈልገውን ዝርዝር መረጃ የያዘውን የፔንስልቬንያ የንግድ አሽከርካሪ መመሪያ PUB 223 መውሰድ አለባቸው። ይህ መመሪያ በፔንዶት (PennDOT) አሽከርካሪዎች እና ተሽከርካሪዎች ድህረ ገጽ በንግድ አሽከርካሪ መረጃ ማዕከል ውስጥ ማግኘት ይቻላል።

ፈተናዎች

የእውቀት መመዘኛ ፈተና

የእውቀት መመዘኛ ፈተናው የትራፊክ ምልክቶችን ፣የፔንስልቬንያ የመንዳት ህጎችን እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመንዳት ልምዶችን በተመለከተ ያለዎትን እውቀት ይለካል። የእውቀት መመዘኛ ፈተናው በጽሑፍ እና በድምጽ ቅርጸት በሚከተሉት ቋንቋዎች ማለትም በ ስፓኒሽ፣ አረብኛ፣ ቻይንኛ (ማንዳሪን)፣ ፈረንሳይኛ፣ ህንድኛ፣ ኮሪያኛ፣ ራሽያኛ፣ ዩክሬንኛ፣ ቬትናምኛ፣ እንግሊዝኛ፣ በርማኛ፣ ግሪክ፣ ጣልያንኛ፣ ጃፓንኛ፣ ኔፓሊኛ፣ ፖላንድኛ፣ ሶማሊኛ እና ኡርዱ በሁሉም የኮመንዌልዝ የአሽከርካሪ ፈቃድ መስጫ ማዕከላት ወስጥ ፈተናውን መውሰድ ይችላል። የእውቀት መመዘኛ ፈተናውን ከወደቁ በሚቀጥለው የስራ ቀን ፈተናውን እንደገና እንዲወስዱ ይፈቀድልዎታል። **ህጋዊ የሆነ የተማሪ ፍቃድ ለማግኘት መጀመርያ ይህን ፈተና በውጤታማነት በማለፍ ማጠናቀቅ አለብዎት።**

የእውቀት መመዘኛ ፈተናው ከ18 ያልበዙ ምርጫ ጥያቄዎችን ያካትታል። ፈተናውን ለማለፍ ቢያንስ 15 ጥያቄዎችን በትክክል መመለስ አለብዎት። በሚያሽከረክሩበት ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ የመንዳት ሁኔታዎች በድረገጻችን (www.dmv.pa.gov/Driver-Services/Teen-Drivers/Pages/default.aspx#.VpAM5aMo670) በታዳጊ (በጁኒየር) ሹፌር መረጃ ማእከል እና የዚህ መመርያ መጽሃፍ የኦንላይን እትም በታዳጊ ወጣት አሽከርካሪዎች መረጃ ማዕከል ውስጥ ማግኘት ይቻላሉ። በቀኝ በኩል ያሉትን የQR ኮዶች በመጠቀም የPA መንጃ ፍቃድ የልምምድ ፈተና መተግበሪያን ማውረድ ይችላሉ።

ለእርስዎ አንድሮይድ™ በቀጥታ ከጉግል ፕለይ ያውርዱ፡-
https://play.google.com/store/apps/details?id=com.nicusa.pdta

የPA የመንጃ ፈቃድ ፈተና ማለማመጃ መተግበሪያ

ለእርስዎ iOS Device™ በቀጥታ ከአፕ ስቶር ያውርዱ፡-
https://itunes.apple.com/us/app/pa-drivers-license-practice/id925842053?mt=8

የመንገድ የተግባር ፈተና

ዕድሚያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ ታዳጊ አሽከርካሪዎቻችን የክህሎት ፈተናቸውን እስከ ስድስት (6) ወራት ቀድመው ቀጠሮ እንዲያስይዙ እንፈቅዳለን። ታዳጊ አሽከርካሪዎች አስቀድመው እንዲያቅዱ እና በተቻለ ፍጥነት ቀጠሮ እንዲይዙ ይበረታታሉ። ወጣት አሽከርካሪዎቻችን ይህንን እድል በአግባቡ እንዲጠቀሙ እናበረታታለን።

የንግድ-ያልሆነ የመንገድ የተግባር ፈተና ለመውሰድ ቀጠሮዎች ግዴታ ማስያዝ አለባቸው። የመንገድ የተግባር ፈተናዎን በአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ አገልግሎቶች ድህረ-ገጽ ማለትም በwww.dmv.pa.gov. በኩል ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ። የኢንተርኔት አገልግሎት ከሌልዎት፣ የመንጃ ፈቃድ የተግባር ፈተናውን ወደ 1-800-423-5542 በመደወል ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ።

በተጨማሪም፣ ፔንዶት (PennDOT) የክህሎት መመዘኛ ፈተናውን ገበያውን ያገናዘበ ክፍያ ለሚያስከፍሉ ለሶስተኛ ወገን ቢዝነሶች እንዲያስተዳድሩ ፈቃድ ሰጥቷል። ሁሉም የሶስተኛ ወገን ፈታኞች በፔንዶቲ (PennDOT) እውቅና ያላቸው ሲሆን፣ ፈተናውም በፔንዶቲ (PennDOT) የመንጃ ፈቃድ መስጫ ማዕከል ከሚሰጠው ፈተና ጋር አንድ ዓይነት ነው። በአካባቢዎ ስለ ሚገኙ የሶስተኛ ወገን ፈታኞች ዝርዝር ለማግኘት፣ www.dmv.pa.govን ይጎብኙ።

የመንገድ የተግባር ፈተናዎትን ከመፈተንዎ በፊት የሚከተሉትን ነገሮች ለፈታኙ ማቅረብ አለቦት:-
(ሁሉም እቃዎች ትክክለኛነት ሊኖራቸው እና ለመንገድ የተግባር ፈተናዎ ለሚፈተኑበት ተሽከርካሪ የሚሰሩ መሆን አለባቸው።)

- የእርስዎ ህጋዊ የተማሪ ፈቃድ።
- ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ቢያንስ ለ65 ሰዓታት ተሽከርካሪን የማሽከርከር ልምምድ ማድረግዎትን የሚያረጋግጥ የDL-180C የወላጅ ወይም የአሳዳጊ ፊርማ ያስፈልግዎታል።
- ለመንገድ ላይ የተግባር ፈተና ሊፈተኑበት ላሰቡት ተሽከርካሪ የሚሰራ የምዝገባ ካርድ።
- ተሽከርካሪው በአሁኑ ጊዜ ኢንሹራንስ ያለው መሆኑ የሚገልጽ ማረጋገጫ።
- ወደ መንጃ ፈቃድ ማዕከል ከእርስዎ ጋር የሚመጣው ሰው ቢያንስ 21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ሰው ወይም ወላጅ፣ የወላጅ ተተኪ ወይም 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው የትዳር አጋር የሚሰራ ህጋዊ መንጃ ፈቃድ ያስፈልጋል።

ከላይ የተዘረዘሩትን ዋና ሰነዶች (ኮፒ ሳይሆን) ካላመጡ ፈተናውን መውሰድ አይችሉም።

ፈተናው ከመጀመሩ በፊት የመንጃ ፈቃድ ፈታኙ የተሽከርካሪዎ ትክክለኛ የምዝገባ ወረቀት፣ ወቅታዊ የኢንሹራንስ ሽፋን፣ ህጋዊ የሆነ የስቴት የፍተሻ ምልክት እና አስፈላጊ ከሆነም የሚሰራ የብክለት መቆጣጠሪያ ተለጣፊ ምልክት መኖሩን የሚያረጋግጥ ይሆናል። በተሽከርካሪዎ ላይ ያሉ መብራቶች፣ ጥሩንባዎች (ክላክሶች)፣ ብሬኮች (ፍሬኖች)፣ የንፋስ መከላከያ መጥረጊያዎች፣ የማዞሪያ የትራፊክ መብራት ምልክቶች፣ መስተዋቶች፣ በሮች፣ መቀመጫዎች እና ጎማዎች በትክክል የሚሰሩ መሆናቸውንና የደህንነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ፍተሻ የሚደረግበት ይሆናል። የተሽከርካሪዎ ማንኛውም ክፍል ደህንነቱ ያልተጠበቀ ወይም የስቴት ፍተሻ መስፈርቶችን የማያሟላ ከሆነ የመንገድ የተግባር ፈተናውን እንዲወስዱ አይፈቀድልዎትም። ተሽከርካሪዎ የመቀመጫ የደህንነት ቀበቶዎች ያለው ከሆነ ንጹህ መሆናቸውን እና ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸውን ያረጋግጡ። እርስዎ ሆኑ ፈታኙ በመንገድ ላይ በሚደረገው የተግባር ፈተና ወቅት የመቀመጫ የደህንነት ቀበቶ ማሰር ይጠበቅብዎታል።

ተሽከርካሪዎ ይህንን ፍተሻ ካለፈ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መንዳት መቻልዎን ለማረጋገጥ ፈታኙ የሚፈትኖት ይሆናል።

በአደገኛ ሁኔታ የሚያሽከረክሩ ከሆነ፣ ህጉን የሚጥሱ ከሆነ፣ አደጋ የሚያስከትሉ ከሆነ፣ የፈታኙን መመሪያዎች ካልተከተሉ ወይም በሚያሽከረክሩበት ወቅት በጣም ብዙ ስህተቶችን ከፈጸሙ የመንገድ የተግባር ፈተናውን ይወድቃሉ።

ፈታኙ የመንገድ ላይ ፈተናውን ከመውሰድዎ በፊት የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ሊጠይቅዎት ይችላል:-

- **የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያዎች:-** ክላክስ ማድረግ፣ መብራቶች (የፓርኪንግ መብራቶች፣ የአጭር እና የረጅም ርቀት የግንባር መብራቶች፣ የማዞሪያ ምልክቶች) እንዲያበሩ/እንዲያጠፉ፣ የንፋስ መከላከያ መጥረጊያ እንዲያንቀሳቅሱ፣ የፓርኪንግ (የድንገተኛ) ፍሬን እንዲይዙ፣ ባለ 4-መንገድ የድንገተኛ አደጋ መብራቶች እንዲያበሩ/እንዲያጠፉ፣ በረዶ ማቅለጫ ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን እንዲጠቀሙ ሊያዝዎት ይችላል። ማንኛውንም የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ በአግባቡ መጠቀም አለመቻል የመንገድ የተግባር ፈተናውን እንዲወድቁ ሊያድርግዎት ይችላል።
- **በትይዩ መኪና ማቆም (ፓራለል ፓርኪንግ):-** ተሽከርካሪዎን በሁለት ቀጥ ያሉ ምሰሶዎች መካከል ባለው በ24 ጫማ (feet) ርዝመት እና በስምንት (8) ጫማ ስፋት ባለው ቦታ ላይ ከመሃል ላይ ያቁሙ። ተሽከርካሪዎ ሙሉ በሙሉ በተቀባው ቦታ ውስጥ መግባት አለበት፤ በተጨማሪም የፊትና የኋላ ምሰሶዎችን መንካት፣ የተቀባውን መስመር ማለፍ ወይም የመንገድ ጠርዝ ላይ መውጣት አይፈቀድም። የሚፈቀድልዎት የሙከራ መጠን ከሶስት (3) ያልበለጡ ማስተካከያዎችን በመጠቀም ተሽከርካሪዎን በተሳካ ሁኔታ ለማቆም አንድ (1) ሙከራ ብቻ ነው።

ማሳሰቢያ:- የላቀ የመኪና ማቆሚያ መምሪያ ዘዴ (ራሳቸዉን ፓርክ ማድረግ የሚችሉ ተሽከርካሪዎች) ያላቸዉ ተሽከርካሪዎች ፈተናውን ለመፈተን አገልግሎት ላይ ሊዉሉ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ ራሱን የማቆም አቅሙ ማጥፋት የግድ ይላል፤ በተጨማሪም በመንገድ ላይ በሚደረግ የተግባር ፈተና ጊዜ መጠቅም አይፈቀድም።

በመንገድ ላይ በሚደረገው የተግባር ፈተና ወቅት ተሳፋሪዎ ፈታኙ ብቻ ነው። የመንገድ የተግባር ፈተናው በሚጀመርበት ጊዜ ወዴት እንደሚያሽከረክሩ እና ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎችን እንደሚያደርጉ ይነገረዎታል። **የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን፣ የማቆሚያ ምልክቶችን እና የትራፊክ መብራቶችን ሲያጋጥምዎት ምን እንደሚያደርጉና እንዴት እንደሚታዘዙ ከፍተኛ የሆነ ክትትል ይደረግብዎታል።**ተሽከርካሪዎን እንዴት እንደሚቆጣጠሩ፣ ከሌሎች አሽከርካሪዎች ጋር ለመግባባት የማዞሪያ የትራፊክ መብራት ምልክቶች አጠቃቀምዎት ወይም በፈተናው ወቅት አስፈላጊ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያዎችን እንዴት እንደሚጠቀሙ ፈታኙ የሚመለከት ይሆናል።

በፔንዶት (PennDOT) መንጃ ፍቃድ ማዕከል የመንገድ የተግባር ፈተናውን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ፣ መንጃ ፍቃድዎን ወዲያውኑ እዚያው ይሰጦታል።

በመንገድ ላይ በሚደረገው የተግባር ፈተና የሚወድቁባቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው:-

(እነዚህ የመንገድ ላይ ለሚደረገው የተግባር ፈተና ሊወድቁ የሚችሉባቸው አንዳንድ ምሳሌዎች ናቸው)

- ማንኛውንም የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያዎችን በአግባቡ መጠቀም አለመቻል
- ማንኛቸውም የትራፊክ ህጎችን መጣስ (ለምሳሌ:- የቁም ምልክትን አለማክበር)
- በአደገኛ ሁኔታ ወይም በግዴለሽነት ማሽከርከር
- ደህንነቱ በተጠበቀ የመንዳት ልምምዶች ውስጥ ስህተቶችን መፈጸም
- ፈታኙ የሚሰጠውን መመሪያ አለመከተል
- የትራፊክ አደጋን ማስከተል
- የመታጠፊያ የመብራት ምልክቶችን አለመጠቀም

ዕድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ እና የመንገድ የተግባር ፈተናን ከወደቁ፣ የፔንስልቬንያ ህግ ፈተናውን እንደገና ከመውሰድዎ በፊት ሰባት (7) ቀናት እንዲቆዩ ያስገድድዎታል። ይህ ፈተናውን እንደገና እስኪወስዱ ድረስ የሚደረገው መዘግየት፣ ለመለማመድ እና የመንዳት ችሎታዎን እንዲያዳብሩ እድል ይሰጥዎታል። የመንገድ የተግባር ፈተናን የተማሪ ፍቃድ ከማብቃቱ በፊት ለማለፍ በእያንዳንዱ የለማጅ ፍቃድ ሶስት (3) እድሎች አሉት። ለሶስተኛ ግዜ ከወደቁ በኋላ፣ የለማጅ ተማሪ ፈቃድ ለማራዘም እንደገና ማመልከት አለብዎት።

የመንገድ የተግባር ፈተናዎን ከሶስት (3) ሙከራዎች በኋላ ካላለፉ ወይም የለማጅ ተማሪ ፈቃድዎ ካለቀ፣ የንግድ ያልሆነ የተማሪ ፍቃድ (DL-31) ለመጨመር/ለማራዘም/ለመተካት/ለመቀየር/ለማስተካከል ማመልከቻ መቀበል ይችላሉ። የአካል ምርመራዎን ካደረጉበት ቀን ጀምሮ በ (3) ዓመታት ውስጥ የመንገድ የተግባር ፈተናውን ካላለፉ፣ ሌላ የንግድ ነክ ያልሆነ የለማጅ ተማሪ ፈቃድ ለማግኘት DL-180 ቅጽ በሞምላት ማመልከት እና የእውቀት መመዘኛ ፈተናውን እንደገና መውሰድ ይኖርብዎታል።

ምዕራፍ 2:
የትራፊክ መብራት ምልክቶች፣ የመንገድ ዳር ምልክቶች እና የትራፊክ መስመር ምልክቶች

ይህ ምዕራፍ ስለ ፔንስልቬንያ መንገዶች ማወቅ ያለብዎትን መረጃ ይሰጥዎታል። የሚከተሉትን ይሸፍናል፦

- የትራፊክ መብራት ምልክቶች
- የመንገድ ዳር ምልክቶች
- የትራፊክ መስመር ምልክቶች

የትራፊክ መብራት ምልክቶች



የተሽከርካሪዎችን እና እግረኞችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የትራፊክ መብራት ምልክቶች በመገናኛዎች ወይም መስቀለኛ መንገዶች ላይ ተተክለዋል። የትራፊክ ምልክቶች በአቀባዊ መስመሮች ወይም በአግድም መስመሮች የተደረደሩ ናቸው። በአቀባዊ ሲደረደሩ ሁልጊዜ ቀይ ከላይ አረንጓዴ ከታች ይሆናል። በአግድም ሲደረደሩ ሁልጊዜ ቀይ በግራ በኩል አረንጓዴ ደግሞ በቀኝ በኩል ይሆናል።

ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ የትራፊክ መብራቶች እንዲሁም የቀስት ምልክቶች

ቋሚ ቀይ መብራት ሲበራ ምልክት በተደረገበት የማቆሚያ መስመር ወይም የእግረኛ ማቋረጫ ላይ ከማቋረጥዎ በፊት ማቆም አለቦት። ምንም አይነት መስመሮች ያላዩ እንደሆነ መገናኛው ወይም መስቀለኛ መንገዱ ጋር ከመድረስዎ በፊት ያቁሙ። ለመጀመር አረንጓዴ መብራት እስኪመጣ ድረስ ይጠብቁ።

በመገናኛው ወይም መሰቀለኛ መንገዱ ላይ **ቀይ መብራት ሲኖር መታጠፍ ክልክል ነው** የሚል ምልክት ካልተለጠፈ በስተቀር መብራቱ ቀይ ሲሆን ወደ ቀኝ መታጠፍ ይችላሉ። መጀመሪያ ማቆም፣ እግረኞች እና ሌሎች ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ እና ቅድሚያ መስጠት አለቦት።

እንዲሁም በግራ መስመር ላይ ከሆኑ እና ከባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ ወደ ሌላ ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ እየታጠፉ ከሆነ ምልክቱ እንዳይታጠፉ የሚነግርዎት ካልሆነ በስተቀር፣ በቀይ መብራት ላይ ካቆሙ በኋላ ወደ ግራ መታጠፍ ይችላሉ። በመጀመሪያ ማቆም እና ለእግረኞች እንዲሁም ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለቦት።

ቋሚ ቢጫ መብራት በቅርቡ ቀይ መብራት እንደሚበራ ይነግርዎታል። ወደ መገናኛው ወይም መስቀለኛ መንገዱ እየነዱ እያለ ቢጫ መብራት ቢታይ ፍጥነትዎን ቀነስ በማድረግ ለማቆም ይዘጋጁ። በመገናኛው ውስጥ ከሆኑ ወይም በደህና ለማቆም የማይችሉ ከሆነ በጥንቃቄ በመቀጠል መገናኛውን ይለፉ።

ቋሚ አረንጓዴ መብራት ማለት መንገዱ ክፍት ከሆነ በመገናኛው በኩል መንዳት ይችላሉ። በምልክት ካልተከለከለ በቀር ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ መታጠፍ ይችላሉ። ነገር ግን በሚታጠፉበት ጊዜ በመገናኛው ውስጥ ላሉ ሌሎች ተሽከርካሪዎች እና እግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለብዎት።



ቋሚ ቀይ ቀስት ማለት ማቆም አለብዎት፣ ቀስቱ ወደሚያመለክተው አቅጣጫ መታጠፍ አይችሉም። ከመጀመርዎ በፊት አረንጓዴ ቀስት ወይም ብልጭ የሚል ቢጫ ቀስት እስኪታይ ድረስ ይጠብቁ። ቋሚ ቀይ መብራት የተፈቀዱት መታጠፊያዎች ለቋሚ ቀይ ቀስትም ይፈቀዳሉ።

ቋሚ ቢጫ ቀስት ማለት አረንጓዴው ቀስት ወይም ብልጭ የሚለው ቢጫ ቀስት የፈቀደው እንቅስቃሴ ሊያበቃ እንደሆነ እና ምልክቱ በቅርቡ ቀይ ይሆናል ማለት ነው። ወደ መገናኛው ከመግባትዎ በፊት ፍጥነትዎን በመቀነስ ሙሉ በሙሉ ለማቆም መዘጋጀት ይኖርብዎታል። በመገናኛው ውስጥ ከሆኑ ወይም ወደ መገናኛው ከመግባትዎ በፊት በደህና ማቆም ካልቻሉ አስቀድሞ በተፈቀደው ቀስት የጀመሩትን መታጠፍ በጥንቃቄ ማጠናቀቅ ይችላሉ።

ቋሚ አረንጓዴ ቀስት ማለት ቀስቱ ወደሚያመለክተው አቅጣጫ መታጠፍ ይችላሉ። በአረንጓዴ ቀስት ጊዜ ሲታጠፉ በመምጣት ላይ ያሉት ተሽከርካሪዎች በቀይ መብራት ስለሚቆሙ መታጠፍዎ "የተጠበቀ" ነው። አረንጓዴው ቀስት ወደ አረንጓዴ መብራት ከተቀየረ አሁንም ወደዚያ አቅጣጫ መታጠፍ ይችላሉ። ነገር ግን በመጀመሪያ ለእግረኞች እና ለሚመጡት ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለብዎት።

ብልጭ የሚሉ የትራፊክ መብራት ምልክቶች

ብልጭ የሚል ቀይ መብራት **አቁም** ከሚል ምልክት ጋር ተመሳሳይ ትርጉም አለው። በተሟላ ሁኔታ ማቆም አለብዎት። ከዚያ ሁለቱንም መንገዶች ይመልከቱ እና መገናኛው ነጻ ከሆነ በኋላ ብቻ መጓዝ ይቀጥሉ።

ብልጭ የሚል ቢጫ መብራት ማለት **ጥንቃቄ** ነው። ፍጥነትዎን ይቀንሱ፣ ይመልከቱ እና በጥንቃቄ ይቀጥሉ።



ብልጭ የሚል ቢጫ ቀስት ማለት ወደ ቀስቱ አቅጣጫ በጥንቃቄ መታጠፍ ይችላሉ።
ነገር ግን በመጀመሪያ ለሚመጣው ተሽከርካሪ እና ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለብዎት። ብልጭ የሚል ቢጫ ቀስት ባለበት ወቅት የእርስዎ መታጠፍ የተጠበቀ አይደለም። ምክንያቱም ወደፊት ለሚመጣው ትራፊክ አረንጓዴ መብራት ይኖራል።

የማይሰሩ የትራፊክ መብራቶች

የማይሰራ የትራፊክ መብራት ምልክት እንደ ባለአራት አቅጣጫ **የቁም** ምልክት ተደርጎ መወሰድ አለበት።

ራምፕ-መለኪያ የትራፊክ መብራት ምልክቶች

አንዳንድ አውራ ጎዳና መግቢያ ራምፖች በራምፕ መጨረሻ ላይ በቋሚ አረንጓዴ እና በቋሚ ቀይ መካከል የሚቀያየሩ የትራፊክ መብራት ምልክቶች አሏቸው። የራምፕ መለኪያ ምልክቶች በጣም በተጨናነቁ አውራ ጎዳናዎች ላይ የሚደረገውን የትራፊክ ፍሰት ለመቆጣጠር ያገለግላሉ እና አብዛኛውን ጊዜ በከፍተኛ የትራፊክ ሰዓታት ውስጥ ይሰራሉ። ወደ አውራ ጎዳና ከመግባትዎ በፊት አረንጓዴው ምልክት እስኪበራ መጠበቅ አለብዎት። በነጠላ-መንገድ ራምፖች ላይ መብራቱ ወደ አረንጓዴ በተለወጠ ቁጥር አንድ (1) መኪና ብቻ ወደ አውራ ጎዳና ሊገባ ይችላል። ባለብዙ የመንገድ መስመር ራምፖች ለእያንዳንዱ መስመር የራምፕ መለኪያ ይኖራቸዋል። **አረንጓዴው መብራት ወደ አውራ ጎዳና እንዳይገቡ አይከለክልዎትም - አሁንም ወደ አውራ ጎዳና ለመግባት ደህንነቱ የተጠበቀ ክፍተት መፈለግ ያስፈልግዎታል።**

የመንገድ መስመር (ሌይን) አጠቃቀም የሚቆጣጠሩ የትራፊክ መብራት ምልክቶች

ትራፊክን ለመቆጣጠር ልዩ የትራፊክ መብራት ምልክቶችም በቀጥታ በመንገድ መስመሮች (ሌይኖች) ላይ ሊቀመጡ ይችላሉ። እነዚህ በተለምዶ በክፍያ ዳሶች፣ በድልድዮች፣ በዋሻዎች እና በተጨናነቀ የትራፊክ ሰዓት ወደ ከተማ ወይም ከከተማ የሚወጣን የትራፊክ ፍሰት ለማቃለል የአንድ የተወሰነ መስመር የአቅጣጫ ለውጥ በሚኖርባቸው የከተማ ባለብዙ መስመር መንገዶች ላይ ያገለግላሉ። የሚከተሉት የትራፊክ መብራት ምልክቶች የአንድን መንገድ ወይም አውራ ጎዳና የተወሰኑ የመንገድ መስመሮች እንዴት መጠቀም እንደሚገባ ያሳያሉ።

በመንገድ ላይ የሚታይ ወደታች የሚያመለክት ቋሚ አረንጓዴ ቀስት የመንገድ መስመሩን (ሌይኑን) መጠቀም እንደሚችሉ ያሳያል።

በመንገድ ላይ የሚታይ ቋሚ ቢጫ "X" ማለት መስመሩን መቀየር አለብዎት ምክንያቱም የመስመሩ የአቅጣጫ ለውጥ በቅርቡ ስለሚቀየር ነው። የመንገድ መስመሩን በደህና ለመልቀቅ ይዘጋጁ።

በመንገድ መስመር ላይ የሚታይ ቀይ "X" መስመሩን መጠቀም አይፈቀድልዎትም ማለት ነው።

በመንገድ መስመሩ (ሌይን) ላይ የሚታይ ነጭ ቋሚ የአንድ አቅጣጫ የግራ መታጠፊያ ቀስት ማለት በዚያ መስመር ላይ ከሆኑ ወደ ግራ ብቻ መታጠፍ ይችላሉ።

በአንድ የመንገድ መስመር ላይ ያለ ነጭ፣ ቋሚ፣ የሁለት አቅጣጫ የግራ መታጠፊያ ቀስት ማለት በዚያ መስመር ላይ ከሆኑ ወደ ግራ ብቻ መታጠፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን መስመሩ ከተቃራኒ አቅጣጫ በሚመጡ የግራ መታጠፊያ አሽከርካሪዎች ጋር ይጋራሉ።

የእግረኛ የትራፊክ መብራት ምልክቶች

እግረኞች የተሽከርካሪዎች እና የእግረኛ የመብራት ምልክቶችን መከተል አለባቸው። መከተል ያለብዎት የእግረኛ የመብራት ምልክቶች **ይራመዱ እና አይራመዱ** የሚሉ መብራቶች ወይም የሚራመድ ሰው ምስል (የእግር ጉዞ ማለት ነው) እና ወደ ላይ ከፍ ያለ እጅ (አይራመዱ ማለት ነው) ናቸው። በመገናኛው ላይ የእግረኛ የመብራት ምልክቶች ከሌሉ እግረኞች ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ የትራፊክ መብራቶችን መከተል አለባቸው።

አንዳንድ ጊዜ እግረኞች በትራፊክ እና በእግረኛ የመብራት ምልክቶች ላይ ስላላቸው ኃላፊነት አያውቁም። የትራፊክ መብራት ምልክቱን ላይከተሉ የሚችሉ እግረኞችን ይጠንቀቁ። ሁልጊዜ ለእግረኞች ቅድሚያ ይስጡ።

ቋሚ **ይራመዱ** የሚል ምልክት ወይም የሚራመድ ሰው ምልክት ሲታይ መሻገር ይጀምሩ፣ ነገር ግን ሕጋዊ በሆነ መንገድ ቅድሚያውን ላይሰጡ የሚችሉ ተሽከርካሪዎችን ይጠብቁ።

አይራመዱ የሚለው ምልክት ብልጭ በሚልበት ጊዜ ወይም ወደ ላይ ከፍ ያለ እጅ ብልጭ ማለት ሲጀምር፦

a. በመንገድ ላይ ከሆኑ መሻገርዎን ይጨርሱ።
b. ከእግረኛው መንገድ ካልወጡ **መሻገር አይጀምሩ ።**

አይራመዱ የሚለው ቋሚ ምልክት ወይም የተነሳ እጅ በሚታይበት ጊዜ አያቋርጡ።

ማየት የተሳናቸው እግረኞች

ማየት የተሳነው እግረኛ ነጭ በትር ይዞ ወይም መሪ ውሻ ይዞ በአቅራቢያዎ ካለ ፍጥነትዎን ይቀንሱ፣ ሁልጊዜ መንገድን ይልቀቁለት፣ ከዚያም ተጠንቅቀው ይሂዱ። እግረኛውን ከጉዳት ወይም ከአደጋ ለመጠበቅ ተሽከርካሪዎን ለማቆም ይዘጋጁ።



የትምህርት ቤት አከባቢ የትራፊክ መብራት ምልክቶች

የትምህርት ቤት አካባቢ የትራፊክ መብራት ምልክቶች በትምህርት ቤት አካባቢ የፍጥነት ገደብ ምልክቶች ላይ የተቀመጡ ብልጭ የሚሉ ቢጫ ምልክቶች ናቸው። ቢጫ የትራፊክ መብራት ምልክቶች ብልጭ በሚሉበት ጊዜ ወይም በምልክቱ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ ወቅት ከ15 ማይል በሰዓት በላይ መጓዝ የለብዎትም። በትምህርት ቤት አካባቢ ውስጥ ከፍጥነት ገደብ በላይ መሄድ በመንዳት ታሪክዎ ላይ 3 ነጥቦችን የሚያስከትል ሲሆን የገንዘብ መቀጮም ይጣልብዎታል።

የባቡር ማቋረጫ የትራፊክ መብራት ምልክቶች

አሽከርካሪዎች የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ ምልክት ሲመለከቱ ወደ የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ እየቀረቡ መሆኑን ይረዳሉ። ወደ ባቡር ሀዲድ መሻገሪያ በምትጠጉበት ጊዜ ሁሉ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። የባቡር ሀዲዱን ከማቋረጥዎ በፊት ሁልጊዜ ወደ ሁለቱም አቅጣጫ መመልከት እንዲሁም የባቡር ድምፅ ወይም የትራፊክ መብራት ምልክቶች ማዳመጥ አለብዎት።

ባቡር እየመጣ መሆኑን የሚጠቁም የትራፊክ ምልክት ካለ የትኛውንም የባቡር ሀዲድ መሻገሪያ ላይ ማቆም ይጠበቅብዎታል። እነዚህ የትራፊክ ምልክቶች ብልጭ የሚሉ ቀይ መብራቶች፣ የወረደ መተላለፊያ በር፣ ምልክት የሚሰጥ ባንዲራ ወይም የባቡር ማስጠንቀቂያ ድምጽን ያካትታሉ። ወደፊት በፍፁም አይሂዱ ወይም በሩን ለማለፍ አይሞክሩ እንዲሁም የሚመጣን ባቡር ምልክት ችላ ማለት የለብዎትም። በባቡር ሐዲድ መሻገሪያ ላይ ምንም ምልክቶች ከሌሉ ባቡር ሲቃረብ ካዩ ወይም ከሰሙ ፍጥነትዎን መቀነስ እና ለማቆም መዘጋጀት አለብዎት።

ሁሉም ምልክቶች ከተጠናቀቁ በኋላ እና ምንም ባቡሮች ወደ መሻገሪያው እንደማይመጡ የሚያሳይ ማስረጃ ሲኖር ብቻ በጥንቃቄ ይቀጥሉ።.

ባቡር እየቀረበ ከሆነ እና ድምጽ ማሰማት ከጀመረ ወይም በግልጽ የሚታይ ከሆነ እና ለመሻገሪያው አደገኛ ቅርብነት ካለው ማቆም አለብዎት።

ባቡር ይምጣ አይምጣ ተሽከርካሪዎን በባቡር መስመር ላይ ማቆም የለብዎትም። የትራፊክ መብራት፣ የማቆሚያ ምልክት ወይም በሌላ ምክንያት ትራፊክ ከተጨናነቀ ተሽከርካሪዎ ከማንኛውም የባቡር ሀዲድ ውጭ የሆነ ቦታ ላይ እንዲቆም ያድርጉ።

የአውራ ጎዳና-ባቡር ሐዲድ መገናኛን እንዴት በደህና ማቋረጥ እንደሚችሉ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 3ን ይመልከቱ።

የባቡር መሻገሪያ ምልክቶችንና የትራፊክ ምልክቶችን ያክብሩ።

ምልክቶች

ምልክቶች በሶስት (3) መሰረታዊ ምድቦች ይከፈላሉ፦ መቆጣጠሪያ፣ ማስጠንቀቂያ እና አቅጣጫ አመልካች ምልክቶች። በእያንዳንዱ ምድብ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ምልክቶች ልዩ ቅርፅ እና ቀለም አላቸው።

የመቆጣጠሪያ ምልክቶች

የመቆጣጠሪያ ምልክቶች በህግ መሰረት ማድረግ የሚገባዎትን እና ማድረግ የሌለብዎትን ይነግሩዎታል። በእነዚህ ምልክቶች ላይ የተለጠፉት ደንቦች ስለ ፍጥነት ገደቦች፣ የትራፊክ አቅጣጫ፣ የመታጠፊያ ገደቦች፣ የመኪና ማቆሚያ ገደቦች ወዘተ ይመክሩዎታል። በመቆጣጠሪያ ምልክቶች ላይ ያሉትን መልእክቶች ካልተከተሉ ህግን በመጣስዎ ምክንያት መቀጣትና በመንዳት ታሪክዎ ላይ ነጥብ ሊጨመር ይችላል። በመቆጣጠሪያ ምልክቶች ላይ ያሉትን መልእክቶች ባለመታዘዝ የራስዎን እና የሌሎችን ደህንነት አደጋ ላይ ይጥላሉ - ለምሳሌ ፣ የማቆሚያ ምልክት ላይ ባለማቆም ፣ ለማለፍ ደህንነቱ ባልተጠበቀ ቦታ ሌላ መኪና በማለፍ ፣ ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ በበለጠ ፍጥነት በማሽከርከር ወይም በአንድ መንገድ መንገድ ላይ በተሳሳተ መንገድ በማሽከርከር።

ብዙውን ጊዜ የመቆጣጠሪያ ምልክቶች ጥቁር እና ነጭ ቀጥ ያሉ አራት ማዕዘኖች ወይም ካሬዎች ናቸው፣ ልክ እንደ **የፍጥነት ገደብ** ምልክቶች። አንዳንድ የመቆጣጠሪያ ምልክቶች ጥቁር፣ ነጭ እና ቀይ ናቸው፣ ልክ እንደ ልክ እንደ ክብ እና ሰረዝ ያለው **ወደ ግራ መታጠፍ የለም** የሚል ምልክት። ሌሎች የመቆጣጠሪያ ምልክቶች ቀይ እና ነጭ ናቸው፣ እንደ **የማቆሚያ፣ ቅድሚያ ይስጡ፣ አይግቡ** እና **የተሳሳተ መንገድ** የሚሉ ምልክቶች።

የቁም ምልክቱ በአውራ ጎዳና ላይ የሚያዩት ብቸኛው ባለ ስምንት ጎን (ባለ 8 ጎን) ምልክት ነው። **የቁም** ምልክት ባለበት መስቀለኛ መንገድ ላይ ሙሉ በሙሉ ማቆም አለብዎት፣ እግረኞችና ተሽከርካሪዎች መሻገራቸውን ካረጋገጡ በኋላ መሄድ አለብዎት። ሙሉ በሙሉ ሳያቆሙ ፍጥነትዎን መቀነስ ህገወጥ ነው።

የእግረኛ ማቋረጫ ወይም የቁም መስመር (ነጭ መስመር) ሲመለከቱ የተሽከርካሪዎ ፊትለፊት ክፍል የመጀመሪያውን መስመር ሳይነካ በፊት ያቁሙ። ተሽካሪካሪዎችን ማየት ካልቻሉ ለእግረኞች ቅድሚያ ይስጡ ከዚያም በግልጽ እስኪያዩ ድረስ ከመስመሩ አልፈው ቀስ ብለው ይሂዱ። የተሽካሪካሪዎችን ፍሰትና እግረኞች መኖራቸውን ካረጋገጡ በኋላ መንገዱ ክፍት ሲሆን ይሂዱ።

ይህ ምልክት ከማቆሚያ ምልክቶች ጋር አብሮም ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ ምልክት አሽከርካሪዎች ሳያቆሙ ወደ ቀኝ እንዲታጠፉ ያስችላቸዋል።

የአራት አቅጣጫ የቁም ምልክት ማለት በዚህ መገናኛ ላይ አራት የቁም ምልክቶች አሉ ማለት ነው። ከአራቱም አቅጣጫ የሚመጡ ተሽከርካሪዎች መቆም ይጠበቅባቸዋል። ወደ መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዱ ቀድሞ የደረሰው ተሽከርካሪ መጀመሪያ መንቀሳቀስ ይኖርበታል። ሁለት ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ወደ መገናኛው ከደረሱ በግራ በኩል ያለው አሽከርካሪ ለቀኝ በኩል ላለው አሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት። እርስ በእርሳቸው ፊት ለፊት የሚተያዩ ከሆነ ሊደረጉ የሚችሉ መታጠፊያዎችን በመመልከት ሁለቱም ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ መቀጠል ይችላሉ።

ቅድሚያ የመስጠት ምልክቶች የሶስት ማዕዘን (3-ጎን) ቅርፅ አላቸው። ይህንን ምልክት ሲመለከቱ ፍጥነትዎን ይቀንሱ፣ ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን ያረጋግጡ እንዲሁም ለእግረኞችና በሚያቋርጥ መንገድ ለሚመጡ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያውን መስጠት አለብዎት። ማቆም የሚኖርብዎት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። በተለመደው የተሽከርካሪዎች ፍሰት ላይ ጣልቃ ሳይገቡ በደህና ማድረግ በሚችሉበት ጊዜ ይቀጥሉ። **የማቆሚያ** ወይም **ቅድሚያ የመስጠት** ምልክት ባለባቸው ቦታዎች ላይ ከመቀጠልዎ በፊት በትራፊኩ መካከል በቂ ክፍተት መኖር እንዳለበት ያስታውሱ።

ይህ ምልክት ከአንድ መስመር ድልድይ ወይም ከመሬት በታች ማለፊያ ላይ ካለው ቅድሚያ የመስጠት ምልክት ጋር በአንድነት የሚውለው ባለ አንድ መስመር መንገድ ተቃራኒ አቅጣጫ ለሚመጡት መኪኖች ቅድሚያ እንዲሰጥ ለአሽከርካሪዎች ለማስገንዘብ ነው።



የባቡር መንገድ መስቀለኛ መንገድ ምልክት ይህ ምልክት የባቡር ሀዲዱ መንገድን በሚያቋርጥበት የባቡር ሀዲድ መሻገሪያ ላይ ተቀምጧል። የባቡር መንገድ መስቀለኛ መንገድን እንደ **ቅድሚያ የመስጠት** ምልክት አድርገው ሊመለከቱት ይገባል፤ ባቡር ሲቃረብ ካዩ ወይም ከሰሙ ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ለማቆም ይዘጋጁ። ስለ የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ ደህንነት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 3ን ይመልከቱ።

አይግቡ እና **የተሳሳተ መንገድ** የሚሉት ምልክቶች እንደ አንድ ስብስብ ሆነው ይሰራሉ። **አይግቡ** የሚል ምልክት በአንድ አቅጣጫ በሚሄዱ መንገዶች መግቢያ ላይ ይቀመጣል። ይህን ምልክት ሲያዩ አሁን ባሉበት አቅጣጫ ወደዚያ መንገድ ወይም መውጫ መሄድ የለብዎትም።

የተሳሳተ መንገድ የሚሉ ምልክቶች በአንድ አቅጣጫ በሚሄዱ ጎዳናዎች ወይም መወጣጫዎች ላይ ትንሽ ራቅ ብለው ይቀመጣሉ። ወደ ጎዳናው ወይም ወደ መወጣጫው በድንገት ከዞሩ ትኩረትዎን ለመሳብ እዚያ ተቀምጠዋል።

ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ ምልክት ተሽከርካሪዎች በምልክቱ በተጠቆመው አቅጣጫ ብቻ መንቀሳቀስ ይችላሉ ማለት ነው። በአንድ አቅጣጫ ብቻ በሚያሄድ ጎዳና በተቃራኒ አቅጣጫ ከዞሩ ከፊትዎ ከሚመጣ ተሽከርካሪ ጋር የመጋጨት አደጋ ሊያጋጥምዎት ይችላል።

የመንገድ አካፋይ ያላቸው አውራ ጎዳናዎች
ይህ ምልክት እርስዎ የሚሄዱበት መንገድ የመንገድ አካፋይ ካለው አውራ ጎዳና ጋር ይገናኛል ማለት ነው። የመንገድ አካፋይ ያለው አውራ ጎዳና ማለት በመሀል በሣር ወይም በብረት አጥር ተለያይተው የሚሄዱ ሁለት (2) መንገዶች ናቸው። በመጀመሪያው መንገድ ወደ ቀኝ ብቻ መታጠፍ ይችላሉ፤ በሁለተኛው መንገድ ደግሞ ወደ ግራ ብቻ መታጠፍ ይችላሉ።

ለጭነት መኪኖች አይፈቀድም

ለብስክሌቶች አይፈቀድም

እግረኞች መሻገር አይፈቀድላቸውም

ለጭነት መኪኖች አይፈቀድም፣ ለብስክሌቶች አይፈቀድም እንዲሁም እግረኞችም መሻገር አይችሉም

የጭነት መኪና አሽከርካሪዎች፣ የብስክሌት አሽከርካሪዎች እና የእግረኛ ተጠቃሚዎች እነዚህ ምልክቶች በተሰቀሉባቸው ቦታዎች ላይ መንገዱን መጠቀም አይችሉም።

የሚከተሉት ምልክቶች የተወሰኑ ተግባራት በማንኛውም ጊዜ ወይም በሁሉም ጊዜያት የተከለከሉባቸው ቦታዎች ላይ ይቀመጣሉ።

ወደ ተቃራኒ ማዞር አይፈቀድም

ይህ ምልክት ወደ ተቃራኒ ማዞርን ይከለክላል። ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ለመሄድ ሙሉ በሙሉ አይታጠፉ።

ወደ ቀኝ መታጠፍ አይፈቀድም

ይህ ምልክት ወደ ቀኝ መታጠፍ የተከለከለ መሆኑን ያሳያል። በዚህ መስቀለኛ መንገድ (መገናኛ) ውስጥ ወደ ቀኝ አይታጠፉ።

ወደ ግራ መታጠፍ አይፈቀድም

ይህ ምልክት ወደ ግራ መታጠፍ የተከለከለ መሆኑን ያሳያል። በዚህ መስቀለኛ መንገድ (መገናኛ) ውስጥ ወደ ግራ አይታጠፉ።

መኪና ማቆም አይፈቀድም

ይህ ምልክት በተለጠፈበት አካባቢ መኪና ማቆም አይፈቀድም።

ማለፍ አይፈቀድም
ይህ ምልክት በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚሄዱ ተሽከርካሪዎችን ማለፍ በማይፈቀድባቸው ቦታዎች ላይ ሊቀመጥ ይችላል። ብዙውን ጊዜ ቢጫ ቀለም ካለው **ማለፊያ የሌለበት ቀጠና** የሚል ምልክት ጋር አብሮ ይመጣል (“የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን” ይመልከቱ)።

የሚከተሉት **የመንገድ መስመር አጠቃቀም መቆጣጠሪያ ምልክቶች (አቅጣጫ)** ከ መገናኛዎች በላይ ወይም አጠገብ ባሉ የትራፊክ መስመሮች ላይ የሚፈቀዱትን እንቅስቃሴዎች ለማሳየት ይቀመጣሉ።

ይህ ምልክት ከፊት ለፊቱ ባለው መገናኛ ላይ በግራ መስመር ያለው ተሽከርካሪ ወደ ግራ መታጠፍ እንዳለበት እና በአጠገቡ ባለው መስመር ያለው ተሽከርካሪ ወደ ግራ መታጠፍ ወይም ቀጥታ መቀጠል እንደሚችል ያመለክታል።

በመሃል መስመር መንገድ ወደ ግራ ብቻ ይታጠፉ
ይህ ምልክት አንድ መስመር በሁለቱም አቅጣጫዎች ግራ ለሚታጠፉ ተሽከርካሪዎች ብቻ እንደተያዘ የሚጠቁም ሲሆን ቀጥታ ለመጓዝ ወይም ለማለፍ መጠቀም እንደሌለበት ያሳያል።

የመንገድ መስመር (ሌይን) አጠቃቀም መቆጣጠሪያ ምልክቶች (የቀጠለ)



ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ይታጠፉ



ቀጥ ብለው ይሂዱ ወይም ወደ ቀኝ ይታጣፉ

እንደዚህ ባሉ ምልክቶች በሚመራ የመንገድ መስመር ውስጥ ካሉ ቀስቶቹ በሚያመለክቱት አቅጣጫ መጓዝ ይችላሉ።

ወደ ቀኝ ብቻ ይታጠፉ

ወደ ግራ ብቻ ይታጠፉ

መታጠፊያ ቀስትና "ብቻ" በሚል ቃል ምልክት ቁጥጥር በተደረገበት መስመር ላይ እየነዱ ከሆነ መስቀለኛ መንገድ ላይ ሲደርሱ መታጠፍ አለቦት። በስህተት ወደ መታጠፊያ መስመር ቢገቡም እንኳ ቀስቱ ወደሚያመለክተው አቅጣጫ ብቻ መሄድ ይፈቀድልዎታል።



በቀኝ በኩል ይቆዩ
እነዚህ ምልክቶች አሽከርካሪዎች ከትራፊክ ደሴት (የመንገድ መሃል) ወይም ከማካፈልያው በስተቀኝ እንዲጓዙ አቅጣጫ ያሳያሉ።

ወደ ቀኝ መታጠፊያ ምልክት
ይህ ምልክት የትራፊክ መብራቱ የቀኝ መታጠፊያ እንቅስቃሴዎችን እንደሚቆጣጠር ለማሳየት ከትራፊክ መብራቱ አጠገብ ይቀመጣል።

የፍጥነት ገድብ ምልክት (የፍጥነት ገደብ ምልክት) በተለጠፈበት አውራ ጎዳና ክፍል ውስጥ በተስማሚ ሁኔታዎች ውስጥ የሚፈቀደውን ከፍተኛውን የህጋዊ ፍጥነት ያመለክታል። ደህንነትዎ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ከተጠቀሰው ፍጥነት በታች ቀስ ብሎ በማሽከርከር ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል።

የታዳጊ ወጣቶች የትራፊክ አደጋ እውነታ

“በሁኔታዎች በጣም በፍጥነት መንዳት” የ16 እና የ17 ዓመት ታዳጊ አሽከርካሪዎች ለአደጋ የሚጋለጡበት ቁጥር 1 ምክንያት ነው።



ከነዚህ ምልክቶች አንዱ በተለጠፈበት መስቀለኛ መንገድ ላይ በቀይ ብርሃን ዑደት ውስጥ መዞር አይችሉም። ሲግናሉ ወደ አረንጓዴ እስኪቀየር ድረስ መጠበቅ አለብዎት።

ብልጭ በሚል ቢጫ ቀስት ላይ በግራ መታጠፍ ላይ ቅድሚያ ይስጡ
ይህ ምልክት ቢጫው ቀስት ብልጭ በሚልበት ጊዜ ወደ ግራ መታጠፍ እንደሚፈቀድ ያመለክታል፤ ነገር ግን ለመጪው ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለብዎት። ይህ ምልክት ብልጭ የሚል ቢጫ ቀስት በሚሰራበት ጊዜ የግራ መታጠፍ ጥበቃ እንደማይደረግላቸው ለአሽከርካሪዎች ለማሳወቅ በተለምዶ ከግራ መታጠፊያ የትራፊክ መብራት አጠገብ መገናኛዎች ላይ ይቀመጣል።

አረንጓዴ ላይ ወደ ግራ ሲታጠፉ ቅድሚያ ይስጡ
ይህ ምልክት ወደ ግራ መታጠፍ እንደሚፈቀድ ያመለክታል፤ ነገር ግን ለሚመጣው ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለብዎት። ብዙውን ጊዜ በመገናኛዎች ላይ ከግራ መታጠፊያ የትራፊክ መብራት አጠገብ የሚቀመጥ ሲሆን የክብ አረንጓዴ መብራት ሲበራ አሽከርካሪዎች የግራ መታጠፍ ጥበቃ እንደማይደረግላቸው ለማሳወቅ ነው።

የተቃራኒ አቅጣጫ ትራፊክ (ተሽከርካሪዎች) የተራዘመ አረንጓዴ መብራት አለው
ይህ ምልክት የተለጠፈው የመብራት ምልክትዎ ወደ ቀይ ከተለወጠ በኋላ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀሱን በሚቀጥልበት ቦታ ነው።

አስቀድሞ የተያዘ የመኪና ማቆሚያ
ይህ ምልክት ጥቁር እና ነጭ ባይሆንም እንኳ የመቆጣጠሪያ ምልክት ነው። ይህ ለአካል ጉዳተኞች ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ላለባቸው የቀድሞ ወታደሮች የመኪና ማቆሚያ ቦታ የተያዘ መሆኑን ያመለክታል። በእነዚህ ቦታዎች ላይ የሚቆሙ ተሽከርካሪዎች የተፈቀደ የትራንስፖርት ፈቃድ ወይም የመኪና ማቆሚያ ካርዶች ሊኖራቸው ይገባል። በእነዚህ ቦታዎች ላይ ያለፈቃድ የቆሙ ተሽከርካሪዎች ለገንዘብ መቀጮ እና ለመጎተት ወጪ ሊዳረጉ ይችላሉ።

የማስጠንቀቂያ ምልክቶች

የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ከፊትዎ ስላለው መንገድ ወይም አካባቢ ሁኔታ ያሳውቁዎታል። ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ አደጋዎች ወይም በመንገድ ላይ ስለሚደረጉ ለውጦች ያስጠነቅቁዎታል። ሁኔታው ከመከሰቱ በፊት ነው የሚለጠፉት፤ ስለዚህ ከፊት ምን እንዳለ ለማየት፣ እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለቦት ለመወሰን እና አስፈላጊ ከሆነ ፍጥነትዎን ለመቀነስ ወይም የመጓጓዣ መንገድዎን ለመቀየር ጊዜ ይኖርዎታል። የማስጠንቀቂያ ምልክቶች በአብዛኛው የአልማዝ ቅርጽ ያላቸው ሲሆን የቢጫ ጀርባ ያላቸው ጥቁር ምልክቶች ወይም ቃላት አሏቸው።

ማለፊያ የሌለበት ቀጠና
ይህ ፔናንት የሚመስል ቅርጽ ያለው ብቸኛው የማስጠንቀቂያ ምልክት ነው። ይህ ምልክት ማለፍ የተከለከለ አካባቢ መጀመሩን የሚያመለክት ሲሆን ከአሽከርካሪው ፊት ለፊት በግራ በኩል ባለው መንገድ ላይ ይቀመጣል።



የሼቭሮን ምልክቶች
መንገዱ ሹል በሆነ ሁኔታ አቅጣጫ ይቀይራል፤ ለምሳሌ ወደ ግራ ወይም ቀኝ መታጠፊያ ሲኖር። መንገዱ የሼቭሮን ማሳያው ወደሚያመለክተው አቅጣጫ ይታጠፋል። በኩርባ ላይ ጥቅም ላይ ሲውል የኩርባ ማስጠንቀቂያ ምልክት ይኖራል፣ እና በማዞሪያው በሙሉ በርካታ የሼቭሮን ምልክቶች ሊቀመጡ ይችላሉ።

የግራ ኩርባ
መንገዱ ወደፊት ወደ ግራ ይጠመዘዛል። ፍጥነትዎን መቀነስ፣ በመስመርዎ መሀል መቆየትና በግራ-በኩል በሚታጠፈው ኩርባ ለመሄድ መዘጋጀት ያስፈልግዎታል።

የቀኝ ኩርባ
መንገዱ ወደፊት ወደ ቀኝ ይጠመዘዛል። ወደ ቀኝ-በኩል በሚታጠፈው ኩርባ ውስጥ ስትነዱ ፍጥነትዎን መቀነስ እና ተሽከርካሪዎን ከመስመርዎ መሀል በትንሹ ወደ ቀኝ ማድረግ ያስፈልግዎታል።

ሹል ወደ ግራ መታጠፊያ
ከፊት ያለው መንገድ በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ግራ ይታጠፋል። በከፍተኛ ፍጥነት መቀነስ፣ በመስመርዎ መሀል መቆየት እና በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ግራ መታጠፊያ ውስጥ ለማለፍ መዘጋጀት ያስፈልግዎታል። አንዳንድ የሹል መታጠፊያ ምልክቶች የሚመከረውን ፍጥነት በምልክቱ ላይ ወይም ከሱ በታች ያሳያሉ።

ሹል ወደ ቀኝ መታጠፊያ
ከፊት ያለው መንገድ ሹል በሆነ ሁኔታ ወደ ቀኝ ይታጠፋል። ፍጥነትዎን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሱ፣ ተሽከርካሪዎን ከመንገድዎ መሀል በትንሹ ወደ ቀኝ ያድርጉ እና ሹል በሆነ ሁኔታ ወደ ቀኝ መታጠፊያ በኩል ለመንዳት ይዘጋጁ። አንዳንድ የሹል መታጠፊያ ምልክቶች የሚመከረውን ፍጥነት በምልክቱ ላይ ወይም ከሱ በታች ያሳያሉ።



ተከታታይ ኩርባዎች
ከፊት ያለው መንገድ መጀመሪያ ወደ አንድ አቅጣጫ ከዚያም ወደ ሌላ አቅጣጫ ይመለሳል (የሁለት (2) ኩርባዎች ስብስብ)። ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና በተከታታይ ኩርባዎች በኩል ለማለፍ ይዘጋጁ።



በቀኝ እና በግራ በኩል ያሉ በከፍተኛ ሁኔታ መታጠፊያዎች
ከፊት ያለው መንገድ መጀመሪያ ወደ አንድ አቅጣጫ ከዚያም ተመልሶ ወደ ሌላ አቅጣጫ በከፍተኛ ሁኔታ ይታጠፋል። ፍጥነትዎን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሱ እና በተከታታይ መታጠፊያዎች በኩል ለማለፍ ይዘጋጁ።

ጠመዝማዛ መንገድ (ተከታታይ ኩርባዎች)
ይህ ምልክት ከፊት ባለው መንገድ ላይ ሶስት (3) ወይም ከዚያ በላይ ኩርባዎች በተከታታይ እንዳሉ ያመለክታል።



አንድ አቅጣጫ ትልቅ ቀስት
ከፊት ያለው መንገድ አቅጣጫን በከፍተኛ መጠን ይቀይራል። እንደዚህ አይነት ከፍተኛ ኩርባ ከመድረስዎ በፊት በአንድ መገናኛ ላይ መታጠፊያ ለማድረግ እንደሚያደርጉት ያህል ፍጥነትዎን ይቀንሱ።

ወደ ኩርባ የሚገባ መንገድ
ዋናው መንገድ ወደ ግራ የሚታጠፍ ሲሆን የጎን መንገድ ከቀኝ በኩል ይገባል። ወደ መገናኛው በከፍተኛ ጥንቃቄ ይቅረቡ። ወደ ዋናው መንገድ ለመግባት የሚሞክር ሹፌር ከመዞሪያው በኩል ሲመጡ ላያይዎት ይችላል፣እና በጣም ፈጥነው እየሄዱ ከሆነ አደጋን ለማስወገድ ትንሽ ቦታ ሳይኖርዎት ከፊትዎ ሊገባ ይችላል።

የጭነት መኪና ተንከባሎ የመውደቅ አደጋ
ይህ ምልክት ከመጠን በላይ በሆነ ፍጥነት የሚጓዙ የጭነት መኪናዎች የመገልበጥ አደጋ ሊያጋጥማቸው የሚችልባቸውን ኩርባዎች ለይቶ ያሳያል።

የሚመከር የፍጥነት ምልክቶች
ይህ ምልክት ከማንኛውም የአልማዝ ቅርጽ ያለው የማስጠንቀቂያ ምልክት ጋር አብሮ ሊያገለግል ይችላል። ወደፊት ባለው ሹል በሆነ ሁኔታ ወደ ግራ በሚታጠፍ ኩርባ ላይ መጓዝ የሚገባዎት ከፍተኛ ፍጥነት 25 ማይል በሰዓት ነው።

የተሽከርካሪዎች ወደ አንድ መስመር መቀላልቀል
ይህ ምልክት በዋናው መንገድ ላይ የሚቀመጠው ተሽከርካሪ ከሌላ መንገድ ወይም መወጣጫ ወደ መስመርዎ ሊቀላቀል እንደሚችል ለማሳወቅ ነው። በዚህ ምሳሌ ተሽከርካሪው ከቀኝ በኩል ወደ እርስዎ የመንገድ መስመር ይገባል። ወደ ዋናው መንገድ የሚገባው ተሽከርካሪ በዋናው መንገድ ላይ ላሉት ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለበት።

የተጨመረ የመንገድ መስመር
ይህ ምልክት ሁለት መንገዶች በሚገናኙበት ቦታ ላይ አስቀድሞ ይቀመጣል። ይህ ማለት የሚገባው ተሽከርካሪ ወደ መንገዱ የተጨመረውን አዲስ መስመር ስለሚጠቀም መዋሃድ አያስፈልግም ማለት ነው።

የመቀላቀያ አካባቢ
ይህ ምልክት አንዳንድ ተሽከርካሪዎች እየወጡ እና መንገድዎን እያቋረጡ እያለ ከሌላ መንገድ ጋር እንደሚዋሃዱ ለማስጠንቀቅ ይጠቅማል።

የመንገድ አካፋይ ያለው አውራ ጎዳና መጀመሪያ

ከፊት ያለው አውራ ጎዳና ሁለት የአንድ አቅጣጫ መንገዶች እና በተቃራኒ አቅጣጫ የሚሄዱ ትራፊክን የሚለይ መካከለኛ ቦታ ወይም የሚከፋፍል የተከፈለ አውራ ጎዳና ይሆናል። ከመከፋፈያው ወይም ከመካከለኛው በስተቀኝ በኩል ይሁኑ።



የተከፋፈለ አውራ ጎዳና መጨረሻ

እየሄዱበት ያለው የተከፈለ አውራ ጎዳና ወደፊት ያበቃል። ከዚያ በኋላ ባለ ሁለት አቅጣጫ ትራፊክ ባለበት መንገድ ላይ ይሆናሉ። ከማዕከላዊው መስመር በስተቀኝ ይሁኑ እና ለሚመጣው ተሽከርካሪ ይጠብቁ።

ወደፊት ባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ አለ

ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ ከፊት ያበቃል። ከዚያ በኋላ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚንቀሳቀሱ ሁለት (2) የተሽከርካሪ መስመሮች ባለው መንገድ ላይ ይጓዛሉ። ከማዕከላዊው መስመር በስተቀኝ ባለው መስመርዎ ላይ ይቆዩ። ይህ ምልክት ባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ ላይ በተለያዩ ክፍተቶች ላይም ሊቀመጥ ይችላል።

የመንገድ መስመር መጨረሻ

እነዚህ ምልክቶች ባለብዙ መስመር መንገድ ላይ አንድ (1) የመንግደ መስመር ወደፊት እንደሚያልቅ ይነግሩዎታል። በእነዚህ ምሳሌዎች በቀኝ በኩል ያለው ተሽከርካሪ ወደ ግራ መቀላቀል አለበት።

የመንገድ መገናኛ ምልክቶች

ከዚህ በታች ያሉት ምልክቶች የተለያዩ የመንገድ መገናኛዎችን ያመለክታሉ። መንገዶቹ እንዴት እንደሚገናኙ አስቀድሞ በማሳየት እየተጓዙበት ያለው መንገድ በመገናኛው ቀጥ ብሎ እንደማይቀጥል ምልክቶቹ ያሳውቁዎታል። ምልክቶቹ ስለ ሌሎች ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ሊኖሩ ስለሚችሉ ችግሮች ያስጠነቅቁዎታል። አስፈላጊ ከሆነ ፍጥነትዎን ለመቀነስ ይዘጋጁና ወደፊት ያለውን በመመልከት ለእነዚህ ሁሉ መገናኛ ቦታዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ ይቅረቡ።



መስቀለኛ መንገድ

ቅርንጫፍ መንገድ

“T” የመንገዶች መገናኛ

“Y” የመንገዶች መገናኛ

ማዞርያ መንገድ



ወደ ሁለት አቅጣጫ የሚይሳይ ትልቅ ቀስት

ይህ ምልክት በ T-ቅርጽ የመንገዶች መገናኛ ሩቅ በኩል የሚቀመጥ ሁኖ ወደ ግራ ወይም ቀኝ ብቻ መሄድ እንደሚችሉ ለመንገር ነው። እየሄዱበት ያለው መንገድ ከመገናኛው በኋላ ቀጥ ብሎ አይቀጥልም።



ጠባብ ድልድይ ወይም የመሬት ውስጥ መተላለፊያ ከፊት አለ

በድልድዩ ወይም በምድር ውስጥ መተላለፊያው ላይ ያለው መስመር እየጠበበ ይሄዳል፣ በአጠቃላይ የዳርቻ ቦታ አይኖርም። ፍጥነትዎን መቀነስ እና በራስዎ መስመር ላይ መሆንዎን ያረጋግጡ። ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣ ሹፌር ሰፊ ተሽከርካሪ ካለው ወይም የመስመርዎን ክፍል እየያዘ ከሆነ አካባቢውን እስኪያልፍ ይጠብቁ ።

እርጥብ በሚሆንበት ጊዜ የሚያንሸራትት

በተለይም እርጥብ በሚሆንበት ጊዜ የሚያንሸራትቱ ሁኔታዎች አሉ። በእርጥብ የአየር ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ከፊት ካለው መኪና ያለዎትን ርቀት ይጨምሩ። በቶሎ ፍጥነትን አይጨምሩ ወይም ፍሬን አይያዙ። ማዞሪያዎች ጋር በጣም በዝግታ ፍጥነት ይታጠፉ።

የአጋዘን መሻገሪያ ቦታ

ይህ ምልክት አጋዘኖች በተደጋጋሚ በሚያልፉባቸው እና ከአጋዘን ጋር ግጭት በደረሰባቸው አካባቢዎች ላይ ይለጠፋል።

ዝቅተኛ ከፍታ ያለው ቦታ

ይህ ምልክት ከመንገድ በታች ባለ መንገድ ላይ ወይም ወደ ዋሻ ወይም የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ መግቢያ ላይ ሊቀመጥ ይችላል። ተሽከርካሪዎ በምልክቱ ላይ ከተገለጸው ቁመት በላይ ከሆነ ወደ ውስጥ አይግቡ።

የመንገድ ዳር ምልክቶች

እነዚህ ምልክቶች የመንገዱ ዳር ከመንገዱ ዝቅ ያለ በሆነባቸው ወይም የመንገድ ዳሩ ለስላሳ (ያልተነጠፈ) በሆኑባቸው ቦታዎች ላይ ይቀመጣሉ። **ዝቅተኛ የመንገድ ዳር** ምልክት ዳሩ ከመንገዱ ደረጃ እስከ ሶስት (3) ኢንች ዝቅ ባለበት ቦታ ላይ ጥቅም ላይ ይውላል። **እጅግ ዝቅተኛ የመንገድ ዳር** ምልክት ይበልጥ ከባድ በሆኑ እጅግ ዝቅተኛ የመንገድ ዳር ሁኔታዎች ላይ ጥቅም ላይ ይውላል። **ከመንገዱ ወጥተው አንድ (1) ጎማዎ ዝቅ ባለ ወይም ለስላሳ በሆነ የመንገድ ዳር ላይ ከሆነ ወደ መንገዱ ለመመለስ በድንገት ፍሬን አይያዙ ወይም መሪውን በድንገት አያዙሩ፤ ምክንያቱም መኪናዎን መቆጣጠር ሊያቅትዎት ይችላል!** ከመንገድ ዳር መንሸራተትን በደህንነት እንዴት ማገገም እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 3ን ይመልከቱ።

ኮረብታ/ቁልቁለት

ከፊት ገደላማ ኮረብታ አለ። ፍጥነትዎን ለመቆጣጠር እና ፍሬንዎ እንዳይጎዳ ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ወደ ዝቅተኛ ማርሽ ለመቀየር ይዘጋጁ።

ከፊት የትራፊክ መብራት ምልክት አለ።

ከፊት ባለው የመንገዶች መገናኛ ላይ የትራፊክ ሲግናል አለ። በኮርባው ወይም በኮረብታው ምክንያት ማየት ልያቅቶት ይችላል። መብራቱ ቀይ ከሆነ (ወይም መብራቱ ወደ አረንጓዴነት ከተቀየረ) የተሽከርካሪዎች መስመር ወደፊት ሊቆም ይችላል። አስፈላጊ ከሆነ ይህን ምልክት በሚያዩበት ጊዜ ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ለማቆም ይዘጋጁ።



ከፊት የማቆሚያ ምልክት አለ።

ከፊት ባለው መገናኛ ላይ የቁም ምልክት አለ። በኩርባ፣ ኮረብታ ወይም እይታዎን በሚከለክል ነገር በመኖሩ ምክንያት በደንብ ላያዩት ይችላሉ። እንዲሁም ማየት በማይችሉት የቁም ምልክት ላይ የቆሙ ተሽከርካሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህን ምልክት ሲያዩ ለማቆም በመዘጋጀት ፍጥነትዎን ይቀንሱ።

ከፊት የብስክሌት መሻገሪያ አለ

ብስክሌተኞች ከፊት ለፊት መንገድዎን እያቋረጡ ሊሆኑ ይችላሉ። አስፈላጊ ከሆነ ፍጥነትዎን ለመቀነስ ዝግጁ ይሁኑ። ይህ ምልክት (በምስሉ ላይ እንደሚታየው) ቢጫ ጀርባ ወይም የፍሎረሰንት ቢጫ-አረንጓዴ ጀርባ ሊኖረው ይችላል።

ከፊት የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ አለ።

ወደ የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ እየተቃረቡ ነው። ይህን ምልክት ሲያዩ ባቡር መመልከት እና ማዳመጥ ይጀምሩ። ይህ ምልክት አስፈላጊ ከሆነ ወደ ሐዲዱ ከመድረስዎ በፊት ለማቆም እንዲችሉ በበቂ ርቀት ላይ ይቀመጣል። ስለ የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ ደህንነት ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 3ን ይመልከቱ።



የላቀ የመገናኛ ወይም መቀለኛ መንገድ/የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ ምልክት
የሚገናኘው መንገድ ከመገናኛው በጣም አጭር ርቀት ላይ የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ አለው። ወደሚገናኘው መንገድ ለመታጠፍ እቅድ ካለዎት እና ባቡር እየመጣ ከሆነ ለማቆም ይዘጋጁ።

ብስክሌት/ሞተር ተሽከርካሪ መንገዱን ይጋራሉ
መንገዱ በሚጠብብባቸው ቦታዎች ላይ ጥቅም ላይ ይውላል (የዳር መንገድ በሌለባቸው፣ ጠባብ መስመሮች፣ ወዘተ) መኪና ነጂ እንደመሆንዎ ብስክሌተኞች መንገዱን እንዲካፈሉ በቂ ቦታ እንዲተዉ እርስዎን ለማስጠንቀቅ።

የእግረኛ መሻገሪያ
መለያ በተደረጉባቸው የእግረኞች ማሻገሪያዎች ላይ ወይም እግረኞች መንገድዎን ሊያቋርጡ በሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ ጥቅም ላይ ይውላል። አስፈላጊ ከሆነ ፍጥነትዎን ለመቀነስ ወይም ለማቆም ይዘጋጁ። ይህ ምልክት (በምስሉ ላይ እንደሚታየው) ቢጫ ጀርባ ወይም የፍሎረሰንት ቢጫ-አረንጓዴ ጀርባ ሊኖረው ይችላል።

ትምህርት ቤት
ይህ በመንገድ ላይ ጥቅም ላይ የሚውለው ብቸኛው ባለ አምስት ጎን ቅርጽ ያለው ምልክት ነው። ይህ ማለት ወደ ትምህርት ቤት አካባቢ እየቀረቡ ነው ማለት ነው። ምልክቱ ወደ ታች የሚያመለክት ቀስት አብሮት ካለ ይህ ማለት በትምህርት ቤቱ አካባቢ መሻገሪያ ላይ ነዎት ማለት ነው። ፍጥነትዎን መቀነስ፣ መንገዱን የሚያቋርጡ ህጻናትን መመልከት እና አስፈላጊ ከሆነ ማቆም አለብዎት። ይህ ምልክት (በምስሉ ላይ እንደሚታየው) ቢጫ ጀርባ ወይም የፍሎረሰንት ቢጫ-አረንጓዴ ጀርባ ሊኖረው ይችላል።



በፈረስ የሚጎተት ተሽከርካሪ
ይህ ምልክት ቀስ ብለው የሚንቀሳቀሱ፣ በፈረስ የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች መንገዱን ከሞተር ተሽከርካሪዎች ጋር በሚያቋርጡ ወይም በሚጋሩባቸው አካባቢዎች ላይ ይለጠፋል።

ከመንገድ አጠገብ ያሉ ነገሮች
ከመንገዱ ጠርዝ አጠገብ ያሉ ነገሮች አንዳንድ ጊዜ አሽከርካሪዎችን ሊከሰት ስለሚችለው አደጋ ለማስጠንቀቅ ምልክት ያስፈልጋቸዋል። እነዚህም በድልድይ ስር ያሉ ድጋፎች፣ የድልድዮች ጫፎች፣ የጎን መከላከያ ብረቶች እና ሌሎች ግንባታዎችን ያካትታሉ። በአንዳንድ አጋጣሚዎች አካላዊ ነገር ላይኖር ይችላል፣ ይልቁኑም እንደ ዝቅተኛ የመንገድ ዳር ወይም በድንገት የሚለወጥ የመንገድ አቀማመጥ ያሉ የመንገድ ዳር ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እንደዚህ ያሉ ከመንገድ ዳር ያሉ ነገሮች እና ሁኔታዎች በሚከተሉት ምልክቶች ይገለፃሉ፤ መስመሮቹ አደጋውን ለማስወገድ ወደ ሚፈልጉበት አቅጣጫ ያጋደሉ ናቸው፦


በቀኝ አደጋ አለ በግራ ይቆዩ


በመሃል አደጋ አለ በግራ ወይም በቀኝ ይቆዩ


በግራ አደጋ አለ በቀኝ ይቆዩ

የሥራ ቀጠና ምልክቶች (የሥራ ቦታ እና የግንባታ ቀጠና ምልክቶች)

የሥራ ቀጠና ምልክቶች እንደ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች በአብዛኛው የአልማዝ ቅርጽ ያላቸው ናቸው፤ ነገር ግን ከጥቁር ጽሑፍ ጋር ብርቱካናማ ቀለም ያላቸው እንጂ ከጥቁር ጽሑፍ ጋር ቢጫ ቀለም ያላቸው አይደሉም። እነዚህ ምልክቶች ሰራተኞች ወይም መሳሪያዎች በመንገድ ላይ ወይም በአቅራቢያ ሊገኙባቸው የሚችሉ የጥገና፣ የግንባታ ወይም የመገልገያ ቦታዎችን ያመለክታሉ። እነዚህን ምልክቶች ሲመለከቱ ንቁ ይሁኑ እና ፍጥነትዎን ይቀንሱ።

በስራ ቀጠና ውስጥ ሲጓዙ የቀኑ ጊዜ ምንም ይሁን የግንባር መብራቶችዎን ያብሩ። ይህ ህግ ለ**ሁሉም** የተለጠፍባቸው የስራ ቀጠናዎችን ይመለከታል፣ ስራ ላይ ለሆኑት ብቻ አይደለም። የግንባር መብራቶችን መጠቀም ተሽከርካሪዎትን ለሌሎች ተሽከርካሪዎች እንዲሁም ለአውራ ጎዳና ሰራተኞች የበለጠ እንዲታይ ያደርገዋል። በሥራ ቀጠና ውስጥ የትራፊክ ጥሰት በመፈጸም በፖሊስ ከተያዙ እና የተሽከርካሪዎ የግንባር መብራቶች ካልበሩ ተጨማሪ 25 ዶላር ይቀጣሉ።

እነዚህ **የስራ ቀጠና** ምልክቶች በአንድ በስራ ላይ ያለ የሥራ ቀጠና መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ ይቀመጣሉ። አንድ ስራ ላይ ያለ የሥራ ቀጠና ማለት የግንባታ፣ የጥገና ወይም የመገልገያ ሠራተኞች በመንገድ ላይ ወይም ከአውራ ጎዳናው መንገድ ዳር አጠገቡ ባለው ክፍት የመጓጓዣ መስመር ላይ የሚገኙበት የሥራ ቀጠና ክፍል ነው።

የመንገድ ስራ ከፊት አለ

ይህ ምልክት ከፊት የመንገድ ሥራ እንዳለ ያሳውቅዎታል እንዲሁም ፍጥነትዎን እንዲቀንሱ ያስጠነቅቅዎታል።

መንገድ በጎርፍ ምክንያት ተዘግቷል

ይህ ምልክት ከፊት ያለው መንገድ በጎርፍ ምክንያት መዘጋቱን ያሳውቅዎታል። ሌላ አማራጭ መንገድ መጠቀም ይኖርብዎታል። በጎርፍ የተጥለቀለቀ መንገድ ካጋጠመዎት ምን ማድረግ እንዳለብዎ በተመለከተ ምዕራፍ 3ን ይመልከቱ።

ከፊት የመንገድ መስመር ተዘግቷል።

ይህ ምልክት አንድ የሆነ የመንገድ መስመር በተወሰነ ርቀት ላይ እንደሚዘጋ ይነግርዎታል።

ከፊት የሚሰሩ ሰራተኞች አሉ

ሰራተኞች በመንገድ ላይ ወይም በጣም ቅርብ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ስለዚህ በአካባቢው በሚጓዙበት ጊዜ ልዩ ጥንቃቄ ያድርጉ።

ይህን ያውቁ ኖሯል?

የአውራ ጎዳና ሰራተኞች በስራ ቀጠናዎች ውስጥ በፍጥነት የሚነዱ ወይም ደህንነት ባልጠበቀ ሁኔታ የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎችን ለፖሊስ ሪፖርት የሚያደርጉበት ቅጾች አሏቸው፣ ፖሊስም የቅጣት ትኬት ሊሰጥ ይችላል፣ ይህም የገንዘብ ቅጣት እና ነጥብን ያስከትላል።

ከፊት አውራ ጎዳና ጠባቂ አለ (ከፊት የመንገድ ግንባታ አለ)

በግራ በኩል ያለው ምልክት አውራ ጎዳና ጠባቂ ከፊት ያለውን ትራፊክ እየተቆጣጠረ መሆኑን ያሳያል። በስተቀኝ እንደሚታየው አውራ ጎዳና ጠባቂዎች እንዲቆሙ ወይም ፍጥነትዎን እንዲቀንሱ ለማመልከት **የማቆሚያ** እና **ፍጥነት ይቀንሱ** የሚሉ ምልክቶችን ወይም ቀይ ባንዲራ ይጠቀማሉ። ወደ ሥራ ቀጠና ሲቃረቡ እና በቀጠናው ሲጓዙ ለአውራ ጎዳና ጠባቂዎች ልዩ ትኩረት ይስጡ።

የኤሌክትሪክ ጠቋሚ ቀስት ፓነሎች

በመንገድ ላይ የሚቀመጡ ወይም በተሽከርካሪዎች ላይ የሚገጠሙ ትልልቅ የኤሌክትሮኒክ ብልጭ የሚሉ የቀስት ፓነሎች (ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ መንቀሳቀስ/መቀላቀል) እየመጡ ላሉ አሽከርካሪዎች ስለ የመንገድ መዘጋት የሚጠቁሙ ናቸው። ምልክቱ ከመታየቱ በፊት መቀላቀልዎን አስቀድመው ይጀምሩ። በስተቀኝ በኩል ባለው ስእል ላይ ከታዩት መልእክቶች ውስጥ አንዱን (ማስጠንቀቂያ) የሚያሳይ የቀስት ፓነል ከመጓጓዣ መስመሩ ቀጥሎ የሥራ ቦታ እንዳለ ያመለክታል። በከፍተኛ ጥንቃቄ ይንዱ።



የሚመሩ መሣሪያዎች

በርሜሎች፣ ቱቦዎች፣ ሾጣጣዎች እና ቀጥ ያሉ ፓነሎች ሁሉም በስራ ቀጠናዎች ውስጥ የትራፊክ ፍሰትን ለመለወጥ እና ከመንገድ ስራ ጋር ከተያያዙ አደጋዎች ለመጠበቅ የሚረዱ መሳሪያዎች ናቸው።



የመመሪያ ምልክቶች

የመመሪያ ምልክቶች ስለሚገናኙ መንገዶች መረጃ ይሰጣሉ፣ ወደ ከተሞች ለመምራት ይረዳሉ፣ እንዲሁም በአውራ ጎዳናው ላይ ያሉ ትኩረት የሚስቡ ቦታዎችን ያሳያሉ። የመመሪያ ምልክቶች ሆስፒታሎችን፣ የአገልግሎት ጣቢያዎችን፣ ምግብ ቤቶችን እና ሞቴሎችን ለማግኘትም ይረዱዎታል። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ምልክቶች አግድም አራት ማዕዘን ቅርጽ አላቸው።

የአውራ ጎዳና/የፍጥነት መንገድ መመሪያ ምልክቶች

የሚከተሉት ሦስት ምልክቶች የአውራ ጎዳና እና የፍጥነት መንገድ መመሪያ ምልክቶች ምሳሌዎች ናቸው። ነጭ ፊደላት ያሏቸው አረንጓዴ ናቸው። አብዛኛዎቹ የአውራ ጎዳና እና የፍጥነት መንገድ ምልክቶች በተመሳሳይ መንገድ ነው የሚለጠፉት። ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ አንድ የማስጠንቀቂያ ምልክት ይኖራል ቀጥሎም ሌላ የማስጠንቀቂያ ምልክት ይመጣል። ሦስተኛው ምልክት ደግሞ በመውጫው ላይ ይለጠፋል። በአውራ ጎዳና ላይ ያለው ከፍተኛ ፍጥነት እና የትራፊክ መጨናነቅ አሽከርካሪዎች አንድ ምልክት እንዳያዩ ስለሚያደርግ ብዙ ምልክቶች ያስፈልጋሉ። እንዲሁም አሽከርካሪዎች ለመውጣት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የመንገድ መስመሮች መቀየር ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

የመውጫ ቁጥሮች

የመውጫ ቁጥሮች ከማይል ርቀት ጠቋሚዎች ጋር ይስተካከላሉ። ይህ ለውጥ አሽከርካሪዎች በመውጫዎች መካከል ያለውን ርቀት በፍጥነት እንዲያሰሉ ያስችላቸዋል፤ ለምሳሌ ከመውጫ 95 እና ከመውጫ 20 ያለው ርቀት 75 ማይል ነው።

በአውራ ጎዳና ላይ **መውጫ ብቻ** የሚል ቢጫ ምልክት ካለ ከምልክቱ ስር ያለው መስመር በመገናኛው ወደ ሌላ መንገድ አይቀጥልም ይልቁኑ ራምፕ ለመስራት መንገዱን ለቆ ወደ መውጫው ያመራል። **መውጫ ብቻ** የሚል በተለጠፈበት መስመር ላይ ከሆኑ መስመር መቀየር ይችላሉ ወይም በዚህ መስመር ላይ ከቆዩ አውራ መንገዱን መልቀቅ አለብዎት።



ከአውራ ጎዳናው ወይም ከሀይዌዩ በየትኛው በኩል እንደሚወጡ ለማወቅ የሚረዱዎት ጥቂት ምክሮች እነሆ፦

ወደ መስመር 22 መውጫ 13 በአውራ ጎዳናው በግራ በኩል ይሆናል።

ወደ መስመር 22 መውጫ 7 በአውራ ጎዳናው በቀኝ በኩል ይሆናል።

- መውጫው በአውራ ጎዳናው በ**ግራ** ጎን ከሆነ በአረንጓዴው አራት ማዕዘን ቅርጽ ባለው ምልክት ላይ ያለው ትንሽ አረንጓዴ **መውጫ** ቁጥር ምልክት በምልክቱ በ**ግራ** በኩል ይሆናል።
- መውጫው በአውራ ጎዳናው በ**ቀኝ** ጎን ከሆነ በአረንጓዴው አራት ማዕዘን ቅርጽ ባለው ምልክት ላይ ያለው ትንሽ አረንጓዴ **መውጫ** ቁጥር ምልክት በምልክቱ በ**ቀኝ** በኩል ይሆናል።
- ምልክቱ ላይ ነጭ ቀስቶች ካሉ ቀስቱ ወደ መውጫው አቅጣጫውን ያመለክታል።

የግዛቶች አገናኝ አውራ ጎዳናዎች የቁጥር አሰጣጥ ስርዓት

ቀይ፣ ነጭ እና ሰማያዊ የጋሻ ምልክት ሀይዌይ ኢንተርስቴት መሆኑን ያሳያል። እነዚህ የግዛቶች አገናኝ መንገዶች አሽከርካሪዎች ባልተለመዱ ቦታዎች ውስጥ ትክክለኛውን መንገድ እንዲያገኙ ለመርዳት በልዩ ሁኔታ ቁጥር ተሰጥቷቸዋል። መንገዱ በዋናነት ወደ ምስራቅ እና ምዕራብ ወይም ወደ ሰሜን እና ደቡብ የሚሄድ ከሆነ ለማሳየት እንዲሁም መንገዱ በዩናይትድ ስቴትስ (አሜሪካ) ውስጥ በምስራቅ ፣ በመሃል ወይም በምዕራብ የሚገኝ መሆኑን ለማሳየት ኮድ ጥቅም ላይ ይውላል።

የኢንተርስቴት (ግዛቶች አገናኝ አውራ ጎደናዎች) የቁጥር አሰጣጥ ስርዓት ትርጉም፡፡ በኢንተርስቴት ምልክቱ ላይ ያሉት ቁጥሮች እንዴት እንደተዘጋጁ ሲረዱ ጥሩ የአሰሳ መርጃ ሊሆኑ ይችላሉ። በአጠቃላይ የሚከተለውን ስርዓት ይከተላሉ፦

- አንድ ወይም ሁለት አሃዝ ያላቸው **ተጋማሽ** ቁጥሮች ኢንተርስቴት አውራ ጎዳናዎች በአጠቃላይ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ የሚሄዱ መንገዶች ናቸው። በሀገር አቀፍ ደረጃ ቁጥሮቹ ከ I-10 በደቡብ ወደ I-94 በሰሜን በኩል ይጨምራሉ። በፔንሲልቬንያ I-76 በክልሉ ደቡባዊ ክፍል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን I-84 እና I-80 በሰሜናዊው ክፍል ይገኛሉ።
- አንድ ወይም ሁለት አሃዝ ያላቸው **ኢ-ተጋማሽ** ቁጥሮች ያላቸው ኢንተርስቴት አውራ ጎዳናዎች በአጠቃላይ ከሰሜን ወደ ደቡብ የሚሄዱ መንገዶች ናቸው። ቁጥሮች ከምዕራብ የባህር ዳርቻ I-5 ወደ ምስራቅ የባህር ዳርቻ I-95 ይጨምራሉ። በፔንስልቬንያ, I-79 በክፍለ-ግዛቱ ምዕራባዊ ክፍል ነው እና I-95 በምስራቅ ክፍል ነው።
- ሶስት አሃዝ ያላቸው ኢንተርስቴት አውራ ጎዳናዎች ከሌሎች ዋና ዋና አውራ ጎዳናዎች ጋር ይገናኛሉ። ከሦስቱ (3) አሃዞች የመጀመሪያው ቁጥር **ኢ-ተጋማሽ** ቁጥር ከሆነ፣ አውራ ጎዳናው አብዛኛውን ጊዜ በሁለቱም ጫፎች ካሉት ኢንተርስቴት አውራ ጎዳናዎች ጋር ይገናኛል፣ ለምሳሌ I-276 ፊላዴልፊያ። ብዙ ጊዜ እንደዚህ ያሉ መንገዶች “ቀለበት” ወይም “የተያያዙ መንገዶች” በመባል ይታወቃሉ።
- ከሶስቱ (3) አሃዞች የመጀመሪያው ቁጥር **ኢ-ተጋማሽ** ቁጥር ሲሆን አውራ ጎዳናው ብዙውን ጊዜ በአንድ (1) ጫፍ ላይ ካለው ሌላ አውራ ጎዳና ጋር የሚገናኝ "መቋጫ ያለው ቅርንጫፍ" መንገድ ነው፤ አንዳንድ ጊዜ ወደ ከተማ መሃል እንደ ዊልያምስፖርት ውስጥ ያለው I-180 ይሄዳል።

የማይል ምልክቶች

የትራፊክ መንገዱ ወደ ግዛቱ ከገባበት ቦታ ጀምሮ ያለውን ርቀት ለማመልከት ወይም ወደ ግዛቱ ድንበር የማይደርስ ከሆነ ደግሞ ከመጀመርያው ጀምሮ ያለውን ርቀት ለማመልከት የማይል ርቀት ምልክቶች በአንዳንድ አውራ ጎዳናዎች ላይ ያገለግላሉ። ቁጥሮቹ ለምስራቅ-ምዕራብ መንገዶች በግዛቱ ምዕራባዊ ክፍል ከዜሮ ጀምሮ የሚጨምሩ ሲሆን ለሰሜን-ደቡብ መንገዶች ደግሞ በግዛቱ ደቡባዊ ክፍል ከዜሮ ጀምሮ ይጨምራሉ። ወደ ምስራቅ ወይም ወደ ሰሜን ሲጓዙ ቁጥሮቹ ይጨምራሉ ወደ ምዕራብ ወይም ወደ ደቡብ ሲጓዙ ይቀንሳሉ። ለምሳሌ በኢንተርስቴት አውራ ጎዳና I-80 ከምዕራብ በኩል ወደ ፔንሲልቬንያ ሲገቡ የማይል ምልክቶቹ ማይል 1 ላይ ይጀምራሉ እና ወደ ምስራቅ ሲጓዙ ይጨምራሉ። የማይል ምልክቶችን እንዴት ማንበብ እንደሚችሉ ማወቅ የት እንዳሉ በትክክል ለማወቅ እና የመንገድ ዳር እርዳታ ለመጠየቅ መደወል ካለብዎት ግምታዊ ቦታ ለመስጠት ይረዳዎታል።

የመንገድ መስመር ምልክቶች

ከዚህ በታች ያሉት ምልክቶች እርስዎ እየተጓዙበት ያለውን መንገድ ያመለክታሉ።

የመንገድ ምልክቱ መንገዱ **የአሜሪካ የመንገድ ቁጥር 22**መሆኑን ያሳየዎታል።

የኪይስቶን ምልክቱ መንገዱ **የፔንሲልቫኒያ የመንገድ ቁጥር 39** መሆኑን ያሳይዎታል።

በዚህ የመንገድ ምልክት ላይ ያለው **የመገናኛ ሰሌዳ** ወደ የአሜሪካ መገናኛ እየተቃረቡ እንደሆነ ያሳያል። የመንገድ ቁጥር 22።

በዚህ የመንገድ ምልክት ላይ ያለው **የአቅጣጫ ሰሌዳ** የሚያሳየው በዩናይትድ ስቴትስ መንገዶች ወደ ምዕራብ እየተጓዙ መሆኑን ነው። የመንገድ ቁጥር 22።

በዚህ የመንገድ ምልክት ስብስብ ላይ ያለው **ተጨማሪ ቀስት** ማለት በአሜሪካ መጓዝ ለመቀጠል ወደ ቀኝ መታጠፊያ እየተቃረቡ ነው ማለት ነው። የመንገድ ቁጥር 22 ምዕራብ።

የመንገድ ምልክቱ እና "ወደ" የሚለው ምልክት እና ተጨማሪው ቀስት ማለት በዩናይትድ ስቴትስ ወደ ተሰየመ መንገድ መግባት ከፈለጉ ማለት ነው። የመንገድ ቁጥር 22፣ ወደፊት መቀጠል አለብዎት።

የአገልግሎት ምልክቶች

የሚከተሉት ምልክቶች የአገልግሎት ምልክቶች ምሳሌዎች ናቸው። ምልክቶቹ ካሬ ወይም አራት ማዕዘን ናቸው፣ ነጭ ፊደላት ወይም ምልክቶች ያላቸው ሰማያዊ ናቸው፣ እና በሚቀጥለው መውጫ ላይ የሚገኙ የተለያዩ አገልግሎቶች ቦታን ያሳያሉ።

ሆስፒታል

ስልክ

ምግብ

ጋዝ

ናፍጣ

ማረፊያ

ቱሪስቶችን ለመርዳት የተተከሉ የአቅጣጫ ምልክቶች

እነዚህ ምልክቶች አራት ማዕዘን ወይም ካሬ ቅርፅ ያላቸው ሲሆን ነጭ ፊደላት ያሉት ቡናማ ወይም ሰማያዊ ቀለም ሊሆኑ ይችላሉ። ምልክቶቹ እንደ ሙዚየሞች፣ ታሪካዊ ቦታዎች ወይም አገራዊ ፓርኮች ወደ መሳሰሉት የቱሪስት መስህቦች አሽከርካሪዎችን ይመራሉ።

የትራፊክ መስመር ምልክቶች

አብዛኛዎቹ መንገዶች የመንገዱን መሃል፣ የመጓጓዣ መስመሮችን ወይም የመንገዱን ዳር ለማሳየት የሚያስችሉ ቋሚ ምልክቶች አሏቸው። የመንገዱን መሀል የሚያሳዩ ምልክቶች ቀጥ ያሉ መስመሮች ወይም የተበጣጠሱ መስመሮች ናቸው። እነዚህ የትራፊክ መስመር ምልክቶች እና ቅቦች ልዩ የመንገድ መስመር አጠቃቀምን ያመለክታሉ። ቢጫ ቀለም ያላቸው መስመሮች ተቃራኒ አቅጣጫ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎችን ይለያሉ። ቢጫ መስመሮች ባለ ሁለት መስመር መንገዶችን ለመክፈል፣ የተከፋፈሉ መንገዶችን የግራ ጠርዝ ለማመልከት እንዲሁም የአንድ አቅጣጫ መንገዶችን እና መወጣጫዎችን ለመለየት ያገለግላሉ። ቀጥ ያሉ ነጭ መስመሮች በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚሄዱ የተሽከርካሪዎች መስመሮችን ይለያሉ። ቀጥ ያሉ ነጭ መስመሮች በተጨማሪ የመንገዱን የቀኝ ዳር ለማመልከት ይጠቅማሉ።

እንደ አጠቃላይ ደንብ፣ የተበጣጠሱትን መስመሮች መሻገር ይቻላል፣ ቀጥ ያሉትን ግን መታጠፊያ ላይ ካልሆነ በቀር መሻገር አይፈቀድም። የተለያዩ የትራፊክ መስመር ምልክቶች እና ትርጉማቸው አንዳንድ ምሳሌዎች ከዚህ በታች ቀርቧል።



አንድ የተበጣጠሰ ቢጫ መስመር ባለ ሁለት አቅጣጫ ባለ ሁለት መስመር መንገድ መሃል ያመለክታል። አስተማማኝ ሁኔታዎች ካሉ በሁለቱም በኩል ማለፍ ይፈቀዳል። በሚያልፉበት ጊዜ ወደ ተቃራኒው አቅጣጫ ያለውን መስመር መጠቀም ይኖርብዎታል።



ድርብ፣ ቀጥ ያለ ቢጫ የመሀከል መስመር ባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ መሃል ያሳያል። ምንም እንኳን **ማለፍ አይፈቀድም** የሚል ምልክት ባይደረግበትም፣ እንደዚህ አይነት ምልክት በተሰጠው መንገድ ላይ በየትኛውም አቅጣጫ የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን ማለፍ አይፈቀድም።



የቀጥ ያለ ቢጫ መስመር እና የተበጣጠሰ ቢጫ መስመር ጥምረትም ባለ ሁለት አቅጣጫ መንገድ መሃል ያሳያል። የተበጣጠሰው መስመር በእርስዎ በኩል ከሆነ እና አስተማማኝ ሁኔታዎች ካሉ ማለፍ ይችላሉ፣ ነገር ግን ቀጥ ያለው ቢጫ መስመር በእርስዎ በኩል በሚሆንበት ጊዜ ማለፍ አይችሉም።

እንደነዚህ ያሉት ምልክቶች በብዙ ባለ ሶስት መስመር ወይም ባለ አምስት መስመር አውራ ጎዳናዎች ላይ ሊገኙ ይችላሉ። ውጫዊው ቀጥ ያለው ቢጫ የመሃል መስመር ማለት ለማለፍ የመሃሉን የመንገድ መስመር መጠቀም አይችሉም ማለት ነው። ውስጣዊው የተበጣጠሰ ቢጫ እና ቀጥ ያለው ቢጫ የመሃል መስመር በሁለቱም አቅጣጫ የሚሄዱ ተሽከርካሪዎች በግራ በኩል ለመታጠፍ ብቻ መሃል ያለውን የመንገድ መስመር መጠቀም እንደሚችሉ ያሳያል። የመሃል መታጠፊያ መስመሮችን በአስተማማኝ ሁኔታ ስለመጠቀም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ምዕራፍ 3ን ይመልከቱ።



መካከል ላይ መለያ የሌላቸው ባለብዙ የመንገድ መስመር አውራ ጎዳናዎች (የመሃል መከፋፈያዎች) ብዙ ጊዜ ምስሉ ላይ እንደሚታየው ምልክት ይደረግባቸዋል። የተበጣጠሱ ነጭ መስመሮች በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚሄዱ ተሽከርካሪዎች የትኛዎቹን መስመሮች መጠቀም እንደሚችሉ ያሳያሉ። ለማለፍ የተበጣጠሱትን ነጭ መስመሮች ማቋረጥ ይችላሉ (የማለፊያ መስመሩ ክፍት መሆኑን ያረጋግጡ) ነገር ግን ለማለፍ ድርብ ቢጫ መስመርን መሻገር አይፈቀድልዎትም። የትራፊክ ፍሰቱ (ተሽከርካሪዎች) ከቢጫው መስመር በስተግራ በኩል በተቃራኒው አቅጣጫ እየተጓዘ ነው።



ይህ ንድፍ በአብዛኛዎቹ የሚከፋፍል መካከለኛ ቦታ ባላቸው (የመሃል መከፋፈያዎች) የተገደቡ የመዳረሻ ባላቸው አውራ ጎዳናዎች ላይ ጥቅም ላይ ይውላል። የመንገዱ ቀኝ ጠርዝ ቀጥ ባለ ነጭ መስመር ምልክት ይደረግበታል። የእያንዳንዱ ጎን የግራ ጠርዝ ቀጥ ባለ ቢጫ መስመር ምልክት ይደረግበታል። ለእያንዳንዱ ጎን ያሉት የመንገድ መስመሮች በተበጣጠሱት ነጭ መስመሮች ምልክት ይደረግባቸዋል፣ እነርሱን መሻገር ይቻላል።

የትራፊክ መስመር ምልክቶች በመቆጣጠሪያ እና የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ላይ የሚለጠፉ መልዕክቶችን የሚደግፉ በመንገድ ላይ የተቀቡ ቃላትን እና ቀስቶችን ያካትታሉ። ለምሳሌ **ከፊት ያቁሙ** የሚል ምልክት ካለበት ከመገናኛ በፊት **ያቁሙ** የሚል ምልክት ያለው፣ **ቅድሚያ ይስጡ** ወይም ነጭ ባለ ሶስት መአዝን ቅርጾች በመንገድ መስመሩ ላይ ቀለም የተቀቡ እየቀረበ ላለው ተሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት እንዳለብዎት ለማመልከት፣ **ትምህርት ቤት** ከትምህርት ቤት አካባቢ በፊት፣ ሀዲድ ከመግባትዎ በፊት **R X R**፣ **የብስክሌት መንገድ** ለብስክሌተኞች የተዘጋጀ መንገድ፣ **ብቻ** ከሚል ምልክት ጋር በግራ ወይም በቀኝ ቀስት መንገዱ ለመታጠፊያ ብቻ መሆኑን ለመጠቆም እና አውራ ጎዳና መወጣጫዎች ላይ የሚደረግን ጉዞ አቅጣጫ የሚያመላክቱ ትላልቅ ነጭ ቀስቶች ይገኙበታል።

ምዕራፍ 2 ማጠቃለያ ጥያቄዎች

1. ይህን ምልክት ሲያዩ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፦



A. ሙሉ በሙሉ ያቁሙ፣ እግረኞችን እና የሚያቋርጥ ተሽከርካሪዎችን ያረጋግጡ።
B. ሙሉ በሙሉ ሳያቆሙ ፍጥነትዎን ይቀንሱ።
C. ሙሉ በሙሉ ያቁሙ እና አረንጓዴ መብራት እስኪበራ ድረስ ይጠብቁ።
D. ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ተሽከርካሪዎች መኖራቸውን ያረጋግጡ።

2. ይህ የ ______________ ምልክት ቅርፅ እና ቀለም ነው።

A. ቁም
B. የተሳሳተ መንገድ
C. ቅድሚያ ይስጡ
D. አይግቡ

3. ይህ ምልክት ማለት፦

A. ያቁሙ
B. ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ መታጠፍ አይፈቀድም
C. ቅድሚያ ይስጡ
D. አይግቡ

4. ይህ ምልክት ማለት፦

A. ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ መታጠፍ አይፈቀድም
B. መታጠፍ አይፈቀድም
C. ወደ ግራ መታጠፍ አይፈቀድም
D. ወደ ቀኝ መታጠፍ አይፈቀድም

5. ይህ ምልክት ማለት፦

A. ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ መታጠፍ አይፈቀድም
B. ወደ ግራ መታጠፍ አይፈቀድም
C. ወደ ቀኝ መታጠፍ አይፈቀድም
D. መታጠፍ አይፈቀድም።

6. ይህ ምልክት ማለት፦

A. ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ መታጠፍ አለብዎት
B. ወደ T-ቅርጽ የመንገዶች መገናኛ እየተቃረቡ ነው
C. አሁን የያዙት መንገድ ከተከፈለ አውራ ጎዳና ላይ ይገናኛል
D. በተከፈለ አውራ ጎዳና ላይ ያለውን ድልድይ መኖሩን ያሳያል።

7. ነጭ በትር የሚጠቀም እግረኛ በአቅራቢያዎ ካለ ተጨማሪ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልግዎታል ምክንያቱም፦

A. መስማት የተሳነው ነው
B. የአእምሮ እክል አለበት
C. ማየት የተሳነው ነው
D. የመራመድ ችግር አለበት

8. ነጭ በተር የያዘ ወይም በውሻ እርዳታ የሚመራ ማየት የተሳነው እግረኛ በአቅራቢያ ካለ ምን ማድረግ አለብዎት፦

A. ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ለማቆም ይዘጋጁ
B. በቅድሚያ እርስዎ ይሂዱ
C. በተለመደው ሁኔታ ይቀጥሉ
D. መኪናዎን በፍጥነት ይንዱ

9. በባቡር መንገድ ማቋረጫ ላይ ምንም የትራፊክ ምልክቶች ከሌሉ ምን ማድረግ አለብዎት፡-

A. ባቡር ሲቃረብ ካዩ ወይም ከሰሙ ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ለማቆም ይዘጋጁ
B. በተቻለ ፍጠነት ቶሎ ብለው በባቡር ሀዲዱ ላይ ይሂዱ
C. በተለመደው ፍጥነት በመሻገር ይቀጥሉ
D. በባቡር ሀዲዱ ላይ ቀስ ባለ ፍጥነት ይቀጥሉ

10. በባቡር ሐዲድ መሻገሪያ ላይ በሮቹ ዙሪያ መንዳት የሚችሉት መቼ ነው፡-

A. ባቡሩ ካለፈ በኋላ
B. በጭራሽ
C. መብራቶቹ ብልጭ ማለት ሲያቆሙ
D. ሌሎች አሽከርካሪዎች በበሩ ዙርያ ሲያሽከረክሩ

11. ይህን ምልክት ከእርስዎ የመንገድ መስመር በላይ ላይ ካዩ፡-

A. በዚህ የመንገድ መስመር ተጠቅመው ከከፍተኛ ፍጥነት መንገድ (ፍሪዌይ) መውጣት አይፈቀድልዎትም
B. በመተላለፊያው መቀጠል ወይም በዚህ የመንገድ መስመር ላይ ካለው የከፍተኛ ፍጥነት መንገድ (ፍሪዌይ) መውጣት ይችላሉ
C. በዚህ የመንገድ መስመር ላይ ሊቆዩ እና በመተላለፊያው ውስጥ ሊቀጥሉ ይችላሉ
D. በዚህ የመንገድ መስመር ውስጥ ከቆዩ ከፍጥነት መንገዱ መውጣት አለብዎት

12. የአውራ ጎዳና (ሀይዌይ) እና የፍጥነት መንገድ (ኤክስፕረስ ዌይ) መመሪያ ምልክቶች፡-

A. ብርቱካናማ ቀለም ከጥቁር ፊደላት ጋር
B. አረንጓዴ ቀለም ከነጭ ፊደላት ጋር
C. ቢጫ ቀለም ከጥቁር ፊደላት ጋር
D. ቀይ ቀለም ከነጭ ፊደላት ጋር

13. ይህ ምልክት ጥቅም ላይ የሚውለው ለአሽከርካሪዎች ስለ ምን ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ነው፡-

A. ከፊት ያሉ የመንገዶች መገናኛዎች
B. የመንገድ ግንባታ
C. ከፊት ያሉ የመንገድ ኩርባዎች
D. በመንገድ መስመሮች ላይ የሚኖሩ ለውጦች

14. ይህ ምልክት የሚነግርዎት፡-

A. በዚህ መንገድ መታጠፍ አይፈቀድም
B. ወደፊት ሲሄዱ መንገዱ እየጠበበ ይሄዳል
C. ወደፊት ተከታታይ ኩርባዎች አሉ
D. መንገዱ እርጥብ በሚሆንበት ጊዜ ሊያንሸራትት ይችላል

15. ይህ ምልክት ማለት፡-

A. ከፊት ወደ ግራ የሚጠመዘዝ ኩርባ አለ
B. ተከታታይ ኩርባዎች አሉ
C. ከፊት S-ቅርጽ ያለው ጠመዝማዛ ኩርባ አለ
D. እርጥብ በሚሆንበት ጊዜ ያንሸራትታል

16. ይህ ምልክት የሚያመለክተው፡-



A. ከፊት ደገታማ ኮረብታ አለ
B. በኮረብታው ላይ የጭነት መኪናዎች አይፈቀዱም
C. ከፊት የእንጨት ማጓጓዣ መንገድ አለ
D. በኮረብታው ላይ የጭነት መኪናዎች አሉ

17. ቢጫ እና ጥቁር የአልማዝ ቅርጽ ያለው ምልክት፡-



A. በመንገዱ ላይ ወይም በአቅራቢያ ስላሉ ሁኔታዎች ያስጠነቅቅዎታል
B. ከፊትዎ ወዳሉ ከተሞችና መንደሮች አቅጣጫ ለመጠቆም ይረዳል
C. ስለ የትራፊክ ህጎች እና ደንቦች ይነግርዎታል
D. ከፊት ስላለ የመንገድ ግንባታ ይነግርዎታል

18. ይህ ቅርፅ እና ቀለም ያለው ምልክት የ ______________ ምልክት ነው።



A. ማለፍ የተከለከለበት አካባቢ
B. የተሳሳተ መንገድ
C. የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ
D. ቁም

19. ከእነዚህ ምልክቶች መካከል የተከፋፈለ አውራ ጎዳና መጨረሻን ለማሳየት ጥቅም ላይ የሚውለው የትኛው ነው?



A. 2
B. 4
C. 3
D. 1

20. ይህ ምልክት ጥቅም ላይ የሚውለው ለአሽከርካሪዎች ስለ ምን ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ነው፦

A. የመንገድ መስመር ያበቃል፣ ወደ ግራ ይቀላቀሉ
B. ከፊት ያሉ የመንገድ ኩርባዎች
C. ከፊት ያሉ የመንገዶች መገናኛዎች
D. የመንገድ ግንባታ

21. ይህ ምልክት የሚያሳየው አይነት፦



A. የመንገዶች መገናኛ
B. የመንገድ ኩርባ
C. ወደ ቀኝ መታጠፍ/መዞር
D. የመንገድ መስመር ለውጥ

22. ይህ ምልክት የሚያሳየው አይነት፦

A. ወደ ቀኝ መታጠፍ/መዞር
B. የመንገዶች መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገድ
C. የመንገድ መስመር ለውጥ
D. የመንገድ ኩርባ

23. ይህን ምልክት ሲያዩ በጣም ሊያሳስብዎት የሚገባው ነገር ምንድን ነው?

A. የመኪናዎ አንድ ጎን ከሌላው ከፍ ያለ ስለሆነ የግንባር መብራቶችዎ ሳይስተካከሉ መንዳት
B. ወደ ዳር ከወጡ የጎማ ጉዳት ሊደርስ ይችላል
C. በመንገዱ ዳር ውሃ ካለ መኪናዎ በውሃው ምክንያት ላይሽከረከር ይችላል
D. እጅግ ዝቅተኛ በሆነ የመንገድ ዳር ምክንያት ወደ ዳር ከወጡ መኪናዎን መቆጣጠር ሊያቅትዎት ይችላል

24. የዚህ ምልክት ትርጉም ምንድን ነው?



A. ከፊት ያለው የትራፊክ መብራት ምልክት ቀይ ነው።
B. ከፊት ያለው የትራፊክ መብራት ምልክት የተሰባበረ ነው።
C. ከፊት ያለው የትራፊክ መብራት ምልክት አረንጓዴ ነው።
D. ከፊት የትራፊክ መብራት ምልክት አለ።

25. ይህ ምልክት ማለት፦

A. የተከፋፈለ አውራ ጎዳና ያበቃል
B. ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ ይጀምራል
C. ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ ያበቃል
D. የተከፋፈለ አውራ ጎዳና ይጀምራል

26. ከሚከተሉት አማራጮች ከላይ እስከ ታች የትራፊክ መብራቶች ትክክለኛው ቅደም ተከተል የትኛው ነው፦



A. ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ
B. ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ
C. አረንጓዴ፣ ቀይ፣ ቢጫ
D. አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ

27. አረንጓዴ ቀስት ወደ አረንጓዴ መብራት ከተቀየረ፡ እርስዎ፡-
- A. አሁንም መታጠፍ ይችላሉ ነገር ግን ለሚመጡ መኪኖች ቅድሚያ መስጠት አለቦት
- B. ከእንግዲህ መታጠፍ አይችሉም እና ቀጥ ብለው መቀጠል አለብዎት
- C. አሁንም የመታጠፍ መብት አልዎት
- D. ከእንግዲህ ቀስቱ በሚያመለክተው መንገድ መታጠፍ የለብዎትም

28. በአንድ የመንገዶች መገናኛ ላይ ቋሚ ቢጫ መብራት ማለት ምን ማለት ነው፡-
- A. ይሂዱ
- B. ለሌሎች መኪኖች ቅድሚያ መስጠት
- C. ፍጥነትዎን በመቀነስ ለማቆም ዝግጁ ይሁኑ
- D. ያቁሙ

29. ብልጭ የሚል ቢጫ ቀስት ማለት እርስዎ፡-
- A. ማቆም ኣለብዎት እና አረንጓዴ ቀስት ሲመጣ መታጠፉን መቀጠል አልብዎት
- B. ፍጥነትዎን መቀነስ እና ለማቆም ዝግጁ መሆን አለብዎት።
- C. መታጠፍ ይችላሉ፤ ነገር ግን መጀመሪያ ለሚመጡት ተሽከርካሪዎች እና እግረኞች ቅድሚያ መሰጠት አለብዎት
- D. የመታጠፍ መብት አለዎት

30. ብልጭ የሚል ቢጫ መብራት ማለት እርስዎ ማድረግ ያለብዎት የትኛውን ነው፡-
- A. ፍጥነትዎን መቀንስ እና በጥንቃቄ መቀጠል
- B. መንገዱ ክፍት ከሆነ መቀጠል
- C. ማቆም እና አረንጓዴ መብራት ሲበራ ጉዞ መቀጠል
- D. ማቆም እና መንገዱ ክፍት ሲሆን መቀጠል

31. ከሚከተሉ የትኛውን ሲያዩ ነው ማቆም ያለቦት፡-
- A. ብልጭ የሚል ቀይ መብራት
- B. ቋሚ ቢጫ መብራት
- C. ቢጫ ቀስት
- D. ብልጭ የሚል ቢጫ መብራት

32. በመገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገድ ላይ ቋሚ አረንጓዴ መብራት ማለት እርስዎ፡-
- A. ፍጥነትዎን መቀነስ እና ለማቆም ዝግጁ መሆን አለብዎት
- B. ጉዞውን ከመቀጠልዎ በፊት ማቆም እና የሚመጡትን ተሽከርካሪዎች ማረጋገጥ አለብዎት
- C. መንገዱ ክፍት ከሆነ በመገናኛው አልፈው መንዳት ይችላሉ
- D. ወደ ቀኝ መታጠፍ አይፈቀድልዎትም

33. ቋሚ ቢጫ መብራት ___________ መብራት በቅርቡ ይታያል ማለት ነው።
- A. ብልጭ የሚል ቢጫ
- B. ቋሚ አረንጓዴ
- C. ቋሚ ቀይ
- D. ብልጭ የሚል ቀይ

34. ቢጫ መብራት ላይ በጥንቃቄ ጉዞዎን መቀጠል የሚችሉት መቼ ነው፡-
- A. መንገድዎን የሚያቋርጥ የአስቸኳይ ጊዜ ተሽከርካሪ (አምቡላንስ ወይም ፖሊስ መኪና) ካለ
- B. መንገዱን የሚሻገሩ እግረኞች ከሌሉ
- C. ወደ ቀኝ እየታጠፉ ከሆነ
- D. በመገናኛ ውስጥ ከሆኑ

35. በቀይ መብራት ጊዜ ወደ ግራ መታጠፍ የሚችሉት ምን አይነት ሁኔታ ሲኖር ነው፡-
- A. በተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣ ተሽከርካሪ ከሌለ
- B. ከባለሁለት አቅጣጫ መንገድ ወደ ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ እየታጠፉ ከሆነ
- C. ከባለአንድ አቅጣጫ መንገድ ወደ ሌላ ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ እየታጠፉ ከሆነ
- D. ከፊትዎ ያለው መኪና ወደ ግራ ከታጠፈ

36. የትራፊክ መብራት ከተበላሸ ወይም የማይሰራ ከሆነ ምን ማድረግ አለብዎት፦

A መቆም እና እስኪስተካከል ድረስ መጠበቅ
B መቆም እና ፖሊስ እስኪመጣ ድረስ መጠበቅ
C. አራት አቅጣጫ ያለው ቁም ምልክት እንደሆነ አስበው መቀጠል
D. ሁልጊዜ እንደሚያደርጉት መቀጠል

37. ቀይ መብራት ላይ ወደ ቀኝ መታጠፍ የሚችሉት መቼ ነው፦

A. መጀመሪያ አቁመው ተሽከርካሪዎችን እና እግረኞችን ካረጋገጡ
B. ወደ ቀኝ መታጠፊያ ቀይ ቀስት መኖሩን ካዩ
C. በግራ የመንገድ መስመር ላይ ከሆኑ
D. መጀመሪያ ፍጥነትዎን ከቀነሱ

38. አረንጓዴ መብራት ላይ ወደ ቀኝ ሲታጠፉ ምን ማድረግ አለብዎት፦

A. የተለመደውን የመንዳት ፍጥነት ጠብቆ መንዳት
B. መቆም እና የሚመጣውን ተሽከርካሪ መመልከት
C. ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት
D. የተለመደውን የመንዳት ፍጥነትዎን መጨመር

39. የትምህርት ቤቱ የፍጥነት ምልክት ቢጫ መብራቶች ሲበሩ የፍጥነት ገደቡ በሰዓት ____________ ማይል ነው።

A. 25
B. 15
C. 20
D. 35

40. በባቡር ሐዲድ መሻገሪያ ላይ ብልጭ የሚል ቀይ መብራት ማለት ምን ማለት ነው፦

A. ያቁሙ እና የትራፊክ ምልክቶቹ እስኪጠናቀቁ ድረስ አይቀጥሉ
B. ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና መንገዱ ክፍት ከሆነ ይቀጥሉ
C. በጥንቃቄ ይቀጥሉ
D. ቅድሚያ የማለፍ መብት አለዎት

41. በመስመር አጠቃቀም መቆጣጠሪያ ምልክት ላይ ያለው ይህ አረንጓዴ ቀስት ምን ማለት ነው፦

A. ይህንን የመንገድ መስመር መጠቀም ይችላሉ
B. በዚህ የመንገድ መስመር ላይ ምንም አይነት ተሽከርካሪዎች እንዲሄዱ አይፈቀድም
C. ቅድሚያ የማለፍ መብት አለዎት
D. ወደዚህ የመንገድ መስመር መቀላቀል አለብዎት

42. ይህ ምልክት ማለት፦

A. ከፊት እግረኞች አሉ
B. የግንባታ ቀጠና መጨረሻ
C. ከፊት የትምህርት ቤት መሻገሪያ አለ
D. ከፊት አስጠንቃቂ ሰው አለ

43. ይህ ምልክት ምን ማለት ነው፦

A. አንድ የማህበረሰብ አገልግሎት ድርጅት ከፊት ባለው አውራ ጎዳና መንገድ ላይ ቆሻሻ እየሰበሰበ ነው
B. ከፊት ባለው የስራ ቀጠና ባለው መንገድ ውስጥ ወይም ለመንገዱ በጣም ቅርብ በሆነ ሁኔታ ሰራተኞች አሉ
C. ከፊት ልጆች እየተጫወቱ ነው
D. ከፊት የእግረኛ መሻገሪያ መንገድ አለ

44. በስራ ቀጠና ውስጥ ያለ የቀስት ፓነል ከሚከተሉት ቅርጾች ውስጥ አንዱን ይሳያል፤ ትርጉሙ ምንድን ነው፦



A. በምልክቱ ላይ ያሉት አምፖሎች ተበላሽተዋል
B. በጥንቃቄ ይንዱ
C. ወዲያውኑ የመንገድ መስመርን ይለውጣል
D. ትራፊክን በተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ሬዲዮ ጣቢያ ያዳምጡ

45. በምሳሌው ውስጥ የሚታየው የመሃል የመንገድ መስመር ጥቅም ላይ የሚውለው ከሚከተሉ ለየትኛው ነው፦

A. ለመደበኛ ጉዞ
B. ወደ ግራ ብቻ ለመታጠፍ
C. ለማለፍ ብቻ
D. ለአስቸኳይ ጊዜ ተሽከርካሪዎች (አምቡላንስ ወይም የፖሊስ መኪና) ብቻ

46. ሁለት የመንገድ መስመሮችን የሚከፍለው መስመር ____________ መስመር ከሆነ ማለፍ ይችላሉ።
A. የተበጣጠሰ ነጭ
B. ድርብ ቀጥ ያለ ቢጫ
C. ቀጥ ያለ ቢጫ
D. ቀጥ ያለ ነጭ

47. በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚጓዙ የተሽከርካሪ የመንገድ መስመሮች በ ____________ መስመሮች ይለያያሉ።
A. ቢጫ
B. ነጭ
C. ቀይ
D. ጥቁር

48. በ ____________ መሃከለኛ መስመር በሁለቱም በኩል ሌላ መኪና ማለፍ አይፈቀድልዎትም።
A. የተጣመረ ቀጥ ያለ እና የተበጣጠሰ ቢጫ
B. ነጠላ የተበጣጠሰ ቢጫ
C. ድርብ ቀጥ ያለ ቢጫ
D. ነጠላ የተበጣጠሰ ነጭ

49. ቀጥ ያሉ ቢጫ መስመሮችን ማለፍ የሚችሉት፦
A. በተመሳሳይ አቅጣጫ የሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪን ለማለፍ
B. የቀን ጊዜ ላይ ብቻ
C. በማንኛውም ጊዜ
D. ሲታጠፉ

50. በቀኝ በኩል ያለው የመንገድ ጠርዝ በ ______________ መስመር ምልክት ይደረግበታል።
A. የተበጣጠሰ ነጭ
B. ቀጥ ያለ ቢጫ
C. ቀጥ ያለ ነጭ
D. የተሰባበረ ቢጫ ድምጽ

51. በተቃራኒ አቅጣጫ የሚሄዱ የትራፊክ መስመሮች በ ______________ መስመሮች ይለያያሉ።
A. ነጭ
B. ቀይ
C. ጥቁር
D. ቢጫ

52. ይህን ጥቁር እና ቢጫ ምልክት ሲያዩ ትርጉሙ ምንድን ነው፦



A. በስተቀኝ ያለው መንገድ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ለመጓዝ የታሰበ ነው
B. በመንገድ ግንባታ ምክንያት ወደ ቀኝ የሚቀይር መንገድ አለ
C. ከፊት ያለው መንገድ በከፍተኛ ሁኔታ አቅጣጫውን ስለሚቀይር ፍጥነትዎን ይቀንሱ
D. ከፊት በስተቀኝዎ በኩል የመንገዶች መገናኛ አለ

53. ይህን ምልክት ሲያዩ ትርጉሙ ምንድን ነው፦

A. በመንገዱ ላይ የሆነ አካላዊ ነገር አለ
B. ከቀኝ በኩል ተሽከርካሪ እየመጣ ነው
C. መንገዱ ሹል በሆነ ሁኔታ ወደ ግራ ይጠመዘዛል
D. ከፊት የመንገዶች መቀላቀያ ነጥብ አለ

54. በማቆሚያ ምልክት ቁጥጥር በሚደረግበት መገናኛ ላይ፣ በድንጋዩ ላይ በተቀባው ነጭ ጫፍ ባር ጀርባ ስትቆሙ የመንገዱን ትራፊክ በደንብ ማየት ካልቻሉ የሚከተለውን ማድረግ ይኖርብዎታል:-

A. ለ 5 ሰከንዶች ይጠብቁ፣ ከዚያ ይቀጥሉ።
B. ከመቀጠልዎ በፊት የመኪናዎ ድምጽን ያሰሙ
C. መስኮቶችዎን ዝቅ ያድርጉ፣ ትራፊክን (ተሽከርካሪዎችን) ያዳምጡ እና ከዚያ ይቀጥሉ
D. በዝግታ ወደፊት ይሂዱ፣ ተሽከርካሪዎች እና እግረኞች መኖራቸውን ያረጋግጡ፣ እና መንገዱ ክፍት ሲሆን ይቀጥሉ።

55. የተለጠፈው የፍጥነት ገደብ ምንም ያሳያል:-

A. በህግ የተፈቀደው ዝቅተኛው የፍጥነት ገደብ
B. የቅጣት ትኬት እንዳይቆረጥብዎት መሄድ የሚገባዎት ትክክለኛ ፍጥነት
C. በተስማሚ መንገድ እና የአየር ሁኔታ ውስጥ ያለው ከፍተኛው ደህንነቱ የተጠበቀ (አስተማማኝ) ፍጥነት
D. በሁሉም የመንገድ ሁኔታዎች ውስጥ ያለው ከፍተኛው ደህንነቱ የተጠበቀ ፍጥነት

56. ባለሁለት አቅጣጫ መንገድ ያለው አውራ ጎዳና (ሀይዌይ) ከእነዚህ ምልክቶች በየትኛው ነው የሚለየው?



A. 1
B. 2
C. 3
D. 4

57. ከመሃል ሌይን (የመንገድ መስመር) ምን አይነት እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ይችላሉ?

A. ወደ ግራ መታጠፍ
B. ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ዞሮ መታጠፍ
C. ቀስ ብሎ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን ማለፍ
D. ሁሉም መልስ ናቸው

58. ከእነዚህ ምልክቶች ውስጥ አሽከርካሪዎች በስተቀኝ በኩል መቆየት እንደ አለባቸው የሚያመላክተው የትኛው ነው?

A. 2
B. 1
C. 3
D. 4

ምዕራፍ 2 የመልስ ቁልፍ

1. A
2. C
3. D
4. A
5. C
6. C
7. C
8. A
9. A
10. B
11. D
12. B
13. C
14. C
15. D
16. A
17. A
18. A
19. A
20. A
21. A
22. B
23. D
24. D
25. D
26. A
27. A
28. C
29. C
30. A
31. A
32. C
33. C
34. D
35. C
36. C
37. A
38. C
39. B
40. A
41. A
42. D
43. B
44. B
45. B
46. A
47. B
48. C
49. D
50. C
51. D
52. C
53. C
54. D
55. C
56. C
57. A
58. A

ምዕራፍ 3፡
ማሽከርከርን መማር

ይህ ምዕራፍ ደህንነቱ የተጠበቀ ብቁ አሽከርካሪ ለመሆን የሚረዱዎት መረጃዎችን ይዟል። የሚከተሉትን ርዕሶች ያካትታል:-

- በመጀመሪያ ደህንነትን መምረጥ
- የዕለት ተዕለት የመንዳት ክህሎቶች
- ከአሽከርካሪው ጋር የተያያዙ ነገሮች
- ልዩ ሁኔታዎች እና ድንገተኛ አደጋዎች

በመጀመሪያ ደህንነትን ማረጋገጥ

አንዳንድ ጊዜ ተሽከርካሪዎን ከማስነሳትዎ በፊት - ከመሪው ጀርባ በሚቀመጡበት ወቅት ደህንነትዎ - አንዳንድ ጊዜ ተሽከርካሪዎን ከመጀመርዎ በፊት እንኳን - ሊወስኗቸው የሚገቡ አስፈላጊ ምርጫዎች አሉዎት። እርስዎም ሆኑ መኪናዎ "ለመንዳት ብቁ" መሆናቹን በማረጋገጥ ይጀምሩ።

የተሽከርካሪ ፍተሻዎች፡- ለመንዳት ስለ መዘጋጀት

1. **የጎማ ደህንነት -** ጎማዎች የማሽከርከር ደህንነት አስፈላጊ አካል ናቸው። መኪናዎን ከመንዳትዎ በፊት ጎማዎችዎ በቂ የሆነ የጎማ ትሬድ ጥልቀት (ጥርስ) እና በቂ የአየር መጠን እንዳላቸው ያረጋግጡ። ወደ ተሽከርካሪው ከመግባትዎ በፊት በተሽከርካሪው መመሪያ መጽሐፍ ወይም በአሽከርካሪው ወንበር በኩል ባለው የበር ፍሬም ላይ የሚገኘውን የሚመከረውን የፒ.ኤስ.አይ. (ፓውንድ ፐር ስኩዌር ኢንች) የአየር ግፊት መጠን ልኬትን በመጠቀም የጎማውን ግፊት ልክ መሆኑን ያረጋግጡ። ፒ.ኤስ.አይዎን (የግፊት መጠን) ለመፈተሽ የጎማ ግፊት መለኪያ መሳሪያ ይጠቀሙ። ጎማዎችዎ "ማሽከርከር ከመጀመርዎ በፊት" ይፈትሹ :- ማሽከርከር ከመጀመርዎ በፊት ወይም ከነዱ በኋላ ቢያንስ ከሦስት ሰዓታት በኋላ የጎማዎችዎን ግፊት መጠን ይለኩ። የእርስዎ ፒ.ኤስ.አይ (የግፊት መጠን) በበርዎ ፍሬም ላይ ከተጠቀሰው ቁጥር በላይ ከሆነ፣ የግፊት መጠኑ ከተጠቀሰው ጋር እስከሚመሳሰል ድረስ አየር ይቀንሱ። የጎማዎችዎ ግፊት መጠን ከተጠቀሰው የግፊት መጠን በታች ከሆነ መጠኑ ልክ እስኪሆን ድረስ አየር ይጨምሩ (ወይም የጎማ ባለሙያ እንዲረዳዎት ይጠይቁ)።

   ፔኒ ቴስት (የሳንቲም ሙከራን) በመጠቀም የጎማዎን ትሬድ ጥልቀት መለካት ይችላሉ። በየወሩ አንድ ጊዜ ወይም ረጅም የመንገድ ጉዞ ከመጀመርዎ በፊት ጎማዎችዎ አለመሳሳታቸውን እና ጉዳት አለባቸው ወይም የለባቸውም የሚለውን ያረጋግጡ። ጎማ ሊሾ መሆኑ አለመሆኑን (መሳሳቱን አለማሳሳቱን) ለማወቅ የሚረዳ አንድ ቀላል መንገድ ፔኒ ቴስት (የሳንቲም ሙከራን) በመጠቀም ነው።

   1. አንድ ፔኒ ሳንቲምን የአብርሃም ሊንከንን ምስል ላይ በአውራ ጣትዎ እና በጠቋሚ ጣትዎ መካከል አድርገው ይያዙ።
   2. የጎማዎ ትሬድ (ጎድጓዳማ ክፍል) ዝቅ ያለው ቦታ ላይ ይምረጡ እና የሊንከንን ራስ የጎማዎ ትሬድ ጥልቀት ውስጥ ያስገቡት።
   3. የትኛውም የሊንከን ጭንቅላት በትሬድ ከተሸፈነ፣ አስተማማኝ በሆነ የጎማ ትሬድ ጥልቀት መጠን እየነዱ ነው ማለት ነው። የጎማዎ ትሬድ ጥልቀት መጠን ከዚህ በታች ከሆነ ግን፣ የተሽከርካሪዎ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ መንገዱን ቆንጥጦ የመያዝ አቅሙ በእጅጉ ይቀንሳል።

   ጎማዎን ለመቀየር የሚያስፈልጉዎትን መሳሪያዎች ሁል ጊዜ በተሽከርካሪዎ ውስጥ ያስቀምጡ፤ ለምሳሌ:- ትርፍ ጎማ፣ የጎማ ብሎን መፍቻ፣ የመኪና ማንሻ (ካር ጃክ)፣ የእጅ ባትሪ፣ የድንገተኛ አደጋ ምልክቶች እና የሚያንፀባርቁ ትሪያንግሎች፣ የጎማ ማቆሚያ ዌጅ፣ የጎማ ጥገና ኪት እና ጓንት የመሳሰሉትን። ጎማን ስለ መቀየር ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን ገጽ 63ን ይመልከቱ።
2. **ፈሳሾች :–** ሁሉንም የፈሳሽ ደረጃዎች ማለትም ሞተር ዘይት፣ የመኪና የንፋስ መከላከያ ማጠቢያ (ዊንድሺልድ ዎሸር) እና ነዳጅ ይፈትሹ፤ እንዲሁም በተሽከርካሪው መመሪያ መጽሃፍ መሰረት እንደ አስፈላጊነቱ ይሞሉ።
3. **የአሽከርካሪውን ወንበር ያስተካክሉ :-** ፔዳሎቹን እና ሌሎች መቆጣጠሪያዎችን በቀላሉ መድረስ መቻል አለብዎት፤ እንዲሁም ከመኪናው የንፋስ መከላከያ መስታወት (ዊንድሺልድ) ውጭ ግልጽ እይታ ሊኖርዎት ይገባል። የተሽከርካሪዎ መመሪያ መጽሃፍ የተሽከርካሪዎን መሳሪያዎች እንዴት ማስተካከል እንደሚችሉ ያብራራል።
4. **የመቀመጫ የደህንነት ቀበቶ ይሰሩ-** በሁሉም ጉዞዎችዎ ላይ ሁለቱንም የደህንነት ቀበቶዎችዎ ማለትም የወገብ እና የትከሻ ቀበቶዎችን ይሰሩ። በምዕራፍ 5 ላይ የሚገኘውን የፔንስልቬንያን የመቀመጫ የደህንነት ቀበቶ ህግ፣ የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መቀመጫ ህግ እና የኤር ባግ ደህንነት መረጃ ትኩረት ይስጡ።

የደህንነት ቀበቶዎን ማድረግ
የሞት ወይም የአካል ጉዳት አደጋን ለመቀነስ ከምታደርጓቸው ነገሮች ሁሉ በጣም ውጤታማው ነው!

ይህን ያውቁ ኖሯል?
እ.ኤ.አ. በ2017 በፔንስልቬንያ የትራፊክ አደጋ ከደረሰባቸው ሰዎች መካከል 80.2% የሚሆኑት የደህንነት ቀበቶ አድርገው ነበር። ዕድሜያቸው ከ16 እስከ 24 አመት የሆናቸው አሽከርካሪዎች ቀበቶ ሳያስሩ አደጋ የደረሰባቸው አሽከርካሪዎች በደረሰ ጉዳት እና ሞት ቁጥር በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ሁሉ የሚበልጡ ሲሆን፣ የድህንነት ቀበቶ አጠቃቀማቸውም ከሁሉም አንፃር ዝቅተኛው ነው።

5. **በተሳፋሪዎች ክፍል ውስጥ የላሉ ነገሮችን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ያስቀምጡ -** በአደጋ ጊዜ፣ በተሽከርካሪዎ ውስጥ ያሉ ያልታሰሩ እቃዎች ግጭት ከማጋጠሙ በፊት ተሽከርካሪዎ ሲንቀሳቀስበት የነበረው ፍጥነት ይዘው የሚወረወሩ ተወርዋሪ ነገሮች ይሆናሉ። እንደ የጀርባ ቦርሳዎች፣ ሻንጣዎች እና መሳሪያዎች ያሉ ከባድ ነገሮችን በተቻለ መጠን የመኪናው የሻንጣ ማስቀመጫው ቦታ ውስጥ ያስቀምጡ፣ ወይም በተሽከርካሪው የደህንነት ቀበቶዎች አጥብቀው ይሰሩ። እቃዎችን ከኋላ መስኮት በታች ባለው መደርደርያ ቦታ ላይ በጭራሽ እንዳያስቀምጡ።
6. **የኋላ መመልከቻ መስታወቱን እና የጎን መስተዋቶችን ያስተካክሉ :-** በተሽከርካሪዎ ዙሪያ ያሉትን ለማየት አዳጋች የሆኑ ቦታዎችን ለማስወገድ የኋላ መመልከቻው እና የጎን መስተዋቶች ማስተካከል፤ ይህም ለእያንዳንዱ ሹፌር በተለየ መንገድ መስተካከል ሊያስፈልጋቸው ይችላል። የኋላ መመልከቻ መስተዋቱ ከተሽከርካሪዎ ጀርባ ያለውን ትራፊክ ማየት እንዲችሉ በሚያስችል መልኩ መስተካከል አለበት። የጎን መስታወት(ዎቹ) እርስዎ ወደ ግራ/ቀኝ ሲያዞነብሉ የተሽከርካሪዎን ጎን በትንሹ ብቻ ማየት እንዲችሉ ተደርገው መስተካከል አለባቸው። መስተዋቶቹን ማስተካከል

ያለብዎት ወንበርዎን ካስተካከሉ በኋላ ነው።

ማሳሰቢያ:- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ማንኛውንም ነገር ወይም እቃ የኋላ መመልከቻ መስታወቱ ላይ ማንጠልጠል በህግ የተከለከለ ነው። የንፋስ መከላከያ መስታወት (ዊንድሺልድ) በኩል ያለውን እይታ ሊገድብ ወይም ሊያዛባ የሚችል ማንኛውንም ነገር የኋላ መመልከቻ መስታወቱ ላይ መስቀል፣ ማስቀመጥ ወይም ማጣበቅ አይፈቀድም። ታጎች፣ ፈቃዶች እና የጽሁፍ ሰሌዳዎች የኋላ መመልከቻ መስታወቱ ላይ ማስቀመጥ የሚችሉት ተሽከርካሪዎ በሚቆምበት ወቅት ብቻ ነው።

7. **የመኪናው የፊትኛው መስታወት (ዊንድሺልድ) :-** የአሽከርካሪውን የመንገድ እይታ የሚከልል ማንኛውንም ነገር የመኪናው የፊትኛው መስታወት ላይ ማስቀመጥ በህግ የተከለከለ ነው።
8. **አየር ማናፈሻን (ቬንትሌሽን) ያስተካክሉ :-** በተሽከርካሪዎ ውስጥ ሁልጊዜ ንጹህ አየር እንዲኖርዎት ማድረግ አለብዎት። ይህም ነቅተው እንዲቆዩ ይረዳዎታል፤ እንዲሁም በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ከካርቦን ሞኖክሳይድ (ከጭስ የሚወጣ ጋዝ) መመረዝ ይጠብቅዎታል። ስለ ካርቦን ሞኖክሳይድ መመረዝ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 6ን ይመልከቱ።
9. **የጭንቅላት ማስደገፊያዎትን ያስተካክሉ :-** የጭንቅላትዎን ጀርባ በአግባቡ የሚደግፍ የጭንቅላት ማስደገፍያ አደጋ በሚደርስበት ጊዜ የአንገት ጉዳቶችን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ ያግዛል። የጭንቅላት ማስደገፍያዎ የላይኛው ክፍል ቢያንስ የጆሮዎትን ያህል ከፍታ ላይ እንዲሆን ያስተካክሉት። መመሪያዎችን ለማግኘት እባክዎትን የተሽከርካሪዎን መመሪያ መጽሃፍ ይመልከቱ።
10. **የታዘዙልዎትን መነጽሮች/ኮንታክት ሌንሶችዎን ያድርጉ :-** እይታዎን የሚያግዝ መነጽር አዘውትረው የሚያደርጉ ከሆነ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሁልጊዜ ያድርጓቸው። ማታ ላይ የፀሐይ መነፅር ወይም ቀለም ያላቸው ኮንታክት ሌንሶችን አያድርጉ።
11. **በሮችዎን ይቆልፉ :-** በሮችዎን መቆለፍና የደህንነት ቀበቶዎን ማድረግ አደጋ በሚደርስበት ግዜ ከተሽከርካሪዎት ተወርውረው እንዳይወድቁ ያግዝዎታል። ከተሽከርካሪ ተወርውረው መውደቅ የመሞት እድልዎን በ75 በመቶ ይጨምራል። እንዲሁም በመገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶች ላይ ሲቆሙ ወይም ወደ መኪና ማቆሚያ ቦታ ሲገቡ የመኪና ስርቆት ወይም በሌላ መንገድ የጥቃት ሰለባ የመሆን እድልዎን ይቀንሳል።

አሽከርካሪ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች

ተሽከርካሪዎ ለመሄድ ዝግጁ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ደህንነትዎ በሚከተሉት የአሽከርካሪው ሁኔታዎች ላይ ጥገኛ ነው።

ትኩረት አለመስጠት

ለአደጋ መንስኤ የሚሆን በቂ ትኩረት አለመስጠት የሚመጣው ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች ሲጋጥምዎት ወይም እንቅልፍ ሲያጡ ነው።

ይህን ያውቁ ኖሯል?

የአሽከርካሪዎች መዘናጋት ወይም ለመንገድ እና ለትራፊክ ሁኔታዎች ትኩረት አለመስጠት ከ25 እስከ 30 በመቶ ለሚሆኑ ለፖሊስ ሪፖርት የተደረጉ የትራፊክ አደጋዎች መንስኤዎች ናቸው። ይህም በቁጥር ሲገለጽ በየዓመቱ ወደ 1.2 ሚሊዮን የሚጠጉ የትራፊክ አደጋዎችን ማለት ነው።

በሚያሽከረክሩበት ወቅት ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች

1) በሚያሽከረክሩበት ወቅት ትኩረትዎን እንዲያዞሩ፣ **2)** አይኖችዎን ከመንገድ ላይ እንዲያነሱ ወይም **3)** እጆችዎን ከመሪው ላይ እንዲያነሱ የሚያደርጉ ማንኛቸውም ነገሮች ናቸው። እርስዎ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ከሆኑ በቶሎ ምላሽ መስጠት አይችሉም:-

- እየበሉ፣ እየጠጡ፣ ወይም እያጨሱ ከሆነ። እነዚህ ሁሉ የደህንነት ችግሮች ይፈጥራሉ፤ ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ እጆችዎን ከመሪው ላይ እና አይኖችዎን ከመንገድ ላይ እንዲያነሱ ያስገድዱዎታል። በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የሚበሉ ወይም የሚጠጡ አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪቸውን መቆጣጠር ይቸገራሉ፤ በመስመራቸው ውስጥ መቆየት ይቸገራሉ፤ እንዲሁም ብዙ ጊዜ ፍሬን እንዲይዙ ይገደዳሉ።
- እንደ ሬዲዮ፣ ካሴት፣ ሲዲ፣ አይፖድ/ኤምፒ3 (Mp3) ማጫወቻ የመሳሰሉ የድምጽ መሳሪያዎችን ማስተካከል። ማሳሰቢያ:- የጆሮ ማዳመጫዎች/ጆሮ ውስጥ የሚገቡ ትንንሽ ድምጽ ማጉያዎች ለመነጋገር ብቻ በአንድ ጆሮ ብቻ መጠቀም ይቻላል።
- በተንቀሳቃሽ ስልክ ማውራት (እጅዎትን ቢጠቀሙም ባይጠቀሙም)። የጽሑፍ መልዕክት ስለ መጻጻፍ የሚከለክሉ ሕጎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 5ን ይመልከቱ።
- ከሌሎች ተሳፋሪዎች ጋር መስተጋብር መፍጠር። ይህም በተለይም በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ ላሉ አሽከርካሪዎች ትልቅ ችግር ሊሆን ይችላል።**ሌሎች ታዳጊዎች እንደ ተሳፋሪዎች ከእርስዎ ካሉ፣ ብቻዎን ከማሽከርከር ወይም ከአዋቂ ተሳፋሪዎች ጋር ከማሽከርከር ይልቅ አደጋ የመጋለጥ እድልዎ ሰፊ እንደሆነ አሃዛዊ መረጃዎች ያሳያሉ።**
- በተሽከርካሪው ውስጥ ያለ ዕቃ መፈለግ ወይም ማንቀሳቀስ።
- ማንበብ፣ መጻፍ ወይም የጽሑፍ መዕክት መላላክ።
- ራስን መንከባከብ (ፀጉር ማበጠር፣ ሜካፕ ማድረግ)።
- የትራፊክ አደጋ የደረሰበት ቦታ ወይም የሥራ ቦታ ሲያልፉ አንገትን አዝሮ መመልከት።
- ከመንገድ ዳር ያሉ ሰዎችን፣ ነገሮችን ወይም ክስተቶችን መመልከት።

ይህን ያውቁ ኖሯል?

ጥናት እንደሚያሳየው አንድ መደበኛ ትኩረቱ ያልተከፋፈለ አሽከርካሪ ሌላ አሽከርካሪ ስህተት ሲሰራ የመሳሰሉ አስፈላጊ የመንገድ ክስተቶችን ሶስት (3) በመቶ የሚሆነውን ጊዜ ልብ አይልም። ሞባይል ስልክ እየደወለ ያለ አዋቂ ሰው ተመሳሳይ ክስተቶች 13 በመቶ የሚሆነውን ግዜ ልብ ሳይል/ሳያስተውል ይቀራል። ሞባይል ስልክ እየደወለ ያለ ታዳጊ ተመሳሳይ ክስተቶች 53 በመቶ የሚሆነውን ግዜ ልብ ሳይል/ሳያስተውል ይቀራል።

የእንቅልፍ እጦት

ሲደክሙ በቶሎ ምላሽ መስጠት ያቅቶታል፤ የአእምሮ ብቃትዎ እና እይታዎ ይጎዳሉ፤ እንዲሁም ነገሮችን ለመረዳትና ለማስታወስ ይቸገራሉ። በድካም

ስሜት ውስጥ ሆነው ማሽከርከር በአልኮል ተጽእኖ ስር ከመንዳት ጋር ተመሳሳይ ተጽእኖ አለው። ለተከታታይ 18 ሰአታት አለመተኛት በደሞዎት ውስጥ .05 በመቶ ያህል የአልኮል መጠን ኖሮ እንደማሽከርከር ይጎዳል። ለተከታታይ 24 ሰአታት አለመተኛት በደሞዎት ውስጥ .10 በመቶ ያህል የአልኮል መጠን ኖሮ እንደማሽከርከር ይጎዳል። በጣም ከደከመዎት እንቅልፍ ሊወስድዎት እና እንቅልፍ እንደወሰድዎትም በጭራሽ ላያውቁት ይችላሉ። እያሽከረከሩ ለጥቂት ሰኮንዶች ብቻ መተኛት እንኳን ህይወትዎን ሊያሳጣዎት ይችላል። በቀን ከስምንት (8) ሰዓታት በታች የሚተኙ ታዳጊዎች ለመኪና አደጋዎች የመጋለጥ እድላቸው ከፍ ያለ ነው። **ሚያሽከረክሩበት ወቅት ድካም ከተሰማዎት፣ ማድረግ ያለብዎት የመጀመሪያው በጣም ጥሩው ነገር መንዳትዎን ማቆም ነው።**

ይህን ያውቁ ኖሯል?

- በሚያሽከረክሩበት ወቅት በሚተኙ ሹፌሮች ምክንያት በየአመቱ በመላው አሜሪካ፣ ቢያንስ 100,000 የሚሆኑ የተሽከርካሪ አደጋዎች ይከሰታሉ።
- በነዚህ የተሽከርካሪ አደጋዎችም 1,500 የሚሆኑ ሰዎች ህይወታቸውን ያጡ ሲሆን፣ 40,000 የሚሆኑት ደግሞ የአካል ጉዳት ይደርስባቸዋል።
- **በየአመቱ በከፍተኛ የድካም ስሜት ውስጥ ሆኖ ከማሽከርከር ጋር ተያይዘው ከሚከሰቱት 100,000 የተሽከርካሪ አደጋዎች ወደ ግማሽ የሚጠጉት በ15 እና 24 ዕድሜ ክልል ውስጥ ባሉ አሽክርካሪዎች የሚከሰቱ ናቸው።**

የጤና ምክንያቶች

የማሽከርከር ደህንነትዎ በዓይን እይታዎ፣ በጆሮ የመስማት ችሎታ ወይም ከጤናዎት ጋር በተያያዙ ችግሮች ተጽዕኖ ሊደርስበት ይችላል።

- የዓይኖችዎ የማየት አቅም ለማረጋገጥ በየአንድ (1) ወይም ሁለት (2) አመታት ምርመራ ያድርጉ። የጎንዮሽ (የጎን) እይታዎ፣ በእርስዎ እና በሌሎች ነገሮች ያለውን ርቀት የመገመት ችሎታዎ እና በዝቅተኛ የብርሃን ሁኔታዎች የማየት አቅምዎ በበሽታ እና እድሜዎት እየገፋ ሲሄድ በተፈጥሯዊ ሂደት ሊቀንሱ ይችላሉ። ዕይታዎትን በመደበኛነት ካልተመረመሩ በስተቀር ይህንን ሁልጊዜ ማወቅ አይችሉም፤ እንዲሁም የእርምት እርምጃዎችን መውሰድ አይችሉም። መነጽሮችን ወይም ኮንታክት ሌንሶች ማድረግ ካለብዎት፣ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሁሉ መነጽርዎን ወይም ሌንስዎን ማድረግ አለብዎት።
- የመስማት ችሎታ ለእርስዎ ለማየት በሚያዳግትዎት ቦታዎች ተሽከርካሪዎች እንዳሉ ማስጠንቀቅን የመሳሰሉ ያልተጠበቁ አደጋዎችን ያስጠነቅቃል። የመስማት ችሎታ የአደጋ ጊዜ መኪና (ፖሊስ፣ የእሳት አደጋ መኪና፣ አምቡላንስ) እየተቃረበ መሆኑን ለመረዳት ወይም የባቡር መሻገሪያ በቅርብ ርቀት መኖሩን ለማወቅ ጭምር ጠቃሚ ነው።
- የተለያዩ በሽታዎች እና የጤና እክሎች፣ እንደ የአንገት ህመም ወይም የዛለ ጉልበት ያሉ ትናንሽ ችግሮችም እንኳ ተሽከርካሪዎን በአግባቡ የመቆጣጠር ችሎታዎ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። በጣም አደገኛ የሆኑ የጤና ችግሮች መካከል የንቃተ ህሊናን የሚያሳጡ የሚጥሉ በሽታዎች፣ የስኳር ህመም እና የልብ ህመሞች ይገኙበታል። በፔንስልቬንያ ውስጥ፣ ሐኪሞች በደህና የመንዳት ችሎታቸውን ሊጎዳ የሚችል ሕመም እንዳለባቸው በህክምና ያረጋገጧቸውን ሰዎች ለፔንዶት (PennDOT) ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

አልኮል እና መንዳት

- በፔንስልቬንያ እና በመላ አገሪቱ፣ ጠጥተው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች በሺዎች ለሚቆጠሩ የትራፊክ አደጋ ሞት እና ጉዳቶች ተጠያቂ ናቸው። ከጠቅላላ የትራፊክ አደጋ ሞቶች 40 በመቶው የሚሆኑት በመጠጥ ተጽዕኖ ሥር ሆነው በሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ምክንያት የሚከሰቱ ናቸው።
- የፔንስልቬንያ የቅርብ ጊዜ አኃዛዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በሞተር ተሽከርካሪ አደጋ ከሞቱት ከ16 እስከ 20 ዓመት ዕድሜ ያላቸው አሽከርካሪዎች 30 በመቶ የሚሆኑት የአልኮል መጠጥ ጠጥተው ነበር። ይህም እዚህ በፔንሲልቬንያ እንዲሁም በሌሎች ሁሉም የዩ.ኤስ. ግዛቶች ከ21 ዓመት በታች ከሆኑ መጠጣትን የሚከለክሉ የዜሮ ቻይነት ሕጎች ቢኖሩም እንኳ ነው።

ይህን ያውቁ ኖሯል?

በዩናይትድ ስቴትስ፣ ጠጥቶ በሚያሽከረክር ሹፌር ምክንያት በየግማሽ ሰዓት አንድ (1) ሰው ይሞታል፤ እንዲሁም በየሁለት (2) ደቂቃው አንድ (1) ሰው የአካል ጉዳት ይደርስበታል።

- ከ21 ዓመት በታች የሆኑ አሽከርካሪ ከሆኑ እና በደምዎ ውስጥ ያለው የአልኮል መጠን (BAC) .02 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፣ በአልኮል ተጽዕኖ ሥር ሆነው (DUI) እያሽከረከሩ እንደሆነ ይቆጠራሉ።
- አነስተኛ መጠን ያለው አልኮል እንኳ ትኩረትዎን፣ የማገናዘብ ችሎታዎ፣ ውሳኔ የመስጠት አቅሞ እና የማስታወስ ችሎታዎን ይቀንሳል፤ እንዲሁም የማሽከርከር ችሎታዎን ይጎዳል። **ማንም ሰው ጠጥቶ በደህና መንዳት አይችልም።**
- አልኮል በደምዎ ውስጥ እየጨመረ በሄደ መጠን፣ በሚያሽከረክሩበት ወቅት የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እየጨመሩ ይሄዳሉ። እይታዎ እና የውሳኔ አሰጣጥ አቅሞ ይበላሻል፤ ምላሽ የመስጠት አቅም መቀነስ ይጀምራል፤ እንዲሁም ተሽከርካሪዎን በአስተማማኝ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ የመቆጣጠር ችሎታዎን ያጣሉ። እንዲሁም፣ በተመሳሳይ ጊዜ አልኮል ችሎታዎን ይነጥቃል፤ ይህም በአደገኛ ሁኔታ ከልክ ያለፈ በራስ መተማመን እንዲሰማዎት ያደርጋል። ስለዚህ ጠጥተው የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎች ከቁጥጥር ውጭ ሊሆኑ ይችላሉ፤ እና ያንን እንኳን ላያውቁ ይችላሉ።
- ብዙ ሰዎች መጠጣት አደገኛ የሚሆነው ከልክ በላይ መጠጣት ብቻ ነው ብለው ያምናሉ። ይህ ከእውነታው የራቀ ነው። በደም ውስጥ ያለው አልኮሆል መጠን .04 (እድሜያቸው 21 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ አዋቂዎች ከሚፈቀደው ህጋዊ ገደብ ማለትም "0.08" ግማሽ) የሆኑ አሽከርካሪዎች ከሁለት (2) እስከ ሰባት (7) መካከል ያሉ አሽከርካሪዎች በደማቸው ውስጥ አልኮል ከሌለባቸው አሽከርካሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ አደጋ ውስጥ የመሳተፍ እድላቸው ከሁለት (2) እስከ ሰባት (7) እጥፍ ይጨምራል። በደምዎ ውስጥ ያለ የአልኮል መጠን ከህጋዊው ገደብ በጣም ያነሰ ቢሆንም እንኳ፣ አሁንም ቢሆን ህይወትዎን እና የሌሎችን ህይወት አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ። **መጠጥ ጠጥተው ከዚያ ማሽከርከር የሚችሉበት ብቸኛው አስተማማኝ የአልኮል መጠን ምንም አለመጠጣት ብቻ ነው።**

- የአልኮል መጠጥ በሰዎች ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ እንደየግለሰቡ የተለያየ ነው። በደምዎ ውስጥ ያለው የአልኮል መጠን በእድሜዎ፣ በክብደትዎ፣ በጾታዎ፣ በአካልዎ ሁኔታ፣ በተመገቡት የምግብ መጠን እና በሰውነትዎ ውስጥ ባለ ማንኛውም መድሃኒት ወይም መድሃኒት ይጎዳል። በተጨማሪም፣ የተለያዩ መጠጦች የተለያየ የአልኮል ይዘት ሊኖራቸው ይችላል። በሚጠጧቸው መጠጦች ውስጥ ምን ያህል የአልኮል መጠን እንዳላቸው ይወቁ። አንድ (1) መጠጥ 1.5 አውንስ የ80 ፕሩፍ አልኮል፣ 12 አውንስ መደበኛ ቢራ ወይም 5 አውንስ የወይን ጠጅ እንደሆነ ማሰብ አለብዎት።
- ለመጠጣት በህጋዊ እድሜ ላይ ከሆኑና ሃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ለመጠጣት ከፈለጉ፣ በሰአት ከአንድ (1) በላይ መጠጥ አይጠጡ። አማካይ ክብደት ያለው ሰው በእያንዳንዱ መጠጥ ውስጥ ያለውን አልኮሆል ከሰውነቱ ለማስወገድ ቢያንስ አንድ (1) ሰዓት ይወስድበታል። በሰዓት ከአንድ በላይ (1) መጠጥ መጠጣት በደምዎ ውስጥ ያለውን የአልኮል መጠን ከህጋዊው ገደብ በላይ የመጉፋት እድሉ ከፍተኛ ነው።

ይህን ያውቁ ኖሯል?

110 ፓውንድ የምትመዝን ሴት 8 አውንስ ቀለል ያለ ቢራ ከጠጣች በኋላ በደምዋ ውስጥ የሚገኝ የአልኮል መጠን .03 ይደርሳል፤ ይህም ከአንድ ሙሉ ጠርሙስ ወይም ጣሳ ያነሰ ነው። አንድ 140 ፓውንድ የሚመዝን ወንድ 12 አውንስ ሙሉ ቢራ ዋይም ቀለል ያለ ጣሳ ከጠጣ በኋላ በኋላ በደሙ ውስጥ የሚገኝ የአልኮል መጠን (BAC) .025 ይደርሳል።

- በሰዓት አንድ (1) መጠጥ የመጠጣት ህግ ለሁሉም ሰው አይሰራም። አልኮሆል በትናንሽ ሰዎች ላይ በብዛት የሚከማች ሲሆን ሰውነታችን አልኮልን ፕሮሰስ የሚያድርግበት መንገድ ልዩነት ስላለ አንዲት ሴት ከወንድ ጋር እኩል መጠን ያለው አልኮል በተመሳሳይ ጊዜ ጠጥታም በደሟ ውስጥ የሚኖረው የአልኮሆል መጠን ከፍ ሊል ይችላል።
- ጊዜ ብቻ ነው "ከስካር የሚመልስልዎት።" ቡና ወይም ሌሎች ካፌይን ያላቸውን ነገሮች በመጠጣት ወይም ቀዝቃዛ ሻወር በመውሰድ በደምዎ ውስጥ ያለውን የአልኮል መጠን መቀነስ አይችሉም።

ደህንነትዎን ይጠብቁ።

ማንኛውንም የአልኮል መጠን ከጠጡ በኋላ በፍጹም እንዳያሽከረክሩ፤ እንዲሁም አልኮል የጠጣ ሰው እንዳያሽከረክሩ ያድርጉ!

ከዕድሜ በታች የሆነ የአልኮል መጠጥ ስለመጠጣት እና አልኮል ጠጥቶ ስለማሽከርከር ቅጣቶች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ምዕራፍ 4ን ይመልከቱ።

አደንዛዥ እጾች እና ማሽከርከር

በአደንዛዥ እጾች ተጽዕኖ ስር ሆነው ማሽከርከር ህገወጥ ከመሆኑም በላይ ለሞት ሊዳርግም ይችላል። ደህንነትዎ በተጠበቀ ሁኔታ የማሽከርከር አቅሞ አደጋ ላይ የሚወድቀው በአልኮል ብቻ ሳይሆን በብዙ ሕገወጥ፣ በሐኪም የሚታዘዙ እና ያለ ሐኪም ትእዛዝ በሚሸጡ መድኃኒቶችም ጭምር ነው። ከአልኮል ውጭ የሆኑ አደንዛዥ ዕፆች (መድኃኒቶች) ምክንያት በየዓመቱ ከሚደርሱት የሞተር አሽከርካሪዎች ሞቶች ውስጥ 20 በመቶውን ይሸፍናሉ። በተጨማሪም፣ አደንዛዥ እጾችን እና አልኮሆልን አንድላይ መውሰድ የጎንዮሽ ጉዳቶችን የበለጠ ይጨምራል፤ ይህም ለአደጋ የመጋለጥ እድልን በእጅጉ ይጨምራል።

አደንዛዥ እጾች የአንጎልዎን ተግባር ይጎዳሉ፤ እንዲሁም ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የመንዳት ችሎታዎን በእጅጉ ይጎዳሉ። ለምሳሌ፣ ያህል ማሪዋና የሰውነት ምላሽ የመስጠት ፍጥነትን ሊቀንስ፣ የጊዜንና የርቀትን ግምት ሊያዛባ እንዲሁም የሰውነትን ቅንጅት ሊቀንስ ይችላል። ኮኬይን ወይም ሜታምፌታሚን አሽከርካሪው በሚያሽከረክርበት ጊዜ ጠበኛ እና ግዴለሽ እንዲሆን ሊያደርጉ ይችላሉ፤ የተወሰኑ ማስታገሻ መድኃኒቶች ደግሞ የማዞር ስሜትና ድብታ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ኦፒዮይድ እንቅልፍ እንዲወስድዎት እና የሰውነትዎ ፈጣን ምላሽ ፍጥነት ሊቀንስ ይችላል። እንደ የእንቅልፍ ክኒኖች፣ የሳል መድሃኒቶች፣ ፀረ-ሂስታሚኖች እና የአፍንጫ መጨናነቅ የሚካሙ ያሉ በሐኪም የታዘዙ እና ያለሐኪም ትዕዛዝ የሚሸጡ መድኃኒቶች የመንዳት ችሎታዎን በተለያዩ መንገዶች ሊነኩ ይችላሉ። ከመንዳትዎ በፊት የመድኃኒቱን የጎንዮሽ ጉዳቶች በተመለከተ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ማንበብ ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው። ስለ መድሃኒት የጎንዮሽ ጉዳቶች ማንኛቸውም አይነት ጥያቄዎች ካሉዎት ከመንዳትዎ በፊት ከሐኪምዎ ወይም ከፋርማሲስትዎ ጋር መማከር አስፈላጊ ነው። ያስታውሱ፡- የማስጠንቀቂያው ምልክት ላይ - ከባድ ማሽነሪዎችን አትንዱ/አታንቀሳቅሱ - የሚል ከሆነ ተሽከርካሪዎ ከባድ ማሽነሪ ተደርጎ የሚቆጠር እንደሆነ ልብ ይበሉ!

የበለጠ ለማወቅ ሊንኩን ይጫኑ። https://youtu.be/c5mNHOhcpwA

ስለምትወዱት ሰው ወይም ስለራስዎ አደንዛዥ እጽ አጠቃቀም ካሳሰብዎት፣ የ PA አሁን እገዛ ያግኙ የእርዳታ መስመር በ1-800-662-HELP (4357) ማግኘት ይችላሉ። ለጥያቄዎችዎ መልስ ለመስጠት እና እርስዎን ከህክምና አቅራቢዎች ጋር ለማገናኘት ይህ ከክፍያ ነጻ የሆነ መስመር ለ24/7 የሚሰራ ነው።

ይህን ያውቁ ኖሯል?

- በ NHTSA 2013-2014 የመንገድ ዳር የአልኮሆል እና የአደንዛዥ ዕጽ አጠቃቀም በአሽከርካሪዎች ላይ ባደረገው ጥናት መሠረት ከ 4 አሽከርካሪዎች ውስጥ 1 (አንዱ) ደህንነቱ የተጠበቀ የመንዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ቢያንስ አንድ መጠቀማቸውን አረጋግጠዋል።
- በአደጋ ከሞቱት አሽከርካሪዎች መካከል 43% የሚሆኑት የአደንዛዥ እፅ በደማቸው የተገኘ ሲሆን... 37% የሚሆኑት ደግሞ አልኮል ጠጥተው ነበር።
- በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶችም መንዳት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። ማንኛውንም አዲስ መድሃኒት ሲጀምሩ ዶክተርዎን ያነጋግሩ እና ሊከሰቱ የሚችሉ የጎንዮሽ ጉዳቶችን ማወቅዎን ያረጋግጡ።

የዕለት ተዕለት የማሽከርከር ክህሎቶች

ይህ ክፍል በፔንስልቬንያ ውስጥ ባሉ አዳዲስ አሽከርካሪዎች መካከል የአደጋ መንስኤዎችን እና ዋና የብልሽት ዓይነቶችን በማብራራት ይጀምራል። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ደህንነትዎ በተጠበቀ ሁኔታ የማሽከርከር ክህሎቶች በዚህ ክፍል ውስጥ ተገልጸዋል፦

- ርቀትን ጠብቆ ስለማሽከርከር
- መገናኛ መንገዶች ላይ በአግባቡ ማሽከርከር
- ፍጥነትን መቆጣጠር
- ኩርባዎች ላይ በአግባቡ ማሽከርከር
- መታጠፍ ፣ ሌላ የትራፊክ መስመር መቀላቀል እና ማለፍ
- አውራ ጎዳናዎች እና የድልድይ መንገዶች ላይ በአግባቡ ማሽከርከር

አብዛኞቹ የትራፊክ አደጋዎች የሚከሰቱት በሰው ስህተት ሳቢያ ነው። ወይ አሽከርካሪው ተሽከርካሪውን ወይም አውራ ጎዳናውን እንዴት መጠቀም እንዳለበት አልተረዳም፤ ወይም ለመንገድ ዳር ምልክቶች፣ ለትራፊክ መብራት ምልክቶች፣ ለመንገድ ላይ መስመሮች እና ቅቦች ወይም የሌሎች አሽከርካሪዎች ድርጊት በቂ ትኩረት አልሰጠም፤ ወይም ደግሞ ተገቢ ያልሆነ ውሳኔ ከመስጠት አደጋ ሊከሰት ይችላል። ከአምስት (5) አመት በታች የማሽከርከር ልምድ ያላቸው አሽከርካሪዎች ወደ የመንገድ አደጋዎች የሚያመሩ ስህተቶችን የመፍጠር እድላቸው ከፍተኛ ነው።

> **የታዳጊ ወጣቶች የትራፊክ አደጋ እውነታ**
> እ.ኤ.አ. በ2017፣ 16 ዓመት የሆናቸው የፔንስልቬንያ አሽከርካሪዎች መካከል 7.2% የሚሆኑት በፔንስልቬንያ ውስጥ ሪፖርት ሊደረጉ የሚችሉ አደጋዎች ውስጥ ነበሩ።

- በፔንስልቬኒያ ውስጥ ያሉ አዲስ አሽከርካሪዎች (16 እና 17 አመት የሆኑ) እ.ኤ.አ. በ2017 አደጋ ውስጥ እንዲገቡ ያደረጓቸው ከፍተኛ 10 ምክንያቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። ወጣት አሽከርካሪዎች እንዲሁም ሁሉም አሽከርካሪዎች እነዚህን ወሳኝ ሁኔታዎች ማወቅ አለባቸው፦
  - **በሁኔታዎች ምክንያት በፍጥነት መንዳት**
  - **ከቆሙ በኋላ መንገዱን ሳይፈትሹ ያለጥንቃቄ ማሽከርከር መጀመር**
  - **ትክክል ያልሆነ ወይም ጥንቃቄ የጎደለው መታጠፍ(መዞር)**
  - **ተገቢ ያልሆነ አነዳድ**
  - **በቂ የሆነ ልምድ አለመኖር**
  - **ያለ ምንም ርቀት እጅግ ተጠግቶ መንዳት**
  - **በፍጥነት መንዳት**
  - **ኩርባ መንገድ ላይ ከልክ በላይ ወይም በታች መታጠፍ**
  - **ትኩረትን የሚከፋፍሉ ነገሮች**
  - **ድንገተኛ የሆነ ፍጥነት መቀነስ ወይም ማቆም**
- በፔንስልቬኒያ ውስጥ አዳዲስ አሽከርካሪዎች (16 እና 17 ዓመት ልጆች) የሚያጋጥሟቸው ዋና ዋና የመንገድ አደጋ ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦ **1)** የቆመ ነገር መምታት፤ **2)** እንደ መግቢያዎች፣ መውጫዎች እና አደባባዮች ባሉ መንገዶች በሚገናኙባቸው ቦታዎች ላይ የሚከሰቱ አደጋዎች **3)** ከሌላ መኪና ጀርባ ጋር የሚደርሱ ግጭቶች፣ እና **4)** ሁለት ተሽከርካሪዎች ፊት ለፊት መጋጨት የመሳሰሉ ይገኛሉ። ከሁሉም አደጋዎች 92 በመቶ እና 93 በመቶው በአደጋ ምክንያት ከሚከሰቱ የሞት አደጋዎች መካከል ከእነዚህ አራት (4) የአደጋ አይነቶች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። የተሽከርካሪ አደጋዎችን ማስቀረት የሚቻለው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ደህንነቱ የተጠበቀ የመንዳት ችሎታዎች መማር እና መተግበርን ይጠይቃል።

ርቀትን ጠብቆ ስለማሽከርከር

- በአቅራቢያዎ ያለ ሌላ አሽከርካሪ ስህተት ከሰራ፣ ለሁኔታው ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ያስፈልግዎታል። ምላሽ ለመስጠት በቂ ጊዜ እንዳለዎት እርግጠኛ ለመሆን ብቸኛው መንገድ በእርስዎ እና በዙሪያዎ ባሉ ተሽከርካሪዎች መካከል በቂ የሆነ ርቀት መተው ነው።
- በቀኝ በኩል ባለው ሥዕል ላይ እንደሚታየው፣ በተሽከርካሪዎ ዙሪያ ማስተዳደር መቻል ያለብዎት **ስድስት (6) ቦታዎች** አሉ።
- በሁሉም የተሽከርካሪዎ ዙርያ በቂ ክፍተት መኖሩን ማርጋገጥ እጅግ የሚመከር ነው።





ከፊት በኩል በቂ ክፍት ርቀት እንዳለ ያረጋግጡ (የ4-ሰከንድ ህግ)

- በተሽከርካሪዎች መካከል ሊኖር የሚገባ ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀት ምን ያህል ነው? የ4 ሰከንድ ርቀት ጠብቆ የማሽከርከር ህግ፣ ከላይ በ**አካባቢ 1** ቦታን በአግባቡ የመጠቀም ዲያግራም ላይ እንደሚታየው፣ በደረቅ መንገድ ላይ የመንገድ አደጋ ለመከላከል መሪ እንዲቆጣጠሩ ወይም ፍሬን እንዲይዙ ያስችልዎታል።
- በጣም በቅርብ ርቀት ሆነው እየነዱ ከሆነ እና ከፊትዎ ያለው ተሽከርካሪ በድንገት ከቆሞ ወይም ፍጥነት ከቀነሰ፣ ግጭትን ማስወገድ አይችሉም።

- ደህንነቱ የተጠበቀ የመከተያ ርቀትን ጠብቆ መጓዝ በድንገት ተደናግጠው ፍሬን መያዝ ሳያስፈልግዎት ከፊት ለሚፈጠር ችግር በጊዜ ምላሽ መስጠት ያስችልዎታል፤ ይህ ካልሆነ ግን እየተከተልዎት ያለ ተሽከርካሪ ከመኪናዎ ጀርባ ጋር ሊጋጭ ይቻላል።
- በምን ያህል ርቀት መከተል እንዳለብዎት ለመወሰን ከፊትዎ ያለውን ተሽከርካሪ የኋላ ባምፐር (መከላከያ) ይመልከቱ። ባምፐሩ (መከላከያው) የመንገድ ምልክት ወይም እንደ የቴሌፎን ምሰሶ ያለ የመንገድ ዳር ነገር ሲያልፍ፣ እርስዎም እዚያው ቦታ ለመድረስ ምን ያህል ሰከንዶች እንደሚፈጅብዎት መቁጠር ይጀምሩ። የመንገድ ምልክቱን ወይም ነገሩን ከአራት (4) ሰከንድ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ካለፉ፣ በጣም በቅርብ ርቀት እየተከተሉ ነው ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ ከፊት ለፊትዎ ተጨማሪ የመከትያ ርቀት ያስፈልግዎታል።

በሚከተሉት ሁኔታዎች ከተለመደው የበለጠ ርቀት እንዲኖር ያድርጉ፦

- በእርጥብ እና በሚያንሸራትቱ መንገዶች ላይ ስትነዱ ጎማዎት የመቆንጠጥ (የመያዝ) አቅሙ ወይም የመቆጣጠር አቅሙ ስለሚቀንስ ለማቆም ተጨማሪ ጊዜ ያስፈልጋል።
- ከኋላዎት ያለው ሹፌር ማለፍ ሲፈልግ - የሚያልፈው ሹፌር ከእርስዎ ፊት ለመግባት በቂ ቦታ መኖር አለበት።
- ከኋላው ያለ ነገር የተከለለባቸው አሽከርካሪዎች ሲከተሉ - የጭነት መኪናዎች፣ አውቶቡሶች፣ ቫኖች ወይም ተነቀሳቃሽ ቤቶችን ወይም ተሳቢዎችን የሚጎትቱ መኪናዎች እርስዎ ከኋላቸው እንደሆኑ ሳያውቁ በድንገት ፍጥነት ሊቀንሱ ይችላሉ።
- ከፊት ያለውን እይታ የሚከለክል ትልቅ ተሽከርካሪ እየተከተሉ ከሆነ - በተሽከርካሪው ዙሪያ ለማየት ተጨማሪ ቦታ ያስፈልግዎታል።
- ከባድ ሸክም የጫነ ወይም ተሳቢ የሚጎትት አሽከርካሪን እየተከተሉ ከሆነ - ተጨማሪው ክብደቱን ለማቆም የበለጠ አስቸጋሪ ያደርገዋል።
- ብስክሌቶችን ጨምሮ በቀስታ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን ስትጠጉ።
- የትምህርት ቤት አውቶቡሶችን፣ ታክሲዎችን፣ የህዝብ እና የግል አውቶቡሶችን እና አደገኛ ንጥረ ነገሮችን የሚያጓጉዙ የጭነት መኪናዎችን እየተከተሉ ከሆነ - እነዚህ ተሽከርካሪዎች በባቡር መሻገሪያዎች ላይ እና ባልተጠበቁ ቦታዎች ላይ ሊቆሙ ይችላሉ።
- ቁልቁለት ላይ እየነዱ ከሆነ - ፍሬንዎ የተሽከርካሪዎን ፍጥነት ለመቀነስ በተለይም በከፍተኛ ፍጥነት እያሽከረከሩ ከነበረ በጣም ከባድ ነው።
- ዳገት ላይ ቆመው ከሆነ - ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ ሲጀምሩ ከፊት ያለው ተሽከርካሪ ወደ ተሽከርካሪዎ ተመልሶ ወደ ኋላ ሊመጣ ይችላል።

በጎን በኩል በቂ የሆነ ቦታ ይተው።

የቦታ አጠቃቀም ዲያግራም (ንድፍ) ውስጥ በ**ቦታ 2ን እና 3ን** አካባቢዎች ላይ እንደሚታየው በሁለቱም ጎን ላይ ያሉ ቦታዎች ሌላ ተሽከርካሪ በድንገት ወደ መስመርዎ ቢገባ እንኳን ምላሽ ለመስጠት ማምለጫ ቦታዎች ይሰጥዎታል። እነዚህ ቦታዎች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉ የአደጋ ጊዜ መውጫ መንገዶች ናቸው።



ማስታወስ ያለብዎት ዋና ዋና ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፦

- በባለብዙ መስመር መንገዶች ላይ በሚያሽከረክሩበት ወቅት ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ጎን ለጎን ሆነው ከመንዳት ይቆጠቡ። እይታዎን ይጋርዳሉ፤ እና የማምለጫ መንገዶችዎን ይዘጋሉ፤ እንዲሁም እርስዎም ለሌሎች አሽከርካሪዎች ለማየት በሚያዳግቱ ቦታቸው ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ።
- በተቻለ መጠን በጎን በኩል ካሉ ተሽከርካሪዎች እና ከተቃራኒ አቅጣጫ ከሚመጡት ተሽከርካሪዎች መካከል በቂ ርቀት መኖሩን ያረጋግጡ።
- ወደ ሀይዌይ (አውራ ጎዳናዎች) ለሚገቡ ተሽከርካሪዎች ምልክት በመስጠት እና ደህንነቱ የተጠበቀ ከሆነ ወደ ውስጥ መስመር በመሄድ ቦታ ይስጡ።
- በተሽከርካሪዎ እና በቆሙ ተሽከርካሪዎች መካከል በቂ ርቀት መኖሩን ያርጋግጡ። የሆነ ሰው የተሽከርካሪ በር ሊክፍትብዎት ወይም ከቆሙ ተሽከርካሪዎች መካከል ሊወጣ ይችላል፤ ወይም አንድ መኪና በድንገት ወደ መንገድዎ ሊገባብዎት ይችላል።
- እንደ ማምለጫ መንገድ የምትጠቀሙበት ቢያንስ ስምንት(8) ጫማ (ፊት) ከተሽከርካሪዎ በአንዱ በኩል ቦታ ከሌልዎት ከፊት ለፊትዎ ያለ ተሽከርካሪ የሚከተሉበት ርቀት መጨመር ሊያስፈልግዎት ይችላል።.

አብዛኛው ግዜ የሚያሽከረክሩት በመንገድ መስመር (ሌን) መሃል ላይ ነው። ነገር ግን አንዳንድ ግዜ፣ በመንገዱ በሁለቱም ጎኖች ላይ አደጋዎች ሊያጋጥምዎት ይችላሉ። በቀኝ በኩል ባለው ምስል ላይ እንደሚታየው በቀኝ በኩል የቆሙ ተሽከርካሪዎችና በግራ በኩል ደግሞ በተቃራኒ አቅጣጫ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ፣ ከሁሉ የተሻለው መፍትሄ የሚሆነው ፍጥነትዎን መቀነስ እና ተቃራኒ አቅጣጫ ከሚመጡት ተሽከርካሪዎች እና ከቆሙ መኪኖች መካከል መሀል ላይ በመሆን ማሽከርከር ነው።



ከኋላዎትም በቂ የሆነ ርቀት መኖሩን ያረጋግጡ

የቦታ አጠቃቅም ዲያግራም ውስጥ በ**6ኛው ቦታ** እንደሚታየው፣ እርስዎን የሚከተል አሽከርካሪ ከእርስዎ የበለጠ ቁጥጥር አለው፤ ነገር ግን ተመሳሳይ ፍጥነት ጠብቀው በመንዳት እና ከመታጠፍዎ በፊት ምልክት በመስጠት አሽከርካሪውን ይበለጥ መርዳት ይችላሉ። አንድ ሰው በጣም በቅርብ ርቀት ሲከተልዎት ካዩ የሚቻል ከሆነ ወደ ቀኝ የመንገድ መስመር (ሌን) ይቀይሩ። የቀኝ መስመር ከሌለ ከፊት ለፊትዎ ያለው የትራፊክ ፍሰት ክፍት እስኪሆን በመጠበቅና ፍጥነትዎን ለመቀነስ ፍሬንዎን በቀስታ በመጫን ከጀርባ በቅርብ ርቀት እየተከተልዎት ያለውን አሽከርካሪ እንዲያልፍ ማድረግ ይችላሉ። እንዲሁም፣ ፍጥነትዎን ለመቅነስ ወይም ለማቆም በሚዘጋጁበት ጊዜ ወደ ጎን የማምለጫ መንገድ ይፈልጉ።





በመጨረሻም፣ ከጀርባዎት በስተግራ እና በስተቀኝ በኩል ባሉት አካባቢዎች (በቦታ አስተዳደር ዲያግራም ውስጥ **4ኛው እና 5ኛው ቦታዎች**) ምን እየተፈጠረ እንዳለ ትኩረት ይስጡ። ሌሎች ተሽከርካሪዎች ለተሽከርካሪዎ ምን ያህል ቅርብ እንደሆኑ እና በምን ያህል ፍጥነት እይተጓዙ እንዳለ ማወቅ አለብዎት። እነዚህ ቦታዎች ለማየት የሚያዳግቱ ስለሆኑ ሁልጊዜ መስመሮችን ከመቀየርዎ በፊት ጭንቅላትዎን በማዞር መመልከት አለብዎት።

ተሽከርካሪዎ በግልጽ በሚታይበት ቦታ ላይ ያቁሙ።

ተሽከርካሪዎን ለሌላ አሽከርካሪ ለማየት በሚያድግት ቦታ ሆነው ከማሽከርከር ይቆጠቡ። ለማየት የሚያዳግት ቦታ ማለት አሽከርካሪው ጭንቅላቱን ሳያንቀሳቅስ ማየት የማይችልበት ማንኛውም ቦታ ማለት ነው። ይህንን ስህተት እንዳይፈጽሙ የሚረዱዎት አንዳንድ ጥሩ ህጎች የሚከተሉት ናቸው፦

- ለረጅም ጊዜ በሌላ ተሽከርካሪ በሁለቱም ጎኖች እና በትንሹ ከኋላው በኩል (ለሌላ አሽከርካሪ ለማየት በሚያዳግቱ ቦታዎች) ሆነው ከመንዳት ይቆጠቡ። ሁለቱም ቦታዎች ለሌሎች አሽከርካሪዎች ለማየት የሚያዳግቱ ቦታዎች ናቸው። ለአሽከርካሪው ከማይታዩ ቦታዎች ለመውጣት ወይ ፍጥነትዎን ይጨምሩ ወይም ወደ ኋላ ይቅሩ።
- ሌላ ተሽከርካሪ በሚያልፉበት ጊዜ፣ በተቻለ ፍጥነት እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለሌላኛው አሽከርካሪ ከማይታየው ቦታ ይለፉ። ለማየት በሚያዳግቱ ቦታዎች በቆዩ ቁጥር ሁለታችሁም ለአደጋ የተጋለጣችሁ ናችሁ።



ወደ ፊት መመልከት



- በምስሉ ላይ ያለው አሽከርካሪ በቅርቡ በሚያልቅ መስመር ላይ ነው። ይህ አሽከርካሪ የያዘውን የመንገድ መስመር (ሌን) ካልቀየረ፣ ድንገተኛ መስመር መቀየር ሊኖርበት ይችላል፤ አለበለዚያ ትራፊኩ እስኪቀንስ መጠበቅ ሊኖርበት ይችላል።
- የመጨረሻ ደቂቃ ላይ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ለማስቀረት ነገሮችን አስቀድመው ለመመልከትና ምላሽ ለመስጠት በቂ ርቀት ያክል መመልከት አለብዎት። የችግር ሁኔታዎችን ከ12 እስከ 15 ሰከንድ (በከተማ ውስጥ አንድ ብሎክ ወይም በሀይዌይ ፍጥነት ሩብ ማይል ያህል) አስቀድመው መለየት መቻል አለብዎት።

አደገኛ የትራፊክ ሁኔታዎችን የመቆጣጠር ችሎታዎ በአብዛኛው የሚውሰነው ችግሮችን ከርቀት በማየት እና በመለየት ችሎታዎ ላይ ነው። ወደ ፊት መመልከት ማለት የመንገዱን መሀል ብቻ ማየት አለብዎት ማለት አይደለም። የመንገዱን ጎኖቹን ጨምሮ መላውን መንገድ ያለማቋረጥ መቃኘት አለቦት።

በሚነዱበት ወቅት አካባቢውን ሲቃኙ፣ ለሚከተሉት ነገሮች ትኩረት ይስጡ:-

- ከፊትዎ ወደ መንገድዎ ሊገቡ የሚችሉ ዛግ ባለ ፍጥነት የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን እና ሰዎችን።
- ለመታጠፍ መንገዱ ክፍት እስኪሆን ድርስ ለመጠበቅ ብሎ ፍጥነቱን እየቀነሰ ያለ ወይም የቆመ ተሽከርካሪን።
- ከፊት ስላለው አደጋ ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ ምልክቶችን።
- ከፊት ስለሚጠብቅዎት ቦታዎች የሚነግሩዎት እና/ወይም እንዴት መድረስ እንደሚችሉ መረጃ የሚሰጡዎት ምልክቶችን።

ወደ ጎን መመልከት

አንድ የትራፊክ ፍሰት መንገድ ከሌላው ጋር በሚገናኝበት በማንኛውም ቦታ ወደ ጎኖቹ መመልከት በተለይም በመገናኛዎች፣ መግቢያዎች፣ የገበያ ማዕከሎች መግቢያዎች እና መውጫዎች እና አውራ ጎዳና መግቢያዎች እና መውጫዎች ላይ በጣም አስፈላጊ ነው።

ወደ መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶችን ሲደርሱ "ግራ-ቀኝ-ግራ" ህግን ይከተሉ:-

- ከግራ የሚመጡ ተሽከርካሪዎች ወደ እርስዎ ስለሚቀርቡ መጀመሪያ ወደ ግራ ይመልከቱ።
- ከዚያ ወደ ቀኝ ይመልከቱ።
- ከመንቀሳቀስዎ በፊት እንደገና ወደ ግራ ይመልከቱ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመለከቱ ያላዩትን ተሽከርካሪ ሊያዩ ይችላሉ።

ወደ መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶች ሲገቡ ወደ ግራ እና ቀኝ እንደገና ይመልከቱ። **የማቆሚያ ምልክት ወይም ሲግናል ቢኖርም እንኳ ሌሎች ተሽከርካሪዎች ሁልጊዜ ያቆማሉ ብለው እንዳያስቡ።** የመስቀለኛ መንገድ እይታዎ በህንፃዎች፣ ቁጥቋጦዎች ወይም በቆሙ ተሽከርካሪዎች ከተከለለ በግልፅ ማየት እስኪችሉ ድረስ በዝግታ ወደፊት ይንዱ።

ወደ ኋላ መመልከት

እንዲሁም በተቻለ መጠን በተደጋጋሚ ከኋላዎ ያለውን ትራፊክ መቃኘት አለብዎት። መስመሮችን ለመቀየር ወይም ወደ ወደ ኋላ ለመመለስ ሲያስቡ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው።

የመንገድ መስመሮችን (ሌን) መቀየር የሚከተሉትን ያካትታል:-

- በመንገድ ላይ ከአንድ መስመር ወደ ሌላ መስመር መቀየር።
- ከመግቢያ መስመር ወደ አውራ ጎዳና መግባት።
- ወደ መንገድ ከኩርባው ወይም ከዳርቻው መግባት።

የመንገድ መስመሮችን ከመቀየርዎ በፊት ትክክለኛውን የማዞሪያ ምልክት ያሳዩ። የኋላ መመከቻ እና የጎን መስታዎቶችን ይመልከቱ እና ማንም እንደማያልፍዎት ያረጋግጡ። በመስታወቶች ወይም የተሽከርካሪዎ ሰንሰሮች ላይ ብቻ አይወሰኑ፤ ለተሽከርካሪዎ የማይታዩ ቦታዎች ላይ ማንም አለመኖሩን ለማረጋገጥ ግራ እና ቀኝ ትከሻዎን ይመልከቱ። እነዚህን ቦታዎች በፍጥነት ይቃኙ። ዓይኖችዎን ከአንድ ሰከንድ በላይ ከፊትዎ ካለው መንገድ ላይ አያንሱ። ሶስት (3) ወይም ከዚያ በላይ መስመሮች ባለባቸው መንገዶች፣ የመስመር (የሌይን) ለውጥ ከማድረግዎ በፊት ሁሉንም መስመሮች ይመልከቱ፤ በሌላ መስመር (ሌይን) ላይ ያለ ሌላ ሰው እርስዎ መሄድ ወደሚፈልጉበት ቦታ ለመሄድ እያሰበ ሊሆን ይችላል።

ወደ ኋላ ስለመንዳት:-

ሁልጊዜ ወደ ኋላ በሚያሽከረክሩበት ወቅት ከተሽከርካሪዎ ጀርባ ይመልከቱ፤ ይህንንም ወደ ተሽከርካሪዎ ከመግባትዎ በፊት ያድርጉ። ህጻናትን ወይም ትናንሽ ነገሮችን ከአሽከርካሪው ወንበር ሆነው ለማየት በጣም አስቸጋሪ ናቸው። ወደ ኋላ መንዳት ከመጀመርዎ በፊት ከኋላ መስኮቱ በኩል ማየት እንዲችሉ ጭንቅላትዎን ያዙሩ። በመስታወቶች ወይም የተሽከርካሪዎ ሰንሰሮች ላይ ብቻ አይወሰኑ።

ፍጥነትን መቆጣጠር

ደህንነቱ የተጠበቀ ፍጥነት ማለት ምን ማለት ነው? ከመጠን በላይ የሚባለው ፍጥነት ምን ያህል ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች ምንም ቀላል መልሶች የሉም፤ ምክንያቱም ለሁሉም ግዜ የሚሆን አስተማማኝ የሆነ አንድ አይነት ፍጥነት የለም። ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ በተጨማሪ፣ ለመንዳት አስተማማኝ ፍጥነትን ለመምረጥ የመንገድ ሁኔታዎችን፣ የእይታ ሁኔታዎችን እና የሌሎችን የትራፊክ ፍሰት ግምት ውስጥ ማስገባት አለብዎት። እንዲሁም፣ ፍጥነት ለመቀየር ሲያስቡ አላማዎን ለሌሎች አሽከርካሪዎች በማንኛውም መንገድ ማሳወቅ ደህንነትዎን እንዲጠብቁ ይረዳዎታል።

የተለጠፉ የፍጥነት ገደቦች

የተለጠፉ የፍጥነት ገደቦች በተሻለ የመንገድ፣ የትራፊክ እና የአየር ሁኔታ ሁኔታዎች ውስጥ ከፍተኛው አስተማማኝ የማሽከርከር ፍጥነት ምን እንደሆነ ይጠቁማሉ።

- በፔንስልቬንያ ያለው ከፍተኛው የፍጥነት ገደብ 70 ነው።
- በኢንተርስቴት አውራ ጎዳናዎች ላይ ያለው ከፍተኛ የፍጥነት ገደብ ከእያንዳንዱ የመንገዶች መገናኛ በኋላ ይለጠፋሉ።
- በሌሎች አውራ ጎዳናዎች ላይ ያለ ከፍተኛው የፍጥነት ገደቦች በግምት በግማሽ ማይል ክፍተቶች ይለጠፋሉ።

የታዳጊ ወጣቶች የትራፊክ አደጋ እውነታ

"በሁኔታዎች በጣም በፍጥነት መንዳት" የ16 እና የ17 ዓመት ታዳጊ አሽከርካሪዎች ለአደጋ የሚጋለጡበት ቁጥር 1 ምክንያት ነው።

- በትምህርት ቤት አካባቢ ያሉ የትራፊክ መብራት ምልክቶች በሚበሩበት ወይም በተጠቀሱ የግዜ ወቅቶች በትምህርት ቤት ቀጠናዎች የሚፈቀደው የፍጥነት ገደብ በሰዓት 15 ማይል ነው። በትምህርት ቤቶች አከባቢ ያሉ የፍጥነት ገደቦች ከሌሎች የፍጥነት ገደቦች ያነሱ ናቸው።

መንገዱ እርጥብ ወይም የሚያንሸራትት ከሆነ፣ በደንብ ማየት በማይችሉበት ወቅት ወይም አጠቃላይ ሁኔታዎች ጥሩ ካልሆኑ ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ በታች ይንዱ። በተለጠፈው የፍጥነት ገደብ ውስጥ እየነዱ ቢሆንም ከሁኔታዎች ጋር በማይስማም መልኩ በፍጥነት ካሽከረከሩ ሊቀጡ ይችላሉ።

ኢኮ-ድራይቪንግ
ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማሽከርከር እርስዎን ከመጠበቅ ባለፈ፣ ገንዘብ ይቆጥብልዎታል፤ እንዲሁም የአየር ብክለትን ይቀንሳል። መኪናን ማሽከርከር ነዳጅን፣ ጥገናን እና ጎማዎችን ጨምሮ ብዙ ወጪዎችን ያካትታል። አሽከርካሪዎች እና የመኪና ባለቤቶች እነዚህን ወጪዎች ያለምንም ተጨማሪ ወጪ ለመቀነስ በርካታ እርምጃዎችን መውሰድ ይችላሉ።

ማድረግ ያለብዎት ብልህ የማሽከርከር ልማዶች

1. ፍጥነትዎን መቀነስ። በሰዓት ከ60 ማይል በላይ ሲነዱ በሰዓት አምስት ማይል በላይ ፍጥነት በጨመሩ ቁጥር የነዳጅ ፍጆታዎ በ 5% ገደማ ይጨምራል።
2. ፔዳሎቹን እምብዛም አይጫኗቸው። ቶሎ ቶሎ መነሳት እና የፍሬን ፔዳሉን በሃይል ጫን ማለት የነዳጅ ፍጆታን እስከ 40% ከፍ ሊያደርግ ይችላል፤ ነገር ግን የጉዞ ጊዜን የሚቀንሰው በ4% ብቻ ነው።
3. ረጋ ብለው ያሽከርክሩ። ቀኑ በጣም ሞቃታማ በሚሆኑበት ግዜያት ከመንዳት ይቆጠቡ። ይበልጥ ቀዝቃዛና ጥቅጥቅ ያለ አየር ጉልበት እና ማይሌጅን ይጨምራል።
4. በቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ ውስጥ ይሁኑ። በሰአት ከ40 ማይል በላይ በሚነዱበት ጊዜ የመኪናዎን አየር ማቀዝቀዣ ይጠቀሙ።
5. ተሽከርካሪዎን ያሙቁ። በጣም ቀዝቃዛ በሆኑ ቀናት እንኳን፣ ተሽከርካሪዎን ለመንዳት ዝግጁ ለማድረግ የሚፈጀው 30 ሰከንዶች ብቻ ነው።
6. ጉዞዎን ይቀጥሉ። ቀጥ ባሉ አውራ ጎዳናዎች ላይ በሚያሽከረክሩበት ወቅት የክሩዝ መቆጣጠሪያን በመጠቀም በአማካይ 7% ነዳጅ መቆጠብ ይችላሉ።
7. መብራቱን ይከታተሉ።. የተሽከርካሪዎ ኦን-ቦርድ ዲያግኖስቲክስ (OBD) መብራት ሲበራ ነዳጅዎ እየባከነ እና ልቀት እየጨመረ ሊሆን ይችላል። የተሽከርካሪዎ ኦን-ቦርድ ዲያግኖስቲክስ (OBD) መብራት ከበራ ለበለጠ መረጃ መኪና ከሸጠልዎት አከፋፋይ ጋር ይነጋገሩ።
8. በጥንቃቄ ያሽከርክሩ። በእርስዎ እና በሌሎች ተሽከርካሪዎች መካከል በቂ ርቀት ይጠብቁ። ይህን ማድረጉ የእርስዎን ደህንነት ከመጠበቅ በተጨማሪ ተሽከርካሪዎ እንዳይበላሽ እና እንዳያረጅ ይረዳል።
9. መኪናዎን ይጠቀሙ። ተሽከርካሪዎ "ECO" የሚል አማራጭ ካለው፣ ይጠቀሙበት። ይህም የነዳጅ ፔዳል በሚረግጡበት ወቅት ለስላሳ ያደርገዋል፤ ማርሽ በሚቀይሩበት ወቅት ቀላል እንዲሆን ያደርጋል፤ እንዲሁም የአየር ማቀዝቀዣው በኤንጅኑ (ሞተሩ) ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ይቀንሳል።
10. ያጥፉት። መኪናን አቁሞ ሞተርን ሳይዘጉ መተው ነዳጅን ያባክናል፤ እንዲሁም በህግ የተከለከለም ሊሆን ይችላል። መቆም ካለብዎት ኢንጅኑ ፍሬንዎ ላይ ጫና እንዳያሳድር እና ተጨማሪ ነዳጅ እንዳይጠቀም፣ መኪናዎትን ኒውትራል ላይ ወይም ፓርክ ላይ ያድርጉ።
11. በተቻለ መጠን መንዳትዎን ይቀንሱ። ተሽከርካሪዎን ማሽከርከር በመቀነስ ወጪን ለመቀነስ እና ገንዘብን ለመቆጠብ የሚያግዙ የተለያዩ አማራጮች አሉ። ከነዚህም መካክል የሕዝብ ማመላለሻን መጠቀም፤ ብስክሌት መንዳት፤ ወይም በእግር መሄድ፤ አለዚያም መኪናን ከሌሎች ጋር መጋራት ናቸው። በተጨማሪም የተለያዩ ስራዎችን በአንድ ላይ በማጣመር መስራት ጊዜንና ነዳጅን ይቆጥባል።
12. እራስዎን ያስተምሩ። ስለምርጥ አስተማማኝ የማሽከርከር ልምዶች ለማግኘት እና ለመማር ብዙ የመረጃ ምንጮች አሉ።

በምሽት ስለማሽከርከር
ከፍተኛው የመንገድ አደጋ መጠን የሚከሰተው በምሽት ሰዓታት ነው። በጣም ከባድ የሆኑ የመንገድ አደጋዎች የሚከሰቱት በድቅድቅ ጨለማ ወይም በጨለማ ጊዜያት ነው። በአጠቃላይ በምሽት ሰዓታት የሚከሰቱ የትራፊክ አደጋ ሞቶች መጠን በቀን ብርሀን ከሚከሰቱት የትራፊክ አደጋዎች ከሦስት (3) እስከ አራት (4) እጥፍ ይበልጣሉ። በቀን ከመንዳት ጋር ሲነጻጸር፣ በምሽት ማሽከርከር የበለጠ አደገኛ ነው።

ለዚህም በርካታ ምክንያቶች አሉ፦

- እይታዎ በምሽት ሰዓታት እጅግ የተገደበ ነው።
- ከሌሎች ተሽከርካሪዎች የሚመጡ የግንባር መብራቶች (headlights) የሚያንጸባርቅ ብርሃን ለጊዜው እይታዎን ሊጋርድ ይችላል።
- በድካም ስሜት ውስጥ ያሉ ወይም በአልኮል/አደንዛዥ ዕጽ ተጽዕኖ ስር ሆነው መኪና የሚያሽከረክሩ ሰዎች መንገድ ላይ በምሽት በብዛት የመገኘት ዕድላቸው ሰፊ ነው።

ብርሃን አነስተኛ በሆነባቸው ሁኔታዎች ርቀቶችን የመገመት ችሎታዎ ይቀንሳል፤ ቀለሞችን የማየት ችሎታዎ ይቀንሳል፤ እንዲሁም በጎን በኩል ያሉትን ነገሮች የማየት ችሎታዎ ይቀንሳል። እንደ ሹፌር ከፊትዎ ባለው መንገድ ላይ ያልተጠበቀ ነገር ቢከሰት በፍጥነት ምላሽ ለመስጠት ሁል ጊዜ ዝግጁ መሆን አለብዎት፤ — ለምሳሌ እንደ እግረኛ፣ ብስክሌተኛ፣ እንስሳት የመሳሰሉ። — እናም ማታ ላይ ድንገተኛ ነገሮች የማጋጠም እድላቸው ሰፊ ነው። ከምልክቶች እና ከሌሎች የመንገድ ዳር ነገሮች ጋር ሲነፃፀሩ፣ እግረኞች በሌሊት ለማየት በጣም አስቸጋሪ ናቸው።

በሕግ በተደነገገው መሰረት የግንባር መብራቶችዎን (headlights) በምሽት እና በሌሎች ጊዜያት በአግባቡ መጠቀም አለብዎት። የግንባር መብራቶች (headlights) ሁለት ጥቅም አላቸው፤ እነዚህም እርስዎ እንዲያዩ መርዳት እና ሌሎችን እርስዎ እንዲያዩ መርዳት ናቸው። የግንባር

መብራቶችዎን (headlights) ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ ያጽዱ። የቆሸሹ የግንባር መብራቶች (headlights) ከሚገባው ያነሰ ብርሃን ብቻ ሊሰጡ ስለሚችሉ — ለተሽከርካሪዎ ነዳጅ በሚሞሉበት ግዜ መብራቶችዎን ያጽዱ።

የስቴቱ ህግ አሽከርካሪዎች የግንባር መብራቶችዎ (headlights) እንዲያበሩ የሚያስገድድባቸው ጊዜያት፦

- በግራጫ ቀናት በቂ ብርሃን ስለሌለ ወይም ተሽከርካሪያቸው ከአካባቢው ጋር የሚዋሃድ በሚመስልበት በተጨናነቀ ትራፊክ የተነሳ ማየት በማይችሉበት ጊዜ።
- እንደ ዝናብ፣ በረዶ፣ የበረዶ ዝናብ፣ ጭጋግ፣ ጭስ ወይም ከባድ የአየር ብክለት ያሉ አስቸጋሪ የከባቢ አየር ሁኔታዎች በሚኖርበት ወቅት። በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ውስጥ አነስተኛ ብርሃን ያላቸውን የግንባር መብራቶች (ሎው-ቢም) ብቻ ይጠቀሙ። ከፍተኛ ጨረሮች ያላችው መብራቶች (ሃይ ቢሞች) በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ በግልጽ እንዳይታይ እንቅፋት ይሆናሉ።
- አሽከርካሪዎች በሚያሽከረክሩበት መንገድ ፊት 1,000 ጫማ (ፊት) ርቀት ላይ ያሉ እግረኞችን ወይም ተሽከርካሪዎችን አውራ ጎዳና ላይ ማየት በማይችሉበት ጊዜ።
- ፀሐይ ከጠለቀችበት ጊዜ አንስቶ እስከ ፀሐይ እስከምትወጣበት ግዜ ድረስ።
- በሥራ ቀጠናዎች በሚያሽከረክሩበት ግዜ።
- የተሽከርካሪዎ የፊት መስታወት መጥረጊያ (ዊንድሺልድ ዋይፐር) በአየር ሁኔታ ምክንያት ያለማቋረጥ ወይም አልፎ አልፎ ጥቅም ላይ በሚውልበት በማንኛውም ጊዜ።

ማሳሰቢያ፡ በቀን የሚሰሩ መብራቶች ብቻ በቂ አይደሉም። የኋላ መብራቶችዎ እንዲሁ መብራት አለባቸው።

በስቴቱ ህግ መሰረት አስገዳጅ በሆኑ ሁኔታዎች የግንባር መብራታቸውን መጠቀም እያለባቸው ላልተጠቀሙ አሽከርካሪዎች የሚጣል ቅጣት ከ 25 ዶላር የሚጀምር ሲሆን ከሌሎች ተያያዥ ወጪዎች ጋር ቅጣቱ እስከ 100 ዶላር ሊደርስ ይችላል!

ስለ የግንባር መብራቶች እና በምሽት ስለማሽከርከር ሌሎች ጠቃሚ የደህንነት መረጃዎች፣ ከዚህ ስር ተዘርዝረዋል፦

- በምሽት በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ከፍተኛ ብርሃን ያለው የፊት መብራት (ሃይ ቢም) ሌላውን ሹፌር "ሊያሳውር" ስለሚችል ሌላ ተሽከርካሪ ወደ እርስዎ ሲመጣ ካዩ ወዲያውኑ የግንባር መብራትዎን (headlights) ወደ ዝቅተኛ ብርሃን (low-beams) ይቀይሩ። የፔንስልቬንያ ህግ ከሚመጣው መኪና በ500 ጫማ (ፊት) ርቀት ላይ በሚሆኑበት ጊዜ እና በ300 ጫማ (ፊት) ርቀት ውስጥ ተሽከርካሪን በሚከተሉበት ግዜ ዝቅተኛ ጨረሮችን (ሎው-ቢም) እንድትጠቀሙ ያስገድድዎታል።
- ከፍተኛ ጨረሮችን የሚጠቀም ተሽከርካሪ ወደ እርስዎ እየመጣ ከሆነ፣ ከፍተኛ ጨረር የግንባር መብራትዎን (ሃይ-ቢሞች) ለጥቂት ጊዜ በፍጥነት አብርተው ያጥፉ። አሽከርካሪው መብራቱን ካላደበዘዘ ወደ የመንገዱ ቀኝ በኩል ይመልከቱ። ይህም በሌላኛው ተሽከርካሪ የግንባር መብራቶች "ከመታወር" ይጠብቅዎታል፤ እንዲሁም ተሽከርካሪው እስኪያልፍ ድረስ በመንገድዎ ላይ እንዲቆዩ በደንብ እንዲያዩ ያስችልዎታል።
- ደማቅ መብራቶችዎን (ሀይ-ቢም) አብርተው በመቆየት ሌላውን አሽከርካሪ ለመቅጣት እንዳይሞክሩ። እንደዛ ካደረጋችሁ ሁለታችሁም “ሊታወሩ (ምንም ላይታያችሁ)” ትችላላችሁ።
- ከኋላ ከሚከተልዎት ተሽከርካሪ የግንባር መብራቶች የሚመጣው የብርሃን ነጸብራቅ የኋላ መመልከቻ መስታወትዎ ላይ እያንጸባረቀ ካስቸገርዎት የውስጥኛውን የኋላ መመልከቻ መስታወት ከቀን ወደ ማታ ቅንብር (ሴትንግ) መቀየር ይችላሉ።
- የግንባር መብራቶችዎ በሚያበሩት የመንገድ ርዝመት ውስጥ የሚታየውን አደጋ ለማስወገድ በጊዜ ማቆም በማይችሉበት ፍጥነት ከመንዳት ይቆጠቡ። ዝቅተኛ ጨረር የግንባር መብራቶች (ሎው-ቢም) የሚያበሩት እስከ 250 ጫማ (ፊት) ርቀት ብቻ ነው። በደረቅ አስፋልት ላይ እንኳን በ55 ማይል በሰአት እየነዱ ከሆነ ለማቆም ከ250 ጫማ (feet) በላይ ያስፈልግዎታል። በምሽት በጨለማ መንገድ ላይ የግንባር መብራቶች ከሚሸፍኑት ርቀት መጠን በላይ ማሽከርከርን ለማስወገድ በሰአት ከ45 ማይል ፍጥነት በላይ ማሽከርከር የለብዎትም።

የመንገድ ሁኔታዎች

የማቆም ችሎታዎ በመንገዱ ሁኔታ ላይ በእጅጉ ይወሰናል። የመንገድ ሁኔታዎች መጥፎ በሚሆኑበት ወቅት ተሽከርካሪዎን መቆጣጠር እንዲችሉ ፍጥነትዎን መቀነስ አለብዎት። በሚያንሸራትቱ መንገዶች ላይ፣ በተለይም በማዞሪያዎች ላይ በጣም በፍጥነት እየነዱ ከሆነ ለከፍተኛ አደጋ ይጋለጣሉ። **መንገዱ አንሸራታች በሚሆንበት ግዜ በመታጥፊያዎች እና በኩርቢያዎች ላይ ፍጥነትዎን በእጅጉ ቀንሰው ይንዱ።**

- **እርጥበታማ መንገዶች**
  ሁሉም መንገዶች እርጥብ ሲሆኑ ያንሸራትታሉ፤ ሆኖም ግን **እርጥብ በሚሆኑበት ጊዜ የሚያንሸራትቱ (SLIPPERY WHEN WET**) የሚሉ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች በተለጠፉባቸው መንገዶች ላይ ይበልጥ ጥንቃቄ ያድርጉ። አስፋልቶች ዝናብ በጀመረ በመጀመሪያዎቹ 10 እና 15 ደቂቃዎች ውስጥ በጣም አንሸራታች ሊሆኑ ይችላሉ። ዝናቡ በአስፓልት ውስጥ ያለው ዘይት ወደ ላይ እንዲወጣ ያደርገዋል። ይህ ችግር በሞቃታማ የአየር ጠባይ ወቅት የበለጠ አስቸጋሪ እየሆነ ይሄዳል፤ ይህም የሚሆነው ሙቀቱ ከውሃው ጋር ተዳምሮ ብዙ ዘይት ወደ መንገዱ ላይ እንዲወጣ ያደርገዋል። በቀዝቃዛ እና በእርጥበት አዘል የአየር ሁኔታዎች በዛፎች ወይም ህንጻዎች በተሸፈኑ መንገዶች ላይ ሲነዱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያድርጉ፤ ምክንያቱም እነዚህ ቦታዎች በቶሎ በረዷማ የሚሆኑና ቶሎ የማይደርቁ ቦታዎች ናቸው።
- **ሃይድሮፕላኒንግ (መንሸራትት)**
  ከመጠን በላይ በሆነ ፍጥነት በሚነዱብት ወቅት ተሽከርካሪዎ እርጥብ በሆነ መንገድ ላይ ሊንሸራተት ይችላል። ሀይድሮፕላኒንግ (መንሸራትት) የሚከሰተው ጎማዎችዎ በመንገዱ ላይ ያላቸውን ቆንጥጦ የመያዝ አቅማቸው ሲያጡ እና በውሃ ሽፋን ላይ እንደ ስኪ ሲንሳፈፉ ነው። በእርጥብ

መንገድ ላይ በፍጥነት በሄዱ ቁጥር ጎማዎችዎ ውሃውን ከመንገድ ላይ እየጠረጉ የመሄድ አቅማቸው እየቀነሰ ይሄዳል። የውሃው ጥልቀት 1/10 ኢንች ብቻ ሆኖም እንኳን በሰዓት እስከ 35 ማይል በሚደርስ ፍጥነት በሚያሽከረክሩበት ወቅትም እንኳን መንሸራተት (ሃይድሮፕሌኒንግ) ሊያጋጥምዎት ይችላል። ያረጁ (ስስ የሆኑ) ጎማዎች ይህንን ችግር ያባብሱታል። በዝግታ በማሽከርከር የውሃ ላይ መንሸራተትን (ሃይድሮፕሌኒንግ) መቀነስ ይቻላል።

መንሸራተት (ሃይድሮፕላኒንግ) እያጋጠመዎት ከሆነ የሚከተሉትን ያድርጉ፦

1. ሁለቱንም እጆችዎን በመሪው ላይ ያድርጉ።
2. ተሽከርካሪዎ ፍጥነት እንዲቀንስ ለማድረግ እግርዎን በቀስታ ከፍጥነት መቆጣጠሪያ ፔዳሉ ላይ ያንሱ። ፍሬኑን በሀይል አይጫኑ ወይም በድንገት ለመዞር አይሞክሩ፤ ምክንያቱም ይህ ተሽከርካሪዎን እንዲንሸራተት ያደርገዋል። ተሽከርካሪዎ ፍጥነት በቀነሰ ቁጥር ከመንገዱ ጋር የሚገናኘው የጎማዎ ትሬድ እየጨመረ ይሄዳል፤ ይህም ጎማዎ የሚኖረው የመቆንጠጥ አቅም የተሻለ ያደርገዋል።
3. ተሽከርካሪዎን ከመንገድ እንዳይወጣ በጣም በቀስታ እና ባስፈላጊው መጠን ብቻ መሪውን ያዙሩ።
4. ፍሬንዎን መጠቀም ካለብዎት በቀስታ ይጫኑ። (መደበኛ ፍሬንን (ብሬክን) ከአንቲ-ሎክ ብሬክ ሲስትም ጋር ስለመጠቀም ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በኋላ የሚገኘውን “በድንገት ፍሬን መጫን ካለብዎት” የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።)

- **በረዶ እና የበረዶ ብናኝ**

በበረዶ ወይም በበረዶ ብናኝ ላይ በሚያሽከረክሩበት ወቅት፣ ማንኛውንም ሁኔታ ለማስተናገድ ዝግጁ መሆን አለብዎት። የጎማዎችዎ የመቆንጠጥ አቅም (ግሪፕ) በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፤ ይህም የማሽከርከር እና ፍሬን የመያዝ አቅምዎትን በእጅጉ ይጎዳል። በተጨማሪም የሙቀት ልኬቱ 32 ዲግሪ ፋራናይት ሆኖ አርጥበታማ የአየር ሁኔታ ወደ ዝናብ ወይም ቀጭን የበረዶ ግግር በሚቀየርበት ወቅት እጅግ አደገኛ ነው — ይህም በበረዶ ላይ ያለ ቀጭን የውሃ ሽፋን በረዶ ለብቻው በላይ የበለጠ የሚያንሸራትት ስለሆነ ነው።
የሙቀት መጠን በሚቀንስበት ጊዜ ንጹህ በሆኑ መንገዶች ላይ የሚፈጠር ቀጭን የበረዶ ሽፋኖች ሁኔታ የሆነውን "ጥቁር በረዶ" ይጠንቀቁ። መንገዱ እርጥብ በሚመስልበት ጊዜ ነገር ግን ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ጎማዎች ላይ ምንም አይነት የሚረጭ ነገር ከሌለ "ጥቁር በረዶ" ሊኖር ይችላል ማለት ነው።

እ.ኤ.አ. ከጁላይ 10 ቀን 2006 ጀምሮ ስራ ላይ በዋለው ህግ መሰረት አሽከርካሪዎች ከተሽከርካሪቸው ላይ የወደቀ በረዶ ወይም የበረዶ ብናኝ በሌሎች አሽከርካሪዎች ወይም እግረኞች ላይ ጉዳት ወይም ሞት ካደረሰ ከባድ ቅጣት ይጠብቃቸዋል። በረዶ ወይም የበረዶ ብናኝ ከሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ ሲወድቅ ወይም ወድቆ ሌላ ተሽከርካሪ ወይም እግረኛን በመምታት ሞት ወይም እጅግ ከባድ የሆነ የአካል ጉዳት ካደረሰ በረዶው የወደቀበት የተሽከርካሪው ሹፌር ለእያንዳንዱ ጥፋት ከ200 እስከ 1,000 ዶላር የሚደርስ ቅጣት ይጣልበታል። ፔንዶት (PennDOT) አሽከርካሪዎች መንዳት ከመጀመራቸው በፊት ሁሉንም በረዶ ከተሽከርካሪዎቻቸው እንዲያስወግዱ ያሳስባል።

መንገዶች በሚያንሸራትቱ ሁኔታዎች በሚሆኑበት ግዜ፣ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይመከራል:-

- በእርጥብ መንገዶች ላይ ፍጥነትዎን ከ5 እስከ 10 ማይል በሰአት ያህል ይቀንሱ፤ እንዲሁም ተከትለው የሚሄዱበትን ርቀት ወደ አምስት (5) ወይም ስድስት (6) ሰከንዶችን ያሳድጉ።
- በተለይም በበረዶ የተሸፈኑ መንገዶች ላይ ይበልጥ ፍጥነትዎን መቀነስ አለብዎት። የበረዶ ብናኝ በበዛበት መንገድ ፍጥነትዎን በግማሽ ያህል ይቀንሱ፤ በበረዶ ላይ ሲነዱ ደግሞ በጣም ቀስ ብለው ይሂዱ። በእርስዎ እና ከፊት ባለው ተሽከርካሪ መካከል ያለ ርቀት ከመደበኛው 10 እጥፍ የሚበልጥ ቦታ ይተው።
- ፍሬኑን በቀስታ ይጫኑ፤ እና መንሸራተት ከጀመሩ ብሬክን ይልቀቁና ተሽከርካሪዎን መቆጣጠር ሲችሉ እንደገና ይጫኑት። (መደበኛ ፍሬንን (ብሬክን) ከአንቲ-ሎክ ብሬክ ሲስትም ጋር ስለመጠቀም ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በኋላ የሚገኘውን “በድንገት ፍሬን መጫን ካለብዎት” የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።)
- በሚያንሸራትቱ መንገዶች ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ክሩዝ ኮንትሮልን አይጠቀሙ። በረዶ፣ የበረዶ ብናኝ፣ እየቀለጠ ያለ በረዶ እና ዝናብ የጎማ መሽከርከር (ዊል-ስፒን) እና የቁጥጥር መጥፋት ሊያስከትሉ ይችላሉ። የጎማዎችን መሽከርከር (ዊል ስፒን) ለማስቆም እና መቆጣጠርን ብቸኛው መንገድ ፍጥነትን መቀነስ ነው። ነገር ግን፣ ክሩዝ ኮንትሮል ከበራ የሃይል አቅርቦት እንዲቀጥል ያደርጋል፤ ይህም ጎማዎችዎ መሽከርከርዎን እንዲቀጥሉ ያደርጋል።
- በክረምት ወቅት እንደ ጥላ በበዛባቸው ቦታዎች እና ደረቅ በርዶ በሚኖርባቸው ድልድዮች ያሉ በሚያንሸራትቱ ቦታዎች ላይ ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ጋር ላለመጋጨት ፍጥነትዎን ያስተካክሉ። ይህም ወደ ሌላ ተሽከርካሪ ተንሸራተው የመጋጨት አደጋን ይቀንሳል።
- በበረዶ ወይም በበረዶ ብናኝ በተሸፈኑ መንገዶች ላይ ተሽከርካሪዎ መብራቱ አረንጓዴ እስኪሆንና ከፊትዎ ያሉት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀስ እስኪጀምሩ ድረስ ሃይል ሳይሰጡ መኪናዎ መስቀለኛ መንገዱ ላይ እንዲደርስ ለማድረግ ግዜ አጠባበቅዎ በማስተካከል ይንዱ። እንደዚያ ካደረጉ፣ ለማቆም እና እንደገና መንዳት ለመጀመር መፍጠን አያስፈልግዎትም። እንዲሁም ወደ ላይ እየወጡ ከሆነ ከፊትዎ ካለው ተሽከርካሪ ርቀትዎን ይጠብቁ፤ ይህም ፍጥነትዎን መቀነስ ወይም ማቆም እንዳያስፈልግዎት ያደርጋል። ቁልቁለት ላይ ማሽከርከር ከመጀመርዎ በፊት የተሻለ ቁጥጥር እንዲኖርዎት ለማድረግ ወደ ዝቅተኛ ማርሽ ይቀይሩ።

የእይታ ሁኔታዎች

ከምሽት በተጨማሪ፣ ጭጋግ እና የበረዶ ብናኝ የማየት ችሎታን የሚቀንሱ ሁኔታዎች ሲሆኑ ወደፊት የማየት ችሎታዎን በእጅጉ ሊቀንሱና በዙሪያዎ ለሚከሰቱ ነገሮች በፍጥነትና በአስተማማኝ ሁኔታ ምላሽ ከመስጠት ሊያግዱዎት ይችላሉ።

ጭጋግ/ጉም ምናልባትም በጣም አደገኛው የሚባል የመንዳት ሁኔታ ነው። እርስዎ ሊመቱት ያሉትን ነገር ማየት አይችሉም፤ እእንዲሁ ሌሎችም እርስዎን ማየት አይችሉም።

ምንም ማየት የማይችሉበት ጥቅጥቅ ያለ ጭጋግ/ጉም ካለ ጉዞ አይጀምሩ። እየነዱ ጥቅጥቅ ያለ ጭጋግ/ጉም ካጋጠምዎት፣ ጭጋጉ/ጉሙ እስኪጠፋ ድረስ ሙሉ በሙሉ ከመንገዱ ይውጡ፤ ወይም ከተቻለ ወደ ማቆሚያ ቦታ ይሂዱ። በቆሙበት ጊዜ፣ ተሽከርካሪዎ ይበልጥ እንዲታይ ለማድረግ የአደጋ መብራቶቹን ያብሩ፤ እንዲሁም የደህንነት ቀበቶዎ ይታጠቁ።

በጭጋጋማ ሁኔታዎች ውስጥ የግዴታ ማሽከርከር ሲኖርብዎ ሁል ጊዜ እነዚህን ሁለት (2) ነገሮች ማድረግዎን ያስታውሱ፡-

1. **ማየት በሚችሉት ርቀት ውስጥ በአስተማማኝ ሁኔታ መቆም እንዲችሉ ፍጥነትዎን ይቀንሱ።**ጭጋግ/ጉም በምን ያህል ፍጥነት እየሄዱ እንዳለ ለማወቅ የሚረዱ አብዛኛዎቹን ምስላዊ መረጃዎች እንዳይታዩ ያርጋል፤ ይህም ሳይታወቅት በቀላሉ እንዲፈጥኑ ሊያድርግዎት ስለሚች የፍጥነት መለኪያዎን በጥንቃቄ መመልከት ያስፈልግዎታል።
2. **ሌሎች እርስዎን ማየት እንዲችሉ ዝቅተኛ ጨረር የግንባር መብራቶችዎን (እና ተሽከርካሪዎ ካለው የጭጋግ መብራቶችን) ያብሩ።** በቀንም ሆነ በምሽት ይህንን ያድርጉ። ሀይ-ቢም መብራቶችን (ከፍተኛ የብርሃን ጨረር መብራቶች) አይጠቀሙ። ብርሃናቸውን ወደ ላይ እና ወደ ጭጋግ ያበራሉ፤ ይህም ብርሃኑን ወደ አይኖችዎ ተመልሶ እንዲያንጸባርቅ ያደርገዋል፤ ይህም ነጸብራቅ ወደ ፊት ለማየት የበለጠ ከባድ ያደርገዋል።

የበረዶ ብናኝም እይታዎን እጅጉን ሊጎዳ ይችላል።

በረዷማ ሁኔታዎች ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የማየት ችሎታዎን ለመጨመር እነዚህን ስድስት (6) ነገሮች ያድርጉ፡-

1. **በረዶ ውስጥ መንዳት ከመጀመርዎ በፊት የተሽከርካሪዎን መስኮቶች፣ ኮፈን (ሁድ)፣ የሻንጣ ማስቀመጫ እና ጣሪያ ያጽዱ።** ይህን ካላደረጉት፣ በረዶ ከተሽከርካሪዎ ላይ ተነስቶ የንፋስ መከላከያ መስታወትዎ (ዊንድሺልድዎ) ላይ ይከማች እና እይታዎን ይጋርዳል፤ ወይም በንፋስ ተጠርጎ ወደ ኋላዎ ወዳለ ሹፌር የንፋስ መከላከያ መስታወት (ዊንድሺልድ) ላይ በረዶ ሊከማችበት ይችላል።

   ከሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪ በረዶ ወይም የበረዶ ብናኝ ሌላ ተሽከርካሪ ወይም እግረኛ ላይ ወድቆ ሞት ወይም እጅግ ከባድ የሆነ የአካል ጉዳት ካደረሰ፣ የተሽከርካሪው አሽከርካሪ ሊቀጣ ይችላል።
2. **በረዶ፣ የበረዶ ብናኝ እና ቆሻሻን የመሳሰሉ ከግንባር መብራቶች፣ ከኋላ መብራቶች እና ከአቅጣጫ አመልካች መብራቶችዎ ላይ ያጽዱ።** እንድዚህ ማድረግ ሌሎች አሽከርካሪዎች እርስዎን እንዲያዩ እና እርስዎም ወደፊት ያለውን እንዲያዩ ያግዝዎታል። የቆሸሸ የግንባር መብራት የማብራት አቅሙን ከ50 በመቶ በላይ ይቀንሳል።
3. **ማሽከርከር ከመጀመርዎ በፊት ኢንጅኑ (ሞተሩ) እንዲሞቅ ያድርጉ።** ይህ በረዶ ማቅለጫው እርስዎ ከፊት መስታወት (ከዊንድሺልዱ) መጥረግ ያልቻሉትን ማንኛውንም በረዶ ለማሞቅ እና ለማቅለጥ እድል ይሰጣል።
4. **የንፋስ መከላከያዎን በተቻለ መጠን ጽዱ ለማድረግ የንፋስ መከላከያ መጥረጊያ (ዊንድሺልድ ዋይፐርስ) ይጠቀሙ።** የንፋስ መከላከያ ማጠብያ (ዊንድሺልድ ዋሸር) ቋትዎ መሙላቱን እና ወደ በረዶነት የማይቀየር ፈሳሽ እየተጠቀሙ መሆኑን ያረጋግጡ።
5. **በእንፋሎት የተሞሉ መስኮቶችን ለማጽዳት በረዶ ማቅለጫ ያብሩ።** ተሽከርካሪዎ አዲስ ከሆነ፣ በረዶ ማቅለጫዎ ከአየር ማቀዝቀዣዉ ጋር አንድ ላይ የተያያዘ ሊሆን ይችላል። የተሽከርካሪዎ የበረዶ በረዶ ማቅለጫ እንዴት ጥቅም ላይ መዋል እንዳለባቸው ለማወቅ የተሽከርካሪዎ መመሪያ መጽሃፍ ያንብቡ።
6. **በቀን ላይም ቢሆን ሎው ቢም መብራቶችን ያብሩ።** ይህም ሌሎቹ አሽከርካሪዎች በቀላሉ እንዲያዩዎት ያደርጋል።

የበረዶ አውሎ ነፋሶች

የበረዶ አውሎ ነፋሶች አደገኛ የክረምት ማሽከርከር አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ። የበረዶ አውሎ ነፋሶች ብዙ ጊዜ የሚከሰቱት ፀሐያማ እና የአየር ሁኔታው ጥሩ በሆነበት ግዜ ኃይለኛ የሆነ በረዶ አዘል ንፋስ በሚነፍስበት ግዜ ሲሆን፣ በሚከሰቱበት ግዜም በሰከንዶች የመንገዱ የመታየት ሁኔታን በእጅጉ ይቀንሰዋል፤ እንዲሁም መንገዱ አንሸራታች ያደርግዋል። እንደ ሹፌር፣ ከግልጽ እና ደረቅ መንገዶች ወደ አደገኛ ሁኔታዎች በቅጽበት መሄድ ሊሸጋገሩ ይችላሉ፤ ይህም በኢንተርስቴቶች በሰዓት ከ60 ማይል በላይ በሆነ ፍጥነት በሚነዱበት ወቅት አብዛኛው ግዜ ምላሽ ለመስጠት በቂ ግዜ

አይሰጥዎትም። እነዚህ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ቀደም ሲል በፔንስልቬኒያ አውራ ጎዳናዎች ላይ ብዙ አደጋዎችን ያደረሱ ሲሆን፣ ጉዳቶችንና ሞትንም አስከትለዋል። የበረዶ አውሎ ንፋስ በሚከሰትበት ጊዜ ለአሽከርካሪዎች ጠቃሚ የሆኑ ምክሮች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፦

- **ይከታተሉ፡** ለመጓዝ ካሰቡ የአየር ሁኔታ ትንበያውን ይመልከቱ። የብሔራዊ የአየር ሁኔታ ትንበያ አገልግሎት እና የቴሌቪዥን ጣቢያ አጋሮች ሃይለኛ ነፋስ ሊኖር በሚችልባቸው ቀናት አስቀድመው ለአሽከርካሪዎች ለማሳወቅ ይሞክራሉ። በአካባቢዎ ስላለው አደጋ መረጃ ለማግኘት የትራንስፖርት መልዕክት ሰሌዳዎችን እና ምልክቶችን ይከታተሉ።

- **ማቀድ፡-** አውሎ ነፋሶችን እንዳያጋጥምዎት ለማድረግ የጉዞ እቅድዎን ሰዓት፣ መንገድ ወይም ሁለቱንም እንደ አስፈላጊነታቸው ያስተካክሉ። በከፍተኛ ፍጥነት መጓዝ እና የትራፊክ መጨናነቅ በመኖሩ አውራ ጎዳናዎች ለአደጋ ተጋላጭ ናቸው።

- **ያስወግዱ፡-** እያሽከረከሩ ከሆነ እና አውሎ ንፋስ እየቀረበ መሆኑን ካዩ ወይም በአቅራቢያዎ አውሎ ንፋስ እንዳለ ካወቁ ከመንገዱ ወጥተው አውሎ ንፋሱ እስኪያልፍ ይጠብቁ።

- **ይጠንቀቁ፡-** የበረዶ አውሎ ንፋስ ካጋጠመዎት ፍጥነትዎን በእጅጉ በመቀነስ እና ሌሎች እንዲያዩዎት የአደጋ ጊዜ መብራቶችዎን በማብራት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያድርጉ። ፍሬንዎን በድንገት በእጅጉ አይጫኑ። አደጋ ካጋጠመዎት በተቻለዎት መጠን፣ በተሽከርካሪዎ ውስጥ ይቆዩ።

የብሔራዊ የአየር ሁኔታ አገልግሎት አሁን እነዚህ አደገኛ አውሎ ነፋሶች በአሽከርካሪዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩባቸው በሚችሉ መንገዶች ላይ "የበረዶ አውሎ ንፋስ ማስጠንቀቂያ" መልዕክቶችን ያወጣል፤ አብዛኛው ግዜ እነዚህ አውሎ ነፋሶች በየመንገዱ የሚቆዩት ለ45 ደቂቃዎች ነው። አሽከርካሪዎች እነዚህን ማንቂያዎች እና ሌሎች የአየር ሁኔታ ማንቂያዎችን ለመቀበል፣ በጽሑፍ መልእክት ወይም ከብዙ የሶስተኛ ወገን አቅራቢዎች መተግበሪያዎች (አፕሊኬሽኖች) ለማግኘት መመዝገብ ይችላሉ። በሚጓዙበት መንገድ ላይ የበረዶ አውሎ ንፋስ ማስጠንቀቂያ ከደረሰዎት የጉዞ እቅድዎን ለማዘግየት ወይም ለመቀየር ከላይ የተጠቀሱትን መመሪያዎች ይከተሉ።

የግንባር መብራቶች(HEADLIGHT)/የንፋስ መከላከያ መስታወት መጥረጊያ (ዊንድሺልድ ዋይፐርስ) ህግ

ይህ እ.ኤ.አ. ጥር 28፣ 2007 ላይ ተግባራዊ የሆነው ህግ አሽከርካሪዎች በአየር ሁኔታዎች ምክንያት የተሽከርካሪዎቻቸው መጥረጊያዎች ቀጣይነት ባለው ወይም አልፎ አልፎ ጥቅም ላይ በሚውሉበት በማንኛውም ጊዜ የግንባር መብራታቸውን እንዲያበሩ ያስገድዳል። በቀን የሚሰሩ መብራቶች ብቻ በቂ አይደሉም። የኋላ መብራቶችዎ እንዲሁ መብራት አለባቸው። ህጉን የማይከተሉ አሽከርካሪዎች 25 ዶላር ቅጣት ሊጣልባቸው ይችላል፤ ነገር ግን ቅጣቱ ከክፍያዎች እና ከሌሎች ተያያዥ ወጪዎች ጋር ተዳምሮ 100 ዶላር ሊደርስ ይችላል።

የትራፊክ ፍሰት

- አደጋዎች ብዙ ጊዜ የሚከሰቱት አንዳንድ አሽከርካሪዎች ከመንገድ ላይ ካሉት ሌሎች ተሽከርካሪዎች በበለጠ ፍጥነት ወይም ቀስ ብለው ሲያሽከረክሩ ነው። ሁሌም በተለጠፈው የፍጥነት ገደብ ውስጥ ከትራፊክ ፍሰት ጋር ለመንዳት ይሞክሩ።

- ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ያልዎትን ርቀት ጠብቀው ለመሄድ በዙሪያዎ ያሉ ተሽከርካሪዎች በሚያደርጉት በመመርኮዝ ፍጥነትዎን ማስተካከል ሊያስፈልግዎ ይችላል። ለምሳሌ አውራ ጎዳና ላይ ብዙ መኪኖች በአንድ ላይ በሚሄዱበት ጊዜ ለአደጋ ጊዜ የሚሆን በቂ ቦታ ሳይኖርዎት፣ እራስዎን ለሌላ አሽከርካሪ በማይታይ ቦታ ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ፍጥነትዎን በሁለት (2) ወይም በሶስት (3) ማይል በሰአት ብቻ መቀነስ፣ በዙሪያዎ ያለውን ትራፊክ እንዲቀንስ ያደርጋል፤ እንዲሁም በተዘጋጋ ቦታ ውስጥ እንዳይቀሩ ያደርጋል።

- ከትራፊክ ፍሰት ጋር ማስተካከል የሚኖርብዎት ሌላ ጊዜ ደግሞ በአንድ ጊዜ ሊያጋጥሙዎት የሚችሉ ከአንድ (1) በላይ አደጋዎች ሲኖሩ ነው። ለምሳሌ፣ በብስክሌተኛ በስተቀኝዎ በኩል ካለ፣ በሚያልፉበት ጊዜ ሰፊ ክፍተት እንዲኖርዎት ለማድረግ ማድረግ ያለብዎት አስተማማኝ ነገር ወደ **ግራ** መንቀሳቀስ ነው። ነገር ግን በተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣ መኪና ካለ፣ ይህ ችግር ይፈጥራል፤ ምክንያቱም በተለምዶ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከመስመርዎት ወደ **ቀኝ** በኩል መሄድ አለብዎት። ይህንን መፍታት ያለብዎት ለእያንዳንዱ የትራፊክ ሁኔታ በተናጠል ምላሽ በመስጠት ነው። የሚመጣው ተሽከርካሪ እንዲያልፍ ፍጥነትዎን ይቀንሱ፤ እና ከዚያ ለደህንነት በቂ ክፍት ቦታ በመተው ብስክሌተኛውን ለማለፍ ወደ ግራ ይሂዱ።

- እንዲሁም፣ ወደ ድንገተኛ አደጋ ቦታ ወይም ፖሊሶች ተሽከርካሪን በሚያስቆሙበት ቦታ እንዲሁም የተበላሸ መኪና ወደሚወስድ የጭነት መኪና ሲቃረቡ በአቅራቢያው ወዳለ ወደማይገናኝ መስመር መቀየር አለብዎት። ወደ ሌላ መስመር መቀየር ካልቻሉ ፍጥነትዎን ከተፈቀደው የፍጥነት ገደብ ከ20 ማይል በሰዓት በታች ዝቅ ማድረግ ይኖርብዎታል።

በአንድ ጊዜ አንድ የትራፊክ ሁኔታን ብቻ ያስተናግዱ



ከብስክሌተኛው ጀርባ በመሆን ፍጥነትዎን ቀንሰው ይሂዱ፤ እንዲሁም ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣው መኪና እንዲያልፍ ይፍቀዱ፤ ከዚያም ብስክሌተኛውን በሰላም ለማለፍ በብስክሌተኛውን በስተግራ በኩል 4 ጫማ (feet) ክፍተት በመተው አልፈው ይሂዱ።

በቀስታ ለሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች የሚሰጡ ምላሾች

ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ጋር አብረው በተመሳሳይ ፍጥነት ለመሄድ የሚቸገሩ ተሽከርካሪዎች ወደ መንገድ ሲገቡ ፍጥነታቸውን ለመጨመር ብዙ ጊዜ ሊወስድባቸው ስለሚችል ይጠንቀቋቸው። እነዚህም አንዳንድ ትላልቅ የጭነት መኪናዎች፣ እንዲሁም የእርሻ መሣሪያዎች እና በፈረስ የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች ይገኙበታል። የጭነት መኪናዎች ወደ ላይ ሲጓዙ በተለይም በረጅም ወይም እጅግ ዳገታማ በሆኑ መንገዶች ሲጓዙ ፍጥነት እየቀነሱ መሆናቸውን ለሌሎች አሽከርካሪዎች ለማሳወቅ ብዙውን ጊዜ የአደጋ መብራታቸውን ይጠቀማሉ።



በገጠር አካባቢዎች ከተለመደው የትራፊክ ፍሰት ፍጥነት ያነሰ የሆነው በሰዓት 25 ማይል ወይም ከዚያ በታች እንዲጓዙ ደዛይን የተደረጉ ትራክተሮች ወይም በፈረስ በሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች ላይ ብርቱካናማ ሶስት መዓዘን ይለጠፋል። በፔንስልቬኒያ በተወሰኑ አካባቢዎች ከእርሻ ትራክተሮች እና በፈረስ ከሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች ጋር በአንድ መንገድ ላይ መጓዝ የተለመደ ነገር ነው። ወደ ኋላ ርቀትዎን ጠብቀው ይጓዙ፤ እንዲሁም ለማለፍ ጥሩንባ አይንፉ (ክላክስ አያድርጉ)።

ለማድርግ ያሰቡትን ነገር ለሌሎች አሽከርካሪዎች ማሳወቅ

ብዙውን ጊዜ የመንገድ አደጋዎች የሚከሰቱት አንዱ (1) አሽከርካሪ ሌላ አሽከርካሪ ያልጠበቀውን ነገር ስለሚያደርግ ነው። የመንገድ አደጋዎችን ለማስቀረት መንገድ ላይ ላሉ አሽከርካሪዎች ለማድረግ ያሰበቱን በምልክት ያሳውቁ።

የት እንዳሉ እና ምን ለማድረግ እንዳሰቡ ለሌሎች በሚከተሉ መንገዶች ያሳውቁ:-

- **ፍጥነትዎን ሲቀንሱ ወይም ሲያቆሙ ምልክት በመስጠት።** የፍሬን (የብሬክ) መብራቶችዎ ፍጥነትዎን እየቀነሱ ወይም እያቆሙ መሆኑን ለሌሎች አሽከርካሪዎች ያሳውቃሉ። ሌሎች አሽከርካሪዎች በማይጠብቁበት ቦታ ፍሬን የሚይዙ ከሆነ፣ የፍሬን ፔዳልዎን በፍጥነት ሶስት (3) ወይም አራት (4) ጊዜ ጫን እያሉ ይልቀቁ። ገደብ ባለው የፍጥነት መንገድ (ሀይዌይ) በ40 ማይል በሰአት ማሽከርከር ካለቦት ከኋላዎ ያሉትን አሽከርካሪዎች ለማስጠንቀቅ የአደጋ ጊዜ መብራቶችን (አራቱም አቅጣጫ ጠቋሚዎች) ያብሩ።
- **አቅጣጫን ሲቀይሩ ምልክት ማድረግ።** ምልክት ማድረግ ለመታጠፍ እንደሚፈልጉ ለሌሎች አሽከርካሪዎች ያሳውቃል እንጂ የመታጠፍ መብት አይሰጥዎትም። በፔንስልቬንያ ህግ መሰረት፣ ከ35 ማይል በሰአት ባነሰ ፍጥነት እየነዱ ከሆነ ለመታጠፍ ከማሰብዎ በፊት ቢያንስ **100 ጫማ (feet)** ቀደም ብለው የመብራት ምልክትዎን መጠቀም አለብዎት። 35 ማይል በሰአት ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ፍጥነት እየነዱ ከሆነ፣ ከመታጠፍዎ ከ **300 ጫማ (feet)** በፊት ምልክት ማድረግ አለብዎት። የተሽከርካሪዎ የመታጠፊያ የመብራት ምልክቶችዎ የማይሰሩ ከሆነ እነዚህን የእጅ ምልክቶች ይጠቀሙ።

- **የአደጋ ጊዜ ምልክቶችን መጠቀም።** ተሽከርካሪዎ አውራ ጎዳናው ላይ ከተበላሸ፣ አውራ ጎዳና መውጣት አለብዎት። ይህን ለማድረግ መጀመርያ ምልክት ያሳዩ፣ ከዚያም በጥንቃቄ ከመንገድ ይውጡ፤ እና ሌሎች አሽከርካሪዎችን ለማስጠንቀቅ የአደጋ ጊዜ መብራቶችን (የአራቱም አቅጣጫ ጠቋሚዎች) ያብሩ። በተቻለ መጠን ከመንገዱ ርቀው በመሄድ ሌሎች አሽከርካሪዎች በቀላሉ ሊያዩዎት በሚችሉበት ቦታ ያቁሙ። ተሽከርካሪዎ መበላሸቱ ለሌሎች አሽከርካሪዎች ለማሳወቅ ኮፈኑን ያንሱ።
- **የተሽከርካሪዎን ጥሩንባ መጠቀም።** ጥሩንባዎት ወዲያውኑ የሌሎችን አሽከርካሪዎች ትኩረት ይስባል። ሌላ አሽከርካሪ ወይም እግረኛ እያየኝ አይደለም ብለው በሚያስቡበት ጊዜ ይጠቀሙበት - ለምሳሌ:- አንድ ልጅ ወደ ጎዳና መሮጥ ከጀመረ ወይም ሌላ ተሽከርካሪ ሊገጨኝ ነው ብለው ካሰቡ። እንዲሁም፣ ተሽከርካሪዎን መቆጣጠር ሲያቅትዎት፣ ጥሩምባዎትን ክላክስ በማሰማት ሌሎች አሽከርካሪዎችን ያሳውቁ።

መታጠፍ፣ የትራፊክ ፍሰትን መቀላቀል እና ማለፍ

በሚታጠፉበት ወቅት ለብዙ ነገሮች ትኩረት መስጠት አለብዎት። ፍጥነት ምናልባትም ከሁሉም በላይ በጣም ወሳኝ ነገር ነው። በሚታጠፉበት ጊዜ ተሽከርካሪዎን መቆጣጠር ወደሚችሉበት ፍጥነት መቀነስ በመስመርዎ ውስጥ እንዲቆዩ እና ባልተጠበቁ ሁኔታዎች ላይ በብቃት ምላሽ እንዲሰጡ ያስችልዎታል። በሚታጠፉበት መንገድ ላይ ያሉ እግረኞችን እና ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ይጠንቀቁ። ብዙ ጎዳናዎች እርስዎን ለመምራት የሚያግዙ የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ የትራፊክ መብራት ምልክቶችን ወይም የትራፊክ መስመር ምልክቶች አሏቸው። አንዳንድ ምልክቶች ሲታጠፉ ምን ዓይነት መስመሮችን መጠቀም እንደሚችሉ ወይም እንዳለብዎት ያሳያሉ።

በአስተማማኝ ሁኔታ መታጠፍዎን ለማጠናቀቅ

1. **ከመታጠፍዎ ከሶስት (3) እስከ አራት (4) ሰከንዶች በፊት ምልክት ያድርጉ።**
2. **ተሽከርካሪዎን በትክክለኛው መስመር ላይ ያድርጉ።**
3. **ፍጥነትዎን ይቆጣጠሩ።**
4. **ሲታጠፉ ተገቢውን መስመር በመጠቀም ያጠናቅቁ።**

የታዳጊ ወጣቶች የትራፊክ አደጋ እውነታ

ተገቢ ያልሆነ ወይም ግድየለሽነት የተሞላበት መታጠፍ በአዲስ እና ወጣት አሽከርካሪዎች መካከል የተለመደ የትራፊክ አደጋዎች መንስኤ ነው። እ.ኤ.አ. በ2017፣ በፔንሲልቬንያ 17 አመት በሆናቸው አሽከርካሪዎች የተከሰቱ በአጠቃላይ 459 የትራፊክ አደጋዎች ተገቢነት በሌለው ወይም ጥንቃቄ በጎደለው መታጠፍ ጋር የተያያዙ ነበሩ።

ወደ ግራ እና ወደ ቀኝ መታጠፍ



በባለ ሁለት መስመር፣ በባለሁለት አቅጣጫ መንገዶች ወይም በአውራ ጎዳናዎች (ሀይዌዮች) ላይ ወደ ግራ ሲታጠፉ በተቻለ መጠን ወደ መሃል መስመር በመጠጋት ይታጠፉ። ወደ ቀኝ ሲታጠፉ በተቻለ መጠን ከመንገዱ የቀኝ ጠርዝ አጠገብ በመሆን ይታጠፉ።

በባለብዙ መስመር ጎዳናዎች እና አውራ ጎዳናዎች ላይ ወደ ግራ ለመታጠፍ ከግራ መስመር ይጀምሩ። ወደ ቀኝ እየታጠፉ ከሆነ፣ ከቀኝ መስመር ይጀምሩ። ለመጓዝ ሚፈልጉበት አቅጣጫ ከአንድ በላይ (1) መስመር ወዳለው አውራ ጎዳና እየታጠፉ ከሆነ ወደዚያ አቅጣጫ ወደ ሚሄደው ቅርብ መስመር ይንቀሳቀሱ። ወደ ግራ ሲታጠፉ ወደ ግራ መስመር ይዝሩ፣ እና ወደ ቀኝ ሲታጠፉ ወደ ቀኝ መስመር ይዝሩ። ወደ ሌላ መስመር መቀየር ከፈለጉ፣ ተሽከርካሪዎ በደህና መታጠፉን ሙሉ ለሙሉ እስኪጨርስ ድረስ ይጠብቁ።

ከ ወይም ወደ መሀል መታጠፊያ መስመር መታጠፍ

በባለ ሁለት አቅጣጫ ጎዳና መካከል በሁለቱም አቅጣጫዎች በኩል በሁለት (2) መስመሮች ምልክት የተደረገበት መስመር ካዩ - አንድ (1) ያልተቆራረጠ የውጭ መስመር እና አንድ (1) የተቆራረጠ የውስጥ መስመር - ይህ ማለት ይህ መስመር ወደ ግራ ለሚታጠፉ ተሽከርካሪዎች ብቻ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል ማለት ነው(ምዕራፍ 2 ላይ ያለውን ንድፍ ይመልከቱ)። በሁለቱም አቅጣጫ የሚጓዙ አሽከርካሪዎች የግራ መታጠፊያቸውን ለመጀመር በዚህ መስመር መጠቀም አለባቸው፤ እና ወደ መንገዱ የሚገቡ አሽከርካሪዎች ወደ የትራፊክ ዥረቱ ከመግባታቸው በፊት ከመንገድ ማቋረጫ የግራ መታጠፊያቸውን በዚህ መስመር ሊጠቀሙ ይችላሉ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ብዙ ሊከሰቱ የሚችሉ የትራፊክ ግጭቶች አሉ:-

- ወደ ድራይቭ ዌይ ወይም ተደራቢ አቋራጭ መንገድ ለመግባት ወደ ግራ ለመታጠፍ የመሀል መስመር ስትገቡ ሁለቱንም ወደ መታጠፊያ መስመር ወደሆነው ወደ መሃል መስመር የሚመጡ ተሽከርካሪዎች ማለትም ከድራይቭ ዌይ እና እና ከመኪና መንገዶች (በግራ በኩል) ወደ መሃል መታጠፊያ መስመር የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን መከታተል አለቦት።
- ከድራይቭ ዌይ ወይም ተደራቢ አቋራጭ መንገድ ወደ ግራ ሲታጠፉ ከግራዎ የሚመጣውን ትራፊክ እንዲሁም ከሁለቱም አቅጣጫ ለመታጠፍ በዝግጅት ላይ ያሉትን አሽከርካሪዎች መከታተል አለቦት።

መሃል ላይ ያሉ መታጠፊያ መስመሮች ደህንነቱ በጠበቀ ሁኔታ ለመጠቀም ከታች ያሉትን መምሪያዎች ይከተሉ:-

1. ወደ ግራ መታጠፊያ መስመር (ሌይን) ከመግባትዎ በፊት ቢያንስ ከሶስት (3) እስከ አራት (4) ሰከንዶች ቀደም ብለው **የግራ መታጠፊያ ምልክትዎን ያብሩ።**
2. **ወደ መሃል መታጠፊያ መስመር ቶሎ አይግቡ።** በመካከለኛው መስመር ረዘም ላለ ግዜ ባሽከረከሩ ቁጥር ከሌላ አቅጣጫ የሚመጣን አሽከርካሪ ጋር ፊት ለፊት የመገናኘት ዕድልዎ እየጨመረ ይሄዳል።
3. **ወደ መሀል መታጠፊያ መስመር ሲገቡ፣ ሙሉ ለሙሉ ይግቡ።** የተሽከርካሪዎ የኋላ ክፍል በተለመደው የትራፊክ መስመር ላይ ወደ ኋላ በመቅረት ትራፊክን እንዳይዘጋ።
4. **ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መታጠፍ ሲችሉ ብቻ ይታጠፉ።** በተመሳሳይ መስመር ወደ እርስዎ የሚመጡ ተሽከርካሪዎችን ይመልከቱ፤ እና ከመታጠፍዎ በፊት ከፊትዎ ወዳለው ትራፊክ ከማዞርዎ በፊት በቂ የሆነ ክፍተት እንዳለ ያረጋግጡ። ከመንገድ ዳር ወደ መሃል መስመር ሲታጠፉ፣ ቀጥታ ስለሚጓዙ ተሽከርካሪዎች እና ለመታጠፍ አስቀድመው በመሃል መስመር ላይ ያሉትን ተሽከርካሪዎችን ይመልከቱ።

U-TURNS (ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ማዞርያዎች)
እነዚህ የሚፈቀዱት ሌሎች ተሽከርካሪዎችን አደጋ ላይ ሳይጥሉ ሊደረጉ የሚችሉ ከሆነ ብቻ ነው። ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ለመዞር የሚቻልበትን ቦታ በሚመርጡበት ጊዜ ከሁሉም አቅጣጫዎች የሚመጡ አሽከርካሪዎች ከእርስዎ ቢያንስ 500 ጫማ (FEET) ርቀት ላይ መሆናቸውን እና በግልጽ ሊያዩዎት እንደሚችሉ ያረጋግጡ። በኩርባዎች ወይም በኮረብታዎች ጫፍ አካባቢ ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ማዞር (U-TURNS ማድረግ) የተከለከለ ነው። ይህ ምልክት በተደረገባቸው ቦታዎች ላይም ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ መዞር (U-TURN ማድርግ) በህገ የተከለከለ ነው።



የትራፊክ መብራት ቀይ ሲሆን ወደ ቀኝ ስለመታጠፍ
ይህን ምልክት ካላዩ በቀር፣ መንገዱ ክፍት ከሆነ የትራፊክ መብራት ቀይ ሲሆን ወደ ቀኝ መታጠፍ ይችላሉ። ወደ ቀኝ ከመታጠፍዎት በፊት ሁል ጊዜ መጀመሪያ ማቆም እና ለእግረኞች እና ለሚሻገሩ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለብዎት። ከባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ ወደ ሌላ ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ እየታጠፉ ከሆነ፣ መንገዱ ክፍት ክሆነ እና **ቀይ መብራት ላይ መታጠፍ አይቻልም** (NO TURN ON RED) የሚል ምልክት ከሌለ የትራፊክ መብራት ቀይ ቢበራም ወደ ግራ መታጠፍ ይችላሉ። ይህ ምልክት በተለምዶ የሚለጠፈው ከመገናኛ መንገዱ አጠገብ ባለው መንገድ አጠገብ እና በመገናኛ መንገዱ ማዶ ላይ ካለው የትራፊክ መብራት ምልክት አጠገብ ነው።

ተሽከርካሪዎችን ማለፍ
ተሽከርካሪን በሚያልፉበት ጊዜ፣ ደህንነትዎ በተጠበቀ ሁኔታ ለማለፍ በቂ ቦታ ያስፈልግዎታል። ተሽከርካሪን ለማለፍ የሚያስፈልግዎ የቦታ መጠን በመንገድ፣ በአየር ሁኔታ እና በሚመጣው የትራፊክ ፍሰት ላይ የተመሰረተ ነው።

ያስታውሱ:-

- በደህንነት በመንገድ መሀል ላይ ማቆም የሚቻለው በመንገድ መሀል ላይ ለመታጠፊያነት የሚያገለግለው የመንገድ መስመር ተሽከርካሪዎን በበቂ ሁኔታ ማቆም የሚያስችል ቦታ ሲኖር ብቻ ነው።
- እየተሻገሩ ወይም እየዞሩ ከሆነ፣ መንገድዎን የሚከልሉ ተሽከርካሪዎች ወይም እግረኞች አለመኖራቸውን ያረጋግጡ። ከተቃራኒ አቅጣጫ ወደ እርስዎ የሚመጣ የትራፊክ ፍሰት መስቀለኛ መንገድ መሀል ላይ መቆም የለብዎትም።
- ምንም እንኳን አረንጓዴ መብራት ቢበራም፣ መንገድዎን የሚዘጉ ተሽከርካሪዎች ካሉ መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶች ውስጥ አይግቡ። መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገድን ለማቋረጥ ከመጀመርዎ በፊት ሙሉ በሙሉ ማለፍ እንደሚችሉ እርግጠኛ እስኪሆኑ ድረስ ይጠብቁ።
- ወደ እርስዎ እየተጠጋ ያለ እና የመታጠፊያ ምልክት ከሚያሳይ መኪና ፊት ለፊት ከመግባት ወይም ከመሻገር ይቆጠቡ። አሽከርካሪው ከእርስዎ ወዲያ ወዳለው ጎዳና ወይም ግቢ ለመግባት እያሰበ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ሃሳቡን ቀይሮ ሊሆን ይችላል፤ አሊያም ምልክቱን ማጥፋት ረስቶትም ሊሆን ይችላል። ይህ በተለይ ሞተር ሳይክሎች ላይ እውነት ነው፤ ምክንያቱም የመብራት ምልክታቸው በራስ ሰር ላይጠፋ ይችላል። **ጉዞዎን ከመቀጠልዎ በፊት ሌላው አሽከርካሪ በትክክል መዞር እስኪጀምር ድረስ ይጠብቁ።**
- ኮረብታዎች ወይም ኩርባዎች ባሉባቸው ቦታዎች ላይ ማየት ወይም መታየት በማይችሉበት ቦታ ላይ ትራፊክ ሲያቋርጡ የበለጠ ጥንቃቄ ያድርጉ።

ከትራፊክ ፍሰት ጋር መቀላቀል
ከትራፊክ ፍሰት ጋር መቀላቀል ጥሩ የአሽከርካሪ ብቃትን ይጠይቃል። ሀይዌይ ላይ መስመሮችን እየቀየሩ ይሁን በመግቢያ መንገድ ወደ ሀይዌይ ሲገቡ በደህና ወደ የትራፊክ ፍሰቱ ለመግባት በቂ ክፍት ቦታ ያስፈልግዎታል።

ወደ አውራ ጎዳናዎች ለመግባት የሚያገለግሉ መንገዶች (ሀይዌይ ራምፕ) ብዙውን ጊዜ የፍጥነት መጨመሪያ የመንገድ መስመሮች አሏቸው። እነዚህ መስመሮችም ከዋናው መንገድ መስመሮች ጎን ለጎን በመሆን የሚሄዱ ናቸው፤ እና ወደ ዋናው የአውራ ጎዳና መንገድ ከመግባትዎ በፊት ከትራፊክ ፍሰት ፍጥነት ጋር እኩል ፍጥነት እንዲኖርዎት የሚያስችሉ ለመሆነ ረጅም መሆን አለባቸው። እነዚህ መስመሮች ወደ ዋናው መንገድ ከመግባትዎ በፊት በዋናው መንገድ ላይ ያሉ አሽከርካሪዎች እርስዎን እንዲያዩ ያስችላቸዋል። **በማፍጠኛ የመንገድ መስመር ላይ ከፊትዎ ያለን ተሽከርካሪን ማለፍ በህግ የተከለከለ ነው።**

ከማፍጠኛ የመንገድ መስመር (ከአክስሌሬሽን ሌይን) ወደ የትራፊክ ፍሰት ጋር ለመቀላቀል እነዚህን ሶስት ደረጃዎች ይከተሉ
1. **የመታጠፊያ ምልክትዎን ያብሩ እና በትራፊክ ፍሰቱ ውስጥ ክፍት ቦታ ይፈልጉ።**
2. **ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ጋር የሚመሳሰል ፍጥነት እስኪይዙ ድረስ ፍጥነትዎን ይጨምሩ።**
3. **ከዚያም በትራፊክ ፍሰት ውስጥ ወዳለ ክፍት ቦታ በመግባት ይቀላቀሉ።**

ማለፍ
ተሽከርካሪን ማለፍ የማሽከርከር ወሳኝ አካል ነው፤ በትክክል ካልተደረገ ተሽከርካሪን ማለፍ በጣም አደገኛ አልፎ ተርፎም ለሞት ሊዳርግ የሚችል እንቅስቃሴ ሊሆን ይችላል። የሚከተሉትን መመሪያዎች ይጠቀሙ።

በአጠቃላይ፣ ከፊትዎ ለማለፍ ለመሞከር የሚሆን በቂ የሆነ ክፍት መንገድ ካለ፣ አሁንም ማለፍ አለብዎት።

1. በተለመደው የመንዳት ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ የሚቻልበትን ወይም የማይቻልበትን ሁኔታዎችን የሚነግሩዎትን የመንገድ ዳር ምልክቶች እና የትራፊክ መስመር ምልክቶችና ቅቦች ይመልከቱ። (የእነዚህ ምሳሌዎች በምዕራፍ 2 ውስጥ ይገኛሉ።)
2. ማለፍ ከመጀመርዎ በፊት በጥንቃቄ ወደፊት ይመልከቱ፣ እና በሚያልፉበት ጊዜ አንድ ተሽከርካሪ ወደ መንገድዎ ሊገባ የሚችልባቸውን መንገዶች ጨምሮ በአካባቢው ያሉትን ማንኛውንም አደጋዎች ይጠንቀቁ።
3. ማለፍ ሲጀምሩ ለእርሶ ለማየት በሚያዳግቱ ቦታዎች ሊያልፉዎት የሚችሉ ተሽከርካሪዎች አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ የጎን እና የኋላ መመልከቻ መስተወቶችዎን ይመልከቱ፤ እንዲሁም በፍጥነት ወደ ሁለቱም ጎን ይመልከቱ።
4. ከማለፍዎ በፊት የማለፊያው መስመር ክፍት መሆኑን ያረጋግጡ፤ እንዲሁም መስመር ለመቀየር መፈለግዎን ለማሳየት ትክክለኛውን ምልክት ያሳዩ። ምን ለማድረግ እንዳሰቡ ሌሎች አሽከርካሪዎች አስቀድመው እንዲያውቁ ለማድረግ አስቀድመው ምልክት ይስጡ።
5. ካለፉ በኋላ፣ ወደ መስመርዎ ለመመለስ ማሰብዎን ምልክት በማሳየት ያሳውቁ።
6. ወደ መስመርዎ ተመልሰው ከመግባትዎ በፊት አልፈውት የሄዱትን ተሽከርካሪ የግንባር መብራቶች ሙሉ በሙሉ የኋላ መመልከቻ መስታወትዎ ላይ እንደሚታዩ ያረጋግጡ።

በሚያልፉበት ጊዜ፣ ተሽከርካሪዎች ወይም እግረኞች መንገዱን ሊያቋርጡ በሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ ከተለመደው የበለጠ ጥንቃቄ ያድርጉ። እነዚህ ቦታዎችም መገናኛ መንገዶችን እና የገበያ ማእከል መግቢያ እና መውጫዎችን ያካትታሉ። እንዲሁም አንድ አሽከርካሪ ወደ መንገድ ሲታጠፍ እና ወደ ግራ መስመር ሲገባ እርስዎ በዚያ መስመር ላይ ይኖራሉ ብሎ ስለማይጥብቅ ወደ እርስዎ በኩል ላይመለከት ይችላል።

የታዳጊ ወጣቶች የትራፊክ አደጋ እውነታ

በተሳሳተ የመንገድ አቅጣጫ ማሽከርከር በ16 እና 17 አመት እድሜ ክልል ውስጥ ባሉ አሽከርካሪዎች መካከል ለሚደርሱ የትራፊክ አደጋዎች በብዛት የሚከሰት መንስኤ ነው። እ.ኤ.አ. ከ2013 እስከ 2017፣ 384 የመንገድ አደጋዎች የደረሱ ሲሆን 15 ሰዎችም ሞተዋል።

- **በ ባለሁለት አቅጣጫ መንገድ ላይ**

  በባለሁለት አቅጣጫ መንገድ ላይ ማለፍ ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣውን መስመር መጠቀም ስለሚኖርብዎት ከፊት ለፊት ከሚመጡ ተሽከርካሪዎች ጋር ላለመጋጨት ከእርስዎ ጥሩ ውሳኔ አሰጣጥን ይጠይቃል። በ45 ማይል በሰዓት ሲጓዙ ቀስ ብሎ የሚሄድ ተሽከርካሪ ጋር ሳይጋጩ ለማለፍ 1/4 ማይል (ሩብ ማይል) የሚሆን ክፍት መንገድ ያስፈልግዎታል ማለት ነው።

  ከሚያልፉት/ፏቸው ተሽከርካሪ(ዎች) ፍጥነት 10 ማይል በሰዓት ፍጥነት በላይ መሄድ ያስፈልግዎታል። ማለፍ ከሚፈልጉት ተሽከርካሪ ፊት ሌሎች ተሽከርካሪዎች ካሉ፣ እነሱንም ማለፍ ይችላሉ፤ ነገር ግን ለማለፍ ማሽከርከር ከመጀመርዎ በፊት ከነዚያ ተሽከርካሪዎች ፊት ለፊት ለመግባት የሚያስችል በቂ ክፍት ቦታ መኖሩን ያረጋግጡ።

  ማታ ላይ በደንብ ማየት ስለማይችሉና ርቀቶችን በትክክል መገመት ስለሚከብድ ምሽት ላይ ማለፍ በጣም አደገኛ እና ከባድ ነው። ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣውን ተሽከርካሪ የግንባር መብራቶች ብቻ በሚያዩበት ወቅት የተሽከርካሪው ርቀት ከእውነተኛው ርቀቱ እጅግ የበለጠ ሊሚስልዎት ይችላል።

- **በቀኝ በኩል ማለፍ**

  በቀኝ በኩል ሌላ ተሽከርካሪን ማለፍ የሚችሉባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች፡-

  - የሚያልፉት አሽከርካሪ ወደ ግራ እየታጠፈ ወይም ምልክት እየሰጠ ከሆነ የሚያልፈው ተሽከርካሪ አሽከርካሪ በመንገዱ ጫፍ ላይ ወይም ጥግ ላይ መቆየት በሚኖርበት ወቅት ማለፍ ይችላሉ።
  - በእያንዳንዱ አቅጣጫ ሁለት (2) ወይም ከዚያ በላይ ምልክት የተደረገባቸው የትራፊክ መስመር ባለው መንገድ ላይ ሲያሽከረክሩ።

- **ማለፍ የማይችሉባቸው ሁኔታዎች፡-**

  - ኦፊሴላዊ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያ ማልፍ እንደሚችሉ ካልገለፀልዎት በስተቀር ከመገናኛ መንገድ ወይም ከባቡር ሀዲድ መሻገሪያ በ100 ጫማ ርቀት ውስጥ በሚሆኑበት ወቅት።
  - ከማንኛውም ድልድይ፣ ከፍ ያለ መዋቅር ወይም ዋሻ በ100 ጫማ (feet) ርቀት ውስጥ በሚሆኑበት ወቅት።
  - ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣውን ትራፊክ በግልጽ ማየት ወደ ማይችሉባቸው እንደ ኩርባ ወይም ኮረብታ ጫፍ እየተቃረቡ ወይም ላይ ከሆኑ።
  - በባለብዙ መስመር አውራ ጎዳና ጥግ ላይ ከሆኑ።

መገናኛ መንገዶች ላይ በአግባቡ ስለማሽከርከር

በመገናኛዎች ላይ ህጉ ለማንም ቅድምያ የመስጠት መብት አይሰጥም፤ ነገር ግን ማን ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ብቻ ግን ይናገራል። አንድ አሽከርካሪ በህጋዊ መንገድ ቅድሚያ እንዲሰጥ የሚገደድ ቢሆንም፣ ይህን ሳያደርግ ሲቀር አደጋ እንዳይደርስ ለማድረግ አስፈላጊ ስለሚሆነ ሌሎች አሽከርካሪዎች ለማቆም ወይም ቅድሚያ እንዲሰጡ ይገደዳሉ። **በፍፁም** ቅድሚያ ለኔ መሰጠት አለበት ብለው አይከራከሩ፤ ምክንያቱም ይህ አደጋ ሊያስከትል ይችላል።

የታዳጊ ወጣቶች የትራፊክ አደጋ እውነታ
ታዳጊ ወጣት አሽከርካሪዎች ላይ ከሚደርሱት አደጋዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ የሚከሰቱት በመገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶች ላይ ነው። በፔንስልቬንያ የ16 አመት አሽከርካሪዎች ካጋጠሟቸው አደጋዎች ውስጥ ከአንድ ሶስተኛ በላይ (1/3) የሚሆኑት፣ ታዳጊው አሽከርካሪ ከማቆሚያ ምልክት ተነስቶ እያሽከረከር ወይም በትራፊክ ፍሰት ውስጥ ወደ ግራ በሚታጠፍበት ወቅት የተከሰቱ ናቸው።

በተለያዩ የማሽከርከር ሁኔታዎች ውስጥ ማን ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት የሚገዙ ህጎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። በመገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገድ ላይ የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ የትራፊክ መብራት ምልክቶች ወይም ፖሊሶች ሳይኖሩ ሲቀሩ ምን ማድረግ እንዳለቦት የሚያዙ የሚከተሉትን ህጎች መከተል አለብዎት፦

1. አሽከርካሪዎች ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት የሚኖርባቸው ሁኔታዎች የሚከትሉት ናቸው፦ **ሀ)** እግረኞች በየትኛውም መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገድ ላይ የትራፊክ መብራት (በእግር መሻገሪያም ሆነ ያለ መሻገሪያ) ሳይኖር በሚሻገሩበት ወቅት፤ **ለ)** በመንገድ ላይ ምልክት በተደረገባቸው የእግረኛ መሻገሪያዎች ላይ ሲያቋርጡ፤ ይህም በመገናኛ መንገድ ላይ ቢሆኑም ባይሆኑም ነው፤ **ሐ)** በእግረኛ መንገድ ላይ ያለ መግቢያ መንገድን ወይም ጠባብ መንገድን ሲሻገሩ፤ እና **መ)** አሽከርካሪው ማዞሪያ ላይ ሲታጠፍ እና እግረኞች ደግሞ የትራፊክ መብራት ተክትለው በሚሻገሩበት ወቅት። አሽከርካሪዎች ነጭ የአይነ ስውራን ዘመናዊ በትር (ኬን) የያዙ ወይም በሚመራ ውሻ ለሚመራ ማንኛውም አይነ ስውር እግረኛ ሁሌጊዜ ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።
2. ወደ ግራ የሚታጠፉ አሽከርካሪዎች፣ በቀጥታ ወደ ፊት ለሚሄዱ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።
3. ወደ ክብ መስቀለኛ መንገድ (ወይም አደባባይ) የሚገቡ አሽከርካሪዎች ቀድሞውኑ አደባባዩ ውስጥ ላሉ አሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።
4. ሁለት ተሽከርካሪዎች በተመሳሳይ ሰዓት ከመጡ ወይም ከመገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዱ ላይ ቢደርሱ ከግራ በኩል የሚመጡት አሽከርካሪዎች ከቀኝ በኩል ለሚመጡት ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።
5. አንድ ተሽከርካሪ ከአንድ ትንሽ መንገድ፣ ከግለሰብ መንገድ ወይም ከመኪና ማቆሚያ ወጥቶ ወደ አውራ ጎዳና ለመግባት ሲፈልግ ዋናው መንገድ ክፍት እስኪሆን ድረስ መጠበቅ አለበት።
6. ባለ አራት አቅጣጫ ማቆሚያ ምልክት ባለባቸው መገናኛዎች ሁሉም ተሽከርካሪዎች መቆም አለባቸው። ወደ መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዱ ቀድሞ የደረሰው ተሽከርካሪ መጀመሪያ መንቀሳቀስ ይኖርበታል። ሁለት (2) ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ወደ መገናኛው ወይም መስቀኛ መንገዱ ከደረሱ በግራ በኩል ያለው አሽከርካሪ ለቀኝ በኩል ላለው አሽከርካሪ ቅድሚያ መስጠት አለበት። እርስ በእርሳቸው ፊት ለፊት የሚተያዩ ከሆነ ሊደረጉ የሚችሉ መታጠፊያዎችን በመመልከት ሁለቱም ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ መቀጠል ይችላሉ።

መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶችን ሲቃረቡ

ወደ መገናኛ መንገዶች ሲቃረቡ፣ ምን ዓይነት እንቅስቃሴዎች ከየትኛው መስመር እንደሚፈቀዱ የሚነግሩ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የትራፊክ መብራት ምልክቶችን እና የትራፊክ መስመር ምልክቶችን ይመልከቱ። ለመታጠፍ ወይም በመገናኛ ወይም በመስቀለኛ መንገዶች ውስጥ ለመጓዝ ወደ ትክክለኛው ቦታ ቀደም ብለው ይግቡ።

የመንገድ መስመር ምደባ የሚያግዙ የመንገድ ዳር ምልክቶች እና የትራፊክ መስመር ምልክቶች እና ቅቦች



ብዙ ጎዳናዎች አንድ የተወሰነ መስመር ለተወሰነ የትራፊክ እንቅስቃሴ እንደሚውል የሚጠቁሙ የመንገድ ዳር ምልክቶች ወይም የትራፊክ መስመር ምልክቶች እና ቅቦች አሏቸው። ለመታጠፍ ብቻ በተዘጋጀ መስመር ላይ ከገቡ ምንም እንኳን ቀጥታ መሄድ ቢፈልጉም መታጠፍ ይኖርብዎታል። መታጠፍ (መዞር) ፈልገው ነገር ግን ቀጥታ ለሚሄዱ መኪኖች በተዘጋጀ መስመር ላይ ከገቡ ቀጥታ መሄድ ይጠበቅብዎታል። በስተቀኝ በኩል በሚታየው መገናኛ መንገድ ላይ የመንገድ ዳር ምልክቶቹ እና የትራፊክ መስምር ምልክቶች እንደሚያመለክቱት በቀኝ በኩል ባለው መስመር ላይ ከሆኑ ወደ ቀኝ ብቻ መታጠፍ ይችላሉ፤ በግራ በኩል ባለው መስመር ላይ ከሆኑ ወደ ግራ መታጠፍ ወይም ቀጥታ በመገናኛ መንገዱ መሄድ ይችላሉ።



በግራ በኩል በሚታየው ሥዕላዊ መግለጫ ላይ ያሉት ምልክቶች እና የመንገድ ላይ ቅብ ምስሎች፣ ባለሁለት የግራ መታጠፊያ መስመሮችን ያካትታሉ። ከማንኛውም መስመር ወደ ግራ መታጠፍ ይችላሉ፤ ነገር ግን ከጎንዎ ያለው ሹፌር በተመሳሳይ ጊዜ ወደ

ግራ ሊታጠፍ ይችላል። በሚታጠፉበት ወቅት መስመሮችን አይቀይሩ፤ አለበለዚያ ከጎንዎ ካለው ሹፌር ጋር ሊጋጩ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ ከጎንዎ ያለው ሹፌር ወደ ሚታጠፉበት መንገድ እንዳይገባብዎት ይጠብቁ። እዚህ ያሉት ምልክቶች እና የመንገድ ላይ የቀብ ምልክቶች በቀኝ መስመር ላይ ከሆኑ ወደ ቀኝ መታጠፍ እንዳለቦት ያመለክታሉ። በግራ መስመር ላይ ክሆኑ ወደ ግራ መታጠፍ አለብዎት። በመሃል መስመር ላይ ከሆኑ፣ ወደ ግራ መታጠፍ ወይም በመገናኛ መንገዱ ቀጥታ መሄድ ይችላሉ።

የትራፊክ መብራት ምልክቶች እና የቁም ምልክቶች

በመገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶች ላይ ያልዎት ደህንነት በአብዛኛው የሚወሰነው በትራፊክ መብራት ምልክቶች ላይ በሚያዩዋቸው አረንጓዴ፣ ቢጫ እና ቀይ መብራቶች: ባለ ሁለት መንገድ እና ባለ አራት መንገድ የቁም ምልክቶች ላይ ባሎት ተገቢ ምላሽ አስጣጥ ላይ ነው።

ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ፣ የተሳሳተ መንገድ እና መግባት አይፈቀድም የሚሉ ምልክቶች

በከተሞች ውስጥ ያሉ ብዙ መንገዶች ባለ አንድ አቅጣጫ መንገዶች ናቸው። በመገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶች ላይ **ባለአንድ አቅጣጫ** የሚሉ ምልክቶችን ካዩ በአንድ (1) አቅጣጫ ብቻ የሚንቀሳቀስ መንገድ መሆኑን ማወቅ ይችላሉ። ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ መሆኑን የሚጦቅም ሌላው ፍንጭ በመንገድ ሁለቱም ጎኖች በኩል ወደ አንድ አይነት አቅጣጫ የቆሙ ተሽከርካሪዎች ሲያዩ ነው።

በአንድ ቦታ ላይ **ባለአንድ አቅጣጫ መንገድ (ONE WAY)** ምልክቶች፣ **የተሳሳተ መንገድ (WRONG WAY)** ምልክቶች እና **መግባት አይፈቀድም (DO NOT ENTER)** የሚሉ ምልክቶችን የመንገድ አካፋይ ካላቸው አውራ ጎዳናዎች ጋር በሚያቆራኙ መንገዶች ላይ ያያሉ። መሀል ላይ የተከፈሉ አውራ ጎዳናዎችን እንደ ሁለት (2) ባለአንድ አቅጣጫ መንገዶች አድርገው መመልከት ይችላሉ። አብዛኞቹ አውራ ጎዳናዎች በእያንዳንዱ አቅጣጫ የሚንቀሳቀሰውን ትራፊክ የሚለይ አካላዊ የሚከፋፍል ነገር አላቸው። ይህም ጠባብ የኮንክሪት ማገጃ ሊሆን ይችላል፤ ወይም ሰፊ በሲሚንቶ የተሰራ ማገጃ ወይም የሳር አካባቢ ሊሆን ይችላል። አብዛኛው ግዜ ወደ መገናኛው ሲቃረቡ በመንገድዎ ላይ **የተከፋፈለ አውራ ጎዳና (DIVIDED HIGHWAY)** የሚል ምልክት ያያሉ።

በተከፋፈለ አውራ ጎዳና ላይ ወደ ቀኝ መታጠፍ በማንኛውም ሌላ መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገድ ላይ ወደ ቀኝ ለመታጠፍ ከሚያደርጉት ነገር የተለየ አይደለም። ወደ ቀኝ ከመታጠፍዎ በፊት ከበስተግራዎ በኩል በሚመጣው የትራፊክ ፍሰት ውስጥ ደህንነትዎ በተጠበቀ ሁኔታ ለመቀጠል የሚያስችልዎት በቂ ክፍተት መኖሩን ያረጋግጡ።

በተከፋፈለ አውራ ጎዳና ላይ ወደ ግራ መታጠፍ ራሱ የቻለ ለየት ያለ አደጋ አለው። ወደ ተከፋፈለ አውራ ጎዳና (ሀይዌይ) እየዞሩ እንደሆነ ካላወቁ፣ ወደ አውራ ጎዳናውን ለሁለት የሚከፋፍለው ቦታ ከመድረስዎ በፊት ወደ ግራ ሊታጠፉ እና ከበስተግራዎ በኩል ከሚመጣው ትራፊክ ጋር ፊት ለፊት ሊጋጩ ይችላሉ። የ**መግባት የተከለከለ ነው (DO NOT ENTER)**እና **የተሳሳተ መንገድ (WRONG WAY)** የሚሉ ምልክቶችን ማስተዋል አለብዎት።

የመንገድ አካፋይ ባላቸው አውራ ጎዳናዎች በትክክለኛ መንገድ ወደ ግራ ለመታጠፍ ከግራዎ በሚመጣው ትራፊክ ውስጥ በቂ ክፍተት ሲኖር "የመጀመሪያውን" መንገድ መሻገር ያስፈልግዎታል፤ ከዚያም "ሁለተኛው" መንገድ ላይ በቀኝዎ ከሚመጣው ትራፊክ ውስጥ በቂ ክፍተት ሲኖር ከክፍትቱ ማዶ በግራ በኩል መታጠፍ ያስፈልግዎታል።

ወደ መገናኛ/መስቅለኛ መንገዶች ደህንነትዎ በተጠበቀ ሁኔታ መግባት እና ማሽከርከር

- **ባለሁለት መንገድ የማቆሚያ ምልክት ያለበትን መገናኛ ለመሻገር -** በሰዓት 30 ማይል በሚያሽከረክሩበት መንገድ ላይ ለመሻገር በሁለቱም አቅጣጫዎች የ6 ሰከንድ ክፍተት ወይም ወደ ቀኝ እና ወደ ግራ አንድ ብሎክ የሚሆን ክፍት ቦታ ያስፈልግዎታል። በማቆሚያ ምልክት ላይ በመጀመሪያ በግራ በኩል ይመልከቱ፤ ከዚያ አስተማማኝ ክፍተት ለማግኘት ወደ ቀኝዎ ይመልከቱ፤ ከዚያም ከመቀጠልዎ በፊት በፍጥነት እንደገና ወደ ግራዎ ይመልከቱ።
- **ወደ ቀኝ ለመታጠፍ -** ምንም የሚመጣ ተሽከርካሪ እንደሌለ ለማረጋገጥ ወደ ግራ፣ ቀጥታ ወደፊት፣ ወደ ቀኝ እና ከዚያም እንደገና ወደ ግራ አቅጣጫ ይመልከቱ። በእርስዎ እና በግራ በኩል በሚመጣ ማንኛውም ተሽከርካሪ መካከል የስምንት (8) ሰከንድ ያህል ርቀት እንዲኖር ያድርጉ።
- **ወደ ግራ ለመታጠፍ -** ከሚመጣው የትራፊክ ፍሰት ፊት ለፊት ለመታጠፍ በቂ የሆነ ክፍት ቦታ እንዳለ እና በተቃራኒው መንገድ ላይ ያለው ትራፊክ ፍሰት ደግሞ መቆሙን ያረጋግጡ። ከትንሽ መንገድ ወደ ትልቅ ጎዳና እየታጠፉ ከሆነ ከቀኝዎ በኩል ከሚመጣው ማንኛውም ተሽከርካሪ ጋር ቢያንስ የ9 ሰከንድ ርቀት ይፍጠሩ።

ወደ ግራ በሚታጠፉበት ጊዜ ከተቃራኒ አቅጣጫ ወደ ግራ ከሚታጠፉ ተሽከርካሪዎች ጋር ሊከሰት የሚችል ግጭትን ማስወገድ እጅግ አስፈላጊ ነው። በቀኝ በኩል ባለው ስዕላዊ መግለጫ ላይ በመስቀለኛ መንገድ መሃል ላይ ያለውን "X"ን ይመልከቱ። "X" ላይ ከመድረስዎ በፊት በመታጠፍ ከሌላው ወደ ግራ ከሚታጠፍ አሽከርካሪ ጋር ሊከሰት የሚችል "መንገድ መዘጋጋት" ያስቀራሉ። ሁልጊዜ ወደ መሀል መስመር በጣም ቅርብ በሆነው መስመር ላይ በመታጠፍ የትራፊክ ፍሰትን ከማቋረጥ እና በተመሳሳይ መንገድ ላይ ወደ ቀኝ እየታጠፍ ያለ ከተቃራኒ አቅጣጫ ከሚመጣ ትራፊክ ጋር ከመጋጨት ይድናሉ።



በጣም አስፈላጊው፡ ሁሉንም መሻገር የሚጠበቅብዎት መስመሮች ክፍት እስኪሆኑ ድረስ እና የመታጠፍ ሂደትዎን በሰላም ማጠናቀቅ እንደሚችሉ እርግጠኛ እስኪሆኑ ድረስ ወደ ግራ መታጠፍ አይጀምሩ።



- **ጀግሃንድልስ፦** በተጨናነቁ የንግድ አካባቢዎች ያሉ አንዳንድ መንገዶች በተቃራኒ አቅጣጫ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን የሚከፋፍል አካላዊ ማገጃ አላቸው፤ እንዲሁም የትራፊክ መብራት በበራባቸው መሰቀልኛ መንገዶች ላይ **ወደግራ መዞር የተከለከለ ነው (NO LEFT TURN)** ወይም **ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ መዞር (NO U-TURN) የተከለከለ ነው** እና **ሁሉም ከቀኝ መስመር መታጠፍያዎች (ALL TURNS FROM RIGHT LANE)** የሚሉ ምልክቶች ይኖራቸዋል። በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ መንገዱ ወደ ግራ አቅጣጫ መታጠፊያዎች ለማዘጋጀት ጀግሃንድል ሊነድፍ(ሊሰራ) ይችላል። በተቃራኒ ትራፊክ ቀጥታ በግራ በኩል ከማቋረጥ ይልቅ፣ ወደ ቀኝ የሚታጠፍ መስመርን ይጠቀሙ፤ ከዚያም ወደ ኋላ በመጠምዘዝ በትራፊክ መብራት ዋናውን መንገድ ይገናኙ ከዚያም ወደ ግራ ይታጠፉ።
- **ክብ መስቀለኛ መንገዶች -** ክብ አደባባዮች እና የትራፊክ ክበቦች የትራፊክ ፍሰት በተቃራኒ ሰዓት አቅጣጫ የሚንቀሳቀስባቸው ክብ መገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገዶች ናቸው፤ ስለዚህ ወደ ክበቡ የሚደረጉ መታጠፎች (መዞር) እና ከክበቡ የሚወጡት መታጠፎች (መዞር) ወደ ቀኝ በኩል የሚደረጉ ናቸው። ይህ የፊት ለፍት ግጭቶችን፣ ወደ ግራ ሲታጠፉ የሚከሰቱ ግጭቶችን እና የቀኝ አንግል ግጭቶችን ያስቀራል። ምንም እንኳን ክብ አደባባዮች ከትራፊክ ክበቦች ጋር የሚመሳሰሉ ቢሆኑም የሚለዩዋቸው ልዩ ህጎች እና ልዩ ንድፍ ግን አሏቸው።

  በደህንነታቸው እና በአሰራራቸው ምክንያት እነዚህ አይነት ክብ ማዞርያዎች (ራውንድባውት) ትላልቅና ያረጁ እንዲሁም በከፍተኛ ፍጥነት የሚሽከረከሩ የትራፊክ ክበቦችን እየተተኩ ሲሆን ወይም በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ የትራፊክ መብራት ምልክቶች ካላቸው መገናኛዎች ይልቅ እየተተከሉ በመሆኑ ክብ ማዞርያዎች (ራውንድባውት) እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ላይ ትኩረት እናደርጋለን። ክብ ማዞርያዎች (ራውንድባውት) አንዳንድ ጊዜ በራምፕ ኢንተርቸንጅ መጨረሻ ላይ ይሰራሉ።

  ክብ ማዞርያዎች (ራውንድባውት) በእያንዳንዱ የመግቢያ ነጥብ ላይ **ቅድሚ ይስጡ (YIELD)** የሚሉ ምልክቶች እና በእያንዳንዱ መግቢያ ላይ በተነጠፈው አስፋልት ላይ የተቀቡ የማለፊያ መስመሮች አሏቸው። አብዛኛዎቹ ክብ ማዞርያዎች (ራውንድባውት) እያንዳንዱ መውጫ መንገድ የት እንደሚወስድዎት እንዲያውቁ የሚረዱ የመዳረሻ ምልክቶች አሏቸው።



> **ይህን ያውቁ ኖሯል?**
>
> በክብ ማዞርያዎች (ራውንድባውት) ላይ የሚከሰቱ የመንገድ አደጋዎች ዋነኛ ምክንያት አሽከርካሪዎች ወደ ማዞርያ ከመግባታቸው በፊት ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት ባለመቻላቸው ነው።

ክብ መስቀለኛ መንገዶች አጠቃቀም

መጠጋት እና መግባት፦

1. ወደ ክብ አደባባዩ ሲቃረቡ ፍጥነትዎን ይቀንሱ፤ እንዲሁም በእግረኛ ማቋረጫ ላይ ላሉ እግረኞች ቅድሚያ ለመስጠት ዝግጁ ይሁኑ።
2. እስከ የተሽከርካሪዎች ማቆሚያ መስመር ድረስ ይምጡ፤ ወደ ግራ ይመልከቱ፤ እና በክብ አደባባዩ እየተዘዋወረ ያለ ተሽከርካሪ መኖሩን እና አለምኖሩን ያረጋግጡ፤ ቀድሞውኑ በአደባባዩ ላሉ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ ይስጡ።
3. በትራፊክ ፍሰቱ ውስጥ በቂ ክፍት ቦታ ሲኖር ወደ አደባባዩ ውስጥ ይግቡ።

ከክብ አደባባዩች መውጣት፦

1. ወደ ክብ መንገዱ ከገቡ በኋላ መውጫዎ ላይ ለመድረስ በግራ በኩል ያለውን መስመር ተከትለው ይሂዱ። አሁን ቅድሚያ የማለፍ መብት አለዎት።
2. ወደ መውጫዎ ሲቃረቡ፣ የቀኝ አቅጣጫ ጠቋሚ መብራትዎን ያብሩ።
3. በእግረኛ ማቋረጫ ላይ እግረኞች መኖራቸውን እና አለመኖራቸውን ይቃኙ፤ እንዲሁም ቅድሚያ ለምስጠት ዝግጁ ይሁኑ።
4. ከክብ አደባባዩ ይውጡ።

ለሚከተሉ ነገሮች ዝግጁ ይሁን፦

የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች - የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች በሚቃረቡበት ወቅት ወደ አደባባዩ አይግቡ፤ ይልቁንስ ወደ ጎን በማቆም ያሳልፉ። ቀድሞውኑ አደባባዩ ውስጥ ከሆኑ ወዲያውኑ ከአደባባዩ በመውጣ ወደ ጎን በመሄድ ያቁሙ። በክብ አድባብይ ዉስጥ መቆም በፍጹም አይፈቀድም።

ብስክሌተኞች - ክብ መንገዶችን (ራውንድባውት) በሚጠቀሙበት ጊዜ ብስክሌተኞች እንደ ተሽከርካሪ ወይም እንደ እግረኛ ሆነው መንቀሳቀስ ይችላሉ። እንደ ተሽከርካሪ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ፣ ተመሳሳይ ደንቦችን ይከተላሉ። በክብ አደባባይ (ራውንድባውት) ውስጥ እንደ ተሽከርካሪ ሆኖ እየተንቀሳቀሰ ያለን ብስክሌተኛን ለማለፍ በፍጹም እንዳይሞክሩ።

እግረኞች - አሽከርካሪዎች ወደ ክብ አደባባዮች (ራውንድባውት) ሲገቡ ሆነ ሲወጡ ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። እግረኞች በተዘጋጁት የእግረኛ ማቋረጫዎች እና የመንገድ አካፋይ ደሴቶችን (Splitter Island) በመጠቀም የእያንዳንዱን ክብ መንገድ ክፍል መሻገር ይችላሉ።

ኩርባዎች ላይ በአግባቡ ማሽከርከር

ኩርባዎችን በተመለከተ ሊረዱት የሚገባው በጣም አስፈላጊው ነገር የፊዚክስ ህጎችን ማሸነፍ እንደማይችሉ ነው። ተሽከርካሪዎች በጣም ከፍተኛ የሆነ ክብደት አላቸው፤ እንዲሁም የመንቀሳቀስ አቅማቸው ከፍተኛ ነው። ይህም ማለት ኩርባዎች ላይ በጣም በፍጥነት እየነዱ ከሆነ፣ ምንም ያህል ለማዞር ቢሞክሩ ወይም በመስመርዎ (ሌይንዎ) ውስጥ ለማቆየት ፍጥነትዎን ቢቀንሱም ተሽከርካሪዎ በኩርቢያ መንገዱ ከመቆየት ይልቅ ቀጥታ ወደፊት መሄዱን ይቀጥላል። ወደ ግራ በሚታጠፍ ኩርባ መንገድ ላይ ከነበሩ ከመንገድ ይወጣሉ፤ ወይም ወደ ቀኝ በሚታጠፍ ኩርባ ከነበሩ ደግሞ ወደ ሌላ የተሽከርካሪ መስመር ውስጥ ይገባሉ። ይህ እንዲሆን የግድ በከፍተኛ ፍጥነት መንዳት አይጠበቅብዎትም። ኩርባው ሹል በሆነ ሁኔታ የሚታጠፍ ከሆነ እና መንገዱ እርጥብ ከሆነ ወይም በረዷማ ከሆነ ፍጥነትዎን በአስቸኳይ በእጅጉ መቀነስ አለብዎት።

የታዳጊ ወጣቶች የትራፊክ አደጋ እውነታ
በፔንሲልቬንያ ውስጥ በ16 አመት ታዳጊ ወጣት አሽከርካሪዎች ዘንድ በብዛት የሚከሰተው አደጋ **አንድ ተሽከርካሪ ብቻውን ከሌላ ተሽከርካሪ ጋር ሳይጋጭ ከመንገድ የመውጣት አደጋ ነው።** እ.ኤ.አ. ከ2013 እስከ 2017፣ 3,291 አደጋዎች የደረሱ ሲሆን፣ 20 ሰዎች ደግሞ ሕይወታቸውን አጥተዋል።

ፎቶው የቀረበው በ በፔንስልቬንያ ስቴት ፖሊስ ነው።

በኩርቢያዎች ላይ የተሽከርካሪዎን ቁጥጥርን ለመጠበቅ ፍጥነትዎን መቀነስ አለብዎት። ይህንንም ማድረግ ያለብዎት ወደ ኩርባ (ማዞርያ) ከመድረስዎ በፊት ነው።

ወደ ኩርባው (መታጠፊያው) ሲቃረቡ መንገዱ እንዴት እንደሚታጠፍ የሚያሳይ ቢጫ የአልማዝ ቅርጽ ያለው የማስጠንቀቂያ ምልክት ያያሉ። መንገዱ በ90 ዲግሪ አንግል የሚታጠፍ ከሆነ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ የሚያመለክት ትልቅ ቀስት ያለው አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው ቢጫ ምልክት ሊያዩ ይችላሉ። አንዳንድ ሹል ኩርባዎች በመታጠፊያው በሙሉ የሚቀመጡ የቼቭሮን የማስጠንቀቂያ ምልክቶችም አሏቸው፤ እነዚህም በሌሊት ወይም ለማየት አስቸጋሪ በሆነ የአየር ሁኔታ ውስጥ በጣም ጠቃሚ ናቸው። በምዕራፍ 2 ላይ የሚታዩትን የተለያዩ የኩርባ መንገዶች ማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ደግመው ያንብቡ።

በኩርባዎች ውስጥ በአስተማማኝ ሁኔታ እንዴት ማሽከርከር እንደሚችሉ እነሆ፡-

1. በቀኝ ኩርባዎች ላይ በሚሆኑበት ግዜ ከመንገዱ የመሀል መስመር ወደ ቀኝ በኩል በመሆን ይንዱ፣ እንዲሁም በግራ ኩርባዎች በሚሆኑብት ግዜ ደግሞ በሌኑ መሀል ላይ ይዘው ይንዱ።
2. ኩርባው በጠነከረ (ሹል በሆነ) ቁጥር ፍጥነትዎን የበለጠ መቀነስ ያስፈልግዎታል።
3. ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣውን ትራፊክ ልብ ይበሉ። በፍጥነት እየነዳ ያለ ሰው በቀላሉ ወደ መስመርዎ ሊገባ ይችላል።
4. ተሽከርካሪዎን እንዴት ማሽከርከር እንደሚችሉ መመሪያ ለማግኘት ወደ ፊት ይቃኙ፣ እና የኩርባውን ውስጣዊው ጠርዝ ይመልከቱ። ብዙ ኩርባዎች ካሉ፣ በተቻለ መጠን ወደፊት በመመልከት የእያንዳንዱን ኩርባ ውስጣዊ ጠርዝ ይመልከቱ።



አውራ ጎዳናዎች ላይ እና የድልድይ መንገዶች ላይ ስለማሽከርከር

በአውራ ጎዳናዎች ላይ ተሽከርካሪዎች በከፍተኛ ፍጥነት ስለሚንቀሳቀሱ በአውራ ጎዳናዎች ላይ የሚከሰቱ አደጋዎች በጣም የከፋ ናቸው። በአውራ ጎዳና መገናኛዎች ላይ መስመር በሚቀይሩበት ጊዜ እና በትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት ባልተጠበቀ ሁኔታ ተሽከርካሪዎች ፍጥነት ሲቀንሱ ወይም ሲቆም ከፍተኛ አደጋ ሊያጋጥምዎት ይችላል።

ወደ አውራ ጎዳናዎች መግባት

ወደ አውራ ጎዳና ሲገቡ ማድርግ ያለብዎት የመጀመሪያው ወሳኝ ነገር በስህተት ወደ መውጫ ራምፕ አለመግባትዎን እና ከሌላ ትራፊክ ፍሰት ጋር ፊት ለፊት እንዳይጋጩ መጠንቀቅ ነው። መውጫ ራምፕ ላይ **ባለ አንድ አቅጣጫ መንገድ (ONE WAY)** ምልክቶች እንዲሁም **DO NOT ENTER** እና **WRONG WAY** የሚሉ ምልክቶች ይኖሩታል። ሁሌም ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ፣ መግቢያው ላይ **ሀይዌይ መግቢያ (HIGHWAY ENTRANCE)** የሚል አረንጓዴ ምልክት ይኖረዋል። በቀኝዎ በኩል ነጭ መስመር ካዩ እና በግራዎ በኩል ደግሞ ቢጫ መስመር ካዩ፣ ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ እያመሩ ነው ማለት ነው።

አንዳንድ የአውራ ጎዳና መግቢያዎች እና መውጫዎች እርስ በርሳቸው በጣም በቅርብ ርቀት የሚገኙ ሲሆን በመካከላቸውም አጭር “መንገድ የማቋረጫ መስመሮች (weaving lane)” ብቻ ነው ያላቸው። ወደ አውራ ጎዳና የሚገቡ እና የሚወጡ ተሽከርካሪዎች የማቋረጫ መስመሩን (weaving lane) በጋራ መጠቀም አለባቸው። በተመሳሳይ ጊዜ ተመሳሳይ ቦታ ለመጠቀም በሚፈልጉ ሁለት (2) አሽከርካሪዎች ምክንያት አደጋ ሊከሰት ይችላል። ወደ አውራ ጎዳና እየገቡ ከሆነ፣ ለመውጣት ለሚፈልጉት አሽከርካሪዎች ቦታውን ቅድሚያ መስጠት አለብዎት። ወደ አውራ ጎዳናዎች ለመግባት የሚያገለግሉ መንገዶች (ሀይዌይ ራምፕ) ብዙውን ጊዜ የፍጥነት መጨመሪያ የመንገድ መስመሮች አሏቸው። እነዚህ መስመሮችም ከዋናው መንገድ መስመሮች ጎን ለጎን በመሆን የሚሄዱ ናቸው፤ እና ወደ ዋናው የአውራ ጎዳና መንገድ ከመግባትዎ በፊት ከትራፊክ ፍሰት ፍጥነት ጋር እኩል ፍጥነት እንዲኖርዎት የሚያስችሉ ለመሆነ ረጅም መሆን አለባቸው። በአውራ ጎዳና መግቢያ ራምፕ ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ክፍተት ማግኘት ሲፈልጉ ወደ ጎንዎ እና የጎን መስታወትዎን ይመልከቱ።

ከአውራ ጎዳናዎች መውጣት

ለመውጣት ሲፈልጉ ለመውጣት ወደሚያስችሎት መስመር ቀደም ብለው ይግቡ። ወደ መውጫው መስመር እስክትገቡ ድረስ ፍጥነትዎን አይቀንሱ። የመውጫ መንገድዎ ካመለጥዎት፣ ቀጥሎ ያለውን መውጫ መንገድ ይጠቀሙ። በአውራ ጎዳናዎች ላይ መቆም ወይም ወደ ኋላ መመለስ አይፈቀድም። በመጨረሻው ሰከንድ ላይ ወደ መውጫው መንገዱ ለመሄድ ብለው ብዙ መስመሮችን በቅጽበት አቋርጠው ለመሄድ አይሞክሩ። ለመዞር ሲፈልጉ መንገዱን የሚከፍለውን ቦታ አቋርጠው ለመሄድ አይሞክሩ። እነደዚህ ያሉ የማሽከርከር ልምዶች ህገ ወጥ ከመሆናቸውም በላይ ለጤናዎ እና ለደህንነትዎ በጣም አደገኛ ናቸው። ከአውራ ጎዳናዎች የሚያስወጡ የመውጫ መንገዶች (ኤክዚት ራምፕ) መንዳት የሚቻልበት የፍጥነት ገደብ የሚግልፁ የማስጠንቀቅያ ምልክቶች አሏቸው።

በአውራ ጉዳናዎች ላይ ማሽከርከር

በአውራ ጎዳናዎች ላይ ከሚደርሱ ገዳይ አደጋዎች ውስጥ ግማሹ የሚሆኑት በፍጥነት እና/ወይም በአሽከርካሪ ድካም ምክንያት ከመንገድ የወጡ ተሽከርካሪዎችን ያካትታሉ፤ - **65 ማይል በሰዓት ማለት በሰከንድ 100 ጫማ (ፊት) ማለት ነው፤ ይህም ከመንገድ ለመውጣት ከአንድ (1) ሰከንድ ያነሰ ጊዜ ይፈጃል ማለት ነው።**

በአውራ ጎዳና (ሀይዌይ) ላይ ቀስ ብሎ የሚንቀሳቀስ ተሽከርካሪን ለማለፍ መስመር ሲቀይሩ በአንድ ጊዜ አንድ (1) መስመር ብቻ ይቀይሩ፤ እንዲሁም መስመር በቀየሩ ቁጥር የማዞሪያ ምልክትዎን ይጠቀሙ፤ ሌሎች አሽከርካሪዎች ምልክቱን እንዲያዩት አስቀድመው ምልክቱን ለበቂ ጊዜ ያህል ያብሩ።

አንድ ተሽከርካሪ ከመግቢያው ወደ አውራ ጎዳናው ሊገባ ሲል ካዩ አሽከርካሪው በቀላሉ ወደ አውራ ጎዳናው እንዲገባ ለማድረግ መስመር መቀየር የተለመደ ጥሩ ተግባር ነው። ምንም እንኳን ወደ አውራ ጎዳናው የሚገባው አሽከርካሪ ለእርስዎ ቅድሚያ መስጠት ግዴታው ቢሆንም እሱ እንዲገባ መስመር መልቀቅዎ የትራፊክ ፍሰት በተቀላጠፈ እንዲቀጥል ያደርጋል። ነገር ግን መስመር ከመቀየርዎ በፊት በተሽከርካሪዎ ዙሪያ ትራፊክ ክፍት መሆንኑን ያረጋግጡ።

በአውራ ጎዳናዎች ላይ በሚያሽከረክሩበት ወቅት ሌላው አደጋ “የሀይዌይ ሂፕኖሲስ (በአውራ ጎዳናዎች ላይ የሚከሰት የመፍዘዝ ስሜት)” ምክንያት ትኩረት ማጣት ነው፤ ይህም የሚከሰተው በመንገዱ ላይ ለረጅም ጊዜ በቀጥታ ወደ ፊት ሲያዩ እና ከፊት፣ ከኋላ እና ከተሽከርካሪዎ አካባቢ በንቃት መቃኘትን ሲያቆሙ ነው። በዚህ መንገድ "በሀሳብ መፍዘዝ (zone out)" ከሆኑ፣ ከፊት ለፊትዎ ፍጥነት እየቀነሰ ወይም በመቆም ላይ ካለ ትራፊክ ጋር ሊጋጩ ይችላሉ። በአውራ ጎዳናዎች ላይ ከሚከሰቱ ገዳይ አደጋዎች ውስጥ 20 በመቶ የሚሆኑት ከፊት ለፊት ያለ ተሽከርካሪ ጀርባ ጋር የሚፈጠሩ ግጭቶች ናቸው። ለእነዚህ የትራፊክ አደጋዎች ዋነኛዎቹ መንስኤዎች የአሽከርካሪው ትኩረት ማጣት እና በቅርብ ርቀት በመሆን መንዳት ናቸው።

ተሽከርካሪ ማቆም

ያሉበት መንገድ የመንገድ ጠርዝ ካለው፣ ተሽከርካሪዎን ሲያቆሙ ከመንገድ ጠርዙ ከ12 ኢንች በማይበልጥ ርቀት ውስጥ ያቁሙ። የመንግድ ጠርዝ ከሌለው በተቻለ መጠን ከመንገዱ ራቅ ብለው ያቁሙ።

በመንገድ ላይ ማቆም ሲኖርብዎት የአደጋ ጊዜ መብራቶን ይጠቀሙ፤ እና ለሚያልፉ ተሽከርካሪዎች በቂ ቦታ ይስጡ። ተሽከርካሪዎ በሁለቱም አቅጣጫ ቢያንስ በ 500 ጫማ (ፊት) ርቀት ላይ በግልጽ መታየት መቻሉን ያረጋግጡ።

ሁልጊዜ መኪናዎን የትራፊክ ፍሰት በሚሄድበት አቅጣጫ ያቁሙ። ተሽከርካሪዎ እንደማይንቀሳቀስ ያረጋግጡ። መኪናዎ አውቶማቲክ ማርሽ ካለው፣ የመኪና የማቆሚያ ፍሬኑን ጎትተው "ፓርክ" ላይ ያድርጉት፤ መኪናዎ በእጅ የሚቀየር ማርሽ ካለው (ማኑዋል ከሆን) "የኋላ ማርሽ ላይ" ወይም "አንደኛ" ማርሽ ላይ ያድርጉት። በዳገታማ መንገድ ላይ መኪናዎን ያቆሙ ከሆነ፣ የመኪናዎን መሪ በምስሉ ላይ እንደሚታየው ያዙሩ። ተሽከርካሪዎን ቁልቁለት ላይ በሚያቆሙበት ጊዜ መንገዱ ጠርዝ ቢኖረውም ባይኖረውም፣ ጎማዎችዎ ሙሉ



ተሽከርካሪዎን ኮረብታማ ቦታ ላይ እንዴት ማቆም እንዳለብዎት

በሙሉ ወደ ቀኝ እንዲሆኑ መሪውን ማዞር አለብዎት።

ድንገተኛ አደጋ ካልተከሰተ ወይም የፖሊስ መኮንን ካላዘዘዎት በስተቀር መኪናዎን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ቦታዎች ላይ በጭራሽ አያቁሙ፣ አያስቀምጡ ወይም ፓርክ አያድርጉ፦

- ቀድሞውኑ በመንገድ ዳር ላይ ከቆሞ ወይም ፓርክ ከተደረገ ተሽከርካሪ ጎን መንገድ ላይ ፓርክ ማድረግ (ድርብ ፓርኪንግ)።
- እግረኛ መንገድ ላይ።
- በመገናኛ ወይም መስቀለኛ መንገድ ላይ።
- የእግረኛ መሻገርያ መንገድ ላይ።
- ከየትኛውም የመንገድ ቁፋሮ ወይም የስራ ቦታ አጠገብ ወይም በተቃራኒው አቅጣጫ ላይ።
- በማንኛውም ድልድይ ወይም ሌላ ከፍ ያለ መዋቅር ወይም በሀይዌይ የዋሻ መንገድ ውስጥ።
- በማንኛውም የባቡር ሀዲድ ላይ።
- ተሻጋሪ መንገዶችን ጨምሮ፣ ለሁለት በተከፈሉ ባለሁለት አቅጣጫ ሀይዌይ መንገዶች መካከል ላይ።
- የባቡር መሻገሪያ ከሚገኝበት ቦታ ከባቡር ሀዲዱ 50 ጫማ ርቀት ውስጥ።
- መኪና ማቆም የተከለከለ ነው የሚል ኦፊሴላዊ ምልክት ባለበት በማንኛውም ቦታ።
- መቆም የተከለከለ ነው የሚል ኦፊሴላዊ ምልክት ባለበት በማንኛውም ቦታ።
- በሕዝብ ወይም በግል የመኪና መግቢያ መንገድ ፊት ለፊት።
- ከእሳት ማጥፊያ ቱቦ (ፋየር ሃይድራንት) በ15 ጫማ (ፊት) ርቅት ውስጥ።
- መንገዶች በሚገናኙበት ቦታ ላይ ካለው የእግረኛ መንገድ በ20 ጫማ (ፊት) ርቀት ውስጥ።
- መንገድ ዳር ላይ በሚገኝ ማንኛውም የሚያበራ የትራፊክ መብራት፣ የማቆሚያ ምልክት፣ የመተላለፊያ ምልክት ወይም የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያ በ30 ጫማ (ፊት) ርቀት ውስጥ።
- ከእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ መኪና መግቢያ በር በ 20 ጫማ (ፊት) ርቀት ዉስጥ።
- ተሽከርካሪዎ ስትሪትካር (streetcar) በነፃነት እንዳይንቀሳቀስ በሚያግድበት ቦታ ላይ።
- ኦፊሴላዊ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ካልፈቀዱውልዎት በስተቀር በተገደቡ መዳርሻ ያላቸው አውራ ጎዳና ላይ።

በትይዩ መኪና የማቆም (ፓራለል ፓርኪንግ) ጠቃሚ ምክሮች

በቀኝ በኩል በሚገኝ የእግረኛ መንገድ ጠርዝ ጎን እንዴት መኪና ማቆም እንደሚቻል ከታች ባሉ ምስሎች በዝርዝር ተብራርቷል።



1. ተሽከርካሪዎ ከፊት ካለው ተሽከርካሪ ጋር ትይዩ በማድረግ የሁለት ጫማ ርቀት ጠብቀው ያቁሙ።
2. መሪውን በደንብ ወደ ቀኝ አዙረው ከኋላዎ ወዳለው መኪና እስኪጠጉ ድረስ ቀስ ብለው ወደ ኋላ ይንዱ።
3. የፊት በርዎ ከፊት ካለው መኪና የኋላ መከላከያ ጋር እኩል ከሆነ በኋላ መሪዎን በፍጥነት ወደ ትክክለኛ ቦታው በመመለስ ወደ ኃላ መመለስ ይችላሉ።
4. ከፊት ያለውን መኪና ካለፉ በኃላ መሪውን በደንብ ወደ ግራ ያዙሩና በቀስታ ወደ ኋላ ወዳለው መኪና ይመለሱ።
5. መሪዎን በደንብ ወደ ቀኝ በማዞር ተሽከርካሪዎን ወደ መኪና ማቆሚያው ቦታ መሃል ይንዱ።

ያሉበት መንገድ የመንገድ ጠርዝ ካለው፣ ተሽከርካሪዎን ሲያቆሙ ከመንገድ ጠርዙ ከ12 ኢንች በማይበልጥ ርቀት ውስጥ ያቁሙ። ምንም የመንገድ ጠርዝ ከሌለ፣ በተቻለ መጠን ከዋናው መንገድ ራቅ ብለው ተሽከርካሪዎን ያቁሙ።

ተሽከርካሪዎን ትተው ከመሄድዎ በፊት፣ ኢንጅኑን ያጥፉ፤ ቁልፉን ያውጡት እንዲሁም ሁሉንም በሮች ይቆልፉ። ከመውጣትዎ በፊት ከኋላዎ ያለውን ትራፊክ ይመልከቱ።

የእኛን ማለትም የፔንዶትን (PennDOT) ትይዩ የመኪና ማቆሚያ ማሰልጠኛ ቪዲዮ ለመመልከት የሚከተለውን ሊንክ ይጫኑ።

https://www.youtube.com/watch?v=iZs-q6PmC7E

የተለዩ ሁኔታዎች እና ድንገተኛ ሁኔታዎች

የሚከተሉት ገጾች በአስተማማኝ ሁኔታ እንዴት መንዳት እንደሚችሉ እና በእነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ውስጥ - በአውራ ጎዳና የሥራ ቀጠናዎች፣ በባቡር መሻገሪያዎች፣ እና እግረኞችን፣ ብስክሌተኞችን፣ የጭነት መኪናዎችን፣ አውቶቡሶችን ወይም የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎችን ሲያጋጥሙዎት - እንዲሁም የመንገድ ቁጣን እና የተለያዩ የአደጋ ጊዜ አደጋዎችን መቋቋም ሲኖርብዎት ለአደጋ የመጋለጥ እድልዎን እንዴት እንደሚቀንሱ መረጃ ይሰጡዎታል ።

ስለ ልዩ ሁኔታዎች እና ድንገተኛ አደጋዎች መረጃ ለአሽከርካሪዎች ጉዞአቸውን እንዲያቅዱ ይጠቅማል። አንድ አሽከርካሪ የማይፈለጉ መዘግየቶችን ወይም አደገኛ የመንገድ ሁኔታዎችን ለማስወገድ ከመነሳቱ በፊት መንገዱ ክፍት መሆኑን ለማረጋገጥ እንደ www.511PA.com ያሉ ሚዲያዎችን መመልከት ይችላል።

የስራ ቀጠናዎች

የስራ ቀጠናዎች ማለት የግንባታ፣ የጥገና ወይም የመገልገያ ሥራ የሚከናወንባቸው ቦታዎች ሲሆኑ እንደ ኮኖች ባሉ ብርቱካናማ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ወይም ሌሎች ጊዜያዊ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ይታወቃሉ። ትራፊክን (የተሽከርካሪዎች ፍሰትን) የሚመራ እና አንጸባራቂ ልብስ የለበሰ ምልክት የሚሰጥ የመንገድ ጠባቂ ሊያጋጥምዎት ይችላል። የማስጠንቀቂያ ምልክቶች፣ አስቀድሞ የማስጠንቀቂያ ተሽከርካሪዎች ወይም ተለዋዋጭ መልእክት ሰሌዳዎች ወደ ሥራ ቦታው ከመድረሳቸው ቢያንስ 200 ጫማ ርቀት ላይ ሊቀመጡ ይችላሉ። የመጀመሪያውን ምልክት ሲመለከቱ ለመንገዱ፣ ለተሽከርካሪዎች፣ ለመሳሪያዎች እና ሊያገኟቸው ለሚችሉ ሰዎች ጥንቃቄ የተሞላበት ትኩረት ይስጡ። አንዳንድ የስራ ቀጠናዎች በፔንስልቬንያ የፖሊስ አባላት ይታጀባሉ።

እንደ መስመር መቀባት፣ ስንጥቅ መሙላት እና ሣር ማጨድ ያሉ ተንቀሳቃሽ ስራዎች ከፊት የስራ ቦታ እንዳለ ለአሽከርካሪዎች ለማስጠንቀቅ እና ለሰራተኞቹ ጥበቃ ለመሆን ከስራው ጀርባ ላይ መከለያ ተሽከርካሪዎችን ምልክት ሰጪ እንዲሆኑ ይጠቀማሉ። መመሪያ ካልተሰጥዎት በስተቀር ተንቀሳቃሽ ሥራዎችን አይለፉ።

ይህን ያውቁ ኖሯል?

በአሜሪካ በየዓመቱ በአማካይ 40,000 ሰዎች የሀይዌይ ሰራተኞችን እና አሽከርካሪዎችን ጨምሮ በስራ ቀጠናዎች ላይ በደረሱ የመኪና አደጋዎች ይጎዳሉ ወይም ይሞታሉ።

በስራ ቀጠናዎች ውስጥ ለሚከሰቱ የሞት አደጋዎች ግድየለሽነት እና ከልክ በላይ ፍጥነት ዋና ምክንያቶች ናቸው።

ንቁ የስራ ቀጠናወይም በስራ ላይ ያለ የስራ ቀጠና ማለት ሰራተኞች በመንገድ ላይ ወይም በአቅራቢያው ያሉበት ነው። **ሁልጊዜ ለግንባታ ሰራተኞች ይጠንቀቁ** እና እንደ ጠባብ መስመሮች፣ ያልተስተካከለ ንጣፍ፣ ያልተስተካከሉ መስመሮች እና ድንገተኛ የመንገድ መስመር ለውጦች ላሉ ያልተለመዱ ሁኔታዎች ዝግጁ ይሁኑ።

አሽከርካሪዎች በስራ ቀጠናዎች ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች እና የግንባታ ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። በህጉ መሰረት፣ በእነዚህ ቦታዎች በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የቀን መብራቶችን ብቻ ሳይሆን የተሽከርካሪዎን የፊት መብራቶች ማብራት ይጠበቅብዎታል። በንቁ (በአገልግሎት ላይ ባለ) የሥራ ቀጠና ላይ የፊት መብራቶችዎን ባለማብራትዎ ምክንያት የገንዘብ መቀጮ ሊጣልብዎት ይችላል። በተጨማሪም፣ በንቁ የሥራ ቀጠናዎች ላይ ከልክ በላይ ፍጥነትን ጨምሮ ለአንዳንድ ጥሰቶች የሚጣለው ቅጣት በእጥፍ ይጨምራል። በተጨማሪም አንዳንድ ጥሰቶች የመንጃ ፈቃድ እንዲታገድ ያደርጋሉ።

በስራ ቀጠናዎች ውስጥ እና አካባቢውን በአስተማማኝ ሁኔታ ስለ መንዳት የሚያሳይ አዲስ ቪዲዮ በሚከተለው አድራሻ ይገኛል https://www.penndot.gov/TravelInPA/Safety/TrafficSafetyAndDriverTopics/WorkZone ላይ ይገኛል።

ይህ ቪዲዮ ለትምህርት ቤት ተኮር የአሽከርካሪዎች ትምህርት ኮርሶችም ይገኛል።

ወደ ሥራ ቀጠና ሲቃረቡ ፍጥነቱ ቀነስ ላለ ወይም ለቆመ ትራፊክ (የተሽከርካሪዎች ፍሰት) ዝግጁ ይሁኑ፣ እና እነዚህን የደህንነት ደንቦች ይከተሉ፦

- ጉዞዎን ያቅዱ። በስራ ቀጠናው አካባቢ ያለ ሌላ አማራጭ መንገድ ከመረጡ የጉዞ መዘግየትን ማስቀረት ይችላሉ።
- በስራ ቀጠናዎች ውስጥ የክሩዝ መቆጣጠሪያዎን አይጠቀሙ።
- የተከታታይ ተሽከርካሪዎች ርቀትዎን እጥፍ ያድርጉ፣ በስራ ዞኖች ውስጥ በጣም የተለመደው የብልሽት አይነት የኋላ-መጨረሻ ግጭት ነው.
- የመንገድ መስመርዎ ወደፊት ዝግ እንደሆነ የሚነግርዎትን መልእክት እንዳዩ የመንገድ መስመር ለመቀየር ይዘጋጁ።
- በስራ ቀጠና ውስጥ ቀጥ ያለ ነጭ መስመር አይለፉ፤ በመንገድ መስመርዎ ላይ ይቆዩ።
- በስራ ቦታው ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ በጥንቃቄ ይንዱ እና ደህንነቱ በተጠበቀ ፍጥነት ይጓዙ፤ የመንገድ ሥራን ለመመልከት ፍጥነትዎን አይቀንሱ ወይም አያቁሙ።
- ከሰራተኞች አቅጣጫ ለመጠየቅ በስራ ክልል ውስጥ አያቁሙ።
- የመንገድ አመላካቾችን ይታዘዙ - የእነሱ መመሪያ ከተለመዱ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች የበለጠ ስልጣን አላቸው።

ያስታውሱ፡ የስራ ቀጠና የመንገድ አመልካቾች አደገኛ አሽከርካሪዎችን፣ ፈጣን አሽከርካሪዎችን እና ጠበኛ አሽከርካሪዎችን የፖሊስ የፍርድ ፎርም በመጠቀም ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ!

በባቡር ሐዲድ መሻገሪያዎች

አብዛኛዎቹ የባቡር ሀዲድ መሻገሪያዎች (ማቋረጫዎች) የሚጠበቁት አስቀድሞ በሚሰጥ የማስጠንቀቂያ ምልክት እና የመስቀለኛ መንገድ ምልክት ብቻ ነው። አብዛኛዎቹ መሻገሪያዎች ትራፊክን ለማስቆም በሮች የላቸውም። ሁሉንም የባቡር ሀዲድ መሻገሪያዎች ሲጠጉ በተለይ መጠንቀቅ አለብዎት።

ብዙ የባቡር ትራፊክ (የባቡሮች ፍሰት) የሌላቸው የታወቁ መሻገሪያዎች በጣም አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ። እንደዚህ አይነት መሻገሪያን ብዙ ጊዜ የሚጠቀሙ ከሆነ እና ብዙ ጊዜ ባቡር ካላዩ ባቡሮች በጭራሽ እንደማያልፉ ማመን ሊጀምሩ ይችላሉ፣ ይህንን ማመን አደገኛ ሊሆን ይችላል።

በባቡር ሀዲድ መሻገሪያዎች ላይ እነዚህን ነጥቦች ያስታውሱ፦

- ወደ የባቡር መሻገሪያው ሲቃረቡ ሁል ጊዜ ወደ ግራ፣ ቀኝ እና እንደገና ወደ ግራ ይመልከቱ። መሻገሪያው በስራ ላይ ቢሆንም እና የትራፊክ መብራት ምልክቶቹ ባይበሩም እንኳ ይህን ያድርጉ - በትክክል እየሰሩ ላይሆኑ ይችላሉ።
- ከአንድ የሃዲድ መስመር በላይ ባለበት የባቡር ሐዲድ መሻገሪያ ላይ ከቆሙ ባቡሩ ካለፈ በኋላ ወዲያውኑ መንዳት መጀመር የለብዎትም። ማቋረጥ (መሻገር) ከመጀመርዎ በፊት ሁለቱንም የሃዲድ መስመሮች በግልጽ እስኪያዩ ድረስ ይጠብቁ። አንድ(1) የሃዲድ መስመር ቢሆንም እንኳ ባቡሩ ካለፈ በኋላ ወዲያውኑ ማቋረጥ አይጀምሩ - እየቀረበ ያለ ሌላ ባቡር አለመኖሩን እንደገና ያረጋግጡ።
- ወደ የባቡር መሻገሪያ ሲቃረቡ ወይም ሲገቡ ማንንም ለማለፍ በጭራሽ አይሞክሩ።
- የሃዲድ መሰምሮችን በሚያቋርጡበት ጊዜ ሌላ ተሽከርካሪን ተከትለው በጭፍን አይሂዱ። ሌላ ተሽከርካሪን እየተከተሉ ከሆነ የሃዲድ መስመሮቹ ላይ ከመውጣትዎ በፊት ሙሉ በሙሉ ለመሻገር በቂ ቦታ መኖሩን ያረጋግጡ። ከፊትዎ ያለው የትራፊክ ፍሰት (ተሽከርካሪዎች) ከቀነሱ መሻገር ከመጀመርዎ በፊት መንገዱ ክፍት እስኪሆን ድረስ ይጠብቁ። **በጭራሽ በባቡር መስመር ላይ ተይዘው መቅረት የለብዎትም።**
- በስህተት የባቡር መሻገሪያ ላይ ተይዘው ከቀሩ እና ባቡር እየመጣ ከሆነ ተሽከርካሪውን በፍጥነት ይልቀቁ እና ከሀዲዱ በተቻለ መጠን ይራቁ።

ይህን ያውቁ ኖሯል?

በየሰዓት ተኩል በአሜሪካ አንድ ባቡር ከተሽከርካሪ ወይም እግረኛ ጋር ይጋጫል። ከሌላ ተሽከርካሪ ጋር በሚጋጩበት ጊዜ ከሚሞቱት ይልቅ ከባቡር ጋር በሚጋጩበት ጊዜ የመሞት እድልዎ 40 እጥፍ ይበልጣል።

መንገዱን ከእግረኞች፣ ከብስክሌተኞች፣ ከሞተር ብስክሌተኞች እና ከሞፔድ አሽከርካሪዎች ጋር መጋራት

እግረኞች እና ብስክሌተኞች እንደ ተሽከርካሪ ነጂዎች ክብር ሊሰጣቸው ይገባል። እነዚህ ቡድኖች በአደጋ ጊዜ ለጉዳት በጣም የተጋለጡ ናቸው፣ ነገር ግን ልክ እንደ እርስዎ የህዝብ መንገዶችን የመጠቀም መብት አላቸው። የሚከተሉትን የደህንነት ምክሮች ያስታውሱ።

እግረኞች

- በመንገዶች መገናኛ ላይ ወይም በእግረኛ ማቋረጫ ላይ ለሚሻገሩ እግረኞች ቅድሚያ ይስጡ።
- ቀይ ላይ ወደ ቀኝ መታጠፍ ማለት ያቁሙ፣ በሁሉም አቅጣጫ ይመልከቱ እና ከዚያ ደህንነቱ በተጠበቀ ጊዜ ይታጠፉ ማለት ነው። እግረኞችን ይመልከቱ እና መሻገሪያ መንገዱ ክፍት እስኪ ሆነ በቂ ጊዜ ይስጧቸው።
- ሁልጊዜ ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ልጆች በአካባቢው በሚኖሩበት ጊዜ ተጨማሪ ጥንቃቄ ያድርጉ። አደጋውን ላይረዱ ስለሚችሉ ሳይመለከቱ ወደፊትዎ ሊሮጡ ይችላሉ።
- የቀይ መብራት ምልክቶች በሚበሩበት ጊዜ የትምህርት ቤት አካባቢ የፍጥነት ገደቦችን መከተል እና ለትምህርት ቤት አውቶቡሶች መቆም አለብዎት። የትምህርት ቤቶች አካባቢዎች እና የትምህርት ቤት አውቶቡስ ማቆሚያዎች ከፍተኛ የህጻናት ክምችት ያለባቸው ቦታዎች ናቸው።
- ለአረጋውያን እግረኞች እና ለአካል ጉዳተኞች እግረኞች ትዕግስት ይንርዎት። መንገድ ለመሻገር ተጨማሪ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል።
- ወደ ኋላ ከመመለስዎ በፊት ሁልጊዜ በመንገድዎ ላይ እግረኞች መኖራቸውን ያረጋግጡ።
- ማየት የተሳናቸው እግረኞች፣ ነጭ በትር ወይም መሪ ውሻ ቢኖራቸው፣ ወይም በሌሎች የሚመሩ ቢሆኑም ቅድሚያ ይስጡዋቸው (ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ለማቆም ይዘጋጁ)።
- ከኋላ ቆሞ ላለ ተሽከርካሪ ጋር ሲቃረቡ ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ከፊት ለፊቱ እግረኞች እንደማያልፉ እርግጠኛ እስኪሆኑ ድረስ አይልፉ።
- እግረኞች እርስዎን ሲያዩ በማንኛውም ጊዜ እና በተለይም ምልክት በሌላቸው ወይም በመሃል ብሎክ ቦታዎች ላይ እግረኛን ወደ ትራፊክ መስመር (የተሽከርካሪዎች መስመር) መጥራት በጭራሽ ደህንነቱ የተጠበቀ አይደለም።

ብስክሌተኞች

የደህንነት ምክሮች (የበለጠ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 5ን ይመልከቱ)

- ወደ ብስክሌት ሲቃረቡ ወይም ሲያልፉ ፍጥነትዎን በመቀነስ አስተማማኝ በሆነ ፍጥነት ይንዱ።
- ብስክሌተኛውን ካለፉ በኋላ ፍጥነትዎን አይቀንሱ ወይም በድንገት አያቁሙ። በድንገት ማቆም ብስክሌተኛው ከተሽከርካሪዎ ጋር እንዲጋጭ ሊያደርግ ይችላል።
- አደጋን ለማስቀረት ካልሆነ በቀር ለብስክሌተኞች የመኪና ድምጽ (ክላክስ) አያሰሙ።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የፔንስልቬንያ የብስክሌት ነጂዎች መመሪያ (PUB 380) በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል፦ http://www.dot.state.pa.us/public/pubsforms/Publications/Pub%20380.pdf

የሞተር ሳይክል እና ሞፔድ ነጂዎች

- በህጉ መሰረት የሞተር ሳይክል ነጂው/ሞፔድ (ቀላል የሞተር ሳክይል) ነጂው አንድ (1) ሙሉ የመንገድ መስመር እንዲጠቀም መፍቀድ አለብዎት።
- አብዛኛዎቹ የሞተር ሳይክል/ተሽከርካሪ ወይም ሞፔድ/ተሽከርካሪ አደጋዎች የሚከሰቱት በመገናኛዎች ላይ ነው። ብዙውን ጊዜ ተሽከርካሪው ቅድሚያ የማለፍ መብት ከፊት ለፊት ላለው ሞተር ሳይክል/ሞፔድ መስጠት ሲገባው ወደ ግራ ይታጠፋል።
- ሞተር ሳይክል/ሞፔድ የመብራት ምልክት እየበራ ሲያዩ እየታጠፈ ነው ብለው እንዳይገምቱ። የሞተር ሳይክል/ሞፔድ የመታጠፊያ የመብራት ምልክቶች እንደ መኪና በራሳቸው ላይጠፉ ይችላሉ። ሞተር ሳይክል/ሞፔድ እየታጠፈ እስኪያዩት ድረስ ከፊት ለፊቱ አይግቡ።
- ለአሽከርካሪዎች ትንሽ የሚመስሉ መሰናክሎች ለሞተር ሳይክል ነጂዎች/ሞፔድ ነጂዎች አደገኛ ሊሆኑ ይችላሉ። ሞተር ሳይክል ነጂዎች/ሞፔድ ነጂዎች በመንገድ ላይ አደጋን ለማስወገድ ድንገተኛ የሌይን (የመንገድ መስመር) ወይም የፍጥነት ለውጥ ሊያደርጉ ስለሚችሉ ዝግጁ ይሁኑ።
- ሌሎች ተሽከርካሪዎችን እንደምትከተሉ ሁሉ ተመሳሳይ የ4-ሰከንድ ወይም ከዚያ በላይ የተከታታይ ተሽከርካሪዎች ርቀት ይፍቀዱ።. የመንገዱ ሁኔታ ወይም የአየር ሁኔታው መጥፎ በሚሆኑበት ጊዜ ከሞተር ሳይክል/ሞፔድ ጀርባ ያለውን ርቀትዎን ይጨምሩ።

የእኛን የፔንስልቬንያ የትራንስፖርት (PennDOT) የሞተር ሳይክል ደህንነት ቪዲዮ ለመመልከት የሚከተለውን ሊንክ ይጫኑ።

https://www.youtube.com/watch?v=SZjHD9iIz-o

መንገዱን ከጭነት መኪናዎች እና ከአውቶቡሶች ጋር መጋራት

ከመኪና፣ ከጭነት መኪና፣ ከአውቶቡስ ወይም ከሌላ ትልቅ ተሽከርካሪ ጋር መንገዱን ቢጋሩ፣ ለደህንነት ሲባል የትራፊክ ህጎችን መከተል፣ የመንገድ ደንቦችን ማክበር እና በጥንቃቄ መንዳት አስፈላጊ ነው። ከጭነት መኪናዎች እና ከአውቶቡሶች ጋር መንገዱን በጋራ ለመጠቀም ልዩ ህጎች አሉ፤ ጉዞዎን ደህንነቱ የተጠበቀ ለማድረግ የሚከተሉትን ይጠቀሙ። ደህንነታቸው የተጠበቀ አውራ ጎዳናዎች የሚረጋገጡበት ዋናው ነገር የጭነት መኪናውን ወይም አውቶቡሱን በሹፌሩ ዓይን የማይታይ ቦታ (ለማየት የሚያዳግት ቦታ)(No-Zone) ማወቅ ነው። የማይታየው ክልል በጭነት መኪናዎች እና በአውቶቡሶች ዙሪያ አደጋዎች ሊከሰቱ የሚችሉባቸውን የአደጋ ቦታዎችን ያመለክታል።

የጭነት መኪናን ማለፍ

በተስተካከለ አውራ ጎዳና ላይ አንድን የጭነት የተለመደውን መኪና ለማለፍ ከሚወስደው ከሶስት (3) እስከ አምስት (5) ሰከንዶች የበለጠ ጊዜ ብቻ ይወስዳል። ወደ ላይ በሚወጣ መንገድ ላይ የጭነት መኪናዎች ፍጥነታቸውን ይቀንሳሉ፤ ስለዚህ ከተለመደው መኪና ይልቅ ለማለፍ ቀላል ይሆናል። በቁልቁለት ላይ የጭነት መኪናው ፍጥነት እንዲጨምር ያደርገዋል፤ ስለዚህ ፍጥነትዎን መጨመር ያስፈልግዎት ይሆናል።

ተሽከርካሪዎች ካለፉ በኋላ ቶሎ ብለው ወደ መስመራቸው ከገቡና ድንገት ፍጥነት ከቀነሱ የጭነት መኪና ሹፌሮች ምላሽ ለመስጠት የሚኖራቸው ጊዜና ቦታ በጣም ትንሽ ነው።

የጭነት መኪናው ወደ መንገድ መስመርዎ ለመግባት ቢሞክር እንዳትጠለፉ በማለፊያ የመንገድ መስመር ላይ ባለው መኪናዎ እና ከፊትዎ ባለው ማንኛውም መኪና መካከል ብዙ ቦታ መኖሩን ያረጋግጡ። በጭነት መኪናው ለማየት የሚያዳግት ቦታ ውስጥ ሳይዘገዩ ቶሎ ብለው ይለፉ። የመነቃቃቱን ተጽዕኖ ለመቆጣጠር ሁለቱንም እጆችዎን በመሪው ላይ አጥብቀው ይያዙ። ከማለፊያው የመንገድ መስመር በስተግራ ቢቆዩ ይመከራል። ማለፊያዎን በተቻለ ፍጥነት ያጠናቅቁ እና ከሌላው ተሽከርካሪ ጋር ጎን ለጎን አብረውም አይጓዙ። የጭነት መኪናውን ፊት በኋለኛው መመልከቻ መስተዋትዎ ውስጥ ሲያዩ ብቻ ወደ ኋላ ይመለሱ። የጭነት መኪናን ካለፉ በኋላ በተያዘው ፍጥነት መጓዝዎን ይቀጥሉ። ስህተት ሊፈጠርና አደጋ ሊከሰት በሚችልባቸው ጠመዝማዛ መንገዶች ላይ ስለማለፍ ሁለት ግዜ ያስቡበት።

እውነታ፦ የጭነት መኪናን ሲያልፉ በቂ ጊዜ ይውሰዱ። አውራ ጎዳና ፍጥነት የጭነት መኪናን በአስተማማኝ ሁኔታ ለማለፍ እስከ 30 ሰከንድ ሊወስድ ይችላል። ሲያልፉ በፍጥነት ይለፉ። ከጭነት መኪና ጋር ጎን ለጎን ባለማቋረጥ አይንዱ - ምክንያቱም እርስዎ ለጭነት መኪናው ሹፌር ለማየት የሚያዳግት ቦታ ላይ ነዎት። ካለፉ በኋላ የጭነት መኪናውን የፊት መብራቶች ወይም የፊት ግሪል (የመኪናው ግድግዳ) በኋለኛው መመልከቻ መስተዋትዎ ውስጥ ሲያዩ ብቻ የመንገድ መስመር ይቀይሩ።

የሚያልፍ የጭነት መኪና



An example of a truck's blind spots (No-Zones).

አንድ የጭነት መኪና ተሽከርካሪዎን ሲያልፍ፣ ወደ መስመርዎ ሩቅ ጫፍ በመሄድ የጭነት መኪናውን ሹፌር መርዳት ይችላሉ። ፍጥነትዎን በመጠኑ ከቀነሱና ፍጥነትዎን በተመሳሳይ ከቀጠሉ ለጭነት መኪናው ሹፌር ቀላል ይሆንለታል። በማንኛውም ሁኔታ የጭነት መኪናው እርስዎን በሚያልፍበት ጊዜ ፍጥነትዎን አይጨምሩ። ጭነት መኪናዎች ከተሳፋሪ ተሽከርካሪዎች ይልቅ በሁለቱም በኩል በጣም ትልቅ በሹፌር የማይታዩ ክልሎች (No-Zones) አሏቸው። በእነዚህ ለሹፌር ለማየት የሚያዳግቱ ቦታዎች (No-Zones) ውስጥ ሲነዱ በጭነት መኪና ሹፌሮች ሊታዩ አይችሉም። ለጭነት መኪናው ሹፌር ለማየት የሚያዳግ ቦታ ላይ ከሆናችሁና ወደ መስመራችሁ መምጣት ከጀመረ ይረጋጉ፤ መኪናችሁ ከጭነት መኪናው ፊት ጋር ሲነጻጸር ያለበትን ቦታ ያስታውሱ። ግጭትን ለማስቀረት ፍጥነትዎን መጨመር ወይም መቀነስ እንዳለብዎት ይወስኑ። የመንገዱን ዳር እንደ ማምለጫ መንገድ አድርገው ይቁጠሩት።

ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣ የጭነት መኪና ሲያጋጥምዎ የጎንዮሽ ግጭትን ለማስወገድ እና በተሽከርካሪዎ እና በጭነት መኪናው መካከል ያለውን የንፋስ ግርግር ለመቀነስ በተቻለ መጠን ወደ ጎን ይራቁ። የንፋስ ግርግሩ/ግፊቱ ተሽከርካሪዎችን ወደ ተለያየ አቅጣጫ እንደሚገፋ ያስታውሱ። ወደ አንድ አያመጣቸውም። በተሽከርካሪዎ እና ከፊትዎ ባለው ማንኛውም ተሽከርካሪ መካከል ብዙ ርቀት ይጠብቁ።

የጭነት መኪናን መከተል

በመጠናቸው ምክንያት የጭነት መኪናዎች ለማቆም ረዘም ያለ ርቀት ያስፈልጋቸዋል። ነገር ግን በጣም በተጠጋ ሁኔታ የሚከተል መኪና የጭነት መኪናውን ከኋላ ላለመጋጨት በበቂ ፍጥነት ማቆም አሁንም ሊያቅተው ይችላል። የጭነት መኪናን የምትከተሉ ከሆነ ለሹፌሩ ከማይታይ ክልል ዉጭ ቆዩ። በጣም ተጠግቶ ከመከተል ይቆጠቡ፣ መኪናዎን የጭነት መኪናው ሹፌር የጎን መስታወቱ ውስጥ በሚያየው ቦታ ላይ ያድርጉ። ከዚያም ከፊትዎ ያለውን መንገድ በደንብ ያያሉ፣ እንዲሁም የጭነት መኪና ሹፌሩ ለማቆም ወይም ለመታጠፍ በቂ ማስጠንቀቂያ ሊሰጥዎት ይችላል። ምላሽ ለመስጠት እና አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ ለማቆም ተጨማሪ ጊዜ ይኖርዎታል። የጭነት መኪና ወይም አውቶቡስ በሚከተሉበት ጊዜ ከፊትዎ ያለውን የተሽከርካሪ የጎን መስተዋቶች ማየት ካልቻሉ፣ የትልቁ ተሽከርካሪ ሹፌር እርስዎን ማየት አይችልም።

ኮረብታ ላይ በሚቆሙበት ጊዜ በርስዎ እና በጭነት መኪናው መካከል ብዙ ቦታ ይተዉ። የጭነት መኪናዎች ሹፌሩ እግሩን ከብሬክ ላይ ሲያነሳ ወደ ኋላ ሊመለሱ ይችላሉ።

በሌሊት የጭነት መኪናን ወይም ማንኛውንም ተሽከርካሪ በሚከተሉበት ጊዜ የፊት መብራቶችዎን ሁልጊዜ ያደበዝዙ። ከኋላ ያለው ተሽከርካሪ የሚወጣ ደማቅ ብርሃን በትልቁ የጭነት መኪና የጎን መስተዋቶች ላይ ሲንፀባረቅ የጭነት መኪና ሹፌሩን ማየት እንዳይችል የደርገዋል።

እውነታ፦ ከጭነት መኪናው የኋላ ለሹፌሩ ለማየት የሚያዳግት ቦታ ለመውጣት ቢያንስ አራት (4) ሰከንዶች ያስፈልጋሉ፣ እና ትክክለኛውን ርቀት ለማስላት ቀላል ዘዴ እንደዚህ ነው፤ የጭነት መኪናው ከመንገዱ ዳር ቆሞ ያለ ነገርን ሲያልፍ መቁጠር ይጀምሩ፣ አንድ ሺህ አንድ፣ አንድ ሺህ ሁለት፣ወዘተ። ከፊትዎ ያለው ባምፐር (መከላከያ) ተመሳሳይ ነገር ላይ ሲደርስ አንድ ሺህ አራት መድረስ አለብዎት። ከአንድ ሺህ አራት ቀድመው ከደረሱ፣ ከጭነት መኪናው ጀርባ በጣም ተጠግተው እየሄዱ ነው።

መታጠፊያዎች

ለጭነት መኪናዎች የመታጠፊያ የመብራት ምልክቶች ከፍተኛ ትኩረት ይስጡ። የጭነት መኪና ሹፌሮች የጭነት መኪናው ጀርባ ወይም የትራክተር ተጎታች ጀርባ ጥግን ወይም ሌላ ማንኛውንም ቋሚ እንቅፋት እንዲያልፍ ሰፋ ባለ ሁኔታ መታጠፍ አለባቸው። አንዳንድ ጊዜ ማዕዘኖችን ክፍት ለማድረግ ከሌሎች የመንገድ መስመሮች ያለው ቦታ ጥቅም ላይ ይውላል። አደጋን ለማስቀረት መታጠፉን እስኪጠናቀቅ ድረስ አይለፉ። በድጋሚ ለመታጠፊያ የመብራት ምልክቶች ከፍተኛ ትኩረት ይስጡ። (ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ ይመልከቱ።)



ሰፊ የቀኝ መታጠፊያ ምሳሌ።

እውነታ፦ የጭነት መኪናዎች ሰፊ መታጠፊያ ያደርጋሉ (ሲታጠፉ ሰፊ ቦታ ይሸፍናሉ)። የጭነት መኪናዎች በትክክል ወደ ቀኝ ሲታጠፉ በቀጥታ የሚሄዱ ወይም ወደ ግራ የሚታጠፉ ሊመስሉ ይችላሉ። ይህ ዘዴ - ከትራክተሩ ጎን ካሉ የጎንዮሽ ለሹፌር ለማየት የሚያዳግቱ ቦታዎች ጋር ተዳምሮ - እየታጠፈ ያለ የጭነት መኪናን ለመቅደም መሞከር አደገኛ አካሄድ ያደርገዋል። የጭነት መኪና ሹፌሮች በነሱ እና የጎን የእግረኛው መንገድ መካከል የሚገቡ ተሽከርካሪዎችን ማየት አይችሉም። ቦታዎን በመያዝ ይጠብቁ እና የጭነት መኪና ሹፌሮች ለመታጠፍ በቂ ቦታ ይስጡ።

ከመጠን ያለፈ ጭነት

ከመጠን በላይ የሆኑ ጭነቶች በሌሎች መኪኖች ይታጀባሉ። ከመጠን ያለፈ የጭነት እንቅስቃሴዎች ልክ እንደ ትራክተር ተጎታች መኪና ይሠራሉ እና እንደ የጭነት መኪናዎች በተመሳሳይ ህጎች መታየት አለባቸው። አብዛኛዎቹ ትላልቅ ጭነቶች በተፈቀደላቸው መስመሮች ውስጥ ይጓዛሉ፤ ሆኖም ግን በስፋታቸው ምክንያት በመንገዱ ዳር ያሉ እንቅፋቶች ቢጫውን ወይም ነጭውን መስመር እንዲያልፉ ሊያስገድዷቸው ይችላል።

አጃቢ ተሽከርካሪዎች አሽከርካሪዎችን ከመጠን ያለፈ ጭነት እና/ወይም ቀስ ብለው ስለሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ለማስጠንቀቅ በህግ ይገደዳሉ። አጃቢ ተሽከርካሪዎች ልዩ ምልክቶች እና መብራቶች ሊኖሯቸው ይገባል፤ ይህም ሰዎች አጃቢ መኪኖች መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል፤ አሽከርካሪዎች ይህንን መኪና ሲያዩ ትልቅ ጭነት እየቀረባቸው እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። እነዚህን ተሽከርካሪዎች ሲያዩ እባክዎን ከፍተኛ ጥንቃቄ ያድርጉ።

ወደ ኋላ መጋጨት

ወደ ኋላ ለመመለስ እየተዘጋጀ ያለ የጭነት መኪና በስተጀርባ ለመሻገር በጭራሽ አይሞክሩ። ብዙውን ጊዜ አንድ የጭነት መኪና ሹፌር የጭነት መኪናውን ከመንገድ ወደ መጫኛ ቦታ ለመመለስ ሲዘጋጅ መንገዱን ለጊዜው ከመዝጋት ሌላ አማራጭ የለም። አንዳንድ ሹፌሮች እና እግረኞች የጭነት መኪናው እንቅስቃሴውን እስኪጨርስ ድረስ ጥቂት ሰከንዶች ከመጠበቅ ይልቅ ከጭነት መኪናው ጀርባ ለማለፍ የሚሞክሩት እዚህ ላይ ነው። ከጭነት መኪናው ጀርባ ጠጋ ብለው በሚያልፉበት ጊዜ ሹፌሩ ወይም እግረኛው የጭነት መኪናው ሹፌር የማይታይ ክልል ውስጥ ይገባሉ በዚህም ምክንያት አደጋ ሊከሰት ይችላል።

ፍሬን መያዝ

ከተሽከርካሪዎች የሃይድሮሊክ ብሬክስ በተለየ የጭነት መኪናዎች እና አውቶቡሶች የአየር ብሬክስ ሊኖራቸው ይችላል እና ለማቆም ረዘም ያለ ርቀት ይወስዳሉ። ጥሩ ጎማዎች እና በአግባቡ የተስተካከለ ብሬክስ ያለው፣ በጠራ እና ደረቅ መንገድ ላይ በሰዓት 65 ማይል የሚጓዝ ጫኝ የጭነት መኪና ሙሉ በሙሉ ለማቆም ቢያንስ 600 ጫማ ያስፈልገዋል (ይህም ከተሳፋሪ ተሽከርካሪዎች 400 ጫማ የማቆሚያ ርቀት ጋር ሲነጻጸር)። በትልቅ ተሽከርካሪ ፊት ለፊት በሚሆኑበት ጊዜ ወደ መንገድ ከመግባት መቆጠብ እንዲሁም ከመንገድ እየወጡ ከሆነ የመንገድ መስመር ከመቀየር መቆጠብ በጣም አስፈላጊ ነው።

የማምለጫ ራምፖች

ረዣዥም ቁልቁለታማ በሆኑ ቦታዎች ላይ የጭነት መኪናዎች የሚጠቀሙባቸው ልዩ "የማምለጫ" ወይም "ድንገተኛ አደጋ" ራምፖች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ራምፖች ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ከቁጥጥር ውጭ ለሆኑ ወይም ፍሬን (ብሬክ) በመበላሸቱ ምክንያት ማቆም ለማይችሉ ትላልቅ ተሽከርካሪዎች ብቻ ነው። በእነዚህ ራምፖች አካባቢ በጭራሽ አያቁሙ ወይም ፓርክ አያድርጉ።

አውቶብሶች/ባሶች

አውቶቡሶች ከተራ ተሽከርካሪ ይልቅ በመንገድ ላይ ብዙ ቦታ የሚይዙ ተሽከርካሪዎች ናቸው። ከአውቶብስ ወይም ከጭነት መኪና ጋር መንገድን በጋራ ስትጠቀሙ ተመሳሳይ ህጎችን መከተል አለባችሁ።

የትምህርት ቤት አውቶቡሶች

ፔንሲልቬኒያ ከአንድ ትምህርት ቤት አውቶቡስ አጠገብ ሲነዱ መከተል ያለብዎት ልዩ ህጎች አሏት። እነዚህ ደንቦች የልጆችን እና አሽከርካሪዎች ደህንነት ይጠብቃሉ።

የትምህርት ቤት አውቶቡስ ለማቆም ሲዘጋጅ፣ አምበር (ቢጫ) መብራቶቹ ብልጭ ማለት ይጀምራሉ። አውቶቡሱ ቀይ መብራቶቹን እያበራ እና ያቁሙ የሚለው ክንድ ተዘርግቶ ሲቆም፣ ከኋላውም ሆኑ በተመሳሳይ መንገድ ላይ ወደ እሱ ሲመጡ ወይም የትምህርት ቤቱ አውቶቡስ ቆሞ ባለበት መገናኛ ላይ ሲቃረቡ ቢያንስ 10 ጫማ ርቀት ላይ ማቆም አለብዎት። ቀይ መብራቶቹ ብልጭ እስኪያቆሙ ያቁሙ የሚለው ክንድ እስኪጠፋ እና ህጻናቱ ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ እስኪደርሱ ድረስ ቆመው ይጠብቁ (ከታች ያለውን ምስል ይመልከቱ)።

> **ሁሉም ተሽከርካሪዎች መቆም አለባቸው!**
> ብልጭ የሚል ቀይ መብራት እና የተዘረጋ ያቁሙ የሚል ክንድ ባለበት አካባቢ ላለ የትምህርት ቤት አውቶቡስ ማቆም አለመቻል የመንጃ ፍቃድዎን የ 60 ቀን እገዳ እንዲሁም በመንዳት ታሪክዎ ላይ አምስት (5) ነጥቦች እና የገንዘብ መቀጮ ያስከትላል።



የትምህርት ቤቱን አውቶቡስ የማቆም መስፈርት አንድ ልዩ ሁኔታ ብቻ ነው ያለው። ቀይ መብራቶቹን እያበራ እና ያቁሙ የሚለው ክንዱን ዘርግቶ ቆሞ ወደ ሚገኝ የትምህርት ቤት አውቶቡስ እየተቃረቡ ከሆነ እና በተከፋፈለ ሀይዌይ በተቃራኒው በኩል እየነዱ ከሆነ (ማለትም የኮንክሪት/የብረት ማገጃዎች፣ የመመሪያ ሀዲዶች ወይም ዛፎች/ድንጋዮች/ወንዞች/የሳር ሜዳ) ማቆም የለብዎትም። ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና በጥንቃቄ መንዳትዎን ይቀጥሉ።

የፔንሲልቬንያን የትምህርት ቤት አውቶቡስ የማቆሚያ ህግን ለማብራራት የሚረዳ ይህን ግራፊክ (ምስላዊ መግለጫ) ይመልከቱ።
https://www.penndot.gov/TravelInPA/Safety/TrafficSafetyAndDriverTopics/Pages/School-Bus-Safety.aspx

የአደጋ ጊዜ መኪናዎች እና ሁኔታዎች

የተወሰኑ ተሽከርካሪዎች ሳይረን እና ብልጭ የሚሉ ቀይ መብራቶች ወይም ብልጭ ድርምግ የሚሉ ጥምር ቀይ እና ሰማያዊ መብራቶች አላቸው። እነዚህ መብራቶች የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች የትራፊክ መጨናነቅን በፍጥነት አልፈው እንዲሄዱ እና ለአስቸኳይ ጥሪዎች ምላሽ እንዲሰጡ ያግዛሉ። የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች የእሳት አደጋ መከላከያ መምሪያ ተሽከርካሪዎች፣ የፖሊስ መኪኖች፣ አምቡላንሶች፣ የደም አቅርቦት ተሽከርካሪዎች እና ከአደጋ አድን ድርጅቶች የተለየ መሳሪያ ያላቸው ተሽከርካሪዎች ያካትታሉ። ከእነዚህ ይጠንቀቁ።

ሳይረን ሲሰሙ ወይም ብልጭ የሚሉ ቀይ መብራቶች ያሉት ወይም ቀይ እና ሰማያዊ መብራቶች ጥምረት ያለው ተሽከርካሪ ከየትኛውም አቅጣጫ ሲቃረብዎት ሲመለከቱ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፦

- ወደ ዳር ወይም ወደ ጎን ይሂዱ እና ያቁሙ።
- ከዳር ጋር ትይዩ በሆነ መንገድ በተቻለ መጠን ወደ ዳር ተጠግታችሁ መንዳት አለብዎት። ባለ አንድ አቅጣጫ ጎዳናዎች ላይ ቅርብ ወደ ሆነው የመንገድ ዳር ይንዱ እና ያቁሙ።
- ከመንገድ መገናኛዎች ይራቁ።
- የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪው ካለፈዎት በኋላ ቢያንስ 500 ጫማ ርቀት ላይ በመቆየት እንደገና መንዳት ይጀምሩ።
- ሌላ የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪ እየመጣ አለመሆኑን ያረጋግጡ።

በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ላይ ሁሉም አሽከርካሪዎች ዩኒፎርም የለበሱ የፖሊስ መኮንኖችን፣ የሸሪፍን፣ ኮንስታብሎች (የፖሊስ አባላትን) ወይም በትክክል የለበሱ ሰዎችን (የእሳት አደጋ ፖሊሶችን ጨምሮ) ትዕዛዝ ማክበር አለባቸው።

ሳይረንን በቁም ነገር በመመልከት ለአምቡላንስ፣ ለእሳት አደጋ መኪና ወይም ለፖሊስ መኪና መንገድ ይልቀቁ። አንድ ቀን እርስዎ እርዳታ የሚጠይቁት ሊሆኑ ይችላሉ፣ ወይም በችግር ላይ ያለው ሕይወት ጓደኛዎ ወይም የቤተሰብዎ አባል ሊሆን ይችላል።

ለድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ቦታ የመልቀቅ ህግ

ለድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ቦታ የመልቀቅ ህግ (Move Over) አሽከርካሪዎች ድንገተኛ አደጋ በሚደርስበት አካባቢ ወይም በተበላሸ ተሽከርካሪ አጠገብ ያልሆነ ወደ ሌላ መስመር እንዲሄዱ ያስገድዳል። የድንገተኛ አደጋ ምላሽ አካባቢ ማለት ፖሊስ፣ ሸሪፍ፣ የሬሳ ምርመራ ባለሙያዎች፣ የሕክምና መርማሪዎች፣ የእሳት አደጋ ተከላካዮች፣ የእሳት አደጋ ፖሊስ፣ የእሳት አደጋ ማርሻል፣ የነፍስ አድን ሠራተኞች፣ የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት ሠራተኞች፣ የጭነት መኪና ሹፌሮች እና የማገገሚያ ሠራተኞች፣ አደገኛ ቁሶች ምላሽ ቡድን አባላት እና/ወይም አውራ ጎዳና ግንባታና ጥገና ሠራተኞች አገልግሎት የሚሰጡበት መንገድ ላይ ወይም በአቅራቢያው ያለ አካባቢ ነው። የተበላሸ ተሽከርካሪ ማለት ቢያንስ በሁለት የምልክት መብራቶች፣ የመንገድ ላይ ችቦዎች፣ የጥንቃቄ ምልክቶች እና/ወይም ሌላ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያ በግልጽ ምልክት የተደረገበት የትራፊክ መስመር ላይ ወይም ጎን ላይ ያለ ተሽከርካሪ ነው። አሽከርካሪዎች በትራፊክ ፍሰት ወይም በሌሎች ሁኔታዎች ምክንያት መንቀሳቀስ ካልቻሉ፣ ፍጥነታቸውን ከተለጠፈው የፍጥነት ወሰን ቢያንስ በ20 ማይል በሰዓት መቀነስ አለባቸው። የሕግ አስከባሪዎች በማይገኙበት ጊዜ፣ ሕጉ የመንገድ ሠራተኞች እና የአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪዎች የአሽከርካሪዎችን ጥሰት ሪፖርት እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል። የሕግ አስከባሪዎች በእነዚህ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ትኬት ሊሰጡ ይችላሉ። ወደ ጎን አለማለፍ ወይም ፍጥነትን አለመቀነስ ለመጀመሪያው ጥፋት እስከ $500፣ ለሁለተኛው ጥፋት $1,000 እና ለሦስተኛው እና ከዚያ በኋላ ላለው ጥፋት $2,000 የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ የሚያስከትል አጭር ቅጣት ሊያስከትል ይችላል። በተጨማሪም በሥራ ቀጠና አካባቢዎች ለሚፈጸሙ የትራፊክ ጥሰቶች የሚጣለው ቅጣት በእጥፍ ይጨምራል። ይህን ህግ በመጣስ ጥፋተኛ የተባለ ማንኛውም ሰው በመንዳት ታሪኩ ላይ 2 ነጥቦች ይመዘገቡበታል። ይህንን ሕግ መጣስ በሌላ ሰው ላይ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ካስከተለ የ90 ቀናት መንጃ ፈቃድ እገዳ የሚጣል ሲሆን እስከ $1,000 የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊያስከትል ይችላል። ይህንን ሕግ መጣስ ለአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪ ወይም በተበላሸ ተሽከርካሪ ውስጥ ወይም አጠገብ ላለ ሰው ከባድ የአካል ጉዳት ካስከተለ የ6 ወር መንጃ ፈቃድ እገዳ የሚጣል ሲሆን እስከ $5,000 የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊያስከትል ይችላል። ይህንን ሕግ መጣስ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪ ወይም በተበላሸ ተሽከርካሪ ውስጥ ወይም አጠገብ ያለ ሰው ሞት ካስከተለ የ1 ዓመት እገዳ የሚጣል ሲሆን እስከ $10,000 የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊያስከትል ይችላል።

በፈረስ የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች እና በፈረስ የሚጓዙ ሰዎች

በፈረስ የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎችን ወይም በፈረስ የሚጓዙ ሰዎችን ሊያጋጥሙዎት በሚችሉባቸው አካባቢዎች ማስታወስ ያለብዎት አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮች አሉ። ብዙ በፈረስ የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች ቀለማቸው ጥቁር ስለሆነ ጎህ ሲቀድ፣ ሲመሽ ወይም ማታ ለማየት አስቸጋሪ ናቸው። በፈረስ የሚጎተትን ተሽከርካሪ በሚከተሉበት ወይም ከኋላው በሚቆሙበት ጊዜ በሁለቱ (2) ተሽከርካሪዎች መካከል በቂ ቦታ መተውዎን ያረጋግጡ። በፈረስ የሚጎተቱ ጋሪዎች ካቆሙ በኋላ ወደ ኋላ የመንቀሳቀስ አዝማሚያ አላቸው፣ እና በጣም ከተጠጉ በፈረስ የሚጎተት ተሽከርካሪ ሹፌር እርስዎን የማየት አቅም ይቀንሳል። ይህ ደግሞ ለማለፍ ሲዘጋጁ በቂ ቦታ እንዲኖርዎት ያደርጋል። በፈረስ የሚጎተትን ተሽከርካሪ ወይም በፈረስ የሚጋልብን ሰው ሲያልፉ ፈረሱን ሊያስደነግጥ ስለሚችል በፍጥነት አይነዱ ወይም የመኪናዎ ድምጽን (ክላክስ) አያሰሙ። በተጨማሪም ካለፉ በኋላ ፈረሱ እንዳይደናገጥ ለመከላከል ወደ ቀኝ መስመር ከመመለስዎ በፊት በተሽከርካሪዎ እና በፈረሱ መካከል በቂ ቦታ መተውዎን ያረጋግጡ። በመንገድ ላይ ሁሉም ሰው እኩል መብት እንዳለው ሁልጊዜ ያስታውሱ።

በክፍት የጭነት መኪና ውስጥ ያሉ ተሳፋሪዎች

ማንኛውም ሰው በጭነት መኪናው ላይ የሚገኝ ከሆነ፣ ክፍት የጭነት መኪና ወይም ክፍት ጠፍጣፋ የጭነት መኪና በሰዓት ከ 35 ማይል በላይ በሆነ ፍጥነት መሄድ አይችልም። ከ18 ዓመት በታች የሆነ ልጅ በጭነት መኪናው ጀርባ ላይ በሚገኝበት ጊዜ እንደዚህ ዓይነት የጭነት መኪና መንዳት አይቻልም።

ለዚህ ሕግ የማይገዙ ልዩ ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፦

- በእርሻው ላይ ወይም በእርሻ ቦታዎች ላይ ሥራን ለማከናወን በእርሻው ባለቤትነት ወይም ቁጥጥር ስር ባሉ እርሻዎች መካከል የሚጓጓዝ የአርሶ አደር ልጅ።
- በልጁ አሠሪ ወይም አሠሪዎች ባለቤትነት ወይም በሚተዳደሩት እርሻዎች መካከል የሚጓጓዝ የእርሻ ሥራ ለመሥራት የተቀጠረ ልጅ።
- በአደን ጊዜ ከአደን ካምፕ ወደ አደን ቦታ ወይም በአደን ቦታዎች መካከል የሚጓጓዝ የአደን ፍቃድ ያለው ልጅ።
- በይፋ በተፈቀደ ሰልፍ ላይ የሚሳተፍ ልጅ፣ በሰልፉ ወቅት ብቻ።

የበረዶ ማጽጃ መኪኖች

በክረምት ወራት በረዶን የሚያስወግዱ በረዶ ማጽጃ መኪኖች ሹፌሮች በመስታወታቸው ውስጥ በጣም የተገደበ ዕይታ አላቸው። ማጽጃ መኪኖች ብዙ ጊዜ መዞር አለባቸው፣ እና ሾፌሮቻቸው ከኋላቸው እርስዎን ማየት አይችሉም። በአስተማማኝ ርቀት መከተልዎን ያረጋግጡ። ይህ ተሽከርካሪዎን ከጨው፣ በረዶ ማስለቀቂያ ፈሳሾች እና ከበረዶ ማጽጃ መኪኖች ከሚወረውሩ ፀረ-መንሸራተት ቅንጣቶች ጉዳት እንዳይደርስ ለመከላከል ይረዳል።

እንዲሁም እነዚህ ተሽከርካሪዎች በጎን በኩል የሚወጡ ክንፍ ያላቸው የበረዶ ማጽጃዎች ሊኖራቸው ይችላል። እነዚህ በአስከፊ የአየር ሁኔታ ወይም በሌሊት ለአሽከርካሪዎች ለማየት አስቸጋሪ ናቸው እና በብዙ የጎንዮሽ ግጭቶች ውስጥ ተሳትፈዋል። ደህንነትዎን ለመጠበቅ ከማጽጃው በግራ በኩልም ሆነ በቀኝ በኩል ለማለፍ መሞከር የለብዎትም።

የመንገድ ላይ ቁጣን መቋቋም

ቁጣዎን በመንገድ ላይ በሌላ ሰው ላይ **በፍፁም** አያውጡ። አንዳንድ ጊዜ የመንገድ ላይ የቁጣ ክስተቶች የሚከሰቱት በአሽከርካሪዎች መካከል ባሉ ቀላል አለመግባባቶች ነው። አንድ ሾፌር ጊዜያዊ የስህተት ውሳኔ ሊወስን ይችላል፣ ይህም ሌላ ሾፌር ምንም እንኳን ያልታሰበ ቢሆንም እንደ ጠበኛ ድርጊት ሊመለከተው ይችላል።

አንድ ሰው መንገድ ሲዘጋዎ ወይም ከፊት ለፊትዎ ሲገባ በግል ጉዳያችሁ አድርጋችሁ **በፍጹም** አትውሰዱት። ዝም ብለው ይተውት እና ሌላውን ሹፌር ችላ ይበሉት።

አንድ ነገር ከተፈጠረ **አጸፋውን አይመልሱ።** ትኩረትዎን ከሌላ ሹፌር ጋር በሚደረግ "ውድድር" ላይ ማተኮር ከባድ ትኩረትን የሚከፋፍል ነገር ነው። አደጋን ለማስወገድ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እንደ ትራፊክ የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ የመብራት ምልክቶች እና የሌሎች ተሽከርካሪዎች ወይም እግረኞች ድርጊቶች ላይ ምላሽ ለመስጠት አቅምዎ ያንሳል።

> **ይህን ያውቁ ኖሯል?**
> በየዓመቱ በፔንሲልቬኒያ ውስጥ ከሚደርሱት 1,500 የሀይዌይ ሞት ውስጥ፣ ወደ 60 በመቶው ወይም ወደ 900 የሚጠጉት የሚከሰቱት በአደገኛ መንዳት ምክንያት ነው።

ለሌላ ሹፌር ትምህርት ለመስጠት በጭራሽ አይሞክሩ። ትክክል ቢሆኑም እንኳን እኔ ትክክል ነኝ ብለው አይከራከሩ። በጣም ትክክል ሊሆኑ ይችላሉ!

ጠበኛ ሹፌር ካጋጠመዎት ደህንነትዎን ለመጠበቅ የሚረዱዎት ጥቂት ምክሮች እነሆ፦

- ከጠበኛው ሹፌር መንገድ ለመውጣት የተቻለዎትን ሁሉ ያድርጉ።
- የማለፊያ መንገድ መስመሩን አይዝጉ። አንድ ሰው ማለፍ ከፈለገ ይፍቀዱለት።
- ጠበኛ ሹፌርን ፍጥነት በመጨመር አትፈታተኑ። ይህ ሹፌሩን የበለጠ ያናድደዋል እንዲሁም እርሶንም አደጋ ላይ ይጥላል።
- ከጠበኛ ሹፌር ጋር የዓይን ግንኙነትን ያስወግዱ።
- የሚሰጥትዎት ምልክቶችን ችላ ይበሉ፣ ምላሽም አይስጡ።
- እጅ ሳይዙ የሚደወል መሳሪያ ካለዎት እና በሰላም መደወል የሚችሉ ከሆነ ለፖሊስ ወይም ለ 911 ይደውሉ፤ ካልሆነ ደግሞ ከጎንዎ ያለ ሰው ይደውል።

አንድ ጠበኛ ሹፌር ቢያሳድድዎት ወደ ቤትዎ አይሂዱ። ይልቁንስ እርዳታ ወደሚያገኙበት እና ምስክሮች ወደሚኖሩበት የፖሊስ ጣቢያ፣ ሱቅ ወይም ሌላ ቦታ ይሂዱ።

ድንገተኛ የመንዳት ሁኔታዎችን መፍታት

እንደ አብዛኞቹ አሽከርካሪዎች ከሆኑ ድንገተኛ ሁኔታ ከመከሰቱ በፊት እንዴት መሆን እንዳለቦት ለመለማመድ እድሉ አይኖርዎትም። ነገር ግን በአንዳንድ ወሳኝ የመንዳት ሁኔታዎች ውስጥ ምን ማድረግ እንዳለቦት ማወቅ አሁንም ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። አንድ ችግር ሲፈጠር የተሳሳተ እርምጃ መውሰድ ወይም ምንም እርምጃ አለመውሰድ ተሽከርካሪዎን የመጋጨት እድልን እንደሚጨምር ግልጽ ነው።

> **ይህን ያውቁ ኖሯል?**
> በ12,000 አደጋዎች ግምገማ 37 በመቶ የሚሆኑት አሽከርካሪዎች አደጋውን ለማስቀረት ምንም ጥረት አላደረጉም።

ከድንገተኛ ሁኔታ ለመውጣት መሪዎን በአግባቡ መጠቀም

ግጭትን ለማስወገድ ፍሬን መያዝ ወይም መሪን መጠቀም ሲኖርብዎት አደጋውን ለማስወገድ መሪውን መጠቀም ፍሬን ከመያዝ የተሻለ ነው፣ በተለይም በሰዓት ከ25 ማይል በላይ በሆነ ፍጥነት። ይህ የሆነበት ምክንያት ለማምለጥ የሚወስዱት የጊዜ ምላሽ ከብሬክ (ፍሬን የመያዝ) ምላሽ ጊዜዎ የበለጠ ፈጣን ስለሆነ ነው። ነገር ግን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ተሽከርካሪዎን ለመቆጣጠር ጥሩ መሪን የመጠቀም ችሎታ ሊኖርዎት ይገባል።

እንደ አጠቃላይ መመሪያ መሪውን በሁለቱም እጆችዎ መያዝ አለብዎት። ይህ በተለይ በድንገተኛ ጊዜዎች በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የማምለጫ መሪ አያያዝ መሪውን ቢያንስ በግማሽ ዙር በአንድ (1) አቅጣጫ በፍጥነት እንዲቀይሩት የሚጠይቅ ሲሆን ከዚያም ነገሩን ካለፉ በኋላ መሪውን በተቃራኒው አቅጣጫ ወደ ሙሉ ክብ ማለት ይቻላል መመለስ ያስፈልግዎታል። ከዚያም በመጀመሪያው የመጓጓዣ አቅጣጫዎ ለመቀጠል ወደ መሃል የመሪ አያያዝ ይመለሳሉ። በከፍተኛ ፍጥነት ተሽከርካሪዎን ወደ ግራ ወይም ቀኝ ለማንቀሳቀስ በአነስተኛ መጠን መሪ መጠቀም ያስፈልጋል።



በቀኝ በኩል ባለው ምስል ላይ እንደሚታየው አድርጎ መሪውን የመያዝ ልማድ ይኑርዎት። መሪውን እንደ ሰዓት ቢቆጥሩት እጆችዎ መሪውን በ 9 እና 3 ሰዓት ወይም በ 8 እና 4 ሰዓት ቦታዎች ላይ መያዝ አለባቸው፤ በጣም ምቹ የሆነውን ይምረጡ። አውራ ጣቶችዎን በጠርዙ ውስጠኛ ክፍል ላይ ከማድረግ ይልቅ መሪው ላይ ያድርጓቸው።

እጆችዎን በዚህ አቀማመጥ በመሪው ላይ በማድረግ፦

- ድንገተኛ መሪን የማዞር እንቅስቃሴ በሚያደርጉበት ጊዜ ከመጠን በላይ የመቆጣጠር እድልዎ ይቀንሳል፤ ይህም ከቁጥጥር ውጭ እንዲሽከረከሩ ወይም ከመንገድ እንዲወጡ ሊያደርግዎት ይችላል።
- አደጋ ቢደርስ የአየር ከረጢቱ እጆችዎን ወደ ፊትዎ የመወርወር እና የመሰባበር እድሉ አነስተኛ ነው (ወይም የአየር ከረጢቱ የእጆችዎን የተሻለ ይጠብቃል)።
- እጆችዎ በረጅም ጉዞዎች ወቅት የበለጠ ምቾት የሚሰማቸው እና ያነሰ ድካም ይኖራቸዋል።

የአስር (10) እና የሁለት (2) ሰዓት የእጅ አቀማመጥ ተቀባይነት አለው፤ ሆኖም የአየር ከረጢትዎ ከተከፈተ ለጉዳት ይጋለጣሉ። በመታጠፊያዎችን ለመታጠፍ መሪውን መጠቀም የሚችሉባቸው ሁለት (2) መንገዶች አሉ፡ “በእጅ-ላይ-እጅ” ዘዴ፦ ሹፌሩ ተቃራኒውን ጎን ለመያዝ መሪውን ተሻግሮ በመድረስ መሪውን ከላይ በኩል ይጎትታል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ይደግማል። በ"ግፋ-ጎትት" ዘዴ አንድ (1) እጅ መሪውን ወደ ላይ ይገፋል ሌላኛው እጅ ወደ ላይ ይንሸራተታል ከዚያም መሪውን ወደ ታች ይጎትታል፣ መታጠፊያው እስኪጠናቀቅ ድረስ ድርጊቱን ይደግማል።

ግጭትን ማስወገድ ካልቻሉ ይህንን ያስታውሱ፦ በአደጋ ውስጥ የአካል ጉዳትን መከላከል በአብዛኛው የሚወሰነው የመቀመጫ ቀበቶዎን በአግባቡ በመልበስ፣ የጭንቅላት መቀመጫዎን በአግባቡ በማስተካከል፣ በተሽከርካሪዎ ውስጥ የአየር ከረጢት እንዲኖርዎት እና ከአየር ከረጢትዎ ቢያንስ አስር (10) ኢንች ርቀት ላይ በመቀመጥ ላይ ነው።

በድንገት ብሬክ ማድረግ (ፍሬን መያዝ) ካለብዎት

ፍሬንዎን በፍጥነት መጫን ከፈለጉ ደህንነትዎ የሚወሰነው ተሽከርካሪዎ መደበኛ ወይም አንቲ-ሎክ ብሬክስ (ABS) እንዳለው እና እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው በማወቅ ላይ ነው።

- **ያለ ABS፣** ፍሬኑን (ብሬኩን) ደጋግመው እየተጫኑ ይልቀቁት። ብሬክን በተደጋጋሚ መጫን እና መልቀቅ የተሽከርካሪዎን ፍጥነት ይቀንሳል እና ቁጥጥር ስር ያደርገዋል። ፍሬን አጥብቆ መጫን ጎማዎችዎን ቆልፎ ተሽከርካሪዎ እንዲንሸራተት ሊያደርግ ይችላል።
- **ከABS ጋር፣** ፍሬን ላይ ጽኑ እና ቀጣይነት ያለው ጫና ያድርጉ - ተሽከርካሪዎ አይንሸራተትም። **የፍሬን ፔዳሉን በተደጋጋሚ እየተጫኑ አይልቀቁት።** በሜካኒካዊ ጫጫታዎች እና/ወይም ትንሽ መወዛወዝ አይደናገጡ።

ተሽከርካሪዎ ምን ዓይነት የብሬኪንግ ሲስተም እንዳለው ለማወቅ የተሽከርካሪዎን ባለቤት መመሪያ መፈተሽ አለብዎት። ይህን ድንገተኛ ሁኔታ ውስጥ ከመግባታችሁ በፊት አድርጉት። **ድንገተኛ ሁኔታ ውስጥ ብሬክዎን እንዴት እንደሚጠቀሙ ማወቅ ሕይወትዎን ሊያድን ይችላል።**

ተሽከርካሪዎ መንሸራተት ቢጀምር

ተሽከርካሪዎ በእርጥብ ወይም በበረዶ መንገድ ላይ መንሸራተት ከጀመረ፣ ወደ ሚፈልጉት አቅጣጫ ይመልከቱ እና ያሽከርክሩ። የተሽከርካሪዎ የኋላ ክፍል ወደ ግራ የሚንሸራተት ከሆነ መሪውን ወደ ግራ አቅጣጫ ያዙሩት። የተሽከርካሪዎ የኋላ ክፍል ወደ ቀኝ የሚንሸራተት ከሆነ መሪውን ወደ ቀኝ አቅጣጫ ያዙሩት። መንሸራተትን ለማስተካከል መሪውን ሲያዞሩ ሌላ መንሸራተት በተቃራኒ አቅጣጫ ሊከሰት ይችላል፣ ነገር ግን ሁለተኛው መንሸራተት ከመጀመሪያው የከፋ አይሆንም። ሁለተኛውን መንሸራተት በተመሳሳይ መንገድ ለማስቆም ዝግጁ ይሁኑ - የተሽከርካሪዎ የኋላ ክፍል በሚንሸራተትበት አቅጣጫ መሪውን በማዞር። ተሽከርካሪዎን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ከመቻልዎ በፊት እነዚህን "ማስተካከያዎች" ጥቂት ጊዜ መድገም ሊያስፈልግዎት ይችላል።



በሚንሸራተቱበት ጊዜ ብሬክ (ፍሬን) አይጠቀሙ። ፍሬን(ብሬክ) ከያዙ መንሸራተቱ የከፋ ይሆናል። ጎምዎችዎን የመቆለፍ እና ሁሉንም የመሪ መቆጣጠሪያ አቅም የማጣት አደጋ ሊያጋጥምዎት ይችላል።

በጎርፍ የተጥለቀለቁ መንገዶች

በጎርፍ የተጥለቀለቁ መንገዶች በትንሽ ፍጥነት እንኳን ቢሆን 6 ኢንች ውሃ መኪናዎን ወይም የጭነት መኪናዎን ከመቆጣጠር ውጭ ሊያደርግ ይችላል፤ እንዲሁም አንዳንድ ትናንሽ መኪኖችን ሊያሰጥም ይችላል። ሁለት (2) ጫማ ውሃ አብዛኛዎቹን ተሽከርካሪዎች፣ የስፖርት መገልገያ ተሽከርካሪዎችን (SUVS) ጨምሮ ይወስዳል። ተሽከርካሪው ከመንገዱ ወጥቶ ወደ ጥልቅ ውሃ ውስጥ ከገባ በኋላ ሊገለበጥና በውሃ ሊሞላ ይችላል፣ ይህም አሽከርካሪውንና ተሳፋሪዎችን በውስጡ ያግዳል። **በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀስ ውሃ ካለ በጣም አስተማማኙ ነገር ሌላ አማራጭ መንገድ መፈለግ ነው።**

ማሳሰቢያ: በአደገኛ ሁኔታዎች ምክንያት አንድን መንገድ ወይም አውራ ጎዳና የሚዘጉ ምልክቶችን ወይም የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን ዞሮ መሄድ ወይም በእነሱ ውስጥ ማሽከርከር ህገወጥ ነው። ስለ ህጉ እና ቅጣቶቹ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ምዕራፍ 5ን ይመልከቱ።

የጎርፍ አደጋ:-

የጎርፍ አደጋ በፔንስልቬንያ ውስጥ ካሉት ዋነኛ አደጋዎች አንዱ ነው። የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከላት እንደገለጸው ከ2006 ጀምሮ በፔንስልቬንያ ከተዘገቡት የጎርፍ አደጋ ሞት ውስጥ ወደ ግማሽ የሚሆኑት ከተሽከርካሪዎች ጋር የተያያዙ ናቸው። እየነዱ ከሆነና በጎርፍ የተጥለቀለቀ መንገድ ላይ ከደረሱ ይህን ቀላል ሐረግ ያስታውሱ፡ "ተመልስ፣ አትስጠም®"። ሌላ የተለየ መንገድ ይፈልጉ፤ እንዲሁም በጎርፍ የተጥለቀለቀውን መንገድ ለማቋረጥ በጭራሽ ሙከራ አያድርጉ። ማንኛውንም የጎርፍ መቆጣጠሪያ ማገጃ ማለፍ ህገወጥ ነው። ይህ ዝርዝር የጎርፍ ውሃዎች በጣም አደገኛ የሆኑባቸውን በርካታ ምክንያቶች ያሳያል:-

- ስድስት ኢንች የሚሆን ውሃ፣ የአንድ ዶላር ኖት ርዝመት ያህል፣ አንዳንድ መኪኖች ሚዛናቸውን እንዲያጡ ወይም ድንገት እንዲቆሙ ሊያደርግ ይችላል።
- አሥራ ሁለት ኢንች የሚሆን የሚንቀሳቀስ ውሃ ብዙ መኪኖችን ማንሳፈፍ ይችላል።
- ሁለት ጫማ የሚሆን የሚንቀሳቀስ ውሃ አብዛኞቹን የ SUVs እና ፒክአፕ የጭነት መኪናዎች ሊያንቀሳቅስ ይችላል።
- በማንኛውም መንገድ ላይ ያለ ውሃ የጎደለ ንጣፍ እና ድልድዮችን ጨምሮ ብዙ አደጋዎችን ሊደብቅ ይችላል። የሚንቀሳቀስ ውሃ መንገዱን ሊያዳክም ይችላል።
- የሌሊት ጉዞ በጎርፍ የተጥለቀለቁ መንገዶችን ሊደብቅ ይችላል።

በጎርፍ በተጥለቀለቀ መንገድ ላይ ሲደርሱ ከሁሉ የተሻለው አማራጭ ወደሚፈልጉበት ቦታ የሚወስድ ሌላ መንገድ መፈለግ ነው። በጎርፍ ውሃ ውስጥ ከተያዙ በፍጥነት ከመኪናዎ ወጥተው ከፍ ወዳለ ቦታ ይሂዱ። ከብሔራዊ የአየር ሁኔታ አገልግሎት ስለ ጎርፍ የበለጠ መረጃ በኢንተርኔት ላይ ይገኛል:- www.weather.gov/safety/flood-turn-around-dont-drown

---

የእርስዎ አክስለሬተር (የፍጥነት መቆጣጠሪያ) የተጣበቀ ከሆነ

የፍጥነት መቆጣጠሪያው (የጋዝ ፔዳል) ከተጣበቀ ተሽከርካሪዎ በፍጥነት እየሄደ ሊቀጥል ይችላል።

ይህ ሁኔታ ከተፈጠረ:-

1. መንገድዎን በትኩረት ይመልከቱ። ፔዳሉን ጥቂት ጊዜ መታ በማድረግ ወደ መደበኛው ቦታው መመለሱን ማረጋገጥ ይችላሉ፤ወይም በእግር ጣትዎ ከፍ ሊያደርጉት ይችላሉ ነገር ግን ፔዳሉን ለማላቀቅ እጅዎን ዝቅ አያድርጉ።
2. ፔዳሉ ተጣብቆ የሚቆይ ከሆነ ወዲያውኑ ወደ ኒውትራል በማዞር ብሬክን ይጠቀሙ። ይህ ሞተርዎ እንዲጮህ ያደርገዋል ነገር ግን ኃይሉ ወደ ጎማዎችዎ እንዳይተላለፍ ያደርገዋል።
3. በማሽከርከር ላይ ትኩረት በማድረግ ፍጥነትዎን ከቀነሱ በኋላ ከመንገድ ዳር ያቁሙ። ያቁሙ፣ ሞተሩን ያጥፉ እና የአደጋ ጊዜ መብራቶችዎን ያብሩ።

ማሳሰቢያ:- በፍጥነት መቀነስ ወይም ማቆም ካስፈለገዎት ቁልፉን ወደ "OFF" ያዙሩ። ነገር ግን የማሽከርከር ችሎታዎን ሊያሳጣዎት ስለሚችል ወደ "LOCK" በጭራሽ አያዙሩት። ከዚያም ፍሬንዎን ይያዙ። ማቀጣጠያዎ (ኢግኒሽን) ጠፍቶ በሚያሽከረክሩበት እና ብሬክ በሚያደርጉበት (ፍሬን በሚይዙበት) ጊዜ ተጨማሪ ጥረት ይጠይቃል።

ተሽከርካሪዎ የፍሬን ችግር ካለው

በአዳዲስ ተሽከርካሪዎች ውስጥ፡ የተከፈለ የብሬኪንግ ሲስተም ሙሉ በሙሉ ፍሬን ያለመስራት ወይም የመበላሸት እድልን ይቀንሳል። የብሬክ ሲስተም ማስጠንቀቂያ መብራት ቢበራ ከአራቱ (4) ጎማዎች ውስጥ በሁለት (2) ላይ ብሬኪንግ ሊኖርዎት ይችላል፣ ምናልባትም አንድ (1) የፊት ጎማ እና አንድ (1) የኋላ ጎማ። ይህ ወደ መንገድ ዳር ለማቆም ወይም ወደሚቀጥለው የአገልግሎት መስጫ ጣቢያ ለመሄድ ያስችልዎታል። ተሽከርካሪው ቀስ እያለ ከመሄዱ በፊት የብሬክ ፔዳሉ ከመደበኛው የበለጠ ወደ ታች ሲወርድ ይሰማዎታል፣ እንዲሁም ፔዳሉን በበለጠ ኃይል መጫን ያስፈልግዎታል። የማቆሚያ ርቀትዎ ይጨምራል ስለዚህ መኪናዎ ወዴት እየሄደ እንደሆነ ልብ ይበሉ። ወደ ዝቅተኛ ማርሽ መቀየር ፍጥነትዎን ለመቀነስ ይረዳዎታል።

አሮጌ መኪና ካለዎትና ፍሬንዎ ድንገት ቢበላሽ የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርብዎታል

1. ወደ ዝቅተኛ ማርሽ ይቀይሩና ቀስ ብለው የሚያቆሙበት ቦታ ይፈልጉ።
2. የፍሬን ፔዳሉን በፍጥነት ደጋግመው ይጫኑ። ይህ ብዙውን ጊዜ ተሽከርካሪውን ለማቆም የሚረዳ በቂ የብሬክ ግፊት ይፈጥራል።
3. የብሬክ ፔዳሉን በተደጋጋሚ መጫን የማይሰራ ከሆነ የመኪና ማቆሚያውን ወይም ፓርክ ማድረጊያ (የአደጋ ጊዜ) ብሬክ ይጠቀሙ። የመኪና ማቆሚያውን ብሬክ መልቀቅ እንዲችሉ የኋላ ተሽከርካሪዎቹ ከተቆለፉና መንሸራተት ከጀመሩ የፍሬን መቆጣጠሪያውን ይያዙ።
4. ዓይኖችዎን በሚሄዱበት ቦታ ላይ ያተኩሩና ከመንገድ ለመውጣት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ይፈልጉ። መሪውን ለማዞር ክፍት ቦታ ይፈልጉ፣ ወይም ወደ ላይ ወደሚወጣ መንገድ ያዙሩ።
5. ተሽከርካሪው አሁንም ካልቆመ እና የመጋጨት አደጋ ላይ ከሆኑ የመጨረሻ አማራጭዎ ማቀጣጠያዎን “OFF” ያድርጉት። መሪዎን ስለሚቆልፈው ወደ “LOCK” ቦታ አያዙሩት። በመቀጠል ወደ ዝቅተኛው ማርሽ ይቀይሩ። ይህ የእሽክርክሪት ማስተላለፊያዎን ሊጎዳ ይችላል ስለዚህ ይህንን የሚያደርጉት ከመጋጨት እራስዎን ለመጠበቅ እንደ የመጨረሻ አማራጭ ብቻ ነው።

ተሽከርካሪዎን ካቆሙ በኋላ ለእርዳታ ይደውሉ። ለመንዳት አይሞክሩ።

የጎማ መፈንዳት ቢያጋጥምዎት

ጎማ ከመፈንዳቱ በፊት አንዳንድ ጊዜ ድብደባ ድምፆች ይጀምራሉ፣ነገር ግን ጎማ መቼ እንደሚተኮስ አስቀድመው አያውቁም። ጎማዎትን በጥሩ ሁኔታ በመጠበቅ እና በልክ በመሙላት ከመፈንዳት መከላከል አለብዎት።

የፊት ጎማ ሲፈነዳ መሪዎ ይንቀጠቀጣል፣ እና ተሽከርካሪው በድንገት ወደ አንድ ጎን ሲጎተት ይሰማዎታል። የኋላ ጎማ ሲፈነዳ የተሽከርካሪው አንድ ጥግ በድንገት ይወርዳል፣ እና የተሽከርካሪው የኋላ ክፍል ወደ ኋላ እና ወደ ፊት ሲወዛወዝ ይሰማዎታል።

ከጎማዎችዎ ውስጥ አንዱ ቢፈነዳ የሚከተሉትን ያድርጉ፦

1. መሪውን አጥብቀው ይያዙ።
2. ፍሬንዎን (ብሬክዎን) አይጠቀሙ! ጎማ ከፈነዳ በኋላ ፍሬን መያዝ እንዲንሸራተቱና በተሽከርካሪዎ ላይ ያለውን ቁጥጥር እንዲያጡ ያደርጋል።
3. እግርዎን ከጋዝ ፔዳሉ ላይ በቀስታ ያንሱ።
4. መሄድ ወደሚፈልጉበት አቅጣጫ ይምሩ፣ ነገር ግን በተረጋጋ ሁኔታ ይምሩ-ትላልቅ ወይም ድንገተኛ የመሪ እንቅስቃሴዎችን አያድርጉ።

ወደ ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ለመድረስ እና ለመቀየር እስከተፈለገ ድረስ በፈንዳ ጎማ መንዳት ይችላሉ። ፍሬንዎን መጠቀም ካለብዎት በቀስታ ይጫኑ። ተሽከርካሪው ቀስ እያለ እንዲቆም ያድርጉ። ጎማውን ከመቀየርዎ በፊት ተሽከርካሪዎ ከመንገድ ውጭ መሆኑን ያረጋግጡ።

የፈነዳ ጎማን እንዴት መቀየር ይቻላል

ጎማዎን ለመቀየር የሚያስፈልጉዎትን መሳሪያዎች ሁል ጊዜ በተሽከርካሪዎ ውስጥ ያስቀምጡ፣ ማለትም፣ መለዋወጫ ጎማ፣ የጎማ ብሎን መፍቻ፣ ማንሻ፣ ካቻብቴ የእጅ ባትሪ፣ ችቦ እና ባለ ሶስት መዐዝን አንጸባራቂ፣ የጎማ መከለከያ፣ የተኛ ጎማ መጠገኛ ኪት፣ ጓንቶች፣ ወዘተ።

ጎማ ለመቀየር መሰረታዊ መመሪያዎች። **ማሳሰቢያ፦** ሂደቱ ከተሽከርካሪ ወደ ተሽከርካሪ ሊለያይ ስለሚችል እባክዎ የተሽከርካሪውን ባለቤት መመሪያ ይመልከቱ።

1. ተሽከርካሪውን ከትራፊክ ፍሰት (ከተሽከርካሪዎች) ራቅ ባለ እና በተቻለ መጠን ከመንገድ ውጭ ባለ ሜዳ መሬት ላይ ያቁሙ።
2. የእጅ ፍሬን ይጫኑ እንዲሁም ጡቦችን፣ የጎማ መደገፍያ ታኮን ወይም የጎማ ማቆሚያዎችን ከቀሩት ጥሩ ጎማዎች በአንዱ የፊትና የኋላ በኩል በማስቀመጥ ተሽከርካሪውን ያስጠብቁ።
3. ተሽከርካሪው የጎማ መሸፈኛ ወይም የጎማ ክዳን ካለው ካቻብቴ ወይም የጎማ ብሎን መፍቻውን ጠፍጣፋ ጫፍ በመጠቀም በጥንቃቄ ይንቀሉት።
4. ተሽከርካሪው መሬት ላይ እያለ ተሽከርካሪው መቀርቀሪያዎችን (ብሎኖችን) በሚስማማው የጎማ ብሎን መፍቻ ጫፍ በመጠቀም ብሎኖቹን ይፍቱ። በዚህ ጊዜ ላይ የጎማዎቹን መቀርቀሪያዎች ከጎማው ላይ ሙሉ በሙሉ አያስወግዱ።
5. መሰኪያውን (ጃኩን) በተሽከርካሪው ፍሬም ወይም ሱስፐንሽን ስር ወይም መሰኪያው (ጃኩ) በትክክል መቀመጥ ያለበትን ቦታ ለማወቅ የተሽከርካሪውን ባለቤት መመሪያ በመመልከት በጠንካራ መሬት ላይ በአስተማማኝ ሁኔታ ያስቀምጡ። ጎማው ከመሬት በግምት 6 ኢንች እስኪነሳ ድረስ ተሽከርካሪውን በመሰኪያው (በጃኩ) ያንሱት።
6. የጎማዎቹን ብሎኖች ሙሉ በሙሉ ያስወግዱ እና ደህንነቱ በተጠበቀ ቦታ ያስቀምጧቸው (በጎማው መሸፈኛ ውስጥ ወይም የጎማ ክዳን ውስጥ ማስቀመጥ ጥሩ ነው)። ጉድለት ያለበትን ጎማ በሁለቱም እጆችዎ በመያዝ እና ከጉድጓዶቹ ላይ ቀጥታ እና በእኩል መጠን በመሳብ ያስወግዱት።
7. መለዋወጫውን የተሽከርካሪ ጎማ፡ በጎማው መቀርቀሪያዎች (ብሎኖች) ላይ ይጫኑ እና ሁሉንም መቀርቀሪያዎች (ብሎኖች) በእጅዎ ያስጠብቁ። መቀርቀሪያዎቹ በትክክል ከተጣበቁ በኋላ የጎማውን መቀርቀሪያ ለማጠንከር መፍቻውን መጠቀም ይቻላል፤ ነገር ግን አነስተኛ ግፊት ብቻ ይጠቀሙ (በዚህ ጊዜ መቀርቀሪያዎቹን ሙሉ በሙሉ አያጥብቁ)።
8. ተሽከርካሪውን (መኪናውን) ቀስ ብለው ወደ መሬት ዝቅ ያድርጉት፣ ነገር ግን በዚህ ጊዜ መሰኪያውን (ጃኩን) ከተሽከርካሪው ስር አያስወግዱት።
9. ትክክለኛውን የማጠንከሪያ ቅደም ተከተል እና መግለጫ ለማግኘት የተሽከርካሪውን ኦፕሬተር መመሪያ ከተመለከቱ በኋላ የጎማዎቹን መቀርቀሪያዎች በመፍቻው አጥብቀው ይዝጉ።
10. መሰኪያውን (ጃክ)፣ ጎማውን/ተሽከርካሪ ጎማውን፣ መሣሪያዎቹን እና የደህንነት መሣሪያዎችን በተሽከርካሪው የኋላ ክፍል ውስጥ ያስቀምጡ።

ተሽከርካሪው የጎማ መሸፈኛዎች ወይም የጎማ ክዳኖች ካሉት፣ የባለቤቱ መመሪያ እንዴት እንደሚገጠሙ መረጃ መስጠት አለበት። ተሽከርካሪው የመሃል ክዳን ካለው የመሃሉን ክዳን ከጎማው ጋር በማያያዝ በእጅዎ ተረክዞ ቀስ አድርገው ይምቱት። ከመነሳትዎ በፊት የጎማውን ሽፋን ወይም የመሃሉ ክዳኑን ደህንነት ያረጋግጡ።

ተሽከርካሪዎ ከመንገዱ ወጥቶ ወደ ዳር ከሄደ

የመንገዱ ዳር ከመንገዱ ወለል ዝቅ ያለ በሚሆንበት ወቅት በመንገድ ጠርዝ አካባቢ "ከመንገድ መውጣት" ካጋጠምዎ በኋላ መሪን እንዴት መልሰው መቆጣጠር እንደሚችሉ ካላወቁ ከባድ አደጋ ሊያስከትል ይችላል። ወደ መንገዱ ዳር በጣም ተጠግተው እየነዱ ከሆነ ወይም በጠመዝማዛ መንገድ

ላይ በከፍተኛ ፍጥነት እየነዱ የፊት ጎማዎ ከመንገዱ እንዲወጣ ከፈቀዱ "ከመንገድ መውጣት" ሊከሰት ይችላል።

"ከመንገድ መውጣት" በተለይም በገጠር መንገዶች ላይ በጣም የተለመዱ ናቸው። መንገዶች እንደ አዲስ እየተነጠፉ ባለባቸው ቦታዎች እና በመንገድ ዳሩ ላይ የቆመ የዳር መከላከያ ባለባቸው ቦታዎች ላይም ሊከሰቱ ይችላሉ።

እንዴት መመለስ እንደሚችሉ ካላወቁ ከ"መንገድ መውጣት" በፍጥነት ድንገተኛ አደጋ ሊሆን ይችላል። ማስታወስ ያለብዎት በጣም አስፈላጊ ነገሮች፦ በድንገት መሪውን አያዙሩ፣ እና በድንገት ፍሬን (ብሬክን) አይያዙ። ወደ መንገዱ ለመመለስ መሪውን በኃይል ካዞሩት ተሽከርካሪው በድንገት ወደ ጎን በመዞር ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ከሚመጣ ተሽከርካሪ ጋር እንዲጋጭ ሊያደርግ ይችላል። ሁለት (2) ጎማዎች በመንገዱ ላይ እና ሁለት (2) ጎማዎች በለስላሳ ዳር ላይ ካሉ በኃይል ፍሬን (ብሬክ) ከያዙ ተሽከርካሪው መቆጣጠር ያቅትዎታል።

ከመንገዱ ከወጡ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት

1. በቀኝ በኩል ያሉት ሁለቱም ጎማዎችዎ ከመንገዱ ሲወጡ ፍጥነትዎን ለመቀነስ እግርዎን ከጋዝ ፔዳሉ በቅስታ ያንሱ። **በድንገት ፍሬን አይያዙ።** በመንገድ ዳሩ ላይ አደጋን ለማስወገድ ፍሬን መያዝ ካለብዎት ጎማዎቹ እንዳይቆለፉ ለመከላከል ቀስ በቀስ እና በተቆጣጠረ መልኩ ፍሬን ይያዙ።
2. መሪውን አጥብቀው ይያዙ፣ እና ከመንገዱ ጋር ትይዩ በመሆን ሁለት (2) ጎማዎች በመንገዱ ላይ እና ሁለት (2) ጎማዎች ከመንገዱ ውጪ (የመንገዱን ጫፍ ተሻግረው) መሪውን በመያዝ ያሽከርክሩ። ጎማዎቹ የመንገድ ንጣፉን ጠርዝ እንዳይፈትጉ ይጠብቁ። ረጋ ይበሉ እና መሪውን አጥብቀው ይያዙ። ለስላሳ ወይም እርጥብ የመንገድ ዳር ተሽከርካሪዎን ወደ ቀኝ ይስባል። **ወደ መንገዱ ለመመለስ በኃይል መሪውን አያዙሩ።**
3. ተሽከርካሪዎን መቆጣጠር እስከሚችሉ ድረስ በቀስታ እንተጓዙ እስካሉ ድረስ ቀስ በቀስ ፍጥነትዎን ይቀንሱ - ከ25 ማይል በሰዓት ያነሰ እና በተለይም ወደ 10 ማይል በሰዓት ቢጠጋ ይመረጣል።
4. ወደ ቀድሞው የመንገድ መስመርዎ ከመመለስዎ በፊት ከኋላ የሚመጣ መኪና መኖር አለመኖሩን ያረጋግጡ። የግራ መታጠፊያ ምልክትዎን ያብሩ።
5. ሁኔታው ምቹ ሲሆን ቀስ ብለው ወደ ግራ በመጠምዘዝ የቀኝ ጎማዎቹን ወደ መንገዱ ይመልሱ። ጎማዎችዎ ወደ መንገዱ እንደተመለሱ ሲሰማዎት ወዲያውኑ ቀጥ ለማድረግ በቀስታ ወደ ቀኝ ያዙሩ።
6. ወደ መንገዱ ላይ በአስተማምኝ ሁኔታ ከተመለሱና ተሽከርካሪዎን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ከቻሉ በኋላ የተሽከርካሪዎን ፍጥነት ከትራፊክ ፍሰት (ከሌሎቹ ተሽከርካሪዎች) ፍጥነት ጋር ያስተካክሉ።

ሌላ ተሽከርካሪ ከፊት ለፊት በእርስዎ ሌይን (የመንገድ መስመር) እየመጣ ከሆነ

መጀመሪያ ትኩረቱን ለመሳብ የመኪናዎ የክላክስ ድምጽ ይጠቀሙ። ሌላው ሹፌር ቦታ ካልለቀቀ የሚቻል ከሆነ ወደ ቀኝ ለማምለጥ ይሞክሩ። ወደ ግራ ቢዞሩ እና ሌላኛው ሹፌር በመጨረሻው ቅጽበት ቢያስተካክል አሁንም ይጋጫሉ። ግጭትን ማስቀረት የማይቻል ከሆነ ጠበቅ በማድረግ እና በጽኑ ሁኔታ ፍሬን ይያዙ። እያንዳንዱን የሚቀንሱት የማይል በሰዓት ፍጥነት የግጭቱን ተጽዕኖ ይቀንሳል።

የቀብር ሥነ-ስርዓት ሰልፍ

በመንገድ ላይ የቀብር ሥነ ሥርዓት ሰልፍ ካዩ ለሰልፉ ተሽከርካሪዎች ቦታ ይልቀቁላቸው። የመጀመሪያው ተሽከርካሪ የመንገድ መገናኛውን ካለፈ በኋላ የተቀረው ሰልፍ ወደ መስቀለኛ መንገዱ መሄድ ይችላል፤ ሌሎች ተሽከርካሪዎች ደግሞ ቦታ መልቀቅ አለባቸው። ሰልፉ እንዲያልፍ ይፍቀዱ እና በፖሊስ መኮንን ወይም በቀብር አስፈፃሚ ወኪል ወይም ሰራተኛ ሌላ መመሪያ ካልተሰጠዎት በስተቀር ወደ ሰልፉ ውስጥ አይግቡ ወይም ከሰልፉ ውስጥ አይውጡ።

በቀብር ሥነ ሥርዓት ሰልፍ ውስጥ ያሉ ሁሉም ተሽከርካሪዎች የፊት መብራታቸውን እና የድንገተኛ አደጋ መብራታቸውን ማብራት እና የሰልፉ አካል መሆናቸውን የሚያመለክት ባንዲራ ወይም ሌላ ምልክት ሊኖራቸው ይገባል። በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ያሉ ተሽከርካሪዎች በሰልፉ ወቅት ብልጭ የሚል ወይም የሚሽከረከር ሐምራዊ ቀለም ያለው መብራት ሊኖራቸው ይችላል።

በቀብር ሥነ ሥርዓት ሰልፍ ውስጥ ያሉ አሽከርካሪዎች መሪው ተሽከርካሪ መብራቱ አረንጓዴ በሚሆንበት ጊዜ የመንገዶች መገናኛውን ማለፍ ከጀመረ ቀይ መብራት ወይም የማቆሚያ ምልክት ቢያጋጥማቸውም መሄድ ይችላሉ። የማቆሚያ ምልክት ባለበት ሁኔታ መሪው ተሽከርካሪ ወደ መስቀለኛ መንገዱ (ወደ መገናኛው) ከመግባቱ በፊት ሙሉ በሙሉ ማቆም ይኖርበታል። የቀብር ሥነ ሥርዓት ሰልፎች ለአስቸኳይ ጊዜ ተሽከርካሪዎች (እንደ አምቡላንስ እና የፖሊስ መኪና ላሉ) ቅድሚያ መስጠት አለባቸው።

ምዕራፍ 3 ማጠቃለያ ጥያቄዎች

1. ታዳጊ ወጣት ሹፌሮች አደጋ ውስጥ ለመግባት የበለጠ የሚጋለጡት መቼ ነው፡-
- A. የቤት እንስሳቸውን እንደ ተሳፋሪ ይዘው ሲነዱ
- B. አዋቂ ተሳፋሪዎች ይዘው ሲነዱ
- C. ታዳጊ ወጣት ተሳፋሪዎች ይዘው ሲነዱ
- D. ያለ ምንም ተሳፋሪ ሲነዱ

2. በሚነዱበት ጊዜ የሚበሉ እና የሚጠጡ አሽከርካሪዎች፡-
- A. ምንም የመንዳት ስህተት የለባቸውም
- B. ፍጥነታቸውን ቀንሰው ለመንዳት ይቸገራሉ
- C. የተራቡ ስላልሆኑ የተሻለ አሽከርካሪዎች ይሆናሉ
- D. ተሽከርካሪዎቻቸውን ለመቆጣጠር ይቸገራሉ

3. በሚያሽከርክሩበት ጊዜ ለማጨስ መዘጋጀት እና ማጨስ፡-
- A. የመንዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ የለውም
- B. የአሽከርካሪው ንቃት ለመጠበቅ ይረዳል
- C. ትኩረትን የሚሰርቁ ተግባራት ናቸው
- D. ትኩረትን የሚሰርቁ ተግባራት አይደሉም

4. በፔንስልቬንያ ለሚገኙ የ16 ዓመት አሽከርካሪዎች ዋነኛው ከፍተኛ የመኪና አደጋ አይነት የትኛው ነው፡-
- A. አንድ ተሽከርካሪ ብቻ የሚያካትት / ከመንገድ ዳር የመውጣት አደጋ
- B. በአውራ ጎዳና ላይ ጎን ለጎን መገጨት አደጋ
- C. በጎንዮሽ መንገድ ላይ ወደኋላ መንዳት
- D. በአውራ ጎዳና ዳር ላይ መንዳት

5. ብስክሌተኛን በሚያልፉበት ጊዜ የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት፡-
- A. ብስክሌተኛውን ለማስጠንቀቅ የመኪናዎ የክላክስ ድምጽ ያሰሙት
- B. በተቻለ መጠን ወደ ግራ በኩል ይንቀሳቀሱ
- C. በመንገዱ መስመር መሃል ላይ ይቆዩ
- D. አራቱንም የአደጋ መብራቶችዎን ያብሩ

6. ልጆች በሚጫወቱበት አካባቢ ሲያሽከረክሩ ከልጆቹ የሚከተሉትን ይጠብቁ፡-
- A. መቼ በደህና መሻገር እንደሚችሉ እንደሚያውቁ
- B. መንገዱን ከመሻገራቸው በፊት ዳር ላይ እንደሚቆሙ
- C. ሳይመለከቱ ከፊትዎ በድንገት ሊሮጡ እንደሚችሉ
- D. ከአዋቂ ሰው ጋር ካልሆኑ በስተቀር እንድማይሻገሩ

7. ከሞተር ሳይክል ጀርባ እየነዱ ከሆነ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
- A. ሞተር ሳይክሉ ሙሉ ሌይን (የመንገድ መስመር) እንዲጠቀም መፍቀድ
- B. ከሞተር ሳይክሉ ጎን ባለው የመንገዱ ዳር መንዳት
- C. ሞተር ሳይክሉ ግማሽ የመንገድ መስመር (ሌይን) ብቻ እንዲጠቀም መፍቀድ
- D. ሞተር ሳይክሉ እየተጓዘበት ባለው የመንገድ መስመር (ሌይን) በኩል ማለፍ

8. ከሞተር ሳይክል ጀርባ በሚጓዙበት ጊዜ፡-
- A. ቢያንስ የ2 መኪና ርዝመት ርቀት በመተው መከተል
- B. ቢያንስ የ2 ሰከንድ ርቀት በመተው መከተል
- C. ቢያንስ የ4 ሰከንድ ርቀት በመተው መከተል
- D. ቢያንስ የ4 ሞተር ሳይክሎች ርዝመት ርቀት በመተው መከተል

9. ነጭ በትር የሚጠቀም እግረኛ በአቅራቢያዎ ካለ ተጨማሪ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልግዎታል ምክንያቱም፡-
- A. መስማት የተሳነው ነው
- B. የአእምሮ እክል አለበት
- C. ማየት የተሳነው ነው
- D. የመራመድ ችግር አለበት

10. ነጭ በተር የያዘ ወይም በውሻ እርዳታ የሚመራ ማየት የተሳነው እግረኛ በአቅራቢያ ካለ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
- A. ፍጥነትዎን ይቀንሱ እና ለማቆም ይዘጋጁ
- B. በቅድሚያ እርስዎ ይሂዱ
- C. በተለመደው ሁኔታ ይቀጥሉ
- D. መኪናዎን በፍጥነት ይንዱ

11. አንድ አሽከርካሪ ሲታጠፍ እና እግረኛው ያለ የትራፊክ መብራት መንገድ ሲያቋርጥ ማን ነው ቅድሚያ መስጠት ያለበት?
- A. መጨረሻ ላይ የጀመረው
- B. አሽከርካሪው
- C. ፍጥነቱን የቀነሰው
- D. እግረኛው

12. በተሽከርካሪ ጀርባ ላይ ያለው ብርቱካናማ ባለ ሶስት መዓዝን ቅርጽ የሚያመለክተው፡ ተሽከርካሪው፡-
- A. ራዲዮአክቲቭ ንጥረ ነገሮችን የያዘ መሆኑን
- B. ሰፋ ብሎ የሚታጠፍ መሆኑን
- C. ከተለመደው የተሽከርካሪ ፍጥነት ባነሰ ፍጥነት የሚሄድ መሆኑን
- D. በተደጋጋሚ የሚቆም መሆኑን

13. በሌሊት ለማየት በጣም አስቸጋሪ የሆነው የትኛው ነው፡-
- A. የመንገድ ምልክቶች
- B. እግረኞች
- C. ሌሎች አሽከርካሪዎች
- D. የመንገድ መብራቶች

14. ከኋላዎ ያለው የጭነት መኪና ሹፌር ተሽከርካሪዎን ማለፍ ሲፈልግ፡ ፍጥነትዎ ምን መሆን አለበት፡-
- A. በነበረበት መቀጠል ወይም መቀነስ
- B. የመንገድ መስመርን መቀየር
- C. መቀየር
- D. መጨመር

15. መንገዱን ከጭነት መኪና ጋር በሚጋሩበት ጊዜ የሚከተለውን ማስታወስ አስፈላጊ ነው፣ በአጠቃላይ የጭነት መኪናዎች፡-
- A. ለማቆም ከተለመዱት መኪናዎች የበለጠ ረጅም ርቀት ይውሰዳሉ
- B. ቁልቁለት ላይ መኪናዎችን ለማለፍ አነስተኛ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል
- C. ከተለመዱት መኪናዎች ያነሰ የማዞሪያ ራዲየስ (ርቀት) ያስፈልጋቸዋል
- D. በዳገት መንገድ ወደ ላይ ለመውጣት ከተለመዱት መኪናዎች ያነሰ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል

16. ከአንድ በላይ ትራክ (የሃዲድ መስመር) ባለው የባቡር ሐዲድ ማቋረጫ ጋር ቢያቆሙ፡-
- A. ሁለቱንም ትራኮች (የሃዲድ መስመሮች) በግልጽ እስክታዩ ድረስ ይጠብቁ
- B. በባቡር ሀዲዱ ላይ ያቁሙ እና ሌላ ባቡር ይመልከቱ
- C. ባቡሩ እንዳለፈ ወዲያውኑ ያቋርጡ
- D. ከሃዲድ መስመሮቹ አንዱ ክፍት ሲሆን ይለፉ

17. በአንድ መገናኛ ላይ ወደ ቀኝ ከመታጠፉ በፊት ወደ ግራ ጠምዘዝ ማለት ያለበት የጭነት መኪና እየተከተሉ ከሆነ ከሚከተሉት ውስጥ በጣም አደገኛ መሆኑን ማስታወስ ያለብዎት፡-

A. ወደ ቀኝ ለመታጠፍ በጭነት መኪናው እና በዳር መካከል ለመግባት/ለመጓዝ መሞከር
B. የጭነት መኪናው ሙሉ ለሙሉ እስኪታጠፍ ድረስ ፍሬንዎን መያዝ
C. የ"4 - ሰከንድ" ርቀት በመተው የመከተል ህግን መጣስ
D. የመኪናዎ የክላክስ ድምጽ ለጭነት መኪና ሹፌሩ ማሰማት

18. ቀይ መብራቶቹ በሚበሩበት እና የቁም ክንድ በተዘረጋበት የትምህርት ቤት አውቶቡስ መቆም የሌለብዎት ብቸኛው ጊዜ መቼ ነው፡-

A. በተከፈለ የቁም ክንድ በተቃራኒው አቅጣጫ በኩል እየነዱ ከሆነ
B. ከአውቶቡሱ በስተጀርባ ከሆኑ
C. ልጆች በአካባቢው እንደሌሉ ሲመለከቱ
D. በግራ በኩል በአስተማማኝ ሁኔታ ማለፍ የሚችሉ ሲሆን

19. የትምህርት ቤቱ አውቶቡስ መብራቶቹን ሲያበራ እና የቁም ክንድ ሲዘረጋ ምን ማድረግ አለብዎት፡-

A. ከአውቶቡሱ ቢያንስ የ10 ጫማ ርቀት ላይ ማቆም
B. ልጆች ከአውቶቡስ ከወጡ ማለፍ
C. አውቶቡሱ ከአጥር በተቃራኒው በኩል ከሆነ ማቆም
D. ከአውቶቡሱ አጠገብ በቀስታ መንዳት

20. አንድ ባቡር ካለፈ በኋላ የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት፡-

A. የሚመጡ ተጨማሪ ባቡሮችን ማረጋገጥ እና በጥንቃቄ ማለፍ
B. አረንጓዴ መብራት መጠበቅ
C. በሃዲዱ መሻገር መቀጠል
D. የክላስ ድምጽ ማሰማት እና መቀጠል

21. ሌሎች አሽከርካሪዎች ባልጠበቁት ሁኔታ ፍጥነትዎን መቀነስ ወይም ማቆም ካለብዎት የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት፡-

A. የፍሬን ፔዳልዎን በፍጥነት ጥቂት ጊዜ ይንኩ
B. የእጅ ፍሬን (ብሬክ) ይጠቀሙ
C. ለማየት በሚያዳግት ቦታ ውስጥ ያለ ተሽከርካሪ ለማየት ወደ ጎን ይመልከቱ
D. የክላክስ ድምጽ ለማሰማት ዝግጁ ይሁኑ

22. ለመታጠፍ ሲያቅዱ የመታጠፊያ የመብራት ምልክቶችዎን ማብራት ያለብዎት መቼ ነው፡-

A. ሌሎች አሽከርካሪዎች እርስዎን እየተከተሉ ከሆነ ብቻ
B. የመኪናዎ የፊት ክፍል ልክ ወደ መገናኛው ሲደርስ
C. መገናኛው ጋር ከመድረስዎ ከ 3 እስከ 4 ሰከንድ በፊት
D. ወደ መገናኛው ከመድረስዎ በፊት የ2 የመኪኖች ርዝመት

23. ሌላ መኪናን ከማለፍዎ በፊት ምን ማድረግ አለብዎት፡-

A. አሽከርካሪውን ለማስጠንቀቅ የፊት መብራቶችዎን ብልጭ ድርግም በማድረግ ያብሩ
B. አሽከርካሪውን ለማስጠንቀቅ አራቱ የአደጋ ጊዜ መብራቶችዎን ያብሩ
C. የመንገድ መስመሩን እየቀየሩ መሆኑን ለማሳየት ትክክለኛውን የመታጠፊያ ምልክት ይስጡ
D. የአሽከርካሪዎችን ትኩረት ለመሳብ የመኪናዎን የክላክስ ድምጽ ያሰሙ

24. ለእርስዎ ለማየት የሚያዳግት ቦታ ማለት፡-

A. ጭንቅላትዎን ሳያዞሩ ማየት የማይችሉት
B. በቀጥታ ከመኪናዎ ጀርባ
C. በኋለኛው መመልከቻ መስታወትዎ የሚያዩት
D. በጎን መስተዋትዎ ውስጥ የሚያዩት

25. ሌላ ተሽከርካሪ ከማለፍዎ በፊት ምልክት (ሲግናል) መስጠት ያለብዎት፦
- A. የመንገድ መስመሩን ከመቀየርዎ በፊት ትንሽ ቀደም ብለው
- B. በማንኛውም ጊዜ
- C. የመንገድ መስመርን ከቀየሩ በኋላ
- D. ሌሎች ሰዎች እቅድዎን እንዲያውቁ በቂ ጊዜ በሚሰጥ ሁኔታ

26. በባለ ብዙ የመንገድ መስመር ሀይዌይ (አውራ ጎዳና) ላይ የመንገድ መስመር (ሌይን) ከመቀየርዎ በፊት ምን ማድረግ ያለብዎት፦
- A. የክላክስ ድምጽ ያሰሙ
- B. የፊት መብራቶችዎን ያብሩ
- C. ፍጥነትዎን ይቀንሱ
- D. መስተዋቶችዎን እና ለማየት የሚያዳግቱ የመንገዱ ቦታዎችን ያረጋግጡ

27. በመንገድ ላይ መኪናዎን በሚያቆሙበት ጊዜ ምን ማድረግ አለብዎት፦
- A. አራቱ የአደጋ ጊዜ መብራቶችዎን ይጠቀሙ
- B. በሰያፍ ማዕዘን አኳሃን ያቁሙ
- C. የመታጠፊያ ምልክትዎን እንደበራ ያቆዩት
- D. መብራቶችዎን ያብሩ

28. ወደ ኋላ ከመንዳትዎ በፊት ምን ማድረግ አለብዎት፦
- A. ለመቀጠል መንገዱን ክፍት እንደ ሆነ ለማየት በመስተዋቶችዎ ላይ ይተማመኑ
- B. መብራቶችዎን ብልጭ ድርግም በማድረግ ያብሩ
- C. ለመቀጠል መንገዱ ክፍት እንደሆነ ለማየት በርዎን ይክፈቱ
- D. ጭንቅላትዎን በማዞር በኋለኛው መስኮት በኩል ይመልከቱ

29. ግጭቶችን ለማስቀረት ለመርዳት ማድረግ ያለብዎት፦
- A. በመንገድ ላይ ካሉ ሌሎች አሽከርካሪዎች ጋር ይነጋገሩ
- B. በመንገድ ላይ ላሉ ሌሎች አሽከርካሪዎችን ትኩረት አይስጡ
- C. በጎን መንገዶች እና በትንንሽ መንገዶች ይንዱ
- D. በትራፊክ መጨናነቅ ሰዓት ላይ ከመንዳት ይቆጠቡ

30. አሽከርካሪው ምን እያደረገ ነው፦

- A. ፍጥነት እየቀነሰ ወይም እያቆመ
- B. ወደ ግራ እየታጠፈ ነው
- C. ወደ ቀኝ እየታጠፈ
- D. በሩን እየከፈተ

31. የመታጠፊያ የመብራት ምልክቶችዎ ካልሰሩ ሊታጠፉ መሆኑዎን ለማመልከት _____ ን መጠቀም አለብዎት።
- A. የመኪናዎ የክላክስ ድምጽ
- B. የፊት መብራቶችዎ
- C. የእጅ ምልክቶች
- D. የአደጋ ጊዜ ብልጭ የሚሉ መብራቶችዎ

32. የተገደበ አገልግሎት ባለው ሀይዌይ (አውራ ጎዳና) ላይ በሰዓት ከ40 ማይል ባነሰ ፍጥነት ሲጓዙ ምን ማድረግ አለብዎት፦
- A. በመንገድ ዳር ይንዱ
- B. ከፍተኛ ጨረር ያላቸውን መብራቶችዎን ይጠቀሙ
- C. ሌሎችን ለማስጠንቀቅ የመኪናዎ የክላክስ ድምጽ ያሰሙ
- D. አራቱ የአደጋ ጊዜ መብራቶችዎን ይጠቀሙ

33. የመኪናዎ የክላክስ ድምጽ ማሰማት ያለብዎት መቼ ነው፦
- A. በመገንዶች መገናኛ ውስጥ ሲጓዙ
- B. ብስክሌተኛን ሲያልፉ
- C. ወደ ተሽከርካሪ መንገድ ሊሮጥ ያለ ልጅ ሲያዩ
- D. መኪናዎን በመንገዱ የዳር መስመር ትዩዩ በማድረግ እያቆሙ ከሆነ

34. የፊት መብራቶችዎን መጠቀም ያለብዎት ሌሎች ተሽከርካሪዎች ከ ______ ጫማ ርቀት ላይ የማይታዩ ከሆነ ነው።

A. 1000
B. 1500
C. 1800
D. 1200

35. ከፍተኛ ጨረር ያላቸውን መብራቶች የሚጠቀም ተሽከርካሪ ወደ እርስዎ ከመጣ ምን ማድረግ አለብዎት፦

A. ከፍተኛ ጨረር ያላቸውን መብራቶችዎን ያብሩ
B. የግንባር መብራቶችዎን ያጥፉ
C. የክላክስ ድምጽ ያሰሙ
D. ከፍተኛ ጨረር ያላቸውን መብራቶችዎን ብልጭ በማድረግ ያብሩ

36. ከፍተኛ ጨረር ያላቸውን መብራቶች የሚጠቀም ተሽከርካሪ ወደ እርስዎ ከመጣ የመንገዱን ______ መመልከት አለብዎት።

A. ሁለቱም ጎኖች
B. የመሃል ክፍል
C. የቀኝ ጎን
D. የግራ ጎን

37. የመኪናዎ የክላክስ ድምጽ መጠቀም የሚችሉት መቼ ነው፦

A. በፍጥነት ማቆም ሲኖርብዎት
B. ሌላ መኪናን ሲያልፉ
C. መኪናዎን መቆጣጠር ሲያቅትዎት
D. ብስክሌተኛን ሲያልፉ

38. የብሬክ (የፍሬን) መብራቶችዎ ለሌሎች አሽከርካሪዎች የሚነግሩት ምንድን ነው፦

A. እየታጠፉ መሆንዎን
B. የድንገተኛ ጊዜ ብሬክዎን (ፍሬንዎን) እየተጠቀሙ መሆንዎን
C. የመንገድ መስመር እየቀየሩ መሆንዎን
D. ፍጥነትዎን እየቀነሱ ወይም እያቆሙ መሆንዎን

39. ከመታጠፍዎ በፊት ማድረግ ያለብዎት፦

A. ምልክትዎን (ሲግናልዎን) ይጠቀሙ
B. ጎማውን ያዙሩ
C. ፍጥነትዎን ይጨምሩ
D. የመንገድ መስመርን ይቀይሩ

40. አሽከርካሪው፦



A. ወደ ግራ እየታጠፈ ነው
B. ፍጥነቱን እየቀነሰ ነው
C. እያቆመ ነው
D. ወደ ቀኝ እየታጠፈ

41. አሽከርካሪው፦

A. ወደ ግራ እየታጠፈ ነው
B. ፍጥነቱን እየቀነሰ ነው
C. እያቆመ ነው
D. ወደ ቀኝ እየታጠፈ

42. ሌላ መኪና ሊመታዎት የሚችልበት አደጋ ካለ ምን ማድረግ አለብዎት፦

A. የክላክስ ድምጽ ያሰሙ
B. እጆችዎን ያውለብልቡ
C. የድንገተኛ (የአደጋ) ጊዜ መብራቶችዎን ይጠቀሙ
D. የግንባር መብራቶችዎን ብልጭ በማድረግ ያብሩ

43. በሚነዱበት ጊዜ ድካም ከተሰማዎት ማድረግ ያለብዎት ከሁሉ የተሻለው ነገር ምንድን ነው፦

A. ቡና ይጠጡ
B. መስኮትዎን ይክፈቱ
C. ማሽከርከር ያቁሙ
D. ሬዲዮኑን ይክፈቱ

44. እንቅልፍ ማጣት በመኪና የመንዳት ደህንነትዎ ላይ ያለው ተፅዕኖ ከሚከተሉት ውስጥ ከየትኛው ጋር ተመሳሳይ ነው፦

A. አልኮል የሚያሳድረው ተጽዕኖ
B. አምፌታሚን የሚያሳድረው ተጽዕኖ
C. ቁጣ የሚያሳድረው ተጽዕኖ
D. ከታዳጊ ወጣቶች ጋር መንዳት የሚያሳድረው ተጽዕኖ

45. ታዳጊዎች ወጣቶች በእንቅልፍ ማጣት የሚመጣ አደጋን ለማስወገድ በየምሽቱ ቢያንስ የ _________ እንቅልፍ ለመተኛት መሞከር አለባቸው።

A. 7 ሰዓታት
B. 6 ሰዓታት
C. 8 ሰዓታት
D. 9 ሰዓታት

46. ሌላ ሹፌር በመንገድ ቢቆርጥዎት ምን ማድረግ አለብዎት፦

A. ከሹፌሩ ጎን በመቆም ይጮኹበት
B. የሌላውን ሹፌር ድርጊት ችላ ይበሉት
C. የከፍተኛ ጨረር መብራቶችዎን ሹፌሩ ላይ ያብሩ
D. ሾፌሩን መንገድ ቆርጠው በመግባት ለመበቀል ይሞክሩ

47. አንድ ሰው ከኋላዎ ነውጠኛ በሆነ አኳሃን እየነዳ ከሆነ ምን ማድረግ አለብዎት፦

A. ከጠበኛው ሹፌር መንገድ ለመውጣት ይሞክሩ
B. ሹፌሩ እርስዎን ሲያልፍ ትኩር ብለው ይመልከቱት
C. ሲያልፉዎት ፍጥነትዎን ይጨምሩ
D. የማለፊያ መንገድ መስመሩን ይዝጉ

48. ለአንድ አማካይ ሰው በአንድ መጠጥ ውስጥ ያለውን አልኮል ሰውነት ውስጥ ለማስወገድ ስንት ደቂቃ ያስፈልገዋል?

A. 15
B. 60
C. 90
D. 30

49. _________ ትኩረትዎን፣ ግንዛቤዎን፣ ፍርድዎን እና ትውስታዎን ይገድባል(ይገድባሉ)።

A. ከህጋዊው ገደብ በላይ የሆነ የደም አልኮል መጠን ብቻ
B. አልኮል ምንም ነገር አይገድብም
C. በጣም ትንሹ የአልኮል መጠን እንኳን
D. የደም አልኮል መጠን ከ .05 በላይ ሲሆን ብቻ

50. መድሃኒቶችን ከአልኮል ጋር መውሰድ፦

A. አደጋ የመድረስ እድልን ይጨምራል
B. ከአልኮል ብቻ የበለጠ አደገኛ አይደለም
C. አልኮል በመንዳት ችሎታዎ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ ይቀንሳል
D. በአጠቃላይ የመንዳት ችሎታዎ ላይ ምንም ለውጥ አያመጣም

51. አልኮሆል በደምዎ ውስጥ ሲከማች፦

A. ምላሽዎን ያዘገያል
B. በራስ መተማመን የበለጠ እንዲያጡ ያደርጋል
C. ራሱን ሰውነት ውስጥ በቶሎ መፈጨት ይጀምራል
D. የመንዳት ስህተቶችዎን ይቀንሳል

52. የደምዎ የአልኮል መጠን .04 ከሆነ፡-
A. ምንም ካልጠጣ ሰው ይልቅ ለአደጋ የመጋለጥ እድልዎ ከ 2 - 7 እጥፍ ይበልጣል
B. ከህጋዊው የደም አልኮል መጠን በላይ ነዎት ነገር ግን ለመንዳት ምንም ችግር የለውም
C. ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ሊነዱ መሆንዎን እርግጠኛ መሆን ይችላሉ
D. ከመኪናዎ ጀርባ ከመቀመጥዎ በፊት ብዙ ቡና መጠጣት አለብዎት

53. የእሳት አደጋ መኪና ድምጽ ሲሰሙ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. እስኪያልፍዎት ድረስ ቀስ ብለው ይንዱ
B. ድንገተኛ መብራቶችዎን እያበሩ ይንዱ
C. ወደ መንገድ ዳር በመሄድ ያቁሙ
D. ፍጥነትዎን በመጨመር በአቅራቢያ ያለውን መውጫ መንገድ ቶሎ ብለው ይጠቀሙ

54. ጎማዎ ቢፈነዳ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. መሪው በፈለገው አቅጣጫ እንዲሄድ ይፍቀዱ
B. መኪናው ፍጥነቱን በመቀነስ እንዲቆም ያድርጉ
C. ጋራዥ እስኪደርሱ ድረስ መንዳትዎን ይቀጥሉ
D. መኪናውን ወዲያውኑ ለማቆም አጥብቀው ፍሬን (ብሬክ) ይያዙ

55. መኪናዎ በሀይዌይ (በአውራ ጎዳና) ላይ ቢበላሽ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. በመኪና ውስጥ በመሆን እርዳታ እስኪደርስ ይጠብቁ
B. ሌሎች አሽከርካሪዎችን ለማስጠንቀቅ አራቱንም የድንገተኛ ጊዜ መብራቶችዎን ይጠቀሙ
C. የሚያልፉትን አሽከርካሪዎች ላይ ድምጽዎን ያሰሙ
D. ወደ እርስዎ ለሚመጣው ተሽከርካሪን ለማስጠንቀቅ የግንባር መብራቶችዎን ያብሩ

56. የድንገተኛ አደጋ መኪና መብራቱን እያበራ ሲመጣ ከትመለከቱ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. ፍጥነትዎን በመቀነስ በሌይንዎ (የመንገድ መስመርዎ) ውስጥ መሄድዎን ይቀጥሉ
B. በመንገድዎ (በሌይንዎ) ውስጥ መንዳትዎን ይቀጥሉ
C. ወደ ዳር በመሄድ መኪናዎን ያቁሙ
D. ልክ ባሉበት ቦታ ላይ ያቁሙ

57. አንድ አቅጣጫ ባለው መንገድ ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜየድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪ ከኋላዎ መብራቱን እያበራ ሲመጣ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. ድንገተኛ መብራቶችዎን እያበሩ ይንዱ
B. ወደሚቀርበው የመንገድ ዳር ይንዱ እና ያቁሙ
C. ፍጥነትዎን በመጨመር በአቅራቢያ ያለውን መውጫ መንገድ ቶሎ ብለው ይጠቀሙ
D. ተሽከርካሪው እርስዎን እስኪያልፍ ድረስ ፍጥነት ቀንሰው ይንዱ

58. የድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪ ሳይረኑን እያሰማ ካለፈዎት በኋላ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. ከፖሊስ መኪናው ጋር ቅርብ በመሆን ይንዱ
B. ከፖሊስ መኪናው ጋር በተመሳሳይ ፍጥነት ይንዱ
C. ከድንገተኛ ጊዜ ተሽከርካሪ ጀርባ ከ500 ጫማ በላይ በቀረበ ርቀት ከመንዳት ይቆጠቡ
D. ወደ ዳር ተጠግተው በጣም በቀስታ ይንዱ

59. በስራ ቀጠናዎች ውስጥ የሚፈጠሩ አደጋዎች በብዛት የሚከሰቱበት ምክንያት፡-
A. የጎማ ፍንዳታዎች
B. በመንገድ ላይ በተረጨ ውሃ ምክንያት ሃይድሮፕላኒንግ (መንዳት አለመቻል)
C. በእርጥብ ቀለም ባለበት ላይ ከነዱ በኋላ መሪውን መቆጣጠር አለመቻል
D. ግድየለሽነት እና ከመጠን በላይ ፍጥነት

60. በስራ ቀጠናዎች ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ወቅት የሚከተለውን የደህንነት ተግባር መከተል ጥሩ ነው፡-
A. የትራፊክ (የተሽከርካሪዎች) ፍሰት ለመጠበቅ ከፊት ያለውን ቅርብ በመሆን ይንዱ
B. የተለመደውን ከፊትዎ ካለው መኪና ጋር የሚኖረው ርቀትዎን በግማሽ ያሳጥሩ
C. የክሩዝ መቆጣጠሪያዎን ይክፈቱ
D. የተለመደውን ከፊትዎ ካለው መኪና ጋር የሚኖረው ርቀትዎን በእጥፍ ያራዝሙ

61. ሁለት ሌይን (የመንገድ መስመር) እና ሁለት አቅጣጫ ባላቸው ጎዳናዎች ወይም አውራጎዳናዎች ላይ ወደ ግራ መታጠፍ መጀመር ያለብዎት፦

A. ወደ መሃል መስመር ቅርብ በመሆን ነው
B. ወደ ውጫዊው መስመር በመጠጋት ነው
C. በሌይኑ (በመንገዱ) መሃል ነው
D. በሌይኑ (በመንገዱ) ውስጥ በማንኛውም ቦታ ነው

62. ብዙ ሌይን (የመንገድ መስመር) ባላቸው ጎዳናዎች እና የቁም ክንድች ላይ ወደ ግራ ለመታጠፍ መጀመር ያለብዎት ከየተኛው ነው፦

A. የመገናኛው መሃል
B. ቀኝ የመንገድ መስመር
C. ግራ የመንገድ መስመር
D. ማንኛውም የመንገድ መስመር

63. ሁለት የመንገድ መስመር ባለው መንገድ ላይ ሌላ ተሽከርካሪ በቀኝ በኩል ማለፍ የሚችሉት መቼ ነው፦

A. አንድ መስመር ባለው መግቢያ መንገድ ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ
B. የሚያልፉት ሹፌር ከተፈቀደው የፍጥነት ገደብ በታች በሚነዳበት ጊዜ
C. በጭራሽ
D. የሚያልፉት ሹፌር ወደ ግራ እየታጠፈ ባለበት ጊዜ

64. ሁለት የመንገድ መስመር ባለው መንገድ ላይ በዝግታ የሚሄድ ተሽከርካሪን ለማለፍ ምን ማድረግ አለብዎት፦

A. የመሃል መስመሩን አያቋርጡ
B. ለሚመጣው ተሽከርካሪ የፊት መብራትዎን ያብሩ
C. የመንገዱን ዳር ይጠቀሙ
D. ለሚመጣው ተሽከርካሪ የሚገባው የመንገድ መስመር ይጠቀሙ

65. እነዚህ የትራፊክ መስመር ምልክቶች ከፊትዎ ባለው መገናኛ ምን እንዳለ ይነግሩዎታል፦



A. የመሃል የመንገድ መስመር ተሽከርካሪ ቀጥታ መሄድ ወይም ወደ ግራ መታጠፍ ይችላል
B. ከመሃል የመንገድ መስመር ወደ ቀኝ ብቻ ነው መታጠፍ የሚችሉት
C. የመሃል የመንገድ መስመር ወደ አንድ የመንገድ መስመር ይቀላቀላል
D. በመሃል የመንገድ መስመር ያለው ተሽከርካሪ ወደ ግራ መታጠፍ አለበት

66. ስለ የፍጥነት አያያዝ እና ኩርባዎች ማስታወስ ያለብዎት በጣም አስፈላጊው ነገር፦

A. ወደ ኩርባው ሲገቡ በተለጠፈው የፍጥነት ገደብ ያሽከርክሩ፣ ከዚያም በኩርባው በጣም በጠነከረበት ክፍል ላይ ፍጥነትዎን ይቀንሱ
B. ወደ ኩርባው ከመግባትዎ በፊት ፍጥነትዎን ይቀንሱ
C. ወደ ኩርባው ከመግባትዎ በፊት ቀስ ብለው ፍጥነትዎን ይጨምሩ
D. ከኩርባው በፊት፣ በውስጡ እና በኋላ በመንገድ ላይ በተለጠፈው የፍጥነት ገደብ ያሽከርክሩ

67. ወደ ክብ መዞሪያ ወይም አደባባይ የሚገቡ አሽከርካሪዎች፦

A. ከመግባታቸው በፊት ማቆም ይኖርባቸዋል
B. በክብ መዞሪያው ወይም አደባባይ ውስጥ ላሉ አሽከርካሪዎች መንገድ መልቀቅ አለባቸው
C. መጀመሪያ ከደረሱ ቅድሚያ የማለፍ መብት አላቸው
D. ሁለት የመንገድ መስመሮች ካሉ ቅድሚያ የማለፍ መብት አላቸው

68. ህጉ _______ በመገናኛዎች ላይ ቅድሚያ የማለፍ መብትን ይሰጣል።

A. ለማንም
B. ወደ ግራ ለሚታጠፉ አሽከርካሪዎች
C. ቀጥ ብለው ለሚሄዱ አሽከርካሪዎች
D. ወደ ቀኝ ለሚታጠፉ አሽከርካሪዎች

69. የቁም ምልክት ባለው የመንገዶች መገናኛ ላይ ማቆም እና የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት፦

A. ተሽከርካሪዎች ተከትለውዎት እየመጡ እንደሆነ ለማረጋገጥ የኋላ መመልከቻ መስታወትዎን ይመልከቱ
B. ከፊትዎ ያለው ተሽከርካሪ ሲሄድ ይሂዱ
C. መጀመሪያ ወደ ቀኝ ይመልከቱ፣ ከዚያ ወደ ግራ፣ ከዚያ እንደገና ወደ ቀኝ ይመልከቱ
C. መጀመሪያ ወደ ግራ፣ ይመልከቱ፣ ከዚያ ወደ ቀኝ ከዚያ እንደገና ወደ ግራ፣ ይመልከቱ

70. ከመግቢያ ራምፕ ወደ አውራ ጎዳና ሲገቡ በአጠቃላይ የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት፡-
A. ሌሎችን ለመቅደም ከትራፊክ ፍጥነት በላይ በማሽከርከር ይግቡ
B. ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ላለመጋጨት ቀስ ብለው ይግቡ
C. መጀመሪያ ያቁሙ፣ ከዚያ ቀስ ብለው ይግቡ
D. ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ጋር እኩል ፍጥነት ለመንዳት ፍጥነትዎን ይጨምሩ

71. ከአውራ ጎዳና ሲወጡ ፍጥነትዎን መቀነስ ያለብዎት፡-
A. በዋናው መንገድ ላይ፣ ከመውጫው መስመር ቀደም ብሎ
B. የክፍያ ቦታውን ከተመለከቱ በኋላ
C. ወደ መውጫው የመንገድ መስመር ከተንቀሳቀሱ በኋላ
D. የመውጫ ምልክቱን መጀመሪያ ሲያዩ

72. በፍጥነት መንገድ (ፊሪወይ) መግቢያ ላይ ስትነዱ በተሽከርካሪ ፍሰት መካከል ያለ ክፍተት መፈለግ ያለብዎት፡-
A. ውስጣዊውን የኋላ መመልከቻ መስታወት ብቻ በመመልከት
B. በጎን መመልከቻ መስታወት ብቻ በመመልከት
C. በሁለቱም የኋላ እና የጎን መመልከቻ መስተዋቶች በመመልከት
D. መስተዋቶችዎን በመመልከት እና ለማየት ጭንቅላትዎን በማዞር

73. ከፍጥነት መንገድ መውጣት ፈልገው ነገር ግን መውጫ መንገድዎን ካለፉ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. ወደሚቀጥለው መውጫ ይሂዱ እና ከዚያ ከፍጥነት መንገዱ ይውጡ
B. በመካከለኛው ከፋፋይ መስመር ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ይዞሩ
C. ወደ መንገዱ ዳር ይጓዙ እና መኪናዎን ወደ መውጫው ይመልሱ
D. ወደ መውጫዎ ለመመለስ ለፖሊስ መኮንን ምልክት ይስጡ እና እንዲሸኙዎት ይጠይቁ

74. ብዙ የመንገድ መስመር ባለበት መገናኛ ላይ ወደ ግራ ለመታጠፍ እየጠበቁ ተቃራኒው የተሽከርካሪዎች መንገድ እይታዎን እየከለከለ ከሆነ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. ሊያቋርጡት የሚፈልጉት የመጀመሪያው የመንገድ መስመር ክፍት ሲሆን ቶሎ ብለው ፍጥነትዎን ይጨምሩ
B. ለመታጠፍ ጉዞን ከመቀጠልዎ በፊት ሊያቋርጡት የሚገባ የመንገድ መስመሮችን (ሌይኖች) በሙሉ እስኪያዩ ድረስ ይጠብቁ
C. ከተቃራኒው መንገድ ያለው ሹፌር መንገዱን እንድታቋርጡ እስኪጠቁምዎት ድረስ ይጠብቁ
D. እያንዳንዱ የተቃራኒ ትራፊክ መስመር ክፍት ሲሆን መኪናዎን ወደ መስመሩ ጠጋ እያደረጉ ይሂዱ

75. በመገናኛ ላይ ምን ማድረግ እንዳለቦት የሚነግርዎት የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ የትራፊክ የመብራት ምልክቶች ወይም ፖሊስ ከሌሉ ህጉ እንዲህ ይላል፡-
A. በስተቀኝ ያሉት አሽከርካሪዎች በስተግራ ላሉት አሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው
B. ማን ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት የሚገልጽ ሕግ የለም
C. ቀጥታ የሚሄዱ አሽከርካሪዎች በመገናኛ ላይ ወደ ግራ ለሚታጠፉ አሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው
D. ወደ ግራ የሚታጠፉ አሽከርካሪዎች በመገናኛ ቀጥታ ለሚሄዱ አሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው

76. "ሀይዌይ ሃይፕኖሲስ" ተብሎ የሚታወቀው የአሽከርካሪ ሁኔታ ከሚከተለው ሊመጣ ይችላል፡-
A. ለረጅም ጊዜ በመንገድ ላይ ትኩር ብሎ በመመልከት
B. እረፍት ለመውሰድ በተደጋጋሚ በማቆም
C. ከጉዞዎ በፊት በነበረው ሌሊት በጣም ብዙ በመተኛት
D. በፍጥነት መንገዶች (ኤክስፕረስዌይስ) ላይ አጫጭር ጉዞዎች በማድረግ

77. ብዙ የመንገድ መስመር ባለው አውራ ጎዳና (ሀይዌይ) በሚያልፉበት ጊዜ፡-
A. የማለፊያው መስመር ክፍት መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ
B. በቀኝ በኩል ብቻ ይለፉ
C. ለሚመጣው ተሽከርካሪ ትኩረት ይስጡ ወይም ይጠንቀቁ
D. ምልክት መስጠት አያስፈልግዎትም

78. "የአራት ሰከንድ ሕግ" አንድ ሰው እንዴት መፈጸም እንዳለበት የሚያመለክተው፡-
A. ለሌሎች መኪኖች ቅድሚያ መስጠት
B. በማቆሚያ ምልክቶች ላይ መታጠፍ
C. ሌላ መኪናን መከተል
D. መገናኛ (መስቀለኛ መንገድ)ን መሻገር

79. ክፍተትን ጠብቆ ለማቆየት በጣም ጥሩው መንገድ፡-
A. ከተሽከርካሪዎ ጀርባ ብቻ
B. በተሽከርካሪዎ በግራ እና በቀኝ በኩል ብቻ
C. ከተሽከርካሪው ፊት ለፊት ብቻ
D. በተሽከርካሪው በሁሉም ጎኖች ላይ

80. ክፍት ቦታን ጠብቆ ማቆየት አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም፡-
A. በሌሎች ተሽከርካሪዎች ትኩረትዎ እንዳይከፋፈል ይከላከላል
B. ለሁኔታዎች ምላሽ ለመስጠት ጊዜ ይሰጥዎታል
C. የትራፊክ ፍሰትን ደህንነቱ በተጠበቀ ፍጥነት ያቆያል
D. ሌሎች አሽከርካሪዎች እንዲጠነቀቁ ያደርጋል

81. የበለጠ ክፍት ቦታ መተው ያለቦት የት ሲያቆሙ ነው፡-
A. ወደ ላይ በሚወጡበት ጊዜ
B. መገናኛ (መስቀለኛ መንገድ) ላይ
C. የቁም ምልክት ላይ
D. በክፍያ ጣብያ ላይ

82. በሚታጠፉበት ጊዜ ፍጥነትዎን _______ አለብዎት።
A. መጨመር
B. ባለበት መጠበቅ
C. መለዋወጥ
D. መቀነስ

83. በክፍተኛ የትርፊክ ፍሰት በሚነዱበት ጊዜ በጣም ደህንነቱ የተጠበቀ ነገር ምንድን ነው፡-
A. ንቁ ሆነው ለመቆየት ፍጥነትዎን መለዋወጥ
B. ከትራፊኩ ፍሰት በበለጠ ፍጥነት መንዳት
C. ከትራፊኩ ፍሰት ባነሰ ፍጥነት መንዳት
D. በትራፊኩ ፍሰት ልክ መንዳት

84. በዚህ ግዛት ውስጥ ያለው ከፍተኛው የፍጥነት ገደብ በሰዓት _____ ማይል ነው።
A. 55
B. 50
C. 60
D. 70

85. ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ በታች መንዳት ያለበዎት መቼ ነው፡-
A. ማንኛውም ነገር ሁኔታዎችን ጥሩ እንዳይሆኑ ካደረገ
B. ሌሎች አሽከርካሪዎች ከፍጥነት ገደቡ በታች ሲነዱ
C. ሌሎች መኪኖች ባሉበት ጊዜ ወደ ሀይዌይ (አውራ ጎዳና) ከገቡ
D. በአራት ሌይን (የመንገድ መስመር) ላይ ከሆኑ

86. ትራፊክን (ተሽከርካሪዎችን) ለማቋረጥ የሚያስፈልግዎ የቦታ መጠን ምን ላይ የተመሰረተ ነው፡-
A. የመንገድ እና የአየር ሁኔታ እንዲሁም የሚመጣው ትራፊክ (የሚመጡት ተሽከርካሪዎች)
B. የማቆሚያ ምልክት መኖር
C. የመታጠፊያ የመብራት ምልክቶችዎን መጠቀም
D. ከኋላዎ የሚመጡ መኪኖች

87. የማቆም ችሎታዎ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሰው:-

A. የሲግናል (ትራፊክ) መብራቶች
B. መንገዱ ላይ ያሉ ሌሎች መኪኖች
C. የቀኑ ሰዓት
D. የመንገዱ ሁኔታ

88. ስለምትጓዝበት ፍጥነት ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ትክክል ነው?

A. ደህንነቱ በተጠበቀ ለመንዳት የሚያስፈልገው ፍጥነት በብዙ ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው
B. በዝግታ መንዳት ደህንነቱ ሁልጊዜ የተሻለ ነው
C. የፍጥነት ገደቡ ሁል ጊዜ አስተማማኝ ፍጥነት ነው
D. ፍጥነት መጨመር ሁልጊዜ አደገኛ ነው

89. በመንገድ ላይ ለሚመጣው ማንኛውም ነገር ለመዘጋጀት ምን ማድረግ አለብዎት:-

A. ሁልጊዜ መንገዱንና ዳር ያሉትን ቦታዎች ያለማቋረጥ ይቃኙ
B. ሁልጊዜ ወደፊት ቀጥ ብሎ ይመልከቱ
C. ግራ እግርዎን በብሬክ ፔዳል ላይ በቀስታ በማሳረፍ ይንዱ
D. ትኩረትዎን በመንገዱ መሃል ላይ ማድረግ

90. በአውራ ጎዳና ፍጥነት፣ ደረቅ በሆነ መንገድ ላይ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ በተከታታይ ተሽከርካሪዎች መካከል የሚኖር ርቀት ቢያንስ ስንት ነው:-

A. ከፊትዎ ካለው መኪና የ3 ሰከንድ ርቀት
B. ከፊትዎ ካለው መኪና የ2 ሰከንድ ርቀት
C. ከፊትዎ ካለው መኪና የ4 ሰከንድ ርቀት
D. ከፊትዎ ካለው መኪና 2 የመኪና ርዝመት ርቀት

91. በክፍተኛ የትርፊክ ፍሰት በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ድንገተኛ (ወይም "ድንጋጤ") ፍሬን መያዝን ለማስቀረት የሚችሉት እንዴት ነው?

A. ሌሎች መኖርዎን እንዲያውቁ ለማድረግ የክላክስ ድምጽዎን ያሰሙ
B. ወደ ፊት ይመልከቱ እና ከፊትዎ ካለው መኪና አስተማማኝ ርቀት ይጠብቁ
C. በቀኝ የመንገድ መስመር ብቻ ይንዱ
D. ከትራፊኩ ፍሰት ባነሰ ፍጥነት መንዳት

92. በግራ በኩል የሚመጣ መኪና እና በቀኝ በኩል ብስክሌተኛ ሲያጋጥምዎ ምን ማድረግ አለብዎት:-

A. ውደ መንገድ ዳር በመውጣት ያቁሙ
B. ከሁለቱ ጋር ያለዎትን ርቀት እኩል በማድረግ መሃል ይሁኑ
C. መኪናው እንዲያልፍ ያድርጉ እና ከዚያ ብስክሌቱን ይለፉ
D. ብስክሌቱን በፍጥነት ይለፉ

93. አንድ ተሽከርካሪ ወደ እርስዎ አቅጣጫ በእርስዎ መስመር እየመጣ ከሆነ ምን ማድረግ አለብዎት:-

A. ወደ ቀኝ አቅጣጫውን ያስተካክሉ፣ የክላክስ ድምጽ ይጠቀሙ እና ፍጥነት ይጨምሩ
B. ወደ ግራ አቅጣጫውን ያስተካክሉ፣ የክላክስ ድምጽ ይጠቀሙ እና ፍሬን ይያዙ
C. ወደ ቀኝ አቅጣጫውን ያስተካክሉ፣ የክላክስ ድምጽ ይጠቀሙ እና ፍሬን ያዙ
D. በሌይንዎ (በመንገድ መስመርዎ) መሃል ላይ ይቆዩ፣ የክላክስ ድምጽ ይጠቀሙ እና ፍሬን ያዙ

94. የተሽከርካሪዎ የኋላ ክፍል ወደ ግራ መንሸራተት ከጀመረ ምን ማድረግ አለብዎት:-

A. መሪ ወደ ግራ ማዞር
B. ፍሬንዎን ይያዙ
C. ፍጥነት ይጨምሩ
D. መሪ ወደ ቀኝ ማዞር

95. በትራፊክ አደጋ የመጎዳት ወይም የመሞት አደጋዎን ለመቀነስ ሊያደርጉት የሚችሉት በጣም ውጤታማው ነገር ምንድነው፡-
A. የመቀመጫ ቀበቶዎን ያድርጉ
B. መንዳትዎን ከሰኞ እስከ ዓርብ ባሉ ቀናት ይገድቡ
C. ባለብዙ የመንገድ መስመር አውራ ጎዳናዎች (ሀይዌዮች) በቀኝ በኩል ባለው መስመር ይንዱ
D. ከምሽቱ 3፡00 እስከ ምሽቱ 6፡00 ከመንዳት መቆጠብ

96. በሚያንሸራትት መንገድ ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. በዝግታ ይታጠፉ
B. የመንገድ መስመሮችን በፍጥነት ይቀይሩ
C. ቶሎ ብለው ፍጥነት ይጨምሩ
D. በሃይል ፍሬን ይያዙ

97. እርጥብ በሆነ መንገድ ላይ ስለ መንዳት ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው እውነት ነው?
A. በፍጥነት ሲያሽከረክሩ ጎማዎችዎ ውጤታማነታቸው እየቀነሰ ይሄዳል
B. ውሃ ጥሩ ጎማ ባላቸው መኪኖች ላይ ተጽዕኖ አይፈጥርም
C. ጥልቀት ያለው ውሃ አደጋው ያነሰ ነው
D. ፍጥነትዎን በቀነሱ ቁጥር መንገዱ ይበልጥ አንሸራታች ይሆናል

98. በአንሸራታች መንገድ ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ምን ማድረግ አለብዎት፡-
A. ሌላ አማራጭ መንገዶችን ይጠቀሙ
B. ደረቅ መንገድ ላይ እንደ ሚነዱት አይነት ይንዱ
C. ከፊትዎ ካለው መኪና ጋር ያለዎትን ርቀት ይጨምሩ
D. ድልድዮችን ወይም መስቀለኛ መንገዶችን ከመጠቀም ይቆጠቡ

99. እርጥብ በሆነ መንገድ ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ማድረግ ያለብዎት፡-
A. በተፈቀደው የፍጥነት ገደብ ይንዱ
B. ከተፈቀደው የፍጥነት ገደብ ትንሽ ከፍ አድርገው ይንዱ
C. ከተፈቀደው የፍጥነት ገደብ ከ5 እስከ 10 ማይል በሰዓት ቀንስ አድርገው ይንዱ
D. ከፊትዎ ላለው መኪና ተጠግተው ይንዱ

100. እርጥብ በሆነ መንገድ ላይ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ማድረግ ያለብዎት፡-
A. ከፊት ካለ መኪና ያለዎትን ርቀት ወደ 5 ወይም 6 ሰከንድ ያሳድጉ
B. ከፊት ካለ መኪና ያለዎትን ርቀት ወደ 2 ሰከንድ ያሳጥሩ
C. ከፊት ካለው መኪና ያለዎትን ርቀት በተመለከተ አይጨነቁ
D. ከፊት ካለው መኪና የ 4-ሰከንድ ርቀትን የመጠበቅ ህግን ይከተሉ

101. መንገዶች ምን ሲሆኑ ነው በቶሎ በረዶ የሚሆኑት፡-
A. ሜዳ
B. ኩርባ
C. በፀሐይ ጊዜ
D. የተጠለሉ

102. መንገዶች በጣም አንሸራታች የሚሆኑት፡-
A. ለአንድ ሰዓት ወይም ከዚያ በላይ ዝናብ ከጣለ
B. ዝናብ ከጣለ በኋላ በሚቀጥለው ቀን
C. ዝናብ መጣል በጀመረ በመጀመሪያዎቹ 10 እና 15 ደቂቃዎች ውስጥ
D. ዝናቡ ካቆመ በኋላ ወዲያውኑ

103. ሃይድሮፕላኒንግ (በውሃ የሚፈጠር የመንዳት ችግር) በአብዛኛው የሚከሰተው በምንድን ነው፡-
A. በጣም ብዙ ማቆሚያዎች
B. በድንገት የሚደረጉ ማቆሚያዎች
C. በድንገት የሚደረጉ መታጠፎች
D. ከመጠን በላይ ፍጥነት

104. ሃይድሮፕላኒንግን በመንዳት መከላከል የሚቻልበት ሁኔታ:-
- A. የውሃው ጥልቅ ባልሆነበት
- B. በፍጥነት
- C. በዝግታ
- D. ውሃው ጥልቅ በሆነበት

105. በጭጋግ ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የእርስዎን _______ መጠቀም አለብዎት።
- A. ዝቅተኛ ጨረር ያላቸው የግንባር መብራቶች
- B. ከፍተኛ ጨረር ያላቸው የፊት መብራቶች
- C. የመኪና ማቆሚያ (ፓርኪንግ) መብራቶች
- D. የአደጋ ጊዜ መብራቶች

106. ከቀን ጋር ሲነጻጸር በሌሊት መንዳት:-
- A. ያነሰ አደገኛ
- B. የማይበልጥም የማያንስም አደገኛነት
- C. የበለጠ አደገኛ
- D. ለዓይኖችዎ ቀላል

107. እርስዎ ________ የሚያስገድድዎ ማንኛውም ነገር አደጋ ሊያስከትልሎት ይችላል።
- A. አይንዎን ከመንገድ ላይ እንዲያነሱ
- B. እጆችዎን ከመሪዎ ላይ እንዲያነሱ
- C. የመንዳት እንቅስቃሴ ትኩረትዎን እንዲያጡ
- D. ሁሉም መልስ ናቸው

108. ትኩረታቸው የተከፋፈለ አሽከርካሪዎች ከሚከተሉት ነገሮች ውስጥ የትኛውን ሲጠቀሙ የመጋጨት እድላቸው ከፍተኛ ይሆናል:-
- A. ሲዲ ማጫወቻ
- B. ሬዲዮ
- C. ሞባይል ስልክ
- D. ሁሉም መልስ ናቸው

109. የትራፊክ ምልክት ወይም በር በሌለበት የባቡር ሐዲድ ላይ በሚያቋርጡ የትራፊክ (የተሽከርካሪ) መስመር ላይ ከሆኑ:-
- A. በመንገዱ ቅድሚያ የማለፍ መብት ስላልዎት ባቡር መኖሩን ማረጋገጥ አያስፈልግዎትም
- B. ሀዲዱን በሚያቋርጡበት ወቅት ቀስ ብለው የሚነዱትን አሽከርካሪዎች ማለፍ ይችላሉ
- C. መሻገር ከመጀመርዎ በፊት ሳይቆሙ ሙሉ በሙሉ ሀዲዱን ለማቋረጥ በቂ ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈልግዎታል
- D. ሁሉም መልስ ናቸው

110. ቀይ መብራቶቹን እያበራና የቁም ክንዱ ዘርግቶ ወደ ቆመ የአውቶቡስ ትምህርት ቤት እየተቃረቡ ከሆነ ምን ማድረግ አለብዎት:-
- A. ከአውቶቡሱ 5 ጫማ ርቀት ላይ ያቁሙ
- B. ልጆች መኖራቸውን ካዩ ብቻ ያቁሙ
- C. ያቁሙ እና ለመቀጠል ደህንነቱ የተጠበቀ እስኪመስል ድረስ ቆመው ይጠብቁ
- D. ያቁሙ እና ቀይ መብራቶቹ ብልጭ ማለታቸውን እስኪያቆሙ እንዲሁም የተዘረጋው የማቆሚያ ክንድ እስኪጠፋ ድረስ ሳይንቀሳቀሱ ይጠብቁ

ምዕራፍ 3 የመልስ ቁልፍ

1.	C	41.	A	81.	A
2.	D	42.	A	82.	D
3.	C	43.	C	83.	D
4.	A	44.	A	84.	D
5.	B	45.	C	85.	A
6.	C	46.	B	86.	A
7.	A	47.	A	87.	D
8.	C	48.	B	88.	A
9.	C	49.	C	89.	A
10.	A	50.	A	90.	C
11.	B	51.	A	91.	B
12.	C	52.	A	92.	C
13.	B	53.	C	93.	C
14.	A	54.	B	94.	A
15.	A	55.	B	95.	A
16.	A	56.	C	96.	A
17.	A	57.	B	97.	A
18.	A	58.	C	98.	C
19.	A	59.	D	99.	C
20.	A	60.	D	100.	A
21.	A	61.	A	101.	D
22.	C	62.	C	102.	C
23.	C	63.	D	103.	D
24.	A	64.	D	104.	C
25.	D	65.	A	105.	A
26.	D	66.	B	106.	C
27.	A	67.	B	107.	D
28.	D	68.	A	108.	D
29.	A	69.	D	109.	C
30.	A	70.	D	110.	D
31.	C	71.	C		
32.	D	72.	D		
33.	C	73.	A		
34.	A	74.	B		
35.	D	75.	D		
36.	C	76.	A		
37.	C	77.	A		
38.	D	78.	C		
39.	A	79.	D		
40.	D	80.	B		

ምዕራፍ 4፡
<u>የመንዳት ታሪክ መረጃ</u>

ይህ ምዕራፍ ስለ መንዳት ታሪክዎ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል። ፔንዶት (የፔንስልቬንያ ትራንስፖርት) በፔንስልቬንያ ላሉ እያንዳንዱ ፍቃድ ላለው ሹፌር የመንዳት ታሪክ ይመዘግባል። የመንጃ ፍቃድ መስጫ ቢሮ (Bureau of Driver Licensing) ከፖሊስ እና ከፍርድ ቤቶች የሚቀበለውን የተለያዩ ጥፋቶችን እና የፍርድ ዉሳኔዎችን ሪፖርት በእያንዳንዱ ሹፌር ላይ ይይዛል። የመንዳት ታሪክዎን ቅጂ በድረ-ገፃችን www.dmv.pa.gov ላይ ማግኘት ይችላሉ። የመንጃ ፍቃድ ቁጥርዎ፣ የልደት ቀንዎ፣ የመጨረሻዎቹ አራት የማህበራዊ ዋስትና (Social Security) ቁጥሮችዎ እና የክሬዲት ካርድ መረጃዎ ያስፈልጎዎታል።.

የፔንሲልቫኒያ የነጥብ አሰጣጥ ስርዓት

የነጥብ አሰጣጥ ስርዓቱ አላማ የመንዳት ልምዶችን ለማሻሻል እና ደህንነቱ የተጠበቀ መንዳትን ለማረጋገጥ ነው። አንድ ሹፌር በተወሰኑ የመንዳት ጥፋቶች ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ነጥቦች በመንዳት ታሪክ ላይ ይጨመራሉ። ፔንዶት (PennDOT) የመንዳት ታሪክ ስድስት (6) ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ሲደርስ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይጀምራል።

የመንዳት ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ስድስት (6) ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ሲደርስ ሹፌሩ ልዩ የነጥብ ፈተና እንዲወስድ የጽሁፍ ማሳሰቢያ ይደርሰዋል። የመንዳት ታሪኩ ከስድስት (6) ነጥብ በታች ሲቀንስ እና ለሁለተኛ ጊዜ ስድስት (6) ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ሲደርስ ሹፌሩ በዲፓርትመንት ችሎት ላይ መገኘት አለበት። ተጨማሪ የስድስት (6) ወይም ከዚያ በላይ ነጥቦች መከማቸት ተጨማሪ የዲፓርትመንት ችሎቶች ያስከትላል እና/ወይም የመንዳት መብትዎ እንዲታገድ ሊያደርግ ይችላል።

ከእነዚህ መስፈርቶች በተጨማሪ እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ሰው ስድስት (6) ወይም ከዚያ በላይ ነጥቦችን ካከማቸ ወይም ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ በላይ በ26 ማይል በሰዓት ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ፍጥነት ሲነዳ ከተያዘ የመንዳት መብቱ ይታገዳል። የመጀመሪያው እገዳ ለ90 ቀናት የሚቆይ ይሆናል። ማንኛውም ተጨማሪ ክስተት የ120 ቀናት እገዳን ያስከትላል።

ለተወሰኑ የትራፊክ ጥሰቶች የሚሰጠውን የነጥብ ብዛት የሚያሳይ ሠንጠረዥ በwww.dmv.pa.gov፣ በ"የፔንስልቬንያ የነጥብ አሰጣጥ ስርዓት" የመረጃ ወረቀት ላይ ይገኛል።

ጥንቃቄ የተሞላበት መንዳት እዲኖር ነጥቦችን መቀነስ

አንድ ሰው እገዳ ወይም መሰረዝ ሳይደረግበት ወይም ነጥቦችን የሚያስከትል ወይም የመንዳት መብትን እገዳ ወይም መሰረዝ የሚያስከትል ምንም ዓይነት ጥሰት ሳይፈጽም ለ12 ተከታታይ ወራት በቆየ ቁጥር ሦስት (3) ነጥቦች ከመንዳት ታሪክ ላይ ይቀነሳሉ። የመንዳት ታሪክ ወደ ዜሮ ከቀነሰ እና ለ12 ተከታታይ ወራት በዜሮ ነጥብ ከቆየ በኋላ ማንኛውም ተጨማሪ የነጥብ ክምችት እንደ መጀመሪያው የነጥብ ክምችት ይቆጠራል።

እገዳዎች እና ስረዛዎች

ከሚከተሉት የትራፊክ ጥሰቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ የመንዳት መብትዎ ይታገዳል ወይም ይሰረዛል (ይህ ሙሉ ዝርዝር አይደለም)፦

- በአደንዛዥ ዕጽ ወይም በአልኮል ተጽዕኖ ስር ሆነው ማሽከርከር።
- ተሽከርካሪን በመጠቀም የሚፈጸም ከባድ ወንጀል።
- ተሽከርካሪን በመጠቀም የሚፈጸም ግድያ።
- በግዴለሽነት መንዳት።
- በአውራ ጎዳናዎች (ሀይዌይ) ላይ መሽቀዳደም።
- ከፖሊስ መኮንን ማምለጥ።
- የመንጃ ፈቃድዎ አስቀድሞ ታግዶ ወይም ተሰርዞ እያለ መንዳት።
- እንዳይታወቁ መብራት ሳያበሩ መንዳት።
- በአደጋ ውስጥ በተሳተፈ ተሽከርካሪ እየነዱ ሳሉ ለማቆም አለመቻል (ገጭቶ መሮጥ)።
- በ 5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ትክክለኛ መንጃ ፈቃድ ሳይኖርዎት የሚፈጸም ሁለተኛ ወይም ማንኛውም ተጨማሪ የመንዳት ጥፋት።
- ቀይ መብራቶቹን እያበራ እና የማቆሚያ ክንዱን ዘርግቶ ለቆመ የትምህርት ቤት አውቶቡስ ለማቆም አለመቻል (የ60 ቀን እገዳ)።
- በባቡር ሀዲድ መሻገሪያ ላይ ያለውን በር ወይም ማገጃን ማለፍ (የ30 ቀናት እገዳ)።
- ለድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ቦታ የመልቀቅ ህግ (Move Over Law) አለማክበር (ለበለጠ መረጃ ገጽ 59 ይመልከቱ)

የመንዳት መብትዎ ሊታገድ፣ ሊሰረዝ እና/ወይም ብቁ እንዳይሆኑ የሚደረግ ከሆነ (ማዕቀብ)፣ ማዕቀቡ የሚጀምርበትን ቀን የሚዘረዝር የጽሁፍ ማሳሰቢያ (ማስታወቂያ) ይደርስዎታል። የመንጃ ፈቃድዎ እና/ወይም የተማሪ ፍቃድዎ ወይም የካሜራ ካርድዎ በማስታወቂያው ላይ በተዘረዘረው ማዕቀብ ተፈጻሚነት ቀን ወደ መንጃ ፈቃድ ቢሮ መመለስ አለበት አለበለዚያ የመንግስት ፖሊስ እና የአካባቢው ፖሊስ የመንጃ ፈቃዱን እንዲወስዱ ይነገራቸዋል።

ሁሉም እገዳዎች፣ ስረዛዎች እና ብቁ አለመሆን (ማዕቀቦች) የመንጃ ፈቃድ ወይም እውቅና መስጫ ቅጽ በተመለሰበት ጊዜ ሳይወሰን በማዕቀቡ ማስታወቂያ ላይ በተዘረዘረው ተፈጻሚነት ቀን ይጀምራሉ። ከማዕቀቡ ተፈጻሚነት ቀን በፊት ከእነዚህ እቃዎች ውስጥ አንዱን ማስረከብ ማዕቀቡን ቀደም ብሎ እንዲጀምር አያደርግም። በህጉ መሰረት የመንጃ ፍቃድ ወይም እውቅና መስጫ ቅጽ መመለስ አለበት። በሚኖሩበት ካውንቲ ውስጥ በሚገኘው የጋራ ፍርድ ቤት (የፍትሐ ብሔር ክፍል) (Court of Common Pleas (Civil Division)) ላይ ማዕቀቡን ይግባኝ ማለት ይችላሉ። ይግባኙ የዲፓርትመንቱ ማስታወቂያ ከተላከበት ቀን ጀምሮ በ 30 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት። ማዕቀቡን ከማጠናቀቅ በተጨማሪ የመንዳት መብትዎ ከመመለሱ በፊት ሁሉም የመመለስ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው።

የመንዳት መብትዎ ከተመለሰ በኋላ፣ ከመታገድዎ በፊት በታሪክዎ ላይ የነበረው የነጥብ ብዛት ምንም ይሁን ምን፣ የመንዳት ሪከርድዎ አምስት (5) ነጥቦችን ያሳያል፣ ከሚከተሉት በስተቀር:-

- ለሁለተኛ ጊዜ ስድስት (6) ነጥብ በማከማቸት ምክንያት ከሚደረግ ችሎት የሚመጣ የ15 ቀን እገዳ።
- ለቀረበ ክስ ምላሽ ባለመስጠት የሚመጣ እገዳ።

ያለ ኢንሹራንስ መንዳት

- በፔንስልቬንያ ግዛት ህግ **መሰረት በተመዘገበ ተሽከርካሪዎ ላይ ሁል ጊዜ የመኪና ተጠያቂነት ኢንሹራንስ ሊኖርዎት ይገባል**።
- ፔንዶት (PennDOT) ተሽከርካሪዎ ለ 31 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ጊዜ ውስጥ በኢንሹራንስ ያልተሸፈነ መሆኑን ካወቀ ምዝገባዎ ለሶስት (3) ወራት ይታገዳል። በተጨማሪም ተሽከርካሪዎን ያለ ኢንሹራንስ ካሽከረከሩት ወይም እንዲሰራ ከፈቀዱ የመንዳት መብትዎ ለሦስት (3) ወራት ይታገዳል።
- የመንዳት መብትዎ እና ምዝገባዎ እንዲመለስ የሚከተሉትን ማቅረብ አለብዎት:-
  - ✦ ተሽከርካሪዎ ኢንሹራንስ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ።
  - ✦ የተፈለገው የማስመለሻ ክፍያ።

ፖሊስ ካቆመዎት ምን ማድረግ አለብዎት

የህግ አስከባሪ መኮንኖች የፔንስልቬንያን የሞተር ተሽከርካሪ ህግ በመጣስ ለተከሰሱ ሰዎች የጽሁፍ የትራፊክ ጥሰት ማሳሰቢያ ይሰጣሉ። በሚቆሙበት ወቅት የፖሊስ መኮንኑን መመሪያ መከተል አለብዎት አለበለዚያ በህግ ቁጥጥር ስር ሊውሉ ይችላሉ። የፖሊስ መኮንን እንዲቆሙ እንደሚፈልግዎት የሚታወቀው በፖሊስ ተሽከርካሪው ላይ የሚበሩትን ቀይ እና ሰማያዊ መብራቶች ሲያበሩ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ምልክት የሌለው የፖሊስ ተሽከርካሪ ቀይ መብራት ብቻ ሊገጠምለት ይችላል።

የፖሊስ ተሽከርካሪ ከኋላዎ በሚቆምበት በማንኛውም ጊዜ ለደህንነትዎ እና ለሌሎች ደህንነት ሲባል ፖሊስ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይመክራል:-

- የመታጠፊያ ምልክትዎን ያብሩ እና በተቻለ መጠን ወደ መንገዱ ቀኝ ጠርዝ ደህንነቱ በተጠበቀ ይንዱ፣ ያቁሙ እና ተሽከርካሪዎን ከትራፊክ (ከተሽከርካሪዎች መስመር) ርቀው በደህና ያቁሙ።
- ከመኮንኑ ጋር መነጋገር እንዲችሉ ሞተርዎን እና ሬዲዮዎን ያጥፉ እና መስኮትዎን ዝቅ ያድርጉ።
- ሌሊት ከሆነ ልክ መኪናዎን እንዳቆሙ እና ፖሊሱ ወደ እርስዎ ከመምጣቱ በፊት የውስጥ መብራቶን ያብሩ።
- እንቅስቃሴዎን እና የተሳፋሪዎችዎን እንቅስቃሴ ይገድቡ - በተሽከርካሪው ውስጥ ምንም ነገር ለመንካት አይሞክሩ።
- ማንኛውንም አይነት የጦር መሳሪያ እያጓጓዙ ከሆነ ወዲያውኑ ለፖሊስ መኮንኑ ያሳውቁ።
- እጆችዎን በመሪው ላይ ያድርጉ እና ማንኛቸውም ተሳፋሪዎች እጆቻቸውን እንዲያሳዩ ይጠይቁ።
- የፖሊስ መኮንኑ ወደ እርስዎ ሲመጣ የመኪናዎን በሮች ዝግ አድርገው ይጠብቁ እና ፖሊሱ ካልጠየቀዎት በስተቀር በመኪናዎ ውስጥ ይቆዩ።
- መኮንኑ ቀበቶዎን በትክክል ማሰርዎን እስኪያረጋግጥ ድረስ ቀበቶዎን አያወልቁ።
- መኮንኑ የመንጃ ፈቃድዎን፣ የምዝገባ እና የኢንሹራንስ ካርዶችን እንዲያመጡ እስኪጠይቅዎት ድረስ ይጠብቁ። ለመኮንኑ የኪስ ቦርሳዎን አይስጡ - የተጠየቁትን ነገሮች ብቻ ይስጡ።
- ሁል ጊዜ ጨዋ ይሁኑ። መኮንኑ ምን ስህተት እንደሰሩ ይነግርዎታል። ማስጠንቀቂያ ብቻ ሊደርስዎት ይችላል ወይም በትራፊክ ጥሰት ሊከሰሱ ይችላሉ። በክሱ ካልተስማሙ ክርክሮችዎን የሚያቀርቡበት የፍርድ ቤት ችሎት የማግኘት መብት አለዎት። በቦታው ላይ ከመኮንኑ ጋር መጨቃጨቅ ለርስዎ ጥቅም አይሰጥም። በሙያዊ መንገድ እንደተያዙ ከተሰማዎት የትራፊክ ማቆሚያውን ተከትሎ በተገቢው ጊዜ አግባብነት ያለውን የፖሊስ መምሪያ ያነጋግሩ እና የበላይ ኃላፊን ይጠይቁ።

ያስታውሱ፣ የፖሊስ መብራቶች ቀይ እና ሰማያዊ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ወይም ምልክት በሌላቸው የፖሊስ ተሽከርካሪዎች ላይ ቀይ ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ። ከእነዚህ መብራቶች በተጨማሪ ብልጭ የሚሉ ነጭ መብራቶችን ሊያዩ ይችላሉ። **ተሽከርካሪው ሰማያዊ መብራቶችን ብቻ እያበራ ከሆነ ፖሊስ አይደለም።** ቀይ እና ሰማያዊ መብራቶች ወይም ቀይ መብራቶች ብቻ ሲበሩ ካዩ እና እያቆመዎት ያለው ሰው ፖሊስ መሆኑን እርግጠኛ ካልሆኑ፣ በአቅራቢያዎ ወዳለው ከፍተኛ ብርሃን ያለው እና ሰዎች ወደሚበዙበት ቦታ መንዳት ይችላሉ፣ ነገር ግን አደጋ መብራቶችን በማብራት እና በዝግታ ፍጥነት በመንዳት ለማቆም የቀረበልዎትን ጥያቄ እንደተረዱት ያሳዩ። መኮንኑን መታወቂያ መጠየቅ ይችላሉ፣ እና ያቆመዎት ግለሰብ ዩኒፎርም ካልለበሰ ወይም ምልክት የሌለው መኪና ካለው ይህን ማድረግ አለብዎት። ብዙውን ጊዜ ምልክት በሌላቸው ተሽከርካሪዎች ውስጥ ያሉ መኮንኖች የፖሊስ ዩኒፎርም ይለብሳሉ፣ የፖሊስ መኮንኖች ደግሞ ሁልጊዜ የፎቶ መታወቂያ ካርድ እና ባጅ ይይዛሉ።

አደጋዎች

እርስዎ በአደጋው ውስጥ ካልተሳተፉ ወይም የአደጋ ጊዜ እርዳታ እስካሁን ካልደረሰ ድረስ አደጋ በደረሰበት ቦታ ላይ አያቁሙ። ትኩረትዎን በመንዳትዎ ላይ ያድርጉ እና መጓዝዎን ይቀጥሉ፣ በመንገድ ላይ ወይም አጠገብ ሊኖሩ የሚችሉ ሰዎችን በጥንቃቄ ይመልከቱ። ፖሊስ፣ የእሳት አደጋ ተከላካዮች፣ አምቡላንሶች፣ የጭነት መኪናዎች እና ሌሎች የነፍስ አድን ተሽከርካሪዎች የሚያልፉበትን መንገድ አይዝጉ።

አደጋ ከደረሰብዎ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት፡-

1. ተሽከርካሪዎን በአደጋው ቦታ ላይ ወይም በአቅራቢያ ያቁሙ። ከቻሉ ትራፊክ (የተሽከርካሪኦውች መንገድ) እንዳያዘጉ ተሽከርካሪዎን ከመንገድ ላይ ያንቀሳቅሱት። ብዙ አደጋዎች የሚከሰቱት ትራፊክ (ተሽከርካሪዎች) በመጀመሪያ አደጋ ምክንያት ሲቆም ወይም ሲቀንስ ነው።
2. ማንም ሰው ቢጎዳ ወይም ቢሞት ለፖሊስ ይደውሉ። የተሽከርካሪዎቹ አሽከርካሪዎች ጉዳት ከደረሰባቸው እና ለፖሊስ መደወል ካልቻሉ በአደጋው ቦታ ላይ ወይም አቅራቢያ ያሉ ምስክሮች ለእርዳታ መደወል አለባቸው።
3. ማንኛውም ተሽከርካሪ መጎተት የሚያስፈልገው ከሆነ ለፖሊስ ይደውሉ።
4. በአደጋው ውስጥ ከተሳተፉት ሌሎች አሽከርካሪዎች የሚከተለውን መረጃ ይውሰዱ፡-
    - ስሞች እና አድራሻዎች
    - የምዝገባ ቁጥሮች
    - የስልክ ቁጥሮች
    - የኢንሹራንስ ኩባንያ ስሞች እና የፖሊሲ ቁጥሮች
5. በአደጋው ውስጥ የተሳተፉ ሌሎች ግለሰቦችን እና የአደጋውን ምስክሮች ስም እና አድራሻ ይውሰዱ።
6. አደጋው የቆመ ተሽከርካሪን ወይም በንብረት ላይ ጉዳት የሚያካትት ከሆነ ወዲያውኑ ያቁሙ እና ባለቤቱን ለማግኘት ይሞክሩ። ባለቤቱን ማግኘት ካልቻሉ በሚታይ ቦታ ላይ ማስታወሻ ያስቀምጡ እና ለፖሊስ ይደውሉ። ማስታወሻው የአደጋው ቀን እና ሰዓት፣ ስምዎን እና ሊያገኙዎት የሚችሉበትን ስልክ ቁጥር ማካተት አለበት።
7. ፖሊስ አደጋውን ካላጣራ እና አንድ ሰው ከሞተ ወይም ከተጎዳ ወይም ተሽከርካሪ መጎተት ካለበት የአሽከርካሪዎች የአደጋ ሪፖርት ቅጽ (AA-600) በአምስት (5) ቀናት ውስጥ ወደሚከተለው አድራሻ ይላኩ፡-

    የፔንሲልቬንያ የትራንስፖርት ዲፓርትመንት
    የሀይዌይ ደህንነት እና የትራፊክ ምህንድስና ቢሮ
    የፖስታ ጽህፈት ቤት ሳጥን 2047
    Harrisburg, PA 17105-2047

እባክዎን ያስተውሉ፡ የአሽከርካሪዎች የአደጋ ሪፖርት ቅጽ (AA-600) ለማግኘት፣ ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ በ www.dmv.pa.gov፣ ወይም የአካባቢዎን ወይም የግዛትዎን ፖሊስን ያነጋግሩ።

ከፖሊስ መሸሽ ወይም ማምለጥ

በየዓመቱ፣ አንድ ሹፌር ከፖሊስ ለመሸሽ ወይም ለማምለጥ ሲሞክር ወደ 450 የሚጠጉ አደጋዎች ይከሰታሉ፣ ይህም በፔንስልቬንያ መንገዶች ላይ ከ40 እስከ 50 የሚደርሱ ከባድ ጉዳቶች ወይም ሞት ያስከትላል።

አንድ ሹፌር ከፖሊስ በመሸሽ ወይም ለማምለጥ በመሞከር ከተከሰሰ ቅጣቱ የአንድ ዓመት የመንጃ ፈቃድ እገዳ፣ 500 ዶላር መቀጮ፣ የፍርድ ቤት ወጪዎች እና ሌሎች ክፍያዎች ሲሆኑ እስርንም ሊያካትት ይችላል።

በአልኮል ወይም በህግ ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር ተጽዕኖ ስር ማሽከርከር

DUI (በተጽዕኖ ስር ማሽከርከር) ምንን ያካትታል?

በአልኮል ወይም በአደንዛዥ እፅ ተጽዕኖ ሥር በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የሚጣሉ ቅጣቶች ከባድ ናቸው። በፔንስልቬንያ፣ ህጋዊ የመጠጥ እድሜ ላይ ከሆኑ (21 ወይም ከዚያ በላይ **በደምዎ ውስጥ ያለው የአልኮል መጠን .08 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ** "በአልኮል ተጽዕኖ ስር" እያሽከረከሩ እንደሆነ ይቆጠራሉ። ነገር ግን ፖሊስ በተሳሳተ መንገድ እየነዱ ነው ብሎ ካስቆመዎት (በጣም በዝግታ፣ በጣም በፍጥነት፣ መስመርዎን ሳይከተሉ፣ ሰፋ ያሉ መታጠፊያዎችን ሲያደርጉ፣ ያለ ምክንያት ሲቆሙ፣ የትራፊክ የመንገድ ዳር ምልክቶችን እና የመብራት ምልክቶችን አለማክበር፣ ወዘተ) ዝቅተኛ የBAC መጠን ቢኖርዎትም በ DUI ሊከሰሱ ይችላሉ።

ዕድሜዎ ከ21 ዓመት በታች ከሆነ የፔንስልቬንያ ህጎች በሰውነትዎ ውስጥ ምንም አይነት የሚለካ የአልኮል መጠን ይዘው መኪና እንዲነዱ አይፈቅዱልዎትም። ዕድሜዎ ከ21 ዓመት በታች ከሆነ፣ የደምዎ አልኮሆል መጠን .02 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ በአልኮል ተጽእኖ ስር እያሽከረከሩ እንደሆነ ይቆጠራሉ።

የፔንስልቬንያ የተዘዋዋሪ ስምምነት ሕግ (ለአልኮል ወይም ለአደንዛዥ ዕፅ ኬሚካላዊ ምርመራ)
እንደ ሹፌር የተዘዋዋሪ ስምምነት ህግ ለእርስዎ በጣም አስፈላጊ ነው። የኬሚካል ምርመራን የሚመለከተው ህግ በፔንስልቬንያ ለመንዳት ፍቃድ በማውጣት ብቻ ለእንደዚህ አይነት ምርመራ ለመቅረብ እንደተስማሙ ይገልጻል። ፖሊስ በአልኮል ወይም በአደንዛዥ እፅ ተጽዕኖ ሥር እያሉ ሲያሽከረክሩ በቁጥጥር ስር ካዋለዎት እና አንድ (1) ወይም ከዚያ በላይ የአተነፋፈስ ወይም የደም ኬሚካላዊ ምርመራዎችን ለመውሰድ ፍቃደኛ ካልሆኑ የመንዳት መብትዎ በአንድ (1) ዓመት ውስጥ በራስ-ሰር ይታገዳል። ይህ እገዳ በአልኮል ተጽዕኖ ስር በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ለጥፋተኝነት ወይም ለተፋጠነ የማገገሚያ ዝግጅት (ARD) ከተጣለው እገዳ በተጨማሪ ነው።

በአልኮል ተጽዕኖ ስር በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ጥፋተኛ አይደሉም ተብለው ቢገኙም እንኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የአተነፋፈስ ወይም የደም ምርመራ ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆኑ የመንዳት መብትዎ ለአንድ (1) ዓመት ይታገዳል። ምርመራ ለማድረግ ፍቃደኛ ካልሆኑ እና DUI ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ፣ በቁጥጥር ስር በዋሉበት ጊዜ በ BAC ደረጃዎ ላይ በመመስረት የመንዳት መብትዎ ለሁለት ዓመት ተኩል (2 1/2) ሊታገድ ይችላል። የኬሚካል ምርመራን ካልተቀበሉ እና ከዚህ በፊት የ DUI ጥፋተኛነት ወይም የኬሚካል ምርመራን አለመቀበል ካለብዎት ለእምቢታው የ18 ወራት እገዳ፣ በተጨማሪም ለ DUI ጥፋተኝነት 18 ተጨማሪ ወራት፣ በአጠቃላይ የሶስት (3) ዓመታት እገዳ ይጣልብዎታል።

የኬሚካል ምርመራን ባለመቀበል የሚጣል የመልሶ ማቋቋሚያ የቅጣት ክፍያ
ለኬሚካላዊ ምርመራ ለማቅረብ ፍቃደኛ ያልሆኑ አሽከርካሪዎች የኬሚካል ምርመራን ባለመቀበል የሚጣል የመልሶ ማቋቋሚያ የመቀጮ ክፍያ መክፈል ይኖርባቸዋል። የመጀመሪያው ጥፋት 500 ዶላር ነው፣ ሁለተኛው ጥፋት 1,000 ዶላር ነው፣ ሶስተኛው ወይም ቀጣይ ጥፋት 2,000 ዶላር ነው። የኬሚካል ምርመራ እምቢተኝነት መልሶ ማቋቋም ክፍያ በፔንስልቬንያ የተሽከርካሪ ህግ አንቀጽ 75 ክፍል 1960 ስር ከሚፈለገው የመልሶ ማቋቋም የመቀጮ ክፍያ በተጨማሪ ነው። የኬሚካል ምርመራ እምቢተኝነት መልሶ ማቋቋም የቅጣት ክፍያ የሚከፈለው በተረጋገጠ ቼክ ወይም በመኒ ኦርደር ነው።

ከባድ ቅጣቶች
ቅጣቶቹ ለነዚህ ሶስት (3) ነገሮች እየከበዱ ይሄዳሉ፦ የደምዎ የአልኮል ክምችት በጨመረ ቁጥር፣ በአልኮል ተጽዕኖ ስር እያሉ መኪና በማሽከርከር ምክንያት የሚደርሰው ጉዳት በጨመረ ቁጥር፣ እና የ DUI ጥፋቶች በበዙ ቁጥር።

የሚከተሉት ሶስት (3) ሰንጠረዦች በተለያዩ የመንዳት አቅም ማነስ ደረጃዎች በአልኮል ተጽዕኖ ስር መንዳት የሚያስከትለውን ቅጣት ያጠቃልላሉ። በእነዚህ ሠንጠረዦች ውስጥ ከተዘረዘሩት ቅጣቶች በተጨማሪ የአልኮል አውራ ጎዳና ደህንነት ትምህርት በማንኛውም በአልኮል መጠቀም ምክንያት የሚመጣ የመንዳት አቅም ማነስ ደረጃ ለመጀመሪያው ወይም ለሁለተኛው ጥፋት ግዴታ ነው። ከፍተኛ የደም አልኮል መጠን ያላቸው የመጀመሪያ ጊዜ እና ተደጋጋሚ የ DUI ጥፋተኞች፣ እና በኬሚካላዊ ምርመራ ጥሰት ምክንያት የአሰራር መብት እገዳ የሚቀበሉ ግለሰቦች መንዳት በሚፈልጉት በማንኛውም ተሽከርካሪ ላይ ማስነሻ መቆለፊያ (Ignition Interlock) እንዲጭኑ ይገደዳሉ። የማስነሻ መቆለፊያ (Ignition Interlock) መስፈርት ማሟላት ያለበት ግለሰብ የማሽከርከር መብታቸውን መልሰው ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ የተገደበ ፈቃድ ለመስጠት እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚነዱት ማንኛውም ተሽከርካሪ የማስነሻ መቆለፊያ ስርዓት የተገጠመለት እንዲሆን እና በተገደበው የፈቃድ ጊዜ ውስጥ እንደዚያው እንዲቆይ ወይም በባለቤትነት የተያዙ፣ የተመዘገቡ ወይም የሚነዱ ተሽከርካሪዎች ከሌሉ በፔንዶት (PennDOT) ደንቦች መሰረት ማረጋገጥ አለባቸው። እንዲሁም ለመጀመሪያ እና ለቀጣይ ጥፋቶች በማንኛውም የመንዳት አቅም ማነስ ደረጃ የአልኮል አላግባብ መጠቀምን ምርመራ እና ህክምና እንዲያደርጉ በፍርድ ቤት ሊጠየቁ ይችላሉ። በተጨማሪ ዳኛ እስከ 150 ሰዓታት የሚደርስ የህዝብ አገልግሎት እንዲያከናውኑ ሊያዝ ይችላል።

ዕድሜዎ ከ 21 ዓመት በታች ከሆነ እና በአልኮል ተጽዕኖ ስር እያሉ ሲያሽከረክሩ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ (BACዎ .02 ወይም ከዚያ በላይ ነው) የ BACዎ ከነዚያ ቅጣቶች ከተጠቀሰው ደረጃ ያነሰ ቢሆንም በሰንጠረዥ 2 ላይ የተዘረዘሩትን ቅጣቶች ("ከፍተኛ መጠን") ሊያገኙ ይችላሉ።

በአካል ጉዳት፣ ሞት ወይም በንብረት ላይ ጉዳት የሚያስከትል አደጋ ውስጥ ከተሳተፉ፣ የእርስዎ BAC በሰንጠረዥ 2፣ “ከፍተኛ መጠን” ላይ ከተዘረዘሩት ደረጃዎች ያነሰ ቢሆንም እንኳ በሰንጠረዥ 1፣ “አጠቃላይ የመንዳት አቅም ማነስ” ላይ ከተዘረዘሩት ይልቅ በሰንጠረዥ 2፣ “ከፍተኛ ደረጃ” ላይ የተዘረዘሩትን ቅጣቶች ሊያገኙ ይችላሉ።

ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮችን ተጽዕኖ ሥር ሆነው የሚያሽከረክሩ እና የኬሚካል ምርመራን የሚቃወሙ አሽከርካሪዎች በሰንጠረዥ 3 ላይ “እጅግ ከፍተኛ መጠን” ላይ የተዘረዘሩትን ቅጣቶች ይቀበላሉ።

በከፍተኛ እና እጅግ ከፍተኛ መጠን የመንዳት አቅም ማነስ ደረጃዎች ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት ከፈጸሙ በተፋጠነ የማገገሚያ ዝግጅት (ARD) ፕሮግራም ውስጥ ሊቀበሉ ይችላሉ።

ሠንጠረዥ 1 - አጠቃላይ የመንዳት አቅም ማነስ፦ ከ.08 እስከ .099 የደም አልኮል ክምችት (ማስታወሻ፡ እነዚህ ቅጣቶች ህጋዊ የመጠጥ እድሜ ባላቸው አሽከርካሪዎች ተግባራዊ ይሆናሉ።)			
ቅጣት	**የመጀመሪያ ጥፋት**	**ሁለተኛ ጥፋት**	**ሦስተኛ ጥፋት**
የቅጣት ፍርድ	6 ወራት የሙከራ ጊዜ	ከ5 ቀናት እስከ 6 ወር የሚደርስ እስራት	ከ10 ቀናት እስከ 2 ዓመት የሚደርስ እስራት
መቀጮ	$300	$300 - $2,500	$500 - $5,000
ፍቃድ	ምንም እርምጃ የለም	የ12-ወር እገዳ እና የ1 አመት የማስነሻ ቁልፍ (Ignition Interlock) መስፈርት	የ12-ወር እገዳ እና የ1 አመት የማስነሻ ቁልፍ (Ignition Interlock) መስፈርት

ሠንጠረዥ 2 - ከፍተኛ መጠን፦ ከ .10 እስከ .159 የደም አልኮል ክምችት (ማስታወሻ፡ ይህ ሠንጠረዥ ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ አሽከርካሪዎች .02 ወይም ከዚያ በላይ BAC ላላቸው፤ የንግድ ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች .04 ወይም ከዚያ በላይ BAC ላላቸው፤ የትምህርት ቤት አውቶቡስ አሽከርካሪዎች .02 ወይም ከዚያ በላይ BAC ላላቸው፤ እንዲሁም .08 እስከ .099 BAC ላላቸው እና ከባድ የአካል ጉዳት፣ ሞት ወይም ተሽከርካሪ ወይም የንብረት ውድመት በሚያስከትል አደጋ ውስጥ ለተሳተፉ አሽከርካሪዎችም ይመለከታል።)			
ቅጣት	**የመጀመሪያ ጥፋት**	**ሁለተኛ ጥፋት**	**ሦስተኛ ጥፋት**
የቅጣት ፍርድ	ከ 2 ቀናት እስከ 6 ወር የሚደርስ እስራት	ከ30 ቀናት እስከ 6 ወር የሚደርስ እስራት	ከ90 ቀናት እስከ 5 ዓመት የሚደርስ እስራት
መቀጮ	$500 - $5,000	$750 - $5,000	$1,500 - $10,000
ፍቃድ	የ12-ወር እገዳ እና የ1 አመት የማስነሻ ቁልፍ (Ignition Interlock) መስፈርት	የ12-ወር እገዳ እና የ1 አመት የማስነሻ ቁልፍ (Ignition Interlock) መስፈርት	የ18-ወር እገዳ እና የ1 አመት የማስነሻ ቁልፍ (Ignition Interlock) መስፈርት

6ሠንጠረዥ 3 - እጅግ ከፍተኛ መጠን፦ ከ .16 የደም አልኮል ክምችት እና ከዚያ በላይ (ማስታወሻ፡ ይህ ሠንጠረዥ በማንኛውም የ BAC ደረጃ የኬሚካል ምርመራን ለማድረግ ፍቃደኛ ያልሆኑ አሽከርካሪዎች እና በህክምና ያልታዘዙ በምድብ I፣ II ወይም III ያሉ ንጥረ ነገሮች ተጽዕኖ ስር ሆነው በማሽከርከር ለተከሰሱ አሽከርካሪዎች፣ የሌላ መድሃኒት እና አልኮል ጥምረት ወይም እንደ የእስትንፋስ ንጥረ ነገሮችም ይመለከታል።)			
ቅጣት	**የመጀመሪያ ጥፋት**	**ሁለተኛ ጥፋት**	**ሦስተኛ ጥፋት**
የቅጣት ፍርድ	ከ3 ቀናት እስከ 6 ወር የሚደርስ እስራት	ከ90 ቀናት እስከ 5 ዓመት የሚደርስ እስራት	ከ 1 አመት እስከ 5 አመታት የሚደርስ እስራት
መቀጮ	$1,000 - $5,000	$1,500	ቢያንስ 2,500 ዶላር
ፍቃድ	የ12-ወር እገዳ እና የ1 አመት የማስነሻ ቁልፍ (Ignition Interlock) መስፈርት	የ18-ወር እገዳ እና የ1 አመት የማስነሻ ቁልፍ (Ignition Interlock) መስፈርት	የ18-ወር እገዳ እና የ1 አመት የማስነሻ ቁልፍ (Ignition Interlock) መስፈርት

ቅጣትዎ ከፍተኛውን የ6 (ስድስት) ወራት የሙከራ ጊዜ ወይም የእስር ጊዜን የሚያካትት ከሆነ (በማንኛውም ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋተኛ ከሆኑ፣ ወይም በ “አጠቃላይ የመንዳት አቅም ማነስ” ወይም በ “ከፍተኛ መጠን” ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋተኛ ከሆኑ) የ DUI ወንጀልዎ ያልተመደበ ቀላል ወንጀል ተብሎ ተከሷል። ያልተመደበ ቀላል ወንጀል ክስ ማለት ጉዳዩን ቢቃወሙትም ለዳኝነት ችሎት መብት የለዎትም ማለት ነው።

በከፍተኛ እና እጅግ ከፍተኛ መጠን የመንዳት አቅም ማነስ ደረጃዎች ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋት ከፈጸሙ በተፋጠነ የማገገሚያ ዝግጅት (ARD) ፕሮግራም ውስጥ ሊቀበሉ ይችላሉ።

በ ARD ፕሮግራም ውስጥ ከተካተቱ፦

- በ ARD ምክንያት እስከ 90 ቀናት ድረስ የመንጃ ፈቃድዎን ያጣሉ።
- ለስድስት (6) ወራት በፍርድ ቤት ክትትል ስር ይቆያሉ።
- ከተያያዙት ክፍያዎች እና ሌሎች ወጪዎች በተጨማሪ ከ 300 እስከ 5,000 ዶላር የሚደርስ ቅጣት ይከፍላሉ።
- የአልኮል እና የአደዛዥ ዕፅ ምርመራ ይደረግልዎታል።
- አስፈላጊ ከሆነ የአልኮል እና የአደንዛዥ ዕፅ ማገገሚያ ሕክምናን ይደረግልዎታል።
- ለ12 ሰዓታት ከግማሽ ያክል የአልኮል አውራ ጎዳና (ሀይዌይ) ደህንነት ትምህርት ይሳተፋሉ።

የዜሮ ትዕግስት ህግ (ከ21 አመት በታች DUI)

ዜሮ ትዕግስት ህግ ከ21 አመት በታች የሆኑ ማንኛውንም የሚለካ የአልኮል መጠን በደማቸው ውስጥ ይዘው ለሚያሽከረክሩ ከባድ ቅጣት ያስከትላል። በህጉ መሰረት የአልኮል ተጽዕኖ ስር በሚያሽከረክሩ ታዳጊዎች(ከ21 አመት በታች) ላይ የሚወሰደው የደም አልኮሆል መጠን ከ .08 ወደ .02 እንዲቀንስ ተደርጓል።

ዜሮ ትዕግስት ለምን አስፈለገ?

በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ለታዳጊ ወጣቶች ቁጥር አንድ (1) የሞት ምክንያት የትራፊክ አደጋዎች ናቸው።

ማሽከርከር ብዙ ተግባራትን የሚያካትት ሲሆን የሚያስፈልጉት ነገሮችም በየጊዜው ይለዋወጣሉ። በአስተማማኝ ሁኔታ ለመንዳት ንቁ መሆን፣ በየጊዜው በሚለዋወጥ አካባቢ ባለው መረጃ ላይ በመመስረት ውሳኔዎችን ማድረግ እና በእነዚህ ውሳኔዎች ላይ በመመስረት መንቀሳቀስ መቻል አለብዎት። አልኮል መጠጣት እነዚህን ተግባራት ለመፈፀም አስፈላጊ የሆኑ በርካታ ክህሎቶችን ያዳክማል።

ከ21 አመት በታች ከሆኑ እና ለመጀመሪያ ጊዜ የDUI ወንጀል ከፈጸሙ (በአልኮል እና አደንዛኝ ዕጽ ተጽዕኖ ስር ካሽከረከሩ) ከሁለት (2) ቀናት እስከ ስድስት (6) ወራት ለሚደርስ ጊዜ እስር ቤት ይገባሉ፣ መንጃ ፈቃድዎ ለአንድ ሙሉ አመት ይታገዳል፣ እንዲሁም ከ$500 እስከ $5,000 ዶላር ቅጣት ይከፍላሉ።

ከህጋዊ ዕድሜ በታች መጠጣት

ዕድሜዎ ከ21 ዓመት በታች ከሆነ አልኮል መግዛት፣ አልኮል መጠጣት፣ አልኮል በእጅዎ መያዝ ወይም በሚያሽከረክሩት ተሽከርካሪ ውስጥ አልኮል መኖር ሕገወጥ ነው። በተጨማሪም ለአካለ መጠን ያልደረሱ ከሆኑ እና ደም፣ ትንፋሽ እና/ወይም የሽንት ምርመራ ለማድረግ ተይዘው ከተያዙ እነዚህን ምርመራዎች ለማድረግ የወላጅ ፈቃድ አያስፈልግም፣ ነገር ግን ፖሊስ ወላጆችዎን ስለ መታሰሩ ያሳውቃል። ከህጋዊ እድሜ በታች አልኮል በመጠጣት የሚቀጣው አነስተኛ የገንዘብ መቀጮ እስከ $500 ዶላር ሲሆን የፍርድ ቤት ወጪዎችን ይጨምራል።

ፍርድ ቤቶች ከአልኮል ጋር ያለዎትን ተሳትፎ መጠን ለማወቅ ምርመራ እንዲያደርጉ ሊጠይቁዎት ይችላሉ እንዲሁም የአልኮል ትምህርት፣ ጣልቃ ገብነት ወይም የምክር መርሃ ግብር በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ ሊጠይቁዎት ይችላሉ።

አንድ እውነታ ይቀራል፦ ከ21 አመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው አልኮልን መጠቀም፣ይዞ መገኘት ወይም ማጓጓዝ በህግ የተከለከለ ነው።

ለሚያስከትለው አደጋ ራስዎን አያጋልጡ።

አዋቂዎች፣ ወላጆችም እንኳ ሆን ብለው እና ሆን ብለው ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች አልኮል ሲያቀርቡ ከተያዙ ለመጀመሪያው ጥፋት ቢያንስ $1,000 ዶላር እና ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ጥፋት $2,500 ዶላር የሚደርስ ቅጣት የሚጣልባቸው ሲሆን እስከ አንድ አመት በሚደርስ እስር ቤትም ሊቀጡ ይችላሉ። አዋቂዎች በቤታቸው ውስጥ ለሚጠጡ እንግዶችም ጭምር ተጠያቂ ናቸው።. ለምሳሌ፣ በቤትዎ ውስጥ ለድግስ 17 ታዳጊዎች ተሰብስበው አልኮል ቢጠጡ ድግሱ 41,000 ዶላር ሊያስከፍልዎት ይችላል። ይህ ማለት ለመጀመሪያው ታዳጊ ጠጪ $1,000 ዶላር እና ለእያንዳንዱ ቀጣይ 16 ጠጪዎች $2,500 ዶላር ማለት ነው።

የመንጃ ፈቃድ ስምምነት (DLC)

DLC በአባል ግዛቶች እና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት መካከል በመላ አገሪቱ የሕግ አስከባሪ ጥረቶችን ከፍ ለማድረግ የተደረገ ስምምነት ነው። አባል ግዛቶች ለመጠበቅ እና ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ የሆኑባቸው የ DLC ዋና ዋና ድንጋጌዎች የሚከተሉት ናቸው፦

- "አንድ የመንጃ ፈቃድ" ጽንሰ-ሀሳብ፣ ይህም በሌላ ግዛት ውስጥ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት ሲያመለክቱ ከግዛት ውጭ የመንጃ ፈቃድ መመለስን ይጠይቃል።
- "አንድ የአሽከርካሪ መዝገብ" ጽንሰ-ሐሳብ፣ ይህም በአሽከርካሪው የነዋሪነት ግዛት ውስጥ የተሟላ የአሽከርካሪ መዝገብ እንዲቆይ የሚጠይቅ ሲሆን ይህም በግዛታቸው ውስጥ የመንዳት ብቁነትን ለመወሰን እንዲሁም በሌሎች ግዛቶች ውስጥ የአሽከርካሪነት መብት ለማግኘት የሚጠቅም ነው።
- ከግዛቱ ውጭ ያሉ የአሽከርካሪው የትራፊክ ጥፋቶች እና የመንጃ ፈቃድ እገዳዎች/ስረዛዎች እንዲሁም ሌሎች ተገቢ መረጃዎች ለግዛቱ መንጃ ፈቃድ ሰጪ ኤጀንሲ ሪፖርት ማድረግ።
- በሌሎች ግዛቶች ውስጥ የሚፈፀሙ ጥፋቶችን በግዛቱ ውስጥ እንደተፈፀሙ አድርጎ በመቁጠር ለአሽከርካሪዎች ወጥ እና ሊገመት የሚችል አያያዝን ማረጋገጥ።

የሚከተሉት ጥፋቶች፣ በአንድ አባል ግዛት ውስጥ ከተፈጸሙ በፔንስልቬንያ ውስጥ የተፈፀሙ ያህል ተቆጥረው በፔንስልቬንያ የትራፊክ ህግ መሰረት ተገቢው ቅጣት ይጣልባቸዋል፦

- ተሽከርካሪን በመጠቀም የሚከሰት ግድያ ወይም በቸልተኝነት የሚፈጸም ግድያ (ክፍል 3732)።
- አሽከርካሪው ተሽከርካሪን በአስተማማኝ ሁኔታ መንዳት ወደማይችልበት ደረጃ የአልኮል መጠጦች ወይም አደንዛዥ ዕፅ ተጠቅሞ ተሽከርካሪ

መንዳት (ክፍል 3802)።

- በሌላ ሰው ሞት ወይም የአካል ጉዳት ያስከተለ የተሽከርካሪ አደጋ ቢከሰት ሳያቆሙ እርዳታ ሳይሰጡ መሄድ (ክፍል 3742)።
- ተሽከርካሪን በመጠቀም የሚፈጸም ማንኛውም ከባድ ወንጀል (የወንጀል ህግ እና አደገኛ ዕፅ ህግ ጥፋቶች)።

ከግዛት ውጭ ለተነሳብዎት ክስ ምላሽ አለመስጠት በክሱ ላይ ለተጠቀሰው ቦታ ምላሽ እስኪሰጥ ድረስ የፔንስልቬንያ የመንዳት መብትዎን ላልተወሰነ ጊዜ እንዲታገድ ያደርጋል።

ምዕራፍ 4 የማጠቃለያ ጥያቄዎች

1. በዚህ ግዛት ውስጥ ያለው መጠጥ መጠጣት የሚፈቀድበት ዝቅተኛው ዕድሜ _______ ዓመታት ነው።
- A. 9
- B. 20
- C. 21
- D. 18

2. አልኮል ለመግዛት የውሸት መታወቂያ የሚጠቀሙ ከ16 አመት በታች የሆኑ ሰዎች፦
- A. በ16 አመት ልደታቸው የሚጀመር የመንዳት እገዳ ይቀበላሉ
- B. እስከ 21ኛ አመት ልደታቸው ድረስ የመንጃ ፈቃድ ፈተና መውሰድ አይችሉም
- C. በ21ኛ አመት ልደታቸው የሚጀመር የመንዳት እገዳ ይቀበላሉ
- D. ወደ አልኮል ደህንነት ትምህርት ክፍል ይላካሉ

3. አንድ ሰው ከ21 አመት በታች ሆኖ አልኮል ከጠጣ ነገር ግን ተሽከርካሪ ካላሽከረከረ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥፋቱ ቅጣቱ የሚከተለው ነው፦
- A. የ90 ቀናት መንጃ ፈቃድ እገዳ እና እስከ 500 ዶላር የሚደርስ ቅጣት
- B. የ6 ወር የሙከራ ጊዜ
- C. ወደ ማረሚያ ተቋም የመላክ ፍርድ
- D. በመንዳት መዝገብ ላይ ነጥብ መጨመር

4. የትንፋሽ፣ የደም እና የሽንት ምርመራ ለማካሄድ የወላጅ ፈቃድ፦
- A. አያስፈልግም
- B. ከአንዱ ወላጅ ብቻ ይፈልጋል
- C. ከ16 ዓመት በታች ለሆኑ ሰዎች ያስፈልጋል
- D. ከሁለቱም ወላጆች ይፈልጋል

5. ከ21 አመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው አልኮል ________ ህገወጥ ነው።
- A. የሚያስተዋውቁ ልብሶችን መልበስ
- B. ባለበት መገኘት
- C. መጠቀም
- D. ማቅረብ

6. ከ21 አመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው አልኮል ________ ህገወጥ ነው።
- A. የሚያስተዋውቁ ልብሶችን መልበስ
- B. መያዝ
- C. ማቅረብ
- D. ባለበት መገኘት

7. ከ21 አመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው አልኮል ________ ህገወጥ ነው።
- A. ማቅረብ
- B. የሚያስተዋውቁ ልብሶችን መልበስ
- C. ባለበት መገኘት
- D. ማጓጓዝ

8. በአልኮል ተጽእኖ ስር በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ከሚጣሉ ቅጣቶች አንዱ፦
- A. የ5 - አመት የመንጃ ፍቃድ እገዳ
- B. የ100 ዶላር ቅጣት
- C. የአልኮል አውራ ጎዳና ደህንነት ትምህርት ቤት መግባት
- D. የ12 ሰአት የእስር ቅጣት

9. በአልኮል ተጽእና ሲነዱ ከተያዙ እና የደም ምርመራውን ለመውሰድ ፈቃደኛ ካልሆኑ የሚጣልብዎት፡-
- A. የአደንዛዥ ዕፅ ምክር ሕክምና
- B. የአንድ ቀን የእስር ቅጣት
- C. የመንጃ ፍቃድ እገዳ
- D. የ300 ዶላር ቅጣት

10. አንድ የፖሊስ መኮንን የደም፣ የትንፋሽ ወይም የሽንት ምርመራ እንዲያደርጉ ከጠየቀዎት እርስዎ፡-
- A. የሚፈልጉትን ምርመራ መምረጥ ይችላሉ
- B. የስምምነት ቅጽ መፈረም አለብዎት
- C. ከእድሜ በታች ከሆኑ ፍቃደኛ አለመሆን ይችላሉ
- D. ምርመራውን መውሰድ አለቦት ካልሆነ ግን መንጃ ፈቃድዎ ይታገዳል

11. በማንኛውም የደም አልኮሆል ክምችት መጠን ተጽእና ስር እያሉ በመንዳት ለመጀመሪያ ጊዜ ከተከሰሱ ሊከተል የሚችል፡-
- A. መንጃ ፈቃድዎን እስከ 5 አመት ድረስ ሊያጡ ይችላሉ
- B. በአልኮል ተጽእና ስር መንዳት የሚያስከትለውን አደጋ በተመለከተ የህዝብ ትምህርት ክፍል እንዲያካሂዱ ሊጠየቁ ይችላሉ
- C. በተገደበ የሙያ መንጃ ፈቃድ መንዳት ሊጠየቁ ይችላሉ
- D. ቢያንስ 300 ዶላር መቀጮ ይከፍላሉ

12. ከ21 አመት በታች ከሆኑ እና በአልኮል ተጽእና ስር ሆነው እየነዱ እንደሆነ የሚቆጠረው በደምዎ ውስጥ ያለው የአልኮል መጠን ምን ያክል ሲሆን ነው፡-
- A. .08 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ
- B. .10 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ
- C. .05 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ
- D. .02 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ

13. ከ21 አመት በታች ከሆኑ እና በአልኮል ተጽእና ስር በመንዳት ከተከሰሱ ለመጀመሪያ ጥፋት የ _______ የመንጃ ፈቃድ እገዳ ይጣልብዎታል።
- A. 60-ቀን
- B. 30-ቀን
- C. 6-ወር
- D. 1-አመት

14. ከ21 አመት በታች ከሆኑ እና የውሸት መታወቂያ ካርድ በመያዝ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ 500 ዶላር የገንዘብ መቀጮ እንዲከፍሉ የሚጠየቁ ሲሆን የመንጃ ፈቃድዎ ለ90 ቀናት ይታገዳል።
- A. የደምዎ የአልኮል ክምችት (BAC) .02 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ብቻ
- B. እየነዱ ባይሆኑም እንኳ
- C. በቁጥጥር ስር በዋሉበት ጊዜ እየነዱ ከነበረ ብቻ
- D. የደምዎ የአልኮል ክምችት (BAC) .02 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ እና በቁጥጥር ስር በዋሉበት ጊዜ እየነዱ ከነበረ ብቻ

15. የዜሮ ትዕግስት ህግ ከ21 አመት በታች የሆኑ አሽከርካሪዎች በመጠጥ ተጽእና ስር ሆነው ሲነዱ እንዲከሰሱ የደም ውስጥ የአልኮሆል መጠንን (BAC) ከ .08% ወደ ________ እንዲቀንስ አድርጓል።
- A. .02%
- B. .05%
- C. .07%
- D. .00%

16. የፖሊስ መኮንን ቢያቆሙዎት ምን ማድረግ አለብዎት፡-
- A. የመቀመጫ ቀበቶዎን ይፍቱ እና መስኮትዎን ዝቅ ያድርጉ
- B. መኮንኑ ወደ መኪናዎ ጋር ከመድረሱ በፊት ወረቀቶችዎን ያዘጋጁ
- C. እጆችዎ መሪው ላይ በማድረግ በመኪናዎ ውስጥ ይቆዩ እና መኮንኑ ወደ እርስዎ እስኪመጣ ድረስ ይጠብቁ
- D. ከመኪናዎ ወጥተው ወደ ፖሊስ መኪና ይሂዱ

ምዕራፍ 4 የመልስ ቁልፍ

1. C
2. A
3. A
4. A
5. C
6. B
7. D
8. C
9. C
10. D
11. D
12. D
13. D
14. B
15. A
16. C

ምዕራፍ 5:
ህጎች እና ተዛማጅ ጉዳዮች

ይህ ምዕራፍ በቅርብ ጊዜ የወጡ የፔንስልቬንያ ህጎችን ወይም ሌሎች አሽከርካሪን የሚመለከቱ ህጎችን በተመለከተ ማወቅ ያለብዎትን መረጃ ያቀርባል።
ስለ ፔንስልቬንያ ሕጎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን www.dmv.pa.govን ይጎብኙ፣ በመረጃ ማዕከላት ስር የተዘረዘሩትን ህጎች እና ደንቦች ይምረጡ።

ስም ወይም አድራሻ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ የሚያስፈልግ ማስታወቂያ

በፔንስልቬንያ የተሽከርካሪ ህግ ክፍል 1515 መሰረት ስምዎ ወይም አድራሻዎ ከተቀየረ ከግዛት ውጭ ቢሄዱም እንኳ ያንን ለውጥ በ15 ቀናት ውስጥ ለፔንዶት (PennDOT) ማሳወቅ አለብዎት። የአድራሻ ለውጥዎን www.dmv.pa.gov በመጎብኘት ወይም ወደ ደንበኛ ጥሪ ማእከላችን በ717-412-5300 በመደወል ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። የፔንስልቬንያ የተሽከርካሪ ህግ የፔንስልቬንያ ነዋሪ ላልሆነ ማንኛውም ሰው የመንጃ ፈቃድ መስጠትን ይከለክላል። በህጉ መሰረት፣ በፔንስልቬንያ የተመዘገበ መራጭ ከሆኑ ይህ ማመልከቻ የአድራሻ ለውጥዎን ለካውንቲዎ የምርጫ ጽሕፈት ቤት ለማሳወቅ ያስችለናል። በድረ-ገጹ ላይ የሚገኘውን ለመቀየር/ለማስተካከል/ለመተካት የሚውል የንግድ ያልሆነ የመንጃ ፍቃድ ማመልከቻ (ቅፅ DL-80) በማጠናቀቅ ስምዎን መቀየር ይችላሉ። አዲሱን መረጃ የያዘ የተሻሻለ የመንጃ ፍቃድ ካርድ ይሰጥዎታል። ይህ ካርድ ከመንጃ ፍቃድዎ ጋር መያያዝ አለበት። ይህ አገልግሎት ለንግድ ላልሆኑ አሽከርካሪዎች ያለክፍያ ይሰጣል።

የመቀመጫ ቀበቶ ህግ

በፔንስልቬንያ የትራፊክ ህግ አንቀጽ 4581 መሰረት በፔንስልቬንያ የሚከተሉት እንዲፈጽሙ የሚጠይቅ ይህ ህግ ነው፦

- በተሽከርካሪዎች፣ ቀላል መኪኖች እና ሞተር ቤቶች ውስጥ ያሉ ሁሉም አሽከርካሪዎች እና የፊት ወንበር ተሳፋሪዎች የመቀመጫ ቀበቶ ማድረግ አለባቸው።
- ተሳፋሪዎችዎ ስምንት (8) አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው ነገር ግን ከ18 አመት በታች ከሆኑ ተሽከርካሪው ውስጥ የትም ቢቀመጡ የመቀመጫ ቀበቶ ማድረግ አለባቸው።
- ከ 18 አመት በታች የሆኑ አሽከርካሪ ከሆኑ የተሳፋሪዎች ቁጥር በተሽከርካሪው ውስጥ ካለው የመቀመጫ ቀበቶዎች መብለጥ የለበትም።

ቀበቶዎን እንዲያስሩ በህግ ይገደዳሉ። የመቀመጫ ቀበቶዎን ቢያደርጉ መልካም ነው።

ብዙ ሰዎች በሚደርስ አደጋ እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን ተጠቅመው ወደ ተሽከርካሪው እንዳይጋጩ መከላከል እንደሚችሉ ያስባሉ፣ ነገር ግን ተሳስተዋል። ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ ተሽከርካሪዎ ይቆማል፤ ነገር ግን ሰውነትዎ በመሳሪያ ፓነል ወይም የንፋስ መከላከያ መስታወት (ዊንድሺልድ) እስኪመታ ድረስ መኪናዎ እየተንቀሳቀሰበት በነበረው ተመሳሳይ ፍጥነት መንቀሳቀሱን ይቀጥላል። በአብዛኛዎቹ አደጋዎች የተሳፋሪዎች እና የአሽከርካሪዎች አካል በተሽከርካሪው ውስጣዊ ገጽታዎችን በከፍተኛ ኃይል ይመታል። ይህ በጣም ጠንካራ የሆኑትን ክንዶች እና እግሮች እንኳን ይሰባብራል። በ 30 ማይል በሰዓት ላይ፣ ይህ ከሶስት ፎቅ ሕንፃ ላይ ወድቆ ከመሬት ጋር እንደ መጋጨት ነው። በዚህ ምክንያት ነው በእጆችዎ ራስዎን መከላከል የማይችሉት። ቀበቶውን ያላሰረ አሽከርካሪ ወይም ተሳፋሪ ተሽከርካሪው በሰአት በ12 ማይል በዝግታ ቢጓዝ እንኳ በደረሰበት አደጋ ሊሞት ይችላል።

ሰውነትዎን በአስተማማኝ ሁኔታ ሊያዘገዩ የሚችሉት የመቀመጫ ቀበቶዎች ብቻ ናቸው። ተሽከርካሪው አደጋ ከደረሰበት በኋላ ሰውነትዎን ለማስቆም የሚኖርዎት ጊዜ 1/50ኛ ሰከንድ ብቻ ነው። እጆች እና እግሮች በዚያ ፍጥነት አይሰሩም፤ ነገር ግን የመቀመጫ ቀበቶዎች በፍጠነት ይሠራሉ። የመቀመጫ ቀበቶዎች ሰውነትዎን ከጠንካራ የመሳሪያ ፓነል፣ ከመሪው ወይም ከንፋስ መከላከያው ይልቅ በጣም በረጋ መንፈስ ያዘገዩታል። በአደጋ ጊዜ የታሰሩ ቀበቶዎች ድንገተኛ ፍጥነት መቀነስ የሚያስከትለውን ኃይል በደረት፣ በወገብና በትከሻዎ ባሉ ትላልቅ እና ጠንካራ የሰውነት ክፍሎች ላይ ያሰራጫሉ። የአየር ከረጢቶች በድንገት ፍጥነት መቀነስ ያስከተለውን ሃይል ተጽዕኖ በመቀነስ የበለጠ ትልቅ ጥቅም ይሰጣሉ። ይሁን እንጂ የአየር ከረጢት ቢኖርም እንኳ የመቀመጫ ቀበቶ መታሰር አለበት።

የመቀመጫ ቀበቶዎች በተሽከርካሪዎ ውስጥ እንዲቆዩ ያደርግዎታል። ከተሽከርካሪዎ ወደ ውጪ ከተወረወሩ የመሞት እድልዎ በ25 እጥፍ ይጨምራል። ወደ ውጭ መወርወር ማለት አብዛኛውን ጊዜ የንፋስ መከላከያ መስታወቱን ሰብሮ በመውጣት የሆነ ቦታ ላይ በሃይል መውደቅ ማለት ነው። በአደጋ ጊዜ የሚፈጠረው ሃይል እስከ 150 ጫማ (15 መኪኖች በሚሰለፉበት ርቀት) ሊጥልዎት ይችላል። መንገድ ላይ ከወደቁ በዚያ በተኙበት ሁኔታ ሌላ መኪና ሊረግጥዎት ይችላል። ወደ ውጭ በመወርወር ከሞቱት ሰዎች መካከል ከአምስት (5) ሰዎች ውስጥ አራቱ (4) በተሽከርካሪው ውስጥ መቆየት ቢችሉ ኖሮ በህይወት ይኖሩ ነበር።

የመቀመጫ ቀበቶዎች እና የአየር ከረጢቶች ህይወትን ያድናሉ። ሁሉም ሰው ቀበቶውን ሲያስር እና ልጆች የኋላ ወንበር ላይ በአግባቡ ሲቀመጡ በተሻለ ሁኔታ ይሰራሉ።

የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መቀመጫ ህግ

የተሽከርካሪ አደጋ በአሜሪካ ውስጥ ለህፃናት ዋነኛው የሞት እና የአካል ጉዳት መንስኤ ነው። በፔንስልቬንያ በየዓመቱ በአምስት (5) አመት በታች የሆኑ ወደ 7,000 የሚጠጉ ህጻናት በአደጋዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።

የህጻን ተሳፋሪዎች ጥበቃ ህግ 229 የሚከተሉትን ያዛል

- ከአራት (4) አመት በታች የሆኑ ህጻናት የትም ቢቀመጡ (የፊት ወይም የኋላ ወንበር) በመቀመጫ ቀበቶ ስርዓት (ወይም በአዲሶቹ ተሽከርካሪዎች ውስጥ የሚገኘውን የተሽከርካሪውን LATCH ስርዓት በመጠቀም) በተሽከርካሪው ላይ በተጠበቀ በፌደራል-የተፈቀደ የልጅ ተሳፋሪ መቆጣጠሪያ ስርዓት (የልጅ ደህንነት መቀመጫ) ውስጥ መታሰር አለባቸው።
- አራት (4) አመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገር ግን ከስምንት (8) አመት በታች የሆኑ ህጻናት የትም ቢቀመጡ (የፊት ወይም የኋላ ወንበር) በመቀመጫ ቀበቶ ስርዓት በተሽከርካሪው ላይ በተጠበቀ በፌደራል-የተፈቀደ የልጅ የተስተካከለ መቀመጫ ውስጥ መታሰር አለባቸው። የተስተካከሉ የህጻናት መቀመጫዎች ከወገብ እና ከትከሻ ቀበቶዎች ጋር በአንድነት ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።
- ስምንት (8) አመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገር ግን ከ18 አመት በታች የሆኑ ህጻናት የትም ቢቀመጡ (የፊት ወይም የኋላ ወንበር) በመቀመጫ ቀበቶ መታሰር አለባቸው።
- አሽከርካሪዎች ህጻናትን በተፈቀደ የህፃናት ተሳፋሪ መቆጣጠሪያ ስርዓት ውስጥ የማስጠበቅ እና ከ18 አመት በታች የሆኑ ህጻናት ቀበቶ ማሰራቸውን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው።

ሕጉን የሚጥሱ ሊቀጡ ይችላሉ እና ለፍርድ ቤት ወጪዎች በሙሉ ተጠያቂ ይሆናሉ።

ከ2 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት የመኪና ወንበር አምራቹ በገለጸው መሰረት ህጻኑ የመኪና ወንበር ከፍተኛውን የክብደት እና ቁመት ገደቦችን እስኪያልፍ ድረስ ፊቱ ወደኋላ የሚያይ የህጻናት የመኪና ወንበር ላይ መቀመጥ አለባቸው።ወንበር ከፍተኛውን የክብደት እና ቁመት ገደቦችን እስኪያልፍ ድረስ ፊቱ ወደ **የአየር ከረጢት ባለበት የፊት ወንበር ላይ ፊቱ ወደኋላ የሚያይ የህጻናት የመኪና ወንበር በጭራሽ አይግጠሙ።** በአደጋ ጊዜ የአየር ከረጢቱ በከፍተኛ ኃይል የሕፃኑን መቀመጫ ጀርባ ይመታል፣ ይህም ወደ ሕፃኑ ራስ የሚተላለፍ ሲሆን ይህም ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ሞት ያስከትላል።

በህግ በፌደራል የተፈቀደ የህጻናት የድህንነት ወንበር ወይም የተስተካከለ ወንበር ላይ በመቀመጥ መጓዝ ያለባቸው ዕድሚያቸው ከ ስምንት (8) ዓመት በታች የሆኑ ልጆች እያጓጓዙ ከሆነ የህጻናት መቀመጫውን በተሽከርካሪዎ ወንበር ላይ አጥብቀው እንዴት ማያያዝ እንደሚችሉ እና ህጻናትን በልጆቻቸው መቀመጫዎች ውስጥ እንዴት አድርጎ ማቆየት እንደሚችሉ እንዲያውቁ የተሽከርካሪዎን ባለቤት መመሪያ እና ከህጻናት መቀመጫው ጋር የመጣውን መመሪያ ያንብቡ።

ለልጆች እና ለቤት እንስሳት የደህንነት ምክሮች

ከመኪና ጋር በተያያዘ የሚከሰትን ሂትስትሮክ (የሙቀት መጨመር)ን መከላከል

የውጭ ሙቀት እየጨመረ በሄደ መጠን ልጆችና የቤት እንስሳት በሞቃት መኪና ውስጥ ብቻቸውን ሲቀሩ ከባድ የአካል ጉዳት አልፎ ተርፎም ህይወታቸውን ሊያጡ የሚችሉበት አጋጣሚ እየሰፋ ይሄዳል። ተሽከርካሪዎች በፍጥነት ይሞቃሉ - መስኮቱ በሁለት ኢንች ቢወርድም የውጭው ሙቀት በ 80 ዎቹ ፋራናይት ውስጥ ከሆነ በተሽከርካሪ ውስጥ ያለው ሙቀት በ 10 ደቂቃዎች ውስጥ ገዳይ ደርጃ ላይ ሊደርስ ይችላል።

አሳዛኝ የሙቀት መጨመርን (ሂትስትሮክ) ለማስወገድ የመከላከያ ምክሮች፦

- ምንም እንኳን መስኮቶቹ በትንሹ ቢከፈቱም ህጻናትን ሆነ የቤት እንስሳትን በመኪና ውስጥ ብቻቸውን በጭራሽ አይተዉ።
- ልጆች ያለ ክትትል በተሽከርካሪ ውስጥ እንዲጫወቱ በፍፁም አይፍቀዱ።
- የእጅ ቦርሳዎን፣ ቦርሳዎን፣ ሞባይል ስልክዎን ወይም የሚያስፈልግዎትን ነገር የኋላ ወንበር ላይ ያስቀምጡ፤ ይህ በመኪናው ውስጥ ያለን ልጅ ለማየት ያስችሎታል።
- መቀመጫው ባዶ በሚሆንበት ጊዜ ትልቅ ቴዲ ድብ አሻንጉሊት ወይም ሌላ በጨርቅ የተሰራ ለስላሳ አሻንጉሊት በመኪናው ውስጥ ያድርጉ። ልጁን በመኪና መቀመጫ ላይ ሲያስቀምጡት እንደ ምስላዊ ማስታወሻ ዕቃውን ወደ ፊት ወንበር ያዛውሩት።
- የሙቀት መጨመርን (ሂትስትሮክን) ስለመከላከል ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት https://www.safercar.gov/parents/InandAroundtheCar/heatstroke.htmን ይጎብኙ።

የክረምት ካፖርት እና የመኪና መቀመጫዎች

የክረምቱ በጣም ቀዝቃዛው ክፍል ሲቃረብ ወላጆች በተሽከርካሪ ጉዞ ወቅት እንዲሞቁ ለማድረግ የልጃቸውን ትልቅ የክረምት ካፖርት ይይዛሉ። ነገር ግን፣ ወፍራም የክረምት ኮት የልጁን የመኪና መቀመጫ ደህንነት ሊቀንስ ይችላል። ሁሉም ኮት እና ልብሶች በአደጋ ጊዜ ይጨመቃሉ፣ ነገር ግን ወፍራም የክረምት ኮት በቂ ኃይል ከያዘ ቀበቶው ላይ ከፍተኛ ልልነትን ወይም ክፍተት ይፈጥራል። የመኪና መቀመጫ ቀበቶ ህፃኑን በመኪናው ወንበር ላይ በአስተማማኝ ሁኔታ ይይዛል፣ እንዲሁም በአደጋ ጊዜ የተሻለ ጥበቃ ለመስጠት በልጁ አካል ላይ በትክክል መያያዝ አለበት። የክረምት ደህንነት ምክሮች ለልጆችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የፔንዶትን (PennDOT) ድህረ ገጽ በhttp://www.penndot.gov ይጎብኙ

የአየር ከረጢት ደህንነት መረጃ

- የአየር ከረጢቶች ተጨማሪ የመከላከያ መሳሪያዎች ናቸው። የወገብ እና የትከሻ ቀበቶዎች ሁል ጊዜ መደረግ አለባቸው። የመቀመጫ ቀበቶዎን በወገብዎ ላይ አድርገው፣ የትከሻውን ማሰሪያ ደግሞ ከአንገትዎ ርቆ በደረትዎ ላይ አጥብቀው ይያዙ።
- የአሽከርካሪው እና የፊት ተሳፋሪ መቀመጫዎች በተቻለ መጠን ወደ ኋላ መመለስ አለባቸው፣ በተለይ ለአጭር ሰዎች። የጋዝ እና የፍሬን ፔዳሎችን ለመድረስ እና ለመጠቀም፣ በተጨማሪም በመሳሪያ ፓኔል እና በመሪው ላይ ያሉትን መቆጣጠሪያዎች ለመጠቀም ሳያስቸግርዎ በተቻለ መጠን ከአየር ከረጢቱ ርቀው መቀመጥ አለብዎት። የአየር ከረጢቱ ቢከፈትም ደህንነትዎን ለመጠበቅ ቢያንስ ከመሪው 10 ኢንች ርቀት ላይ መሆን አለብዎት።
- መሪውን በ9 ሰዓት እና በ3 ሰዓት ወይም በ8 ሰዓት እና በ4 ሰዓት ቦታዎች ላይ አጥብቀው ይያዙ። ይህ የአየር ከረጢቱ ቢከፈት እንኳ እንጓዎችዎን እና ክንዶችዎን ከመቁሰል ወይም ከመሰበር ወይም ፊትዎ ላይ በኃይል እንዳይመታ ያደርጋል። እንዲሁም አውራ ጣትዎን ከመሪው ውስጠኛ ክፍል ከመያዝ ይልቅ በመሪው የላይኛው ጫፍ ወይም በውጭኛው ጫፍ ላይ ያድርጉ።
- ወደ ኋላ የሚያዩ የሕፃን መቀመጫዎች ያላቸው ሕፃናት **በፍጹም እንደገና** በተሳፋሪው በኩል የአየር ከረጢት ባለበት ተሽከርካሪ የፊት ወንበር ላይ መጓዝ የለባቸውም።
- ሁሉም ልጆች እድሜያቸው 12 እና ከዚያ በታች የሆኑ በኋለኛው ወንበር ላይ እንዲቀመጡ ይመከራል። ለዚህ ሁለት(2) ምክንያቶች አሉ፦ አንደኛ፣ አብዛኛዎቹ ግጭቶች የፊት ለፊት ግጭቶች ናቸው ስለዚህ ልጆችን ከኋላ ወንበር ላይ ማስቀመጥ ከግጭቱ ነጥብ ያርቃቸዋል፤ ሁለተኛ፣ ልጆች በመቀመጫቸው ላይ የመንቀሳቀስ አዝማሚያ አላቸው እና የፊት ወንበር ላይ ከሆኑ ለአየር ከረጢቱ በጣም ሊቀርቡ ይችላሉ ይህም አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ የአየር ከረጢቱ ቢከፈት ለጉዳት ያጋልጣቸዋል።

የአሜሪካውያን አካል ጉዳተኞች ህግ (ADA)

የአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች መብት ህግ 1990ን ለማክበር ፔንዶት (PennDOT) ሁሉም የአሽከርካሪ ፍቃድ መስጫ ማእከላትና የፎቶ ፍቃድ መስጫ ማእከላት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ አድርጓል። በተጨማሪም የእውቀት እና የመንገድ ፈተናዎችን መውሰድ ለሚፈልጉ እና የመስማት ወይም የማንበብ ችግር ላለባቸው ሰዎች የሚከተሉት አገልግሎቶች ይገኛሉ።

መስማት ለተሳናቸውና የመስማት ችግር ላለባቸው አስተርጓሚዎች

የፔንዶት (PennDOT) የአሽከርካሪ ፈቃድ ቢሮ የመስማት ችግር ላለባቸው እና የምልክት ቋንቋን በመጠቀም ለሚግባቡ ግለሰቦች አስተርጓሚ በጠየቁ ጊዜ ያቀርባል። ይህ አገልግሎት የአሽከርካሪዎችን የእውቀት እና/ወይም የመንገድ ፈተናዎችን መውሰድ ለሚፈልጉ ወይም ልዩ የነጥብ ፈተና መውሰድ ለሚኖርባቸው ደንበኞች ይገኛል።

ፈተናውን መውሰድ ሲፈልጉ ቢያንስ ከሁለት (2) ሳምንታት አስቀድመው ከፔንዶት (PennDOT) ጋር የመጀመሪያ ግንኙነትዎን ያድርጉ፣ እና PennDOT የእርስዎን ተመራጭ ተርጓሚ ለማግኘት የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል።

አስተርጓሚ እንዲኖርዎት የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት

1. ፈተናዎን ለመውሰድ ቀጠሮ ለመያዝ በ 717-412-5300 ይደውሉ። የጽሑፍ መሣሪያ (TDD) የሚጠቀሙ ከሆነ ወደ 711 ይደውሉ። ፈተናውን መውሰድ የሚፈልጉበትን የአሽከርካሪ ፈቃድ መስጫ ማዕከል ይግለጹ እና ፈተናውን መውሰድ የሚችሉባቸውን ቢያንስ ሶስት (3) ቀናትን ይስጡ።

   ፈተናዎን ለመውሰድ ቀጠሮ ሲይዙ የፔንስልቬንያ ሪሌይ አገልግሎትንም መጠቀም ይችላሉ (የመናገር ወይም የመስማት ችግር ላለባቸው ሰዎች)። ይህ አገልግሎት የጽሑፍ መሣሪያ (TDD) ሥርዓት ያለው ሰው እና የሌለው ሰው መካከል የስልክ ግንኙነትን ያቀርባል። ይህ ሥርዓት በሰሚዎች እና መስማት የተሳናቸው ሰዎች መካከል ላለ ጥሪ እንደ መካከለኛ ሆኖ የሚያገለግል ኦፕሬተርን ይጠቀማል። የጽሑፍ መሣሪያ (TDD) ሥርዓት ካለዎት የፔንስልቬንያ ሪሌይ አገልግሎትን ለመጠቀም በ 1-800-654-5984 መደዎል አለብዎት። አገልግሎቱን እንደ ሰሚ ተደዋይ እየተጠቀሙ ከሆነ 1-800-654-5988 ን መጠቀም ይኖርብዎታል። አስተርጓሚ ለፈተናዎ እንዲረዳዎ ከተቀጠረ የፈተናውን ቀን ለማረጋገጥ ተመልሰው ጥሪ ይደረግልዎታል።

2. ቀጠሮዎን ሲይዙ፣ መጠቀም የሚመርጡት የምልክት ቋንቋ ካለ መጥቀስ ይኖርብዎታል። የሚገኙት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው:
   - የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ASL)
   - በምልክት የተደገፈ እንግሊዝኛ (SEE)
   - ፒድጂን የምልክት ቋንቋ (PSE)
   - የቃል አስተርጓሚ (ከንፈር የሚያነብ ሰው)

አማራጭ የፈተና ዘዴ

የእውቀት ፈተናውን የሚወስዱ አንዳንድ ሰዎች ማንበብ ሊቸገሩ ይችላሉ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች ማንበብ የማይችሉ ሊሆኑ ይችላሉ እና ፈተናው ቢነበብላቸው የበለጠ ምቾት ሊሰማቸው ይችላል። በጥያቄ መሰረት የድምጽ ፈተናዎች በመላው ግዛቱ በሚገኙ ሁሉም የአሽከርካሪ ፈቃድ መስጫ ማዕከላት ውስጥ ይሰጣሉ።

ለአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች

በፔንስልቬንያ ህግ መሰረት አንድ ግለሰብ ለአካል ጉዳተኞች በተዘጋጀ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ውስጥ በህጋዊ መንገድ ከማቆሙ በፊት ሁለት (2) ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው:-

1. ተሽከርካሪው በሚቆምበት ጊዜ የአካል ጉዳተኛ ወይም የአካል ጉዳተኛ የቀድሞ ወታደር መለያ ታርጋ/የማቆሚያ ምልክት መታየት አለበት።
2. ተሽከርካሪው የሚነዳው በአካል ጉዳተኛው ወይም ከባድ የአካል ጉዳት ላለበት የቀድሞ ወታደር ወይም እነሱን ለማጓጓዝ መሆን አለበት።

ማንኛውም ተሽከርካሪ ለአካል ጉዳተኞች በተዘጋጀ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ላይ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ከቆመ በመጎተት ከዚያ ቦታ ሊወገድ እና የመጎተት ወጪዎችን በመክፈል ሊመለስ ይችላል። ይህ የመኪና ማቆሚያ ጥሰት ቀላል ጥፋት ነው። በዚህ ጥፋት የተከሰሱ ግለሰቦች ከ50 እስከ 200 ዶላር ይቀጣሉ።

ቆሻሻን መጣልን የሚከለክል ህግ

ከተሽከርካሪ ማንኛውንም ቆሻሻ ወረቀት፣ መጥረጊያ፣ አመድ፣ የቤት ውስጥ ቆሻሻ፣ ብርጭቆ፣ ብረት፣ ቆሻሻ ወይም ማንኛውንም አደገኛ ወይም ጎጂ ንጥረ ነገር በየትኛውም አውራ ጎዳና ላይ፣ በሌላ በማንኛውም የህዝብ ወይም የግል ንብረት ላይ (ባለቤቶቹ ሳይፈቅዱ) ወይም ወደዚህ የጋራ ሀብት ውሃ ውስጥ መጣል ወይም ማስቀመጥ ወንጀል ነው ወይም ከላይ የተጠቀሱትን እቃዎች ወዲያውኑ ሳያስወግዱ ወይም እንዲወገዱ ሳያደርጉ መፍቀድም ወንጀል ነው። ይህንን ህግ መጣስ፣ እርስዎ ሹፌር በሆኑበት በማንኛውም ተሽከርካሪ ውስጥ ባሉ ሌሎች ሰዎች ባህሪ ምክንያት የሚመጣ ማንኛውም ጥሰትን ጨምሮ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ እስከ 300 ዶላር የሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ሊያስከትል ይችላል።

የተሽከርካሪ ደህንነት እና ልቀቶች ፍተሻ

ተሽከርካሪዎ በየ 12 ወሩ በተፈቀደ የፍተሻ ጣቢያ የደህንነት ፍተሻ ሊደረግለት ይገባል። በተለጣፊው ላይ ያለው ቀን ተሽከርካሪዎ መቼ እንደገና መፈተሽ እንዳለበት ይነግርዎታል። አንድ ተሽከርካሪ ቀጣዩ ጊዜው ከሚያለፍበት ቀን በፊት እስከ 90 ቀናት ድረስ ሊፈተሽ ይችላል። እንዲሁም አንድ ፖሊስ መኮንን በተሽከርካሪዎ ላይ የተበላሸ መሣሪያዎች ካየ የክስ መዝገብ ለማስቀረት በአምስት (5) ቀናት ውስጥ እንዲጠግኑት ሊጠየቁ ይችላሉ። በብዙ ካውንቲዎች የመኪናዎን፣ የቫንዎን ወይም ቀላል የጭነት መኪናዎን (የሞዴል ዓመት 1975 ወይም ከዚያ በኋላ) የደህንነት ፍተሻ ከማጠናቀቅዎ በፊት የልቀት መቆጣጠሪያ ስርዓቱን መመርመር ይኖርብዎታል። የልቀት ፍተሻዎች የሚከናወኑት በ ፔንዶት (PennDOT) በተረጋገጡ በግል ባለቤትነት በተያዙ ንግዶች ነው። በካውንቲዎ ስላሉት መስፈርቶች ለማወቅ ወደ ልቀት የደንበኞች የስልክ መስመር በ1-800-265-0921 ይደውሉ።

ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ማለፍ ህጉ ነው



1. ከማለፍዎ በፊት በመጀመሪያ በብስክሌተኛው ዙሪያ ማለፍ ይችሉ እንደሆነ መወሰን አለብዎት። የሚመጣውን ትራፊክ (ተሽከርካሪ) መመልከትዎን እርግጠኛ ይሁኑ። በሚያልፉበት ጊዜ **ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለማለፍ ተሽከርካሪዎ እና በብስክሌት መካከል ቢያንስ አራት (4) ጫማ** መተው አለብዎት። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘና በአስተማማኝ ሁኔታ መሻገር ከተቻለ ተሽከርካሪዎንና ብስክሌቱን በአራት (4) ጫማ ርቀት ለማቆየት ማዕከላዊውን ድርብ ቢጫ መስመር መሻገር ይችላሉ።
2. ወደ ግራ ካልታጠፉ በስተቀር የሚያልፉ ተሽከርካሪዎች ይልቅ ቀስ ብለው የሚጓዙ ብስክሌተኞች ከመንገዱ በስተቀኝ በኩል መሄድ እና እንደሌላው ትራፊክ (ተሽከርካሪ) በተመሳሳይ አቅጣጫ መጓዝ አለባቸው። ይሁን እንጂ ይህ መስፈርት በእያንዳንዱ አቅጣጫ አንድ መስመር ባላቸው መንገዶች ላይ አይተገበርም።
3. አንድ መስመር ብቻ ባለበት መንገድ ላይ ብስክሌተኞች በመንገድ ላይ ያሉ አደጋዎችን ለማስወገድ ማንኛውንም የመንገዱን ክፍል መጠቀም ይችላሉ ይህም ማለት ከቆሙ እና ከተሽከርካሪዎች ን ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀት መጠበቅን ይጨምራል።
4. አሽከርካሪዎች በመንገድ ወይም ዳር ላይ ቀጥ ብሎ የሚሄድ ብስክሌተኛ ወደሚገኝበት አቅጣጫ መታጠፍ የለባቸውም።
5. ብስክሌተኛውን ከመንገድ ላይ ማስወጣት አይችሉም። ይህን ካደረጉ በወንጀል ክስ ሊከሰሱ ይችላሉ።
6. ብስክሌተኞች የተሽከርካሪ ኦፕሬተሮች እንደሆኑ ተደርገው የሚቆጠሩ ሲሆን ሁሉንም የትራፊክ ህጎች እንዲያከብሩ ይጠበቃል፤ ሆኖም ከተለጠፈው ዝቅተኛ ፍጥነት በታች ሊጓዙ ይችላሉ እንዲሁም ትራፊክን በማስተጓጎል ሊከሰሱ አይችሉም። ብስክሌተኞች በመንገድ ዳር ወይም ዳርቻ ላይ መንዳት ይችላሉ ነገር ግን አይገደዱም.

ለተጨማሪ መረጃ፣ የፔንስልቬንያ የብስክሌት ነጂዎች መመሪያ (PUB 380) በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይቻላል:-
http://www.dot.state.pa.us/public/pubsforms/Publications/Pub%20380.pdf

የተከፈቱ በሮች ለብስክሌተኞች የሚያደርሱት አደጋ

የተከፈቱ የተሽከርካሪ በሮች ለብስክሌተኞች በጣም አሳሳቢ ስጋት ይፈጥራሉ። የተሽከርካሪ በር ሲከፍቱ አሽከርካሪዎች እና ተሳፋሪዎች የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይመከራሉ።

1. የኋላ መመልከቻ መስታወትዎን ይመልከቱ።
2. የጎን መመልከቻ መስታወትዎን ይመልከቱ።
3. በሩን በሩቅ እጅዎ ይክፈቱ (በሩ ከሚገኝበት የራቀው እጅ)

ይህ "የደች ሪች" ዘዴ ተብሎ ይጠራል ምክያቱም በኔዘርላንድስ ውስጥ የተፈጠረ ዘዴ ነው። ይህ ሰውነትዎ እንዲዞር ያስገድድዎታል በዚህም ምክንያት ወደ እርስዎ የሚመጡ ብስክሌተኞችን በተሻለ ሁኔታ ለመመልከት ያስችልዎታል። እንዲሁም የተሽከርካሪው በር በጣም በፍጥነት እንዳይከፈት ይከላከላል። ይህ ብስክሌተኞችን መጠበቅ ብቻ ሳይሆን በርዎ በሚመጣ ተሽከርካሪ እንዳይጎዳ ወይም እንዳይነቃነቅ ሊከላከል ይችላል።



ብስክሌተኞች በብስክሌት መስመር ባላቸው እና በሌላቸው ጎዳናዎች ላይ በሮችን ለማስወገድ ከቆሙ መኪኖች ቢያንስ ሦስት ጫማ ርቀት ላይ መንዳት አለባቸው። ይህ ብስክሌተኞችን ከ "የበር ክልል" ውጭ የሚያደርግ ሲሆን ይህም በሮች ሲከፈቱ ከመመታት ይጠብቃቸዋል።

የጽሑፍ መልእክት መላላክን የሚከለክል ሕግ

ሕጉ ማርች 8 ቀን 2012 ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን ሕጉን መጣስ የ50 ዶላር ቅጣት የሚያስከትል መሠረታዊና ቀላል ጥፋት ነው።

ሕጉ ምን ያደርጋል

- መስተጋብራዊ ገመድ አልባ መገናኛ መሣሪያን (IWCD)፡ ጽሑፍ ለመጻፍ፣ ፈጣን መልእክት ለመላክ፣ ኢሜይል ለመላክ ወይም በይነመረብን ለመፈለግ የሚያገለግል ገመድ አልባ ስልክ፣ የግል ዲጂታል ረዳት፣ ስማርት ስልክ፣ ተንቀሳቃሽ ወይም ሞባይል ኮምፒውተር ወይም ተመሳሳይ መሣሪያዎች በማለት ይገልጻል።
- ጽሑፍ ላይ የተመሠረተ ግንኙነትን፡ በ IWCD ላይ እንደተቀናበረ ወይም እንደተቀበለ የጽሑፍ መልእክት፣ ፈጣን መልእክት፣ ኢሜይል ወይም ሌላ የጽሑፍ ግንኙነት በማለት ይገልጻል።
- ይህ ሕግ አሽከርካሪዎች መስተጋብራዊ ገመድ አልባ መሣሪያዎችን ከመጠቀም የሚገድቡ ማናቸውንም የአካባቢ ድንጋጌዎች እንደሚሽርና እንደሚቀድም ግልጽ ያደርጋል።

ሕጉ IWCD ለመያዝ ሥልጣን አይሰጥም። የጽሑፍ መልእክት መላክ ክልከላ የጂ ፒ ኤስ መሣሪያን፣ በተሽከርካሪው ውስጥ በአካልም ሆነ በኤሌክትሮኒክ መንገድ የተዋሃደ ሥርዓትን ወይም መሣሪያን ወይም በጅምላ ማመላለሻ ተሽከርካሪ፣ አውቶቡስ ወይም ትምህርት ቤት አውቶቡስ ላይ የተገጠመ የመገናኛ መሣሪያን አያካትትም።

አደገኛ ሁኔታዎችን ስለሚያመለክቱ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎች ሕግ መታዘዝ

ይህ ሕግ መስከረም 6 ቀን 2012 ሥራ ላይ የዋለ ሲሆን እንደ ጎርፍ ያሉ አደገኛ ሁኔታዎች በመከሰታቸው ምክንያት መንገድ ወይም አውራ ጎዳናን የሚዘጉ ምልክቶችን ወይም የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሣሪያዎችን ዙሪያ መንዳት ወይም በእነሱ ውስጥ ማለፍ ሕገወጥ ያደርጋል። ይህንን ሕግ በመጣስ የተገኘው ውሳኔ በመንዳት ሪከርድዎ ላይ 2 ነጥቦችን የሚጨምር ከመሆኑም በላይ እስከ 250 ዶላር የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ያስከትላል። በተጨማሪም በእርስዎ ድርጊት ምክንያት የአደጋ ጊዜ ምላሽ ሰጪዎች ከተጠሩ ቅጣቱ እስከ 500 ዶላር የሚጨምር ከመሆኑም በላይ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ወጪዎችን ለመክፈል ተጠያቂ ይሆናሉ።

ምዕራፍ 6:
ማጣቀሻዎች

ይህ ምዕራፍ አጋዥ መረጃዎችን፣ ቅጾችን፣ ሕትመቶችንና ጽሑፎችን በተመለከተ ፈጣን ማጣቀሻዎችን ያቀርባል።

የደንበኛ ጥሪ ማዕከል

መደበኛ የቤት ስልክ የሚጠቀሙ ከሆነ የአሽከርካሪ እና የተሽከርካሪ አገልግሎቶችን በተመለከተ መረጃ በቀን ለ24 ሰዓታት ማግኘት ይችላሉ።

ከጠዋቱ 8 ኤ.ኤም እስከ ቀኑ 5 ፒ.ኤም ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ የደንበኞች አገልግሎት ተወካዮችን ማግኘት ይችላሉ። - ከሰኞ እስከ አርብ

ከበዓላት ውጪ ባሉ ቀናት ቀጥታ ድጋፍ ለማግኘት: 717-412-5300 TDD: 711

የመንገድ ላይ የተግባር ፈተና እና ልዩ የነጥብ ፈተና ቀጠሮዎች

የልዩ ነጥብ ፈተና እና የንግድ ያልሆነ የመንገድ ፈተና ለመውሰድ ቀጠሮዎች መያዝ አለባቸው። የመንገድ የተግባር ፈተናን ወይም የልዩ ነጥብ ፈተናን ለመውሰድ ዝግጁ ሲሆኑ፣ ፈተናዎን ኦንላይን ላይ በአሽከርካሪና ተሽከርካሪ አገልግሎቶች ድህረ ገጽ በwww.dmv.pa.gov አመካኝነት ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ። የኢንተርኔት አገልግሎት ከሌልዎት ከበዓል ቀናት በስተቀር ባሉት ቀናት ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 8 ኤ.ኤም እስከ ቀኑ 5 ፒ.ኤም ባለው ጊዜ ውስጥ በ1-800-423-5542 በመደወል ፈተናዎን ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ።

ያስታውሱ:- እድሜዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ፣ የለማጅ ተማሪ ፈቃድዎን ከተቀበሉ በኋላ የመንገድ ፈተናዎን ለስድስት (6) ወራት መውሰድ አይችሉም፤ እንዲሁም የ 65 ሰዓታት ተሽከርካሪ የመንዳት ክህሎት ግንባታ መስፈርቶችን ማጠናቀቅ አለብዎት።

ለንግድ አላማዎች የማይውል መንጃ ፍቃድ የሶስተኛ ወገን የፈተና ፕሮግራም

ፔንዶት (PennDOT) የመንገድ የተግባር ፈተናውን ገበያውን ያገናዘበ ክፍያ ለሚያስከፍሉ ለሶስተኛ ወገን ቢዝነሶች እንዲያስተዳድሩ ፈቃድ ሰጥቷል። ሁሉም የሶስተኛ ወገን ፈታኞች በፔንዶቲ (PennDOT) እውቅና ያላቸው ሲሆን፣ ፈተናውም በፔንዶቲ (PennDOT) የመንጃ ፈቃድ መስጫ ማዕከል ከሚሰጠው ፈተና ጋር አንድ ዓይነት ነው። በአካባቢዎ ስለ ሚገኙ የሶስተኛ ወገን ፈታኞች ዝርዝር ለማግኘት፣ www.dmv.pa.govን ይጎብኙ።

በበይነመረብ ላይ የሚገኙ የዲፓርትመንት ቅጾች እና ህትመቶች

የመንጃ ፍቃድ እና የሞተር ተሽከርካሪዎችን የሚመለከቱ መረጃዎች፣ ቅጾች፣ ህትመቶች እና ፋክት ሺቶች (fact sheets) ለደንበኞች ምቾት ተብለው የተዘጋጁ ሲሆን በፔንዶት የአሽከርካሪዎች እና የተሽከርካሪዎች አገልግሎቶች ድረ-ገጽ ላይ www.dmv.pa.gov ይገኛሉ።

ክልል አቀፍ እና ካውንቲ አቀፍ ካርታዎች

የክልል እና የካውንቲ ካርታዎች የተመለከተ መረጃ ለማግኘት ከሰኞ እስከ አርብ ከጥዋቱ 8 ኤ.ኤም እስከ ከሰዓት 4 ኤ.ኤም ባለው ጊዜ ውስጥ በ1-717-787-6746 ይደውሉ።

ሌላ መረጃ

የዩናይትድ ስቴትስ የትራንስፖርት ክፍል የአውቶ ሴፍቲ በ1-800-424-9393 የስልክ መስመር ወይም በ www.nhtsa.dot.gov ድር-ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

511PA

511PA የትራፊክ መዘግየት ማስጠንቀቂያዎችን፣ የአየር ሁኔታ ትንበያዎችን፣ የክልል የቱሪዝም መረጃን፣ የትራንዚት ኤጀንሲዎች እና ከአውሮፕላን ማረፊያዎች ጋር የሚያገናኙ አገናኞችን ጨምሮ ነፃ የ24 ሰዓት የመረጃ አገልግሎቶችን ይሰጣል። ተንቀሳቃሽ ስልኮን ወይም የቤት ስልኮን በመጠቀም ወደ 511 በመደወል ወይም በበይነመረብ በኩል www.511PA.com.ን በመጎብኘት አገልግሎቱን ማግኘት ይችላሉ። የ511PA የመንገድ አውታረ መረብ የፔንስልቬንያን ጨምሮ ሁሉንም 1,759 ማይል አውራ ጎዳናዎች እንዲሁም በሃሪስበርግ፣ ፊላዴልፊያ እና ፒትስበርግ ያሉ ሌሎች ዋና ዋና መንገዶችን ያጠቃልላል። የዚህ አውታረ መረብ አብዛኛው ክፍል የሚመለከት የትራፊክ መረጃ እንደ አደጋዎች፣ የግንባታ እንቅስቃሴዎች እና የክረምት የመንገድ ሁኔታዎችን የመሳሰሉ ክስተቶችን ያካትታል። በተጨማሪም፣ ለተለያዩ አውራ ጎዳናዎች እና በከተማ ውስጥ ላሉ ሌሎች ዋና መንገዶች የሚፈቀድ አማካኝ የትራፊክ ፍጥነት ገደብ መረጃም ተካቷል። በተጨማሪም፣ ተጠቃሚዎች በኢሜይል እና በጽሁፍ መልዕክቶች አማካኝነት ለግል የተበጁ የጉዞ ማንቂያዎችን ለመቀበል በዌብሳይቱ ላይ መመዝገብ ይችላሉ። ፔንዶት (PennDOT) አሽከርካሪዎች በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ወደ 511PA እንዳይደውሉ ያሳስባል። ደዋዮች ወደ ስልኩ ከመደወላቸው በፊት ከመንገድ ዳር መቆም አለባቸው ወይም የቆሙ የትራፊክ ፍሰቶች

መንቀሳቀስ አለመጀመራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

በካርቦን ሞኖክሳይድ መመረዝ

ሁሉም በነዳጅ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ካርቦን ሞኖክሳይድ ያመነጫሉ፤ ይህም ከተሽከርካሪው የጭስ ማውጫ ቱቦ የሚወጣ ገዳይ ሽታ የሌለው ጋዝ ነው። የካርቦን ሞኖክሳይድ ጋዝ ማሽተት አይችሉም። እንቅልፍ እንቅልፍ ካልዎት ወይም የማቅለሽለሽ ስሜት ከተሰማዎት የካርቦን ሞኖክሳይድ መመረዝ ሊሆን ይችላል።

የካርቦን ሞኖክሳይድ መመረዝ ምልክቶች

- የድካም ስሜት አሊያም ጉልበት ማጣት
- የማዞር ስሜት
- ራስ ምታት
- ማቅለሽለሽ እና/ወይም ማስታወክ
- ፈጣን የልብ ምት
- የተዛባ አተነፋፈስ
- ግራ መጋባት ወይም አቅጣጫን አለማወቅ
- ማሳል
- የደረት ህመም

በተሽከርካሪዎች ውስጥ የካርቦን ሞኖክሳይድ መርዝን ለመከላከል የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮች

- በተሽከርካሪዎ ውስጥ የካርቦን ሞኖክሳይድ መመረዝን ለመከላከል የተሽከርካሪዎን የጭስ ማውጫ ስርዓት እና መፍለሮች (mufflers) አዘውትሮ መፈተሽ እና መጠገን አስፈላጊ ነው። የተሽከርካሪዎ በጭስ ማውጫ ስርዓት ውስጥ ቀዳዳዎች ወይም ሌሎች ጉድለቶች እንዳሉ ካስተዋሉ በአፋጣኝ በተሽከርካሪ ባለሙያ እንዲፈተሽ ያድርጉ።
- ተሽከርካሪዎ የጋራዡ በር ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በተዘጋበት ጋራዥ ውስጥ አያሙቁት። ተሽከርካሪዎ በጋራዡ ውስጥ ሆነው ካስነሱት የጋራዥዎን በር ሙሉ በሙሉ ይክፈቱ።
- ተሽከርካሪዎ ኪ-ለስ ከሆነ (ያለ ቁልፍ የሚሰራ) እና ከቤትዎ ጋር በተገናኘ ጋራዥ ውስጥ ካቆሙት ተሽከርካሪውን ማጥፋትዎን በጭራሽ አይርሱ።
- በረዷማ በሆኑ ቀናት ሁል ጊዜ የጭስ ማውጫ ቱቦዎን ይፈትሹ እና የተሽከርካሪዎን የጭስ ማውጫ ቱቦ ሊዘጋ የሚችል ማንኛውንም በረዶ ወይም የበረዶ ብናኝ ያስለቅቁ።
- በትራፊክ መጨናነቅ ውስጥ ከቆሙ ወይም ቆሞ ያለ ተሽከርካሪ ውስጥ ከተቀመጡ በከፊል መስኮትዎን ይክፈቱ።
- በተሽከርካሪዎ ውስጥ በባትሪ የሚሠራ የካርቦን ሞኖክሳይድ መመምርያ መሳርያ መግጠምን ያስቡበት፤ ከገጠሙ በኋላ በየዓመቱ በፀደይ እና በመኸር ወቅት ሰዓቶችዎን ግዜ በሚቀይሩበት ጊዜ ባትሪዉን ይፈትሹ ወይም ይቀይሩ።
- በተሽከርካሪዎ ውስጥ የካርቦን ሞኖክሳይድ መመረዝ አለ ብለው ካሰቡ፣ ወዲያውኑ ከተሽከርካሪው በመውጣት ንጹህ አየር ያግኙ፤ እንዲሁም ወዲያውኑ ድንገተኛ ህክምና ያግኙ።

ርዕስ	ገጽ
የማፍጠኛ ፔዳል መጣበቅ	**62**
አደጋዎች (ግጭቶችን ይመልከቱ)	
አድራሻ፣ ለውጥ	**89**
የኤር-ባግ (የአየር-ከረጢት) ደህንነት መረጃ	**91**
አልኮል እና መንዳት	**33**
አማራጭ የፈተና ዘዴዎች	**92**
የአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ሕግ ድንጋጌ (ADA)	**91**
ቀጠሮዎች፡-	
የመንገድ ላይ ፈተና (የተግባር ፈተና)	5, 94
የልዩ ነጥብ ፈተና	94
ወደ ኋላ መንዳት	**38**
ብስክሌተኞች	**55, 56, 92, 93**
ማየት የተሳናቸው እግረኞች	**9**
ለማየት የሚያዳግቱ ቦታዎች	**37**
የፍሬን ብልሽት	**62**
ፍሬን መያዝ	**58, 60**
አውቶቡሶች	**56**
የትምህርት ቤት አውቶቡሶች	58
የካርቦን ሞኖክሳይድ መመረዝ	**95**
መስመሮችን መቀየር	**38**
የህፃናት ደህንነት መጠበቂያ መቀመጫዎች አጠቃቀም ህግ	**90**
ክብ መገናኛ መንገዶች	**49**
የመንጃ ፍቃዶች ክፍሎች	**4**
ሐሳብዎን ለሌሎች አሽከርካሪዎች ማሳወቅ	**43**
ቁጥጥር የሚደረግባቸ መድሃኒቶች (ዕጾች)፡	
በአልኮል/አደንዛዥ ዕጽ ተጽእኖ ስር ሆኖ መንዳት (DUI)	81
ግጭቶች	**34, 81**
ወሳኝ የማሽከርከር ስህተቶች	**34**
መንገዶችን ማቋረጥ	**46**
ኩርባዎች፣ መግባባት	**51**
የደንበኞች ጥሪ ማዕከል	**94**
ሙሉ በሙሉ መስማት ለተሳናቸው/የመስማት እክል ላለባቸው የሚሆኑ አስተርጓሚዎች	**91**
ከአሽከርካሪው ጋር የተያያዙ ነገሮች	**32**
አልኮል እና መንዳት	33
በሽታዎች እና የጤና እክሎች	33
በማሽከርከር ላይ ትኩረትን የሚረብሹ ነገሮች	32
መድሃኒቶች (አደንዛዥ ዕፆች) እና ማሽከርከር	34
የጤና ምክንያቶች	33
መስማት	33
ትኩረት አለመስጠት	32
የእንቅልፍ እጦት	32
እይታ	33
የመንጃ ፍቃድ ህጎች ስምምነት (DLC)	**84**
የመንጃ ፍቃድ/የተማሪ ፍቃድ፡-	
የመንጃ ፍቃዶች ክፍሎች	4
የጀማሪዎች መንጃ ፍቃድ መረጃ	3
የጀማሪ ተማሪዎች ፍቃድ መረጃ	3
ምን አይነት ክፍል ይፈልጋሉ?	4
የመንጃ ፍቃድ/የተማሪ ፍቃድ፡-	
ማን ያስፈልገዋል	3
በምሽት መንዳት	**39**
የማሽከርከር ድንገተኛ ሁኔታዎች፣ ማስተናገድ፡-	
የማፍጠኛ ፔዳል መጣበቅ	62
የፍሬን ብልሽት	62
በድንገት ፍሬን መያዝ	61
ፍሬን መያዝ	58
ከአስፋልት ተንሸራቶ መውጣት	63
በጎርፍ የተጥለቀለቁ መንገዶች	61
ጥሩንባ (ክላክስ) ስለመጠቀም	44
ሀይድሮፕላኒንግ	41
የትራፊክ መብራት ምልክቶች፣ በመጠቀም	44
መንሸራተት	61
አንሸራታች ወለሎች - የመንገድ ሁኔታዎች	40
በረዶ እና የበረዶ ብናኝ	41
መሪ ማዞር	60
የጎማ ፍንዳታ	62
የተሽከርካሪዎች በፊት ለፊት መቀራረብ	64
እርጥብ አስፋልቶች	40
የመንዳት ታሪክ መረጃ	**79**
በአልኮል/አደንዛዥ ዕጽ ተጽእኖ ስር ሆኖ መንዳት (DUI)	**33, 34, 81**
መድሃኒቶች (አደንዛዥ ዕፆች) እና መንዳት	**34, 81**
የጭስ ልቀቶች፣ የተሽከርካሪ ደህንነት ፍተሻ	**92**
የአደጋ ጊዜ ተሽከርካሪዎች	**59**
ከፖሊስ ማምለጥ ወይም መሸሽ	**81**
በጎርፍ የተጥለቀለቁ መንገዶች	**61**
ጭጋግ/ጉም	**42**
የውጭ መንጃ ፍቃድ ያላቸው አሽከርካሪዎች	**3**
ቅጾች እና ህትመቶች፣ የዲፓርትመንት	**94**
"የአራት-ሰከንድ ህግ"	**35**
የቀብር ሂደት ሲያጋጥሞት	**64**
አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች	**19**
የግንባር መብራቶች	**39, 40**
የግንባር መብራቶች/የመኪና የንፋስ መከላከያ መጥረጊያ ህግ	**42**
የጭንቅላት ማስደገፍያዎች፣ ማስተካከል	**32**
የጤና ምክንያቶች	**33**
አውራ ጎዳናዎች እና መገናኛዎች፣ መግባባት፡-	
ወደ አውራ ጎዳናዎች መግባት	52
ከአውራ ጎዳናዎች መውጣት	52
በአውራ ጎዳናዎች ላይ መጓዝ	52
ጥሩንባ (ክላክስ)፣ የእርስዎን በመጠቀም	**44**
በፈረስ የሚጎተቱ ተሽከርካሪዎች እና ፈረስ ጋላቢዎች	**59**
ሀይድሮፕላኒንግ	**41**
ትኩረት ማጣት (መንዳትዎን እንዴት እንደሚጎዳ)	**32**
ሌሎች መረጃዎች	**94**
ፍተሻ፣ የተሽከርካሪ ደህንነት እና የጭስ ልቀቶች	**92**

ርዕስ	ገጽ
ኢንሹራንስ፣ ያለ ኢንሹራንስ ስለማሽከርከር	**80**
በይነመረብ	**92**
መስማት ለተሳናቸው/የመስማት እክል ላለባቸው የሚሆኑ አስተርጓሚዎች	**91**
መገናኛ መንገዶች/መስቀለኛ መንገዶች፡-	
ወደ መገናኛ መንገዶች/መስቀለኛ መንገዶች መቃረብ	48
ጀግሃንድሎች (Jughandles)	50
ቅድሚያ ማን መስጠት እንዳለበት መግባባት	48
ክብ አደባባዮች (ራውንድባውት) እና ማዞርያዎች	50
ለመንገድ መስመር ምደባ የሚውሉ የመንገድ ዳር ምልክቶች እና የትራፊክ መስመር ምልክቶች 48 የትራፊክ ምልክቶች እና የማቆሚያ ምልክቶች።	49
በመጓዝ ላይ	49
ወደ ግራ መታጠፍ	45, 48, 49
ወደ ቀኝ በመታጠፍ	45, 46, 48
የኢንተርስቴት የመንገድ መስመር ቁጥር ስርዓት	**20**
የጀማሪዎች መንጃ ፍቃድ መረጃ	**3**
የጀማሪ ተማሪዎች ፍቃድ መረጃ	**3**
ተሽከርካሪዎን በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ	**37**
ህጎች፡-	
የአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ሕግ ድንጋጌ (ADA)	91
ቆሻሻን መጣልን የሚከለክል ህግ	92
ብስክሌት	92
ህጻናትን ደህንነታቸው በተጠበቀ መልኩ የማስቀመጥ ህግ	90
ህጻናትን እና የቤት እንስሳትን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያግዙ ጠቃሚ ምክሮች	90
የመንጃ ፍቃድ ህጎች ስምምነት (DLC)	84
በአልኮል ወይም ቁጥጥር በሚደረግበት ንጥረ ነገር ተጽእኖ ስር ሆነው ማሽከርከር	81
የግንባር መብራቶች (Headlight)/የንፋስ መከላከያ መጥረጊያዎች (Windshield Wipers)	42
በፍቃድ ላይ የተመሰረተ ምርመራ (ለአልኮል ወይም ለአደንዛዥ እጽ ኬሚካላዊ ምርመራ ማድርግ)	82
ኢንሹራንስ፣ ያለ ኢንሹራንስ ስለማሽከርከር	80
ስም ወይም አድራሻ	89
አደገኛ ሁኔታዎችን የሚያስጠነቅቁ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን የመታዘዝ ህግ	93
ክፍት በሆነ የጭነት መኪና ጀርባ ላይ የሚጓዙ መንገደኞች	59
ስም ወይም አድራሻ ለውጥ በሚኖርበት ጊዜ የሚያስፈልግ ማስታወቂያ	89
የአካል ጉዳተኞች የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች	92
የደህንነት ቀበቶ	89
የበረዶ ብናኝ/በርዶ ማስወገድ	41
ቦታ መልቀቅ	59
የጽሑፍ መልእክት መላላክ	93
ዕድሜዎ ሳይደርስ መጠጥ መጠጣት	84
ዜሮ ቻይነት (በተጽዕኖ ስር ሆነው ለሚነዱ ከ21 አመት በታች አሽከርካሪዎች)	84
የተማሪ ፈቃድ፡-	
ለተማሪ ፈቃድ ማመልከት	1
የጀማሪ ተማሪዎች ፍቃድ መረጃ	3
የጀማሪዎች መንጃ ፍቃድ መረጃ	3
መንዳትን መማር	**31**
መመልከት፡-	
ከፊትዎ	37
ከኋላ	38
ወደ ጎኖቹ።	38
ርቀትን ጠብቆ ስለማሽከርከር	**35**
ፍጥነትን በአግባቡ መቆጣጠር	**38**
ካርታዎች፣ ግዛት አቀፍ እና በካውንቲ ደረጃ	**94**
ከትራፊክ ፍሰት ጋር መቀላቀል	**46**
የወታደር አባል	**3**
መስተዋቶች	**31**
ሞተር ሳይክሎች/ሞፔዶች፣ መንገዱን መጋራት	**55**
ስም፣ ይቀይሩ	**89**
መገናኛ መንገዶች/መስቀለኛ መንገዶች ላይ በአግባቡ መንዳት	**48**
ምሽት ላይ ስለማሽከርከር	**39**
የአካል ክፍል ልገሳ ትረስት ፈንድ	**2**
የአካል ክፍል ለጋሽነት መለያ	**2**
ተሽከርካሪን ማቆም (ፓርኪንግ)	**52**
ለአካል ጉዳተኞች የሚሆኑ ቦታዎች	92
ፓራለል ፓርኪንግ (በትይዩ ማቆም)	6, 52, 53
ማለፍ፡	
በአጠቃላይ	46, 47
አይቻልም	47
በባለሁለት መስመር መንገድ	47
በቀኝ በኩል	47
መንገድ(አስፋልት)፡	
ተንሸራቶ መውጣት	63
ምልክቶች	22
እግረኞች	**55**
ማየት የተሳናቸው	9
የትራፊክ መብራት ምልክቶች	9
ጥንቃቄ ለተሞላበት መንዳት ነጥቦችን ማስወገድ	**79**
የፔንስልቬንያ የነጥብ አሰጣጥ ስርዓት	**79**
ፖሊስ፣ ቢያስቆምዎት ምን ማድረግ እንዳለበዎት	**80**
የባቡር መንገድ መስቀለኛ መንገድ ምልክት	**10**
የባቡር ሐዲድ መሻገሪያዎች	**55**
የባቡር ማቋረጫ ምልክቶች	**9**
ማጣቀሻዎች	**94**
የመቆጣጠሪያ ምልክቶች	**10**
የመንገድ፣ ሁኔታዎች፡	
በጎርፍ የተጥለቀለቁ መንገዶች	61
ሀይድሮፕላኒንግ	41
የሚያንሸርትቱ መንገዶች/መሬቶች	40, 41
በረዶ እና የበረዶ ብናኝ	41
እርጥብ አስፋልቶች	40
የመንገድ ላይ ቁጣን መቋቋም	**60**

ርዕስ	ገጽ
ክብ አደባባዮች (Roundabouts)	**50**
የትምህርት ቤት አውቶቡሶች	**58**
የአሽከርካሪውን ወንበር ያስተካክሉ	**31**
የደህንነት ቀበቶዎ፣ ይሰሩ	**31**
ምልክት መስጠት፦	
የአደጋ ጊዜ የትራፊክ መብራት ምልክቶችን መጠቀም	44
አቅጣጫ ሲቀይሩ	44
ፍጥነት ሲቀንሱ ወይም ሲቆም	43
የትራፊክ መብራት ምልክቶች (ትራፊክ):	
ብልጭ የሚሉ ምልክቶች	8
የመንገድ መስመር (የሌይን) አጠቃቀም የቁጥጥር ምልክቶች	8
መብራቶች እና ጠቋሚ ቀስቶች	7
የማይሰሩ የትራፊክ መብራቶች	8
የእግረኛ ምልክቶች	9
የባቡር መንገድ ማቋረጫ	9
የራምፕ ርቀት መለኪያ	8
የትምህርት ቤት አከባቢ (ዞን) ምልክቶች	9
ምልክቶች፦	
አቅጣጫ ጠቋሚ ምልክቶች	19
የመውጫ ቁጥሮች	19
አውራ ጎዳና/ኤክስፕረስ ዌይ	19
የኢንተርስቴት የመንገድ መስመር ቁጥር ስርዓት	20
የማይል ምልክቶች	20
የመንገድ መስመር ምልክቶች (Route Markers)	20
አገልግሎት	21
ቱሪስቶችን ለመርዳት የተተከሉ የአቅጣጫ ምልክቶች	21
የመቆጣጠሪያ ምልክቶች	10
የማስጠንቀቂያ ምልክቶች	13
የሚመሩ መሣሪያዎች	19
ኤሌክትሮኒካዊ አቅጣጫ ጠቋሚ ፓነሎች	19
አደገኛ ሁኔታዎችን የሚያስጠነቅቁ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎችን የመታዘዝ ህግ	93
ከመንገድ አጠገብ ያሉ ነገሮች	17
የስራ ቀጠና	18
መንሸራተት	**61**
የሚያንሸራትቱ መንገዶች	**40, 41**
ቀስ ብሎ ለሚንቀሳቀስ ትራፊክ፣ የሚደረጉ ምላሾች	**43**
የበረዶ ብናኝ/በርዶ ማስወገድ	**41**
በረዶ የሚያጸዱ ተሽከርካሪዎች	**60**
የበረዶ አውሎ ንፋስ	**42**
የማህበራዊ ዋስትና (ሶሻል ሴኩሪቲ) ቁጥር መረጃ	**3**
በተሽከርካሪዎች መካከል ያለ ርቀት፦	
ከፊትዎ	35
ከኋላ	37
"የአራት-ሰከንድ ህግ፣"	35
ወደ ጎኖቹ	36
ፍጥነት፡	
ፍጥነትን በአግባቡ መቆጣጠር	38
የተለጠፈ ገደቦች	38
ለድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ቦታ የመልቀቅ ህግ	**59**
መሪ ማዞር	**60**
የመንጃ ፍቃድ አገዳዎች እና መሰረዞች	**79**
ፈተናዎች፦	
አማራጭ የፈተና ዘዴዎች	92
ፈተናውን ከወደቁ	6
ፈተናውን ካለፉ	6
እውቀት	5
መንገድ	5
ጎማዎች፦	
መፈንዳት	62, 63
ትራፊክ፡	
ማዞርያዎች፣ ክብ አደባባዮች (Roundabouts)	50
የትራፊክ ሁኔታዎችን አንድ በአንድ ማስተናገድ	40, 41, 42
ቀርፋፋ ተንቀሳቃሽ ትራፊክ	43
የትራፊክ ፍሰት	43
የትራፊክ መብራቶች (የትራፊክ መብራት ምልክቶችን ይመልከቱ)፣	
የጭነት መኪናዎች፦	
ወደ ኋላ ሲነዱ የሚያጋጥሙ አድጋዎች	58
ፍሬን መያዝ	58
ማምለጫ ራምፖች	58
የጭነት መኪናን መከተል	57
ከመጠን በላይ ጭነቶች	58
የጭነት መኪና ማለፍ	56
የሚያልፍ የጭነት መኪና	57
መታጠፍ/መዞር	57
መታጠፍ፣ ወደ መስመር መግባት እና ማለፍ	**45**
መንገዶችን ማቋረጥ	46
ወደ ግራ እና ቀኝ መታጠፍ	45
ከትራፊክ ጋር መቀላቀል	46
ማለፍ	46
ከ ወይም ወደ መሃል መታጠፊያ መስመር መታጠፍ	45
ቀይ የትራፊክ መበራት ላይ ወደ ቀኝ መታጠፍ	46
U-turns	46
ዕድሜዎ ሳይደርስ መጠጥ መጠጣት	**84**
የተሽከርካሪ ፍተሻዎች፣ ለመንዳት በመዘጋጀት ላይ	**331**
የቀድሞ ወታደሮች መለያ	**2**
የታይነት ሁኔታዎች፦	
ጭጋግ/ጉም	42
በረዶ	42
እይታ	**3, 33**
የማስጠንቀቂያ ምልክቶች	**13**
እርጥብ አስፋልቶች	**40, 41**
የክረምት መንገዶች፣ የሚያንሸራትቱ	**41**
የስራ ዞኖች	**18, 54**
የሚመሩ መሣሪያዎች	19
የሥራ ቀጠና ምልክቶች	54
ዜሮ ቻይነት (በተጽዕኖ ስር ሆነው ለሚነዱ ከ21 አመት በታች አሽከርካሪዎች)	**84**

የቶምሰንስ ድግስ በፍጹም አይረሱትም።

ቶምሰንስም አይረሱትም።

ምክንያቱም ሕጉ እንደሚለው ማንኛውም አዋቂ ሰው ቢራ፣ ወይን፣ የወይን ማቀዝቀዣዎች ወይም አልኮልን ከ21 ዓመት በታች ላለ ሰው የሚሰጥ ወይም የሚሸጥ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እስራት፣ ለመጀመሪያው ልጅ ላቀረበው አገልግሎት ዝቅተኛው 1,000 ዶላር እና ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ታዳጊ ደግሞ 2,500 ዶላር ቅጣት ይጣልበታል።

ለራስዎ ልጅ ወንድ ልጅም ይሁን ሴት ልጅ መጠጥ መስጠትም ሕገወጥ ነው። ስህተት ከመሥራትዎ በፊት፣ በነጻ የሚገኘውን “ኃላፊነት የሚሰማው ወላጅ” የሚል ብሮሹራችንን ለማግኘት ይደውሉልን ወይም ይጻፉልን እና ያንብቡት።

ሊወርድ የሚችል ፒዲኤፍ ፋይልም እንዲሁ በኢንተርነት በዚህ ድረገጽ ማግኘት ይቻላል፡- http://www.lcb.state.pa.us/ webapp/ Education/Materials/ Materials_Order_form.asp

ለረጅም፣ ለረጅም ጊዜ የሚታወሱት ነገር እንደሚሆን ዋስትና እንሰጣለን።



Pennsylvania Liquor
Control Board
Northwest Office Building
Harrisburg, PA 17124

Pennsylvania Chapter
American Academy of
Pediatrics

Commonwealth of
Pennsylvania Department of
Transportation

ሊታወሱ የሚገባቸው አስፈላጊ ቃላት

ፈቃድዎን ሲያገኙ እነዚህን ጠቃሚ ቃላት ያስታውሱ

እነዚህ ሕይወትን የሚያድኑ የአካል ክፍሎችን እና ሕብረ ሕዋሳትን ንቅለ ተከላ ለሚጠባበቁ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ጠቃሚ ቃላት ናቸው። ሌሎች ሰዎች የዓይን ሞራ ግርዶሽ ንቅለ ተከላዎችን በማድረግ የማየት ችሎታቸውን እንዲያገኙ፣ በተበረከተ ቆዳ አማካኝነት ከቃጠሎ በፍጥነት እንዲድኑ ወይም በተተከለው አጥንት ያለ ህመም እንዲራመዱ የሚረዱ ቃላት።

የአካል ክፍሎችን እና ሕብረ ሕዋሳትን (ቲሹ) በመለገስ ሕይወትን ለማዳን "እሺ" ለማለት የመረጡ ግለሰቦች የለጋሽነት ምልክቱን በፈቃዱ ላይ ማስቀመጥ እና የለጋሽ ካርድ መፈረም አለባቸው። ለሌሎችን ለመርዳት የተደረገውን አስፈላጊ ውሳኔ እንዲያውቁ የመለገስ ፍላጎት ለቤተሰብ እና ጓደኞች መገለጽ አለበት።

ስለ አካል እና ቲሹ ልገሳ አንዳንድ አጫጭር እውነታዎች

- አንድ የአካል እና የቲሹ ለጋሽ እስከ 8 ህይወትን ማዳን እና ከ 75 በላይ ሰዎችን መርዳት ይችላል።
- ማንኛውም ሰው፣ ዕድሜ ወይም የሕክምና ታሪክ ሳይገድበው ለጋሽ ለመሆን መመዝገብ ይችላል።
- በአሜሪካ ውስጥ ያሉ ሁሉም ዋና ዋና ሃይማኖቶች የአካል ክፍሎችን እና ሕብረ ሕዋሳትን ልገሳን ይደግፋሉ እንዲሁም ልገሳን ለሌሎች የመጨረሻ የፍቅር እና የልግስና ተግባር አድርገው ይመለከቱታል።
- ለጋሾችም ሆኑ ለቤተሰቦቻቸው የአካል ክፍል ወይም የቲሹ ልገሳ ለማድረግ ምንም ዓይነት ክፍያ አይጠየቁም።

\- ለበለጠ መረጃ donatelifepa.org ን ይጎብኙ

የአካል እና የቲሹ ለጋሽ ካርድ ለማግኘት ይደውሉ፡-

በምስራቅ ፔንስልቬንያ፡-

የህይወት ስጦታ ለጋሽ ፕሮግራም 1-888-DONORS-1

በምዕራብ ፔንስልቬንያ፡-

የአካል ክፍሎች ማገገሚያ እና
የትምህርት ማዕከል (CORE)። 1-800-DONORS-7

ተጨማሪ የአካል እና ቲሹ ሀብት መረጃ ለማግኘት ይደውሉ፡-

የፔንስልቬንያ የጤና ዲፓርትመንት 1-877-PAHEALTH